# ጃፓን
# እንደምን ሠለጠነች?

952.047
ከበሚ

ከከበደ ሚካኤል

# ጃፓን
# እንደምን ሠለጠነች?

ከከበደ ሚካኤል

የአ.አ ከተማ ሕዝብ ቤተ መጻሕፍት
A.A. City Public Library

ሜጋ አሳታሚ ድርጅት

© ሜጋ አሳታሚ ድርጅት ፲፱፻፺

ስልክ ቁጥር፣ 504470

504498

የመ.ሣ.ቁጥር 413 ኮድ 1110

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

ፈንፈኔ ማተሚያና ፐብሊሺንግ አ. ማ.
ታተመ

# መ ግ ቢ ያ ።

ከትልቁ ፡ ደራሲ ፡ ከገት ፡ በተገኘው ፡ ውብ ፡ ሥራ ፡ ሆኖ ፡ በሚቈጠረው ፡ በፎስት ፡ ድርሰት ፡ ውስጥ ፡ ትልቅ ፡ ምሳሌ ፡ እናገኛበታለን ። ሊቁ ፡ ፎስት ፡ የዓለምን ፡ ዕውቀቶችና ፡ ጥበቦች ፡ ለመመርመርና ፡ ለማወቅ ፡ ፈልጎ ፡ ዕድሜውን ፡ ሙሉ ፡ መጻሕፍት ፡ በማንበብ ፡ ዓይኖቹ ፡ ፈዝዘው ፤ ሥሮቹ ፡ ደንዝዘው ፤ መልኩም ፡ ተጨማድዶ ፡ አረጀ ። ሽምግልና ፡ የሰውነቱን ፡ እኸ ፡ ሁሉ ፡ ጨርሶ ፡ እንደ ፡ እንጨት ፡ አደረቀው ። ሞት ፡ ከቤቱ ፡ በራፍ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ታየው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሜፊስቶፌሌስ ፡ መጥቶ ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ቀዝቅዞ ፡ በነበረው ፡ ልቡ ፡ ውስጥ ፡ የዓለምን ፡ ደስታ ፡ የሚያስታውስ ፡ የምኞት ፡ እሳት ፡ ለኮሰበት ። ረቂቅ ፡ በሆነው ፡ ምክሩ ፡ ድል ፡ አድርጎት ፡ የዓለምን ፡ ደስታ ፡ ካስወደደው ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጠንቋይ ፡ ዘንድ ፡ ወስዶ ፡ በምትሐት ፡ ሰውነቱን ፡ በሙሉ ፡ አድሶ ፡ ወጣት ፡ ጎልማሳ ፡ አደረገው ።

ፎስት ፡ ማለት ፡ ማነው ? ፎስት ፡ ማለት ፡ በዚች ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ናቸው ። ጥንት ፡ በነ ፡ ህንድ ፤ በነ ፡ ሺና ፤ በነ ፡ ግብፅ ፤ በነ ፡ ባቢሎን ፤ በነ ፡ ግሪክ ፤ በነ ፡ ሮማ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥበብና ፡ ዕውቀት ፡ አብበው ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ የሥጣኔ ፡ ሥራዎችም ፡ ተሠርተው ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ክብር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ ትልቅ ፡ ደረጃ ፡ ደርሶ ፡ ነበር ። በኋላም ፡ ዕውቀታቸው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደታች ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ ሄዶ ፡ በቅጽበት ፡ ፈረሰ ፤ ከጨለማም ፡ ውስጥ ፡ ወደቀ ። የሰው ፡ ልጆችን ፡ ታሪክ ፡ የሚመለከቱና ፡ የሚመረምሩ ፡ ሊቃውንትም ፡ ይህን ፡ በማስተዋል ፡ ሥልጣኔ ፡ እንግዲህ ፡ በቃት ፡ አረጀች ፤ ሞተች ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ የዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ተስፋ ፡ የለውም ፡ ብለው ፡ አሰቡ ። ነገር ፡ ግን ፡ የዓለም ፡ አዱኛ ፡ ጨርሳ ፡ አለፈች ፡ ተብሎ ፡ ተስፋ ፡ ከተቆረጠ ፡ በኋላ ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ሁለተኛ ፡ ልደት ፡ በሚባለው ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ በበጋ ፡ የደረቀ ፡ ቅጠል ፡ ዝናብ ፡ ሲመጣ ፡ እንደገና ፡ እንደሚያቆጠቁጥ ፡ ሁሉ ፡ ዕውቀትና ፡ ጥበብም ፡ ታድሰው ፡ ለመለሙ ። ከዚያም ፡ ወዲያው ፡ የእንፋሎት ፡

# መ ግ ቢ ያ ፡፡

ኃይል ፡ የሚባለው ፡ ጥበብ ፡ ተገኘና ፡ ብረትን ፡ ስላንቀሳቀሰው ፡ የኢንዱስትሪ ፤ የፋብሪካ ፡ ጥበብ ፡ ተወለደ ፡፡ አርጅቶ ፡ የነበረውም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ዘር ፡ ዕውቀቱ ፡ ተመልሶ ፡ ስለጎለመሰ ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ ታይቶ ፡ የማይታወቅ ፡ መልካም ፡ እድል ፡ አግኝቶ ፡ ኃይ ሉና ፡ ሀብቱ ፡ በጣም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እየላቀ ፡ ሄዶ ፡፡ አዲስ ፡ የሲሳ ይና ፡ የክብር ፡ ዘመንም ፡ ተከፈተለት ፡፡

እነሆ ፡ የፎስት ፡ ቅኔ ፡ ምሥጢሩ ፡ ለመላው ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ታሪክ ፡ የሚያገለግል ፡ ስለሆነ ፡ ትልቁ ፡ ደራሲ ፡ ገቴ ፡ በባለቅኔነቱ ፡ በጀርመን ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የተወደደ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘበት ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ የዓለምን ፡ ሕዝቦች ፡ ጥበብ ፡ ከእርጅና ፡ ወደ ፡ ጎልማሳነት ፡ ለውጦ ፡ አዲስ ፡ የሀብትና ፡ የኃይል ፡ ዘመን ፡ የከፈተለት ፡ ይህ ፡ ምትሐት ፡ ወይም ፡ አስማት ፡ የተባለው ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ዕውቀት ፡ መሆኑን ፡ አንዘንጋው ፡፡

እንግዲህ ፡ የሰው ፡ ዕውቀት ፡ ተመልሶ ፡ ከታደሰ ፡ በኋላ ፡ ባሁኑ ፡ ሥልጣኔ ፡ ዘመን ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ከሠለጠኑት ፤ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ጋር ፡ የጦር ፡ ጉልበቱን ፡ አጠንክሮ ፤ ነፃነቱን ፡ ጠብቆ ፡ መኖር ፡ ሲፈልግ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ዋና ፡ መሣሪያው ፡ ነው ፡፡ ጃፓኖች ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ቶሎ ፡ ስለተረዱት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀሩትን ፡ ያህል ፡ በጥ ቂት ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ መራመድ ፡ አስፈላጊነቱን ፡ ተረድተውት ፡ በት ጋትና ፡ ባስተዋይነት ፡ ሠሩ ፡፡

ከዚህ ፡ ካሰቡት ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ የቻሉትም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፤ መንግሥታቸው ፤ ባለሥልጣኖቻቸውና ፡ ሕዝቡም ፡ ባጠ ቃላው ፤ ባንድ ፡ መንፈስና ፡ ባንድ ፡ ዓይነት ፡ ምኞት ፡ ተባብረው ፡ አገራቸውን ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ ባስደናቂ ፡ ትጋትና ፡ በማይዛባ ፡ አመ ራር ፡ እየሠሩ ፡ ስለተራመዱ ፡ ነው ፡፡

አንድ ፡ ትልቅ ፡ የጃፓን ፡ ሰው ፡ ሲናገር ፡ የጭስ ፡ መውጫ ዎቻቸውን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ተክለው ፡ ጢሳቸው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ሲኸ ጎደጎድ ፡ የሚታይ ፡ ብዙ ፡ ፋብሪካዎች ፡ የሚገኙበት ፡ አንድ ፡ አገር ፡ ባተመለከትኩ ፡ ጊዜ ፡ ለልቤ ፡ ትልቅ ፡ ደስታ ፡ ይሰማኛል ፡ አለ ፡ ይባ ላል ፡፡ ጃፓኖች ፡ በተፈጥሮአቸው ፡ አስተዋይነት ፡ ያደረባቸው ፡ በመሆ ናቸው ፡ ዛሬ ፡ ኃያላን ፡ በሆኑት ፡ ታላላቅ ፡ መንግሥታትና ፡ ደከ

# መ ግ ቢ ያ ።

ሞች ፡ በተባሉት ፡ ታናናሾች ፡ መንግሥታት ፡ መካከል ፡ የሚገኘውን ፡ ይህን ፡ ልዩነታቸውን ፡ እንዲፈጠር ፡ ያደረገው ፡ ጉዳይ ፡ የኢንዱስ ትሪ ፡ ጥበብ ፡ መሆኑ ፡ በቶሎ ፡ ስለገባቸው ፡ የለውን ፡ ዕድልና ፡ አጋ ጋር ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ለውጠ ፡ ከእርጅና ፡ ወደ ፡ ጎልማሳነት ፡ የሚለው ጠውን ፡ ይህን ፡ ኢንዱስትሪ ፡ የተባለውን ፡ ምትሐታዊ ፡ የሆነ ፡ ዕው ቀት ፡ ለማግኘት ፡ ጠንክረው ፡ ስለሠሩ ፡ ደረሱበት ። ጃፓኖች ፡ ያው ሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ በቶሎ ፡ ለመውረስ ፡ ቻሉ ፡ ሲባል ፡ ዋናው ፡ ትር ጉም ፡ ይህ ፡ ነው ።

ጃፓኖች ፡ የአውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ መቀበል ፡ ሲጀምሩ ፡ (ይኸ ውም ፡ በኢትዮጵያ ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በሞቱበት ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ መሆኑ ፡ ነው ፡) መጀመሪያ ፤ ለወጣቶቻቸው ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ እየመረጡ ፡ አስተማሩ ። ይህንንም ፡ ሲያደርጉ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ነገር ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ መሆኑን ፡ ስለተረዱት ፡ ንግዳቸውና ፡ ኢንዱ ስትሪያቸው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ እንዳይገቡ ፡ አድር ገው ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ራሳቸውን ፡ ለመቻል ፡ ጠንክረው ፡ ተጣጣሩ ። እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ የተከተሉትን ፡ መንገድ ፡ በዝርዝር ፡ እና ስተውለዋለን ።

ባጭሩ ፡ ጃፓኖች ፡ ሀ ፡ ሁ ፡ ብለው ፡ የአውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ መማር ፡ እንደ ፡ ጀመሩና ፡ ከተማሩትም ፡ በኋላ ፡ በሰላሳና ፡ በስድሳ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ አገራቸውን ፡ ትልቅ ፡ መንግሥት ፡ አድርገው ፡ እስካሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሠሩ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ አንባቢ ፡ ያገኘዋል ።

ኢትዮጵያም ፡ የትምህርትንና ፡ የኢንዱስትሪን ፡ ሥራዎች ፡ አጣምራ ፡ አብረው ፡ እንዲራመዱና ፡ እንዲስፋፉ ፡ ብታደርግ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቷ ፡ ወደሚመኙላት ፡ ታላቅ ፡ ዓላማ ፡ በቶሎ ፡ እንደ ምትደርስ ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ።

የዓለምን ፡ መንግሥታት ፡ ታሪክ ፡ ለየብቻው ፡ እየለየን ፡ ብን መለከተው ፡ ታሪካቸው ፡ በሁለት ፡ ይከፈላል ። አንደኞቹ ፡ አገራ ቸው ፡ ደሀ ፡ የሆነ ፡ አንጎላቸው ፡ ግን ፡ ሀብት ፡ የሞላበት ፡ ናቸው ። ሁለተኞቹ ፡ አገራቸው ፡ ሀብታም ፡ ሆኖ ፡ አንጎላቸው ፡ ግን ፡ በዘ መናችን ፡ ሥልጣኔ ፡ በኩል ፡ ደሀ ፡ የሆነ ፡ ናቸው ።

# መ ግ ቢ ያ ።

ሥልጣኔ ፡ ተስፋፍታ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ መጉረፍ ፡ ከጀመረችበት ፡ ከሰስትና ፡ ኳራት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ጀምሮ ፡ ባንደኛው ፡ ክፍል ፡ የጠራናቸው ፡ የውሮፓ ፡ ሕዝቦች ፡ ፓርቱጊዞች ፣ እስፓኛሎች ፣ ሆላንዶች ፣ ፈረንሣዮችና ፡ እንግሊዞች ፡ በቅኝ ፡ አገር ፣ በፕሮቴክቶራና ፡ በማንዳ ፡ ስም ፡ እያደረጉ ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ በጠራናቸው ፡ ሕዝቦች ፣ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ሀብት ፡ እየቀሙ ፡ ወደ ፣ አገራቸው ፡ ወስደው ፡ በፋብሪኮቻቸው ፡ ውስጥ ፡ አግብተው ፡ የተሠራ ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ አድርገው ፡ በማውጣት ፡ በውድ ፡ ዋጋ ፡ ይሸጡታል ። ለምሳሌ ፡ እንግሊዞች ፡ ከህንድ ፡ አገር ፡ ባንድ ፡ ብር ፡ የገዙትን ፡ ጥጥ ፡ ጨርቅ ፡ አድርገው ፡ በሠሩት ፡ ጊዜ ፡ ባሥር ፣ ወይም ፡ በስምንት ፣ ወይም ፡ በስድስት ፡ ብር ፡ መልሰው ፡ ይሸጡታል ።

ያውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ትልቅነት ፡ የተመሠረተው ፡ በዚህ ፡ ምሥጢር ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንደዚሁም ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ፋብሪኮችን ፡ የሚያንቀሳቅሳቸው ፡ የድንጊያ ፡ ከሰል ፡ ነበር ። ባገርዋ ፡ ውስጥ ፡ በብዛቱና ፡ በጥሩነቱ ፡ የበለጠ ፡ የድንጊያ ከሰል ፡ ያላት ፡ እንግሊዝ ፡ ስለሆነች ፡ ኃይልዋ ፡ የገነነ ፡ ሆኖ ፡ የኖረበት ፡ አንዱም ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ፋብሪኮችን ፡ የሚያንቀሳቅስ ፡ የኤሌክትሪክ ፡ ኃይል ፡ ስለተገኘ ፡ የፏፏቴ ፡ ውሀ ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ግድብ ፡ ለመሥራት ፡ የመሬቱ ፡ ሁኔታ ፡ የተመቸ ፡ ቦታ ፡ የሆነላቸው ፡ አገሮች ፡ ያለድንጊያ ፡ ከሰል ፡ እንዱስትሪያቸውን ፡ በኤሌክትሪክ ፡ ለማስኬድ ፡ የሚችሉ ፡ ሆነው ፡ ተገኙ ።

እንግዲህ ፡ በሁለተኛው ፡ ደረጃ ፡ የጠራናቸው ፡ አገሮች ፡ ይጎድላቸው ፡ የነበረውን ፡ የአንጎል ፡ ሀብት ፡ እያገኙ ፡ የኢንዱስትሪን ፡ ጥበብ ፡ ለመማርና ፡ ባገራቸው ፡ ለማቋቋም ፡ ሲችሉ ፡ ያውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ኃይል ፡ እየደከመ ፡ ሂደ ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚበልጠው ፡ የዓለም ፡ ክፍል ፡ የተያዘው ፡ በእነሱ ፡ እጅ ፡ በመሆኑ ፡ በዕውቀት ፡ እንዲራመድ ፡ አልፈቀዱለትም ። ነፃነቷን ፡ ለመጠበቅ ፡ ችላ ፡ በራሷ ፡ ፈቃድና ፡ ራሷ ፡ ባቀደችው ፡ መንገድ ፡ የትምህርቷን ፡ ፕሮግራም ፡ ለመምራት ፡ የቻለች ፡ ጃፓን ፡ ብቻ ፡ ነች ። የእሷን ፡ ታሪክ ፡ እየመረመርን ፡ ምሳሌ ፡ አድርገን ፡ ብንከተል በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ልንሠራ ፡ እንችላለን ።

# መ ግ ቢ ያ።

ይህን ፡ አሳብ ፡ ለአንባቢዎች ፡ ሳቀርብ ፡ ባንድ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ሙሉ ፡ እምነት ፡ ያለኝ ፡ መሆኔን ፡ ልገልጥ ፡ እወዳለሁ ። የኢንዱስትሪንና ፡ የትምህርትን ፡ ጉዳዮች ፡ የተያያዙ ፡ አድርገን ፡ የሠራን ፡ እንደሆነ ፡ በጥቂቶች ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ አኤሮፕላኖች ፡ ሠርተን ፡ ከምንመኘው ፡ ግብ ፡ ለመድረስና ፡ አገራችንን ፡ ትልቅ ፡ መንግሥት ፡ ለማድረግ ፡ እንችላለን ። ነገር ፡ ግን ፡ የታቀደ ፡ ፕላን ፡ ሳይኖረን ፡ የትምህርትንና ፡ የኢንዱስትሪን ፡ ሥራዎች ፡ እንደተገኘ ፡ የመራናቸው ፡ እንደሆነ ፡ መቼም ፡ ቢሆን ፡ ራሳችንን ፡ አንችልም ።

ስለ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ጉዳይ ፡ ስንናገር ፡ የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራዎች ፡ ላንድ ፡ መንግሥትና ፡ ላንድ ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ደም ፡ ሥር ፡ የሚቈጠሩ ፡ ዋና ፡ ጉዳዮች ፡ መሆናቸውን ፡ አለመዘንጋት ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ ዛሬ ፡ ባገራችን ፡ እንደምንመለከተው ፡ ዋና ፡ ዋናውን ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ በእጃቸው ፡ ይዘውት ፡ ያሉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። አንድ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ በዛሬ ፡ ዘመን ፡ በትምህርትም ፡ ሆነ ፡ በጦር ፡ በኩል ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ያስፈልገዋል ። ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ደግሞ ፡ በንግድና ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ሥራዎች ፡ የሠለጠኑ ፡ መሆን ፡ ያሻል ። ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሥልጣኔ ፡ እንድትራመድ ፡ ለማድረግ ፡ ልጆቿ ፡ ራሳቸው ፡ የሀብታቸው ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ መሆን ፡ አለባቸው ። ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ ልጆቿ ፡ የዘመናዊው ፡ ሥልጣኔ ፡ ትምህርት ፡ ኖሮዋቸው ፡ ንግድንና ፡ ኢንዱስትሪን ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ አውጥተው ፡ በእጃቸው ፡ ማግባት ፡ ያስፈልጋቸዋል ። የኢትዮጵያ ፡ ነጋዴዎች ፡ ልጆቻችንን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እየላኩ ፡ የንግድን ፡ ሥራ ፡ ተምረው ፡ እንዲመጡና ፡ ሀብታችንን ፡ በዘመኑ ፡ ሥልጣኔ ፡ ዕውቀት ፡ እንዲያስኬዱት ፡ እንፈልጋለን ፡ ብለው ፡ እንዲያስቡና ፡ እንዲፈጽሙት ፡ ያስፈልጋል ። አለዚያ ፡ ግን ፡ ሁል ጊዜ ፡ በገዛ ፡ አገራቸው ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በታች ፡ ሆነው ፡ ይኖራሉ ። ልጆችን ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ እየላኩ ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ እንዲማሩ ፡ የማድረግን ፡ ተግባር ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ አድርገን ፡ ከፍ ጸሚ ፡ እንዲደርስ ፡ ተግተን ፡ መሥራት ፡ ይገባናል ።

# መግቢያ ።

ኢትዮጵያ ያውሮፓን ሥልጣኔ ተቀብላ ራሷን እንድትችል ለማድረግ በሰፊው ሲደክምበት ይታያል:: የኢትዮጵያ ሕፃናት በየትምህርት ቤቶች ገብተው ብዙዎቹም ወደ ውጭ አገር ሄደው ይማራሉ:: ነጋዴዎችም የውጭ አገር ተወላጆች ከሆኑት ነጋዴዎች ጋር ተቀላቅለውና ጐን ለጐን ሆነው ሀብታቸውን ለማስፋፋት ይጣጣራሉ::

ነገር ፡ ግን ፡ በትምህርትም ፡ ሆነ ፡ በንግድ ፡ በኩል ፡ የሚደረገው ፡ አካሔድ ፡ በጥንቃቄ ፡ በተጠና ፡ መንገድ ፡ እንዲከናወን ፡ ካልተደረገ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ እንደሚያመጣ ፡ በብዙ ፡ አገሮች ፡ የተፈጸሙት ፡ ነገሮች ፡ ምሳሌ ፡ ሆነው ፡ ያስተምሩናል ። በንግድና ፡ በኢንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ራሳቸው ፡ እያስኬዱት ፡ ያገራቸውን ፡ ሀብቶች ፡ እንዲጠቀሙበት ፡ ለማድረግ ፡ ቢችሉ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አገራቸውን ፡ ከሌሎቹ ፡ ከሠለጠኑት ፡ አገሮች ፡ እኩል ፡ አደረጓት ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ማንኛውም ፡ የባዕድ ፡ መንግሥት ፡ ሊያጠቃቸው ፡ አይችልም ። ማንኛውም ፡ ኃይለኛ ፡ እንዳይመጣባቸው ፡ የሚሰጉ ፡ መሆናቸው ፡ ቀርቶ ፡ ራሳቸው ፡ የተፈሩ ፡ ይሆናሉ ።

እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ከመሰለው ፡ ከፍ ፡ ካለው ፡ ዓላማ ፡ ለመድረስ ፡ እንዲችሉ ፡ ሊከተሉት ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ መንገድ ፡ ሊያውቁትና ፡ ሊረዱት ፡ ይገባል ። ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የሚያገለግለን ፡ አንድ ፡ ምሳሌ ፡ ለማግኘት ፡ በዓለም ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ከፈለግሁ ፡ በኋላ ፡ ጃፓን ፡ የተከተለችውን ፡ መንገድ ፡ ከመከተል ፡ የተሻለ ፡ ሌላ ፡ ምሳሌ ፡ ላገኝ ፡ አልቻልኩም ። ጃፓን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ተነሥታ ፡ ከታላላቅ ፡ መንግሥታት ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ሆነች ፡ ሲባል ፡ እንሰማለን ፤ ይህም ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደምን ፡ ያለ ፡ መንገድ ፡ ተከትላ ፡ ይህን ፡ ለማድረግ ፡ እንደቻለች ፡ መመርመር ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ላገራችን ፡ ሰዎች ፡ ለመግለጥና ፡ ለማስረዳት ፡ አስቤ ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ የሚያገለግሉኝን ፡ ስለ ፡ ጃፓን ፡ ታሪክ ፡ የሚናገሩትን ፡ በያይነቱ ፡ መጻሕፍት ፡ ሰብስቤ ፡ በማንበብ ፡ አዋጥቼ ፡ ያዘጋጀሁትን ፡ በዚህ ፡

# መ ግ ቢ ያ ።

መጽሐፍ ሳቀርበው ላገራችን የሚጠቅም ነገር ይገኝበታል፤
እኛም ይህን ተከትለን በመስራት ፍሬ ያለው አገልግሎት ላገራችን
እንሰጣለን ብዬ በሙሉ ልብ አምናለሁ።

ይህን ፡ የመሰለውን ፡ አሳብ ፡ ስንከተል ፡ ልንዘነጋቸው ፡ የማ
ይገባን ፡ ዋና ፡ ዋኖች ፡ የሆኑ ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ አሉ ።

አንደኛ ፡ ሥልጣኔ ፡ የሰውን ፡ ክብር ፡ ከፍ ፡ አድርጋ ፡ የምታ
ሳይ ፡ ትልቅ ፡ ዋጋ ፡ ያላት ፡ መሆንዋን ፡ በማሰብ ፡ ከልብ ፡ ልንወ
ዳት ፡ ይገባናል ። ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ እንድንችል ፡ የተወደደች ፡
ለመሆን ፡ የተገባች ፡ የሚያደርጋት ፡ ጠባይዋ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡
ለማወቅ ፡ ከመጣጣር ፡ አለማቋረጥ ፡ ያሻል ። ሁለተኛ ፡ የሥልጣኔን ፡
ጥበቦች ፡ ሁሉ ፡ ሊያስተምሩን ፡ የሚችሉ ፡ ነጮች ፡ ስለሆኑ ፡ የም
ንፈልገውን ፡ ጥበብ ፡ ከእነሱ ፡ ለመማር ፡ ተግተን ፡ መሥራት ፡ እንደ
ሚገባን ፡ አለመዘንጋት ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ የምንችለው ፡
ትእግሥትንና ፡ መስዋዕትነትን ፡ መሣሪያ ፡ በማድረግ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
ሦስተኛ ፡ በነጮች ፡ ዘንድ ፡ ጥቁሮች ፡ ምንም ፡ ቢማሩ ፡ ከፍ ፡ ባሉት ፡
ዕውቀቶች ፡ መሐንዲስነትን ፤ ሕክምናንና ፡ ኢንዱስትሪን ፡ በመሰሉት ፡
ጥበቦች ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ ለመሥራት ፡ አይችሉም ፡ እየተባልን ፡
ስለምንናቅ ፡ ይህንኑ ፡ አውቀነው ፡ ሐሰትነቱን ፡ በፍ ፡ ሳይሆን ፡
በሥራ ፡ ለዓለም ፡ ለመግለጥና ፡ ይህን ፡ ሐሜት ፡ ለማስተባበል ፡
መጣጣር ፡ አለብን ። ጃፓኖች ፡ በታሪካቸው ፡ ውስጥ ፡ እንደምንመ
ለከተው ፡ ሁሉ ፡ አገራቸውን ፡ ትልቅ ፡ መንግሥት ፡ ሊያደርጉት ፡
የቻሉት ፡ እነዚህን ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ የዘረዘርናቸውን ፡ ነገሮች ፡ ፈጽ
መው ፡ በመገኘታቸው ፡ ነው ። ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡
መንግሥት ፡ የኀይሉ ፡ አውታር ፡ ተዘርግቶ ፡ የተቋቋመበትን ፡ ዋና ፡
ዋኖች ፡ ሥራዎች ፡ ባዕድ ፡ ሰው ፡ ሳይገባብን ፡ እኛው ፡ ራሳችን ፡
ለማስኬድ ፡ እንድንችል ፡ ጥበቡን ፡ ከነጮች ፡ መማር ፡ ይገባናል ፡
ብለው ፡ ቊርጥ ፡ አሳብ ፡ ስላደረጉ ፡ ከዚህ ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ በሚ
ያስደንቅ ፡ ትእግሥትና ፡ ትጋት ፡ ስለሠሩ ፡ ቀናቸው ።
ነገር ፡ ግን ፡ ተመልካች ፡ የሆነ ፡ አንባቢ ፡ ጃፓኖች ፡ በጠባያ
ቸውና ፡ በባህሪያቸው ፡ ልዩነት ፡ ያላቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ፡ ስለ

መ ግ ቢ ያ ።

ዚህ ፡ ልንመስላቸው ፡ እንዴት ፡ እንችላለን ? ይል ፡ ይሆናል ።

ነገር ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ ይበልጥ ፡ የታደለ ፡ የሆነበት ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ መኖሩን ፡ ማሰብ ፡ አለብን ። ጃፓን ፡ መሬቷ ፡ በእርሻም ፡ ሆነ ፡ በማዕድን ፡ ረገድ ፡ ደሀ ፡ በመሆኑ ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ ተምራ ፡ የኢንዱስትሪ ፡ አገር ፡ ከሆነች ፡ በኋላ ፡ ጎረቤቶቿ ፡ የሆኑትን ፡ አገሮች ፡ እየወረረች ፡ ሀብታቸውን ፡ መቀማት ፡ ግድ ፡ ሆኖባታል ። ይህም ፡ አደራረግ ፡ ከማንድሹሪ ፤ ከሞንጎሊ ፤ ከኮሬ ፤ ከመስኮብና ፡ ከሺና ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ እንድትጋጭ ፡ እያደረጋት ፡ ቂምንና ፡ በቀልን ፡ አትርፋለች ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ ተግቶ ፡ በመሥራት ፡ የአውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ ተምሮ ፡ ኢንዱስትሪን ፡ እያስፋፋ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ራሱ ፡ ቢሠራ ፡ ባለጸጋ ፡ ከሆነችው ፡ መሬቱ ፡ የሚያገኘው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀብት ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ስለሆነ ፡ ከማንም ፡ አገር ፡ ጋር ፡ ሳይጋጭና ፡ ሳይቀያየም ፡ በሰላም ፡ መኖር ፡ ይችላል ። በብልጠትና ፡ በግፍ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ፖሊቲካቸውን ፡ መሥርተው ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ለጊዜው ፡ የማይደፈሩ ፡ መስለው ፡ ቢታዩን ፡ ይህ ፡ የብልጠታቸው ፡ ፖሊቲካ ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ የማይዘልቅ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጡልን ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ ዛሬ ፡ ሲፈጸሙ ፡ በማየት ፡ ላይ ፡ ነን ።

# ማ ው ጫ


ገጽ

ጃፓን ካሮጌው ዘመን ወደ አዲሱ ዘመን ስለመተላለፍዋ ........... ፩

የጃፓኖች የትምህርት እቅድ (ፕላን) ........... ፫

የኤንዱስትሪ ሥራ ስለመስፋፋቱ ሚትሱኢና ሚትሱቢሺ ........... ፲፬

የጃፓን ሕዝብ ቁጥር ........... ፴፩

የጦር ሠራዊት በሲቪል ወገኖች ላይ ስለመነሣቱ ........... ፴፱

ጃፓን በመርከብ ሥራ ........... ፵፫

ጃፓን በማንድሹሪ ........... ፶

ጃፓንና መስኮብ በሲቤሪ ........... ፶፬

የጃፓን ታላላቅ ሰዎች ........... ፶፱

ንጉሠ ነገሥቱና ሕዝቡ ........... ፷፫

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ........... ፷፱

ሊቲራቱር በጃፓን አገር ........... ፸፪

መደምደሚያ ........... ፸፯

ጃፓን ፣ ካሮጌው ፣ ዘመን ፣ ወደ ፣ አዲሱ ፣ ዘመን ፣ ስለመተላለፉ ።

የፓርቱጋል ፣ ሰዎች ፣ በጃፓን ፣ አገር ፣ ከ1549 ፣ ዓ. ም. (እ. አ. አ.) ጀምረው ፣ እየገቡ ፣ የክርስቲያንን ፣ ሃይማኖት ፣ ከሰበኩና ፣ ብዙ ፣ ጃፓኖችን ፣ ካጠመቁ ፣ በኋላ ፣ በሃይማኖት ፣ ምክንያት ፣ አድር ገው ፣ ነጮች ፣ አገራችንን ፣ ሊይዙብን ፣ ነው ፣ የማለት ፣ ስጋት ፣ በባለሥ ልጣኖቹ ፣ መንፈስ ፣ ውሥጥ ፣ ስላደረባቸው ፣ ሁሉንም ፣ ካገራቸው ፣ አስወጧ ቸው ። የተጠመቁትንም ፣ ክርስቲያኖች ፣ ፈጁዋቸው ። የክርስቲያን ፣ ሃይማ ኖት ፣ ባገራቸው ፣ ውስጥ ፣ መከልከሉን ፣ በ1638 ፣ ዓ. ም. (እ. አ. አ.) በዋጅ ፣ አስታወቁ ። ቀድሞ ፣ ጃፓኖች ፣ መርከቦቻቸው ፣ ሩቅ ፣ አገር ፣ ድረስ ፣ እየሄዱ ፣ በየባሕሩ ፣ ላይ ፣ ይዘዋወሩ ፣ ነበር ። ይህ ፣ አዋጅ ፣ ከወጣ ፣ በኋላ ፣ ግን ፣ ትልልቅ ፣ መርከቦች ፣ እንዳይሠሩና ፣ ወደ ፣ ሩቅ ፣ አገር ፣ እንዳይሄዱ ፣ የጃፓን ፣ ተወላጆች ፣ የሆኑት ፣ ሁሉ ፣ ተከለከሉ ።

"ከእንግዲህ ፣ ወዲያ ፣ ፀሐይ ፣ ብርሃኗን ፣ በመሬት ፣ ላይ ፣ አብርታ ፣ እስከምትኖርበት ፣ ጊዜ ፣ ድረስ ፣ ማንም ፣ ሰው ፣ ቢሆን ፣ ወደ ፣ ጃፓን ፣ አገር ፣ ለመግባት ፣ አይድፈር ፤ ሌላው ፣ ቀርቶ ፣ የመንግሥት ፣ መልክተኛ ፣ ( አምባሳደር ፣ ) ነኝ ፣ የሚል ፣ ሰው ፣ እንኳ ፣ እንዳይገባ ፣ ክልክል ፣ ነው ። ይህን ፣ አዋጅ ፣ ጥሶ ፣ ሲገባ ፣ የተገኘ ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ሰው ፣ ሁሉ ፣ በሞት ፣ ይቀጣል ፣" የሚል ፣ አዋጅ ፣ ተነገረ ።

የጃፓን ፣ መንግሥት ፣ ክርስቲያኖችን ፣ ከግዛቱ ፣ ውስጥ ፣ ለማ ጥፋት ፣ ውሳኔ ፣ ለማድረግ ፣ የደረሰበት ፣ ምክንያት ፣ ከዚህ ፣ ቀጥሎ ፣ ያለው ፣ ነው ፣ ይባላል ። ነገር ፣ ግን ፣ ምክንያቱ ፣ በእርግጥ ፣ ይህ ፣ ይሁን ፣ ወይም ፣ ሌላ ፣ አይታወቅም ። ጃፓኖች ፣ መጀመሪያ ፣ ጊዜ ፣ የፓርቱጋል ፣ ተወላጆች ፣ የሆኑ ፣ ካህናት ፣ ወደ ፣ አገራቸው ፣ በገቡ ፣ ጊዜ ፣ የክርቲያንን ፣ ሃይማኖት ፣ ትምህርት ፣ በደግ ፣ ዓይን ፣ ተመ ልከተው ፣ እንዲያስተምሩ ፣ ፈቅደው ፣ አበረታቷቸው ።

ከዚያን ፣ በፊት ፣ በጃፓን ፣ አገር ፣ በጣም ፣ ተስፋፍቶ ፣ የነበ ረው ፣ የቡዲስም ፣ ሃይማኖት ፣ በመሆኑ ፣ የቡዲስም ፣ ካህናት ፣ በዘ መን ፣ ብዛት ፣ ኃይለኞችና ፣ ባለጸጎች ፣ ሆነው ፣ ብዙ ፣ ወታደሮች ፣

እያሳደሩ ፡ በሃይማኖታቸው ፡ ሕግ ፡ የታናናሾቹን ፡ ነፍሳት ፡ ደም ፡ ማፍ
ሰስ ፡ እንኳ ፡ ክልክል ፡ መሆኑን ፡ ዘንግተውት ፡ ጥቅማቸውን ፡ ለመ
ጠበቅና ፡ ሀብታቸውን ፡ ለማስፋፋት ፡ ሲሉ ፡ ውጊያ ፡ እያደረጉ ፡
የሰው ፡ ደም ፡ ያላንድ ፡ ቅሬታ ፡ ሲያፈስሱ ፡ ይታዩ ፡ ነበር ። በዚ
ያን ፡ ጊዜ ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ ጠቅላይ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሆነው ፡ የሚ
ያስተዳድሩ ፡ "ሾጉኖች" የሚባሉት ፡ መሳፍንት ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡
በመመልከትና ፡ በማመዛዘን ፡ የቡዲስም ፡ ሃይማኖት ፡ እንደተበላሸ ፡
አውቀው ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ይህ ፡ አዲስ ፡ የመጣው ፡ የክርስቲ
ያን ፡ ሃይማኖት ፡ እየተስፋፋ ፡ በመሄድ ፡ በቡዲስም ፡ ቦታ ፡ ቢተኩ፡
የሚፈቅዱ ፡ መሆናቸውን ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ ሳይገልጡ ፡ አልቀሩም ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡
ተስፋፍቶ ፡ የተጠመቁትም ፡ ሰዎች ፡ ቁጥራቸው ፡ በብዙ ፡ መቶ ፡ ሺ ፡
የሚቈጠር ፡ ሆኖ ፡ በውስጣቸውም ፡ የታላላቅ ፡ መሳፍንት ፡ ወገኖች ፡
ይገኙባቸው ፡ ነበር ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ፖርቱጌዞችና ፡ እስፓኞሎች ፡
ግዛታቸውን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ለማስፋፋት ፡ ተግተው ፡ በመወዳደር ፡
የሚሠሩበት ፡ ጊዜ ፡ ስለነበረ ፡ ሁለቱም ፡ በየበኩላቸው ፡ ወገኖቻ
ቸው ፡ የሆኑት ፡ ካህናት ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ ኃይል ፡ እንዲያገኙና ፡
እንዲስፋፉ ፡ ይረዷቸው ፡ ነበር ። የእስፓኛም ፡ መንግሥት ፡ በጃ
ፓን ፡ አገር ፡ አጠገብ ፡ የደሴቶች ፡ ግዛት ፡ ነበረው ።

አንድ ፡ ጊዜ ፡ "ሳን ፡ ፊሊፔ ፡" የሚባል ፡ የእስፓኛ ፡ መር
ከብ ፡ ተበላሽቶ ፡ በችግር ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ጃፓኖች ፡ አግኝተውት ፡
መርከብ ፡ በተበላሸ ፡ ጊዜ ፡ የሚሠራበት ፡ ቦታ ፡ አለ ፡ ብለው ፡
ወደ ፡ ጠረፋቸው ፡ ወሰዱት ። እነዚህም ፡ ሕዝቦች ፡ ቅሚያና ፡ ዝረፋ ፡
የለመዱ ፡ በመሆናቸው ፡ ወደ ፡ ወደባቸው ፡ እንዲገባ ፡ ካደረጉት ፡
በኋላ ፡ ባገራቸው ፡ የተለመደ ፡ ሆኖ ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ መና
ሩንና ፡ በሱ ፡ መሠረት ፡ ተበላሽቶ ፡ የተገኘ ፡ መርከብ ፡ ሁሉ ፡ ላገ
ኙት ፡ ሰዎች ፡ እንዲሰጥ ፡ የተፈቀደ ፡ መሆኑን ፡ ነግረውት ፡ በው
ስጡ ፡ የሚገኘውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ዘርፈው ፡ ተከፋፈሉት ።

የዚሁ ፡ የእስፓኛ ፡ መርከብ ፡ ሹም ፤ ያገሩ ፡ ዋና ፡ ባለሥልጣን ፡
ለነበረው ፡ ለጃፓን ፡ ሹም ፡ አቤቱታውን ፡ ቢያሰማ ፡ መስፍኑ ፡ የዘ
ረፉት ፡ ሰዎች ፡ የሚገባ ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ የሠሩት ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የመርከቡ ፡ ሹም ፡ በጣም ፡ ተናደደና ፡ ጃፓኖች ፡ ለጊዜው ፡ አገራቸው ፡ ሆኖ ፡ ይህን ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ ቢሠራ ፡ የእስፓኛ ፡ መንግሥት ፡ ደግም ፡ በኃይለኛነቱና ፡ በብልጽግናው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ገናና ፡ መሆኑን ፡ ሊገልጥላቸው ፡ ፈልጎ ፡ የዓለም ፡ ካርታ ፡ አወጣና ፡ በእስፓኛ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ አገሮች ፡ በካርታው ፡ ላይ ፡ አሳያቸው ። እነሱም ፡ በጣም ፡ ተደንቀው ፡ እስፓኛ ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ አገሮች ፡ እንዴት ፡ አድርጋ ፡ ለመያዝ ፡ ቻለች ? ሲሉ ፡ ጠየቁት ። እሱም ፡ « መጀመሪያ ፡ ቄሶች ፡ ትልካለች ፡ በኋላም ፡ ከገሩ ፡ ተወላጆች ፡ ብዙዎች ፡ ሲጠመቁ ፡ የተጠመቁት ፡ ሰዎች ፡ ባገራቸው ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንዲነሱ ፡ አድርጋ ፡ እነሱን ፡ የሚረዱ ፡ ወታደሮች ፡ ትልክና ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ አገራቸውን ፡ ትይዛለች ። » ብሎ ፡ መለሰላቸው ። የእስፓኛ ፡ መርከብ ፡ ሹም ፡ ይህን ፡ ሲናገር ፡ የሰሙት ፡ ሰዎች ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፈው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በሥልጣን ፡ ላይ ፡ ለነበረው ፡ ሂዴዮሺ ፡ ለሚባለው ፡ መስፍን ፡ እንዲያውቀው ፡ ሰላደረጉ ፡ መስፍኑ ፡ ወዲያውኑ ፡ በገሩ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ነጮችና ፡ ክርስቲያኖች ፡ እንዲጠፉ ፡ አዋጅ ፡ አስነገረ ። ናጋሳኪ ፡ በምትባለው ፡ ከተማ ፡ ዙሪያ ፡ ብቻ ፡ ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተቃጠሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ከጃፓን ፡ አገር ፡ ጠርሶ ፡ ተነቀለ ፤ ነጮችም ፡ ወደ ፡ ጃፓን ፡ አገር ፡ እንዳይገቡ ፡ በሞት ፡ ቅጣት ፡ ተከለከሉ ።

እንደዚህ ፡ አድርገው ፡ ጃፓኖች ፡ ከዓለም ፡ ጋር ፡ ተለያይተው ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ በላይ ፡ ለብቻቸው ፡ ኖሩ ። በዚህ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ዓለም ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ ምን ፡ እንደሚሠራ ፡ አታውቅም ፡ ነበር ። ጃፓንም ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ይሠራ ፡ እንደነበረ ፡ አታውቅም ፡ ነበር ። በዚህም ፡ አኳኋን ፤ " ዓለምና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተረሳሱ ። „ ሲል ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊው ፡ ጊበን ፡ ኢትዮጵያና ፡ ዓለም ፡ እስላሞች ፡ የባህሩን ፡ ጠረፎች ፡ ከያዙባት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ተለያይተው ፡ ስለ ኖሩበት ፡ ዘመን ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ በጃፓንም ፡ ላይ ፡ ተፈጸመ ።

ከሁለት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ መጀመሪያ ፡ አሜሪካኖች ፡ ቀጥሎ ፡ ፈረንሳዮችና ፡ እንግሊዞች ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ በርዋን ፡ ሰብረው ፡ ከገቡ በኋላ ፡ ግን ፡ ጃፓን ፡ የአውሮፓ ፡ መንግ

ሥታት ፡ ኃይል ፡ በጣም ፡ የገነነ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ አገ ርዋ ፡ እንዳይገቡ ፡ ለመከልከል ፡ የማትችል ፡ ደካማ ፡ መሆኗን ፡ ዐወ ቀችው ።

ሙትሱሂቶ ፡ የሚባለው ፡ ንጉሥ ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ ጃፓን ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ እንድትቀበልና ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በለ ፈው ፡ እንዲከፈቱ ፡ አዘዘ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ "የሜይጂ ፡ ዘመን" ፡ የሚ ባለው ፡ ተጀመረ ። ትርጓሜውም ፡ "የብርሃን ፡ ዘመን" ፡ ማለት ፡ ነው ። ጃፓኖችም ፡ ከዓለም ፡ ጋር ፡ ተለያይተው ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ በመኖ ራቸው ፡ ምክንያት ፡ በዕውቀትና ፡ በሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርተው ፡ እንደ ፡ ተጐዱ ፡ ተረድተውት ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ተቈጩበት ። ምን ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ተቈጩበት ፡ አንባቢ ፡ እንዲረዳው ፡ ለማድ ረግ ፡ ስንል ፡ በ1921 ዓ. ም. በቶኪዮ ፡ ከተማ ፡ የሚታተም ፡ አንድ ፡ የጃፓን ፡ ጋዜጣ ፡ የጻፈውን ፡ ቃል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ እንጠቅሰዋለን ።

"ያውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ቅኝ ፡ አገሮች ፡ ሲይዙና ፡ ግዛታ ቸውን ፡ ሲያስፋፉ ፡ እኛ ፡ ጃፓኖች ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ዓመት ፡ በቤታችን ፡ ተኝተን ፡ ኖርን ። ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እንዳንሄድና ፡ ትልልቅ ፡ መርከቦች ፡ እንዳንሠራ ፡ ተከልክለን ፡ ነበር ። በቤታችን ፡ ቊጭ ፡ ብለን ፡ ቅኔ ፡ በመጻፍና ፡ የሻይ ፡ ግብዣ ፡ በማድረግ ፡ ጒልበታችንን ፡ ሁሉ ፡ ማባከን ፡ ግዴታ ፡ ሆኖብን ፡ ኖርን ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ዛሬ ፡ ያገኘነው ፡ ትርፍ ፡ የሕዝባችን ፡ ቊጥር ፡ አለመጨመረ ፡ በመሄዱ ፡ መቸ ገርና ፡ በዘር ፡ ምክንያት ፡ የተናቅን ፡ ሕዝብ ፡ ሆነን መታየት ፡ ብቻ ነው ። ባለፈው ፡ በመሳፍንት ፡ ግዛት ፡ ዘመን ፡ ለተሠራው ፡ ስህተት ፡ ዛሬ ፡ እኛ ፡ ዕዳ ፡ ከፋዮች ፡ ሆነናል" ።

እንግዲህ ፡ ከዓለም ፡ ተለያይተው ፡ በመኖራቸው ፡ እንደዚህ ፡ አድርገው ፡ የተቈጩት ፡ ሕዝቦች ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመቀ በል ፡ ቊርጥ ፡ አሳብ ፡ አድርገው ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡ የተከተሉት ፡ መንገድ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ?

የጃፓንና ፡ የእንግሊዝ ፡ ታሪክ ፡ በጣም ፡ ይመሳሰላል ፡ እያሉ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ይነግሩናል ። ለዚሁም ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ ሁለ ቱም ፡ አገሮች ፡ በባሕር ፡ የተከበቡ ፡ ደሴቶች ፡ በመሆናቸውና ፡ በሌላ ም ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ልብ ፡ አድርገን ፡ ስና

ስተውለው ፡ የጃፓንና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ደግሞ ፡ በጣም ፡ ይመሳሰላል ። ሁለቱም ፡ አገሮች ፡ ባንድ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ፖርቱጌዞች ፡ ጎበኟቸው ። ሁለቱም ፡ በንድ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ በሃይማኖት ፡ ጉዳይ ፡ ተጣልተው ፡ ለነፃነታቸው ፡ ስለፈሩ ፡ ከገራቸው ፡ አስወጧቸው ። ሁለቱም ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ ዓመታት ፡ የሚሆን ፡ ከዓለም ፡ ተለይተው ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ በውድም ፡ ሆነ ፡ በግድ ፡ በሮቻቸውን ፡ ከፍተው ፡ ነጮችን ፡ ተቀበሏቸው ። ስለዚህ ፡ ዛሬ ፡ በሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀረችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመድረስ ፡ የምታደርገውን ፡ ግሥገሣ ፡ ለማፋጠን ፡ ስትል ፡ ፍቱን ፡ ሆኖ ፡ የተገኘውን ፡ የጃፓንን ፡ መንገድ ፡ እንዳትከተል ፡ የሚከለክላት ፡ ስንፍና ፡ ከልሆነ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ ሊገኝ ፡ ይችላል ?

---

## የጃፓኖች ፡ የትምህርት ፡ አቅድ ፡ ( ፕላን ። )

ጃፓኖች ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ማናቸውም ፡ ሕዝብ ፤ ወይም ፡ መንግሥት ፡ ቢሆን ፡ ኃይለኛ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ዘመናዊ ፡ በሆነው ፡ ስውቀት ፡ የተሠሩትን ፡ እንደ ፡ መድፍ ፤ ታንክና ፡ አኤሮፕላን ፡ የመሰሉትን ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ለመሥራት ፡ በብዙ ፡ ሚሊያርድ ፡ የሚቈጠር ፡ ገንዘብ ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ ስለተረዱትና ፡ ብዙ ፡ ገንዘብም ፡ ለማግኘት ፡ የሚቻለው ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ እየሠሩ ፡ የዓለምን ፡ ገበያ ፡ በእጃቸው ፡ ጨብጠው ፡ ከያዙት ፡ ሕዝቦች ፤ ወይም ፡ መንግሥቶች ፡ ጋር ፡ በመወዳደር ፡ መሆኑን ፡ ስላወቁት ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ ተግተው ፡ ሠሩ ። ይህንንም ፡ ሲያደርጉ ፡ ብልጽግናን ፡ የሚፈልጉት ፡ ገንዘባቸውን ፡ ለጌጥና ፡ ለምቾት ፡ ኑሮ ፡ ለማዋል ፡ ሳይሆን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የሚጠቅም ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ለመሥሪያ ፡ እያደረጉት ፡ ነው ። ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ እንደ ፡ ባርኔጣ ፤ ሰዓት ፤ ቢራ ፤ ፊርጥ ፤ ቢሲክሌት ፤ መድኃኒት ፤ ጨርቃ ፡ ጨርቅ ፤ ዶሮ ፡ ማርባት ፤ የመሰሉትን ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ ባዲሱ ፡ ጥበብ ፡ አሠራር ፡ እየሠሩ ፡ የዓለሙን ፡ ገበያ ፡ በንግድ ፡ ዕቃቸው ፡ አጥለቀለቁት ። ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ዕውቀት ፡ የሌለው ፡ ነጋዴ ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ እንደማይችል ፡ ስላወቁት ፡ ማናቸውም ፡ የጃፓን ፡ ሰው ፡ ማናቸውንም ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ለመሥራት ፡ ሲያስብ ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡

6

ወይም ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ አገሮች ፡ ሄዶ ፡ ያን ፡ የሚፈልገውን ፡ ነገር ፡ የሠለጠኑት ፡ ነጮች ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርገው ፡ እንደሚሠሩት ፡ ጥበቡን ፡ ተምሮ ፤ ቀድቶ ፣ ሰርቆ ፤ አሠራሩን ፡ በትክክል ፡ ካወቀው ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ተመልሶ ፡ ገብቶ ፡ በዚያ ፡ መዝገብ ፡ ይወራል ።

በዚህ ፡ ረገድ ፡ ጃፓኖች ፡ የሠሩትን ፡ አስደናቂ ፡ ሥራ ፡ ለመረዳት ፡ ኖሮቤርት ፡ ስታንዲሽ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ የአሜሪካ ፡ ሰው ፡ « ሦስት ፡ ሸንበቆች ፡ » በሚል ፡ አርእስት ፡ የልብ ፡ ወለድ ፡ መልክ ፡ ሰጥቶ ፡ የጻፈውን ፡ መጽሐፍ ፡ ማንበብ ፡ ያስፈልጋል ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በአማርኛ ፡ ተተርጒሞ ፡ በየትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ያሉ ፡ ወጣቶች ፡ እንዲያነቡት ፡ ቢደረግ ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ ይሰጣል ። ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ ታሪኩን ፡ በጭሩ ፡ እንገልጣለን ።

ፉሬኖ ፡ የሚባል ፡ ከመኳንንት ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የጃፓን ፡ ሰው ፡ ነበር ። መሳፍንት ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥቱን ፡ ለስም ፡ ብቻ ፡ አስቀምጠው ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ ጨብጠው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የሆኑ ፡ ነጮች ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ እንዳይገቡ ፡ ያገራቸውም ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እንዳይሄዱ ፡ ከልክለው ፡ በኖሩበት ፡ ዘመን ፡ ፉሬኖ ፡ የነጮች ፡ ዕውቀት ፡ ባዲሱ ፡ ሥልጣኔ ፡ ጥበብ ፡ በጣም ፡ የተራቀቀ ፤ ኃይላቸውም ፡ የገነነ ፤ መሆኑን ፡ ሰማ ። እሱም ፡ ቀድሞ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ስለነበረ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ባለሥጣኖች ፡ የሆኑት ፡ መሳፍንት ፡ ጠቁነውት ፡ ድህነት ፡ ላይ ፡ በመውደቁ ፡ የቀድሞ ፡ ክብሩን ፡ መልሶ ፡ ለማግኘት ፡ ከመመኘት ፡ መንፈሱ ፡ አቋርጦ ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ከመሳፍንቶች ፡ ላይ ፡ በወንበዴነት ፡ በመርከብ ፡ የተጫነ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ስላገኘ ፡ ቀምቶ ፡ ሦስት ፡ ወንዶች ፡ ልጆቹን ፡ የነጮችን ፡ ጥበብ ፡ ተምረው ፡ እንዲመጡለትና ፡ የደረሰበትን ፡ ግፍ ፡ እንዲበቀሉለት ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ላከቸው ፡ ትልቁ ፡ ልጁ ፡ ሚስቱንና ፡ ሕፃን ፡ ልጁን ፡ አገሩ ፡ ትቶ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ የንግድና ፡ የባንክ ፡ ሥራ ፡ ተምሮ ፡ ሁለተኛው ፡ ልጁ ፡ መርከብ ፡ መሥራት ፤ ሦስተኛው ፡ ልጁ ፡ የጦር ፡ ሥራ ፡ ተምረው ፡ ተመልሱ ። እነሱም ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፡ የሾጉ

* LES TROIS BAMBOUS የተባለውን ፡ ከ ፡ ROBEBT STANDISH የተጻፈውን ፡ መጽሐፍ ፡ ተመልከት ።

ኖች ፡ (የመሳፍንት ፡ ) ሥልጣን ፡ ቀርቶ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሚይጂ ፡ ዘመን ፡ ተጀምሮ ፡ ደረሱ ።

አባትየው ፡ እንደ ፡ አገራቸው ፡ ልማድ ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ሥልጣን ፡ ለበኩር ፡ ልጁ ፡ ታንገሮ ፡ ለሚባለው ፡ አሳልፎ ፡ ስለሰጠው ፡ ይኸው ፡ ልጁ ፡ በወንድሞቹ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ አገኘ ። እንግዲህ ፡ ሦስቱም ፡ ልጆች ፡ ትምህርታቸውን ፡ ጨርሰው ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ገብተው ፡ በሙያ ፡ በሙያቸው ፡ ሥራቸውን ፡ ሲሠሩ ፡ የበኩር ፡ ልጁ ፡ የተማረውን ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ በንክም ፡ አቋሞ ፡ ገንዘብ፡እያበደረ ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ አግኝቶ ፡ ቀድሞ ፡ የእንጨት ፡ ቤት ፡ በነበረበት ፡ ባባቱ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ በብረትና ፡ በሲሚንቶ ፡ የተገነባ ፡ የመሬት ፡ መናወጥ ፡ የማያስፈራው ፡ ትልቅ ፡ ሕንጻ ፡ ሠራ ።

እንደዚሁም ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ የተዋወቃቸው ፡ ለሥራው ፡ የሚጠቅሙት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ነጮች ፡ ) ከእንግሊዝና ፡ ከጀርመን ፡ አገሮች ፡ እየመጡ ፡ እቤቱ ፡ አርፈው ፡ ከሰነበቱ ፡ በኋላ ፡ ተመልሰው ፡ ይሄዳሉ ። አባትየው ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ በማየት ፡ ልጆቹ ፡ ጃፓንነታቸውን ፡ እየረሱ ፡ የሄዱና ፡ ያገራቸውን ፡ ጠባይና ፡ ባህል ፡ ትተው ፡ የባዕድን ፡ ልማድ ፡ የያዙ ፡ ስለመሰለው ፡ በልቡ ፡ ሥጋት ፡ አደረበት ። ይልቁንም ፡ ባገራቸው ፡ ልማድ ፡ የጨዋና ፡ የመኳንንት ፡ ልጅ ፡ የሆነ ፡ ንግድ ፡ በመነገድ ፡ ገንዘብ ፡ ማግኘት ፡ የማይገባው ፡ ነውር ፡ ስለሆነ ፡ ልጁ ፡ ገንዘብ ፡ በመውደዱና ፡ ነጋዴ ፡ በመሆኑ ፡ በጣም ፡ ቅር ፡ አለው ። በሃይማኖታቸው ፡ እንደሚያስተምርዋቸው ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ከባቶቹና ፡ ካያቶቹ ፡ ጋር ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ሲገናኝ ፡ ያገርን ፡ ፍቅርና ፡ ያገርን ፡ ልማድ ፡ ለልጅ ፡ ልጆቻችን ፡ እንዴት ፡ አድርገህ ፡ አስተማርካቸው ፡ በዚህም ፡ ረገድ ፡ የጣልንብህን ፡ አደራ ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ ፈጸምከው ፡ ብለው ፡ ስለሚጠይቁት ፡ ይህን ፡ በተጠየቅሁ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ እመልስላቸዋለው ፡ ብሎ ፡ አባትየው ፡ አሳብ ፡ ስለገባው ፡ ከመሞቱ ፡ በፊት ፡ ይህን ፡ ያደረበትን ፡ ስጋት ፡ ለልጆቹ ፡ ሊያካፍላቸው ፡ ፈቀደ ። ባጭሩ ፡ በፉሬኖና ፡ በሦስቱ ፡ ልጆቹ ፡ መከከል ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የተደረገው ፡ ንግግር ፡ ጃፓኖች ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ በተቀበሉበት ፡ ዘመን ፡ ባዲሱ ፡ ትውልድና ፡ ባለፈው ፡

ትውልድ ፡ መካከል ፡ የነበረውን ፡ የመንፈስ ፡ ሁኔታ ፡ ስለሚገልጥ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ እንጠቅሰዋለን ።

አባትየው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ንግግር ፡ ይጀምራል ።

"እኔ ፡ የቤተ ፡ ሰባችን ፡ አለቃ ፡ መሆኔን ፡ ሊከራከር ፡ የሚያስብ ፡ ሰው ፡ በመካከላችሁ ፡ ይገኛል ፡ ወይ ? ሲል ፡ ይጠይቃቸዋል ። መልስ ፡ የመለሰለት ፡ ሰው ፡ ስለሌለ ፡ አሁንም ፡ መልስ ፡

በሁሉም ፡ በኩል ፡ ሥልጣኔን ፡ ታውቁልኝ ፡ የለም ፡ ወይ ? ሲል ፡ ደግሞ ፡ ይጠይቃቸዋል ።

አኪራና ፡ ሾዢ ፡ የሚባሉት ፡ ሁለት ፡ ልጆቹ ፤

"በሁሉም ፡ በኩል ፡ እናውቅልሃለን ፡„ ብለው ፡ ይመልሱለታል ፤

የበኩር ፡ ልጁ ፡ ታንዢ ፡ ግን ፡ ዝም ፡ ይላል ።

አባቱም ፡ ተቆጥቶ ፤ " ተናገር ፡ እንጅ ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ አይደለም ? „ ሲል ፡ ይጠይቀዋል ።

ታንዢ ፡ ግን ፡ በአክብሮት ፡ አንገቱን ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ቀለስ ፡ አድርጎ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ይመልስለታል ።

' ወንድሞቼ ፡ አፀቀድመው ፡ በነገሩ ፡ ሳያስቡበት ፡ ነው ፡ የመለሱልህ ፤ እኔ ፡ ከመመለሴ ፡ በፊት ፡ አስባለሁ ። እነሱም ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ አድርገው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ የሰጡህ ፡ መልስ ፡ እንዲህ ፡ በቶሎ ፡ አይመጣላቸውም ፡ ነበር ፡ ብዬ ፡ አስባለሁ ። ለምሳሌ ፡ ወንድሜ ፡ ሾዢ ፡ መርከብ ፡ በሚሠራበት ፡ ቦታ ፡ ለመርከብ ፡ መሥሪያ ፡ የሚሆነውን ፡ ጥሩ ፡ ብረት ፡ ሲያቀልጥ ፡ ከማንኛውም ፡ ሆነ ፡ የብረት ፡ ዓይነት ፡ ጋር ፡ የመቀላቀል ፡ ሥራውን ፡ ሲሠራ ፡ ላንተ ፡ መታዘዝ ፡ የሚገባው ፡ አይመስለኝም ። ወንድሜ ፡ አኪራ ፡ ደግሞ ፡ ስለዘመናዊው ፡ የጦርነት ፡ አቅድ ፡ ጉዳይ ፡ የፈረንሣዮች ፡ ዕውቀት ፡ ከፕሩሲያኖች ፡ ( ከጀርመኖች ፡ ) ዕውቀት ፡ የበለጠ ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ ከኤታ ፡ ማዦሩ ፡ ጋር ፡ ክርክር ፡ በሚያደርግበት ፡ ጊዜ ፡ ላንተ ፡ የሚታዘዝልህ ፡ አይመስለኝም ።

አባቱ ፡ ይህን ፡ አሳብ ፡ ስላልተቀበለው ፡ ልጁ ፡ ታንዢ ፡ ድምፁን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ እንዲህ ፡ ይለዋል ።

" ላቀረብክልኝ ፡ ጥያቄ ፡ ግልጥ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ እመልስልህ ፡ ዘንድ ፡ እሞክራለሁ ። ሳልዋሽህ ፡ እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ ልነግርህ ፡ መፍቀዴ ፡ ይኸውም ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ላለኝ ፡ አክብሮት ፡ አንድ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ። በሁሉም ፡ በኩል ፡ ብለህ ፡ ስትል ፡ ያንተ ፡ አስተዋይነት ፡ የበለጠ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝበት ፡ እውነት ፡ ነው ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አለ ። በዚሁም ፡ ምንም ፡ ሳላመነታ ፡ እታዘዝልሃለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ እኔንና ፡ ወንድሞቼን ፡ አንተ ፡ በማታውቀው ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ገብተን ፡ እንድንማርና ፡ ሥራ ፡ እንድንለምድ ፡ አስበህ ፡ ወደ ፡ ወጭ ፡ አገር ፡ ላክኸን ። በእነዚህም ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ የራሳችን ፡ ዳኞች ፡ እኛው ፡ ራሳችን ፡ ብቻ ፡ ነን ፤ ነገሩ ፡ እንዲህ ፡ እንዲሆን ፡ የማትፈቅድ ፡ ብትሆንማ ፡ ኖሮ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ አትልከንም ፡ ነበር ።

አባትየው ፡ ልጁን ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ተከራክሮ ፡ ሊያሸንፈው ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ ስለተረዳው ፡ ይህንን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አልፎ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ ።

"አሁን ፡ የሰበሰብኳችሁ ፡ የተከበሩትን ፡ አባቶቼን ፡ ልገናኛቸውና ፡ ስለሰጡኝ ፡ አደራ ፡ የሠራሁትን ፡ ልገልጥላቸው ፡ ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ተወላጆቻችሁን ፡ ወዴት እንደምትመሩዋቸው ፡ ለማወቅ ፡ ፈልጌ ፡ ነው ። የምትከተሉት ፡ እርበና ፡ የሌለው ፡ ሕይወታችሁ ፡ እውነተኛ ፡ ዓላማው ፡ ምንድነው ? ፍጻሜውስ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ነው ? ›

የበኩር ፡ ልጁ ፡ ታንዝ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ይመልሳል ።

"አባቴ ፡ ሆይ ፡ ሀብት ፡ የሞላበትን ፡ መርከብ ፡ ከዘረፍንበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ዓላማችን ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የተዛባ ፡ ሆኖ ፡ አያውቅም ። ይኸውም ፡ ጃፓንን ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ የበለጠችና ፡ ያየለች ፡ መንግሥት ፡ ለማድረግ ፡ የፉሬኖንም ፡ ስም ፡ ባገራችን ፡ ካለው ፡ ስም ፡ ሁሉ ፡ የላቀ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ። ከመ አሁንም ፡ መልሼ ፡ እናገራለሁ ። ዓላማዬ ፡ መቼም ፡ ቢሆን ፡ ከመንገዱ ፡ አልተዛባም ። የሥራዬን ፡ አካሄድ ፡ በኖርኩበት ፡ ዓለም ፡ ከሚገኙት ፡ አስፈላጊዎች ፡ ነገሮች ፡ ጋር ፡ የተስማማ ፡ እንዲሆን ፡ አድርጌያለሁ ። ›

አባቱም ፤ እንዲህ ፣ ይለዋል ።

"ልጄ ፣ ሆይ ፤ አንተ ፣ ሳሙራይ ፣ (መኰንን ፣) ነህ ፤ ይህን ፣ ነገር ፣ ረስተኸዋልን ? ሳሙራይ ፣ ሰይፍ ፣ እንደታጠቀ ፣ ኖሮ ፤ ሰይፍ ፣ እንደታጠቀ ፣ ይሞታል ። እንደ ፣ ነጋዴ ፣ በገበያ ፣ ውስጥ ፣ መደብር ፣ አቁሞ ፣ የንግድ ፣ ሥራ ፣ አይሠራም ። አንተ ፣ ግን ፣ ነጋዴ ፣ ሆንክ ፣ ከዚህ ፣ የባሰ ፣ ደግሞ ፣ በለባንክ ፣ ብለህ ፣ የምትጠራውን ፣ ሥራ ፣ ትሠራለህ ፤ እኔ ፣ ግን ፣ በወለድ ፣ አበዳሪ ፣ ብዬ ፣ እጠራሃለሁ ። ለገንዘብ ፣ ብቻ ፣ ከማሰብ ፣ በቀር ፣ ሌላ ፣ አሳብ ፣ ሊኖርህ ፣ ከቶ ፣ አትችልምን ? ›

ልጁም ፣ እንዲህ ፣ ሲል ፣ ይመልሳል ።

"አባቴ ፣ ሆይ ፤ በናንተ ፣ ዘመን ፣ ሰይፍ ፣ ይሠራ ፣ የነበረውን ፣ ሥራ ፣ አሁን ፣ በኛ ፣ ዘመን ፣ የሚሠራው ፣ ገንዘብ ፣ ነው ። ያለ ፣ ገንዘብ ፣ ደካሞች ፣ እንሆናለን ።

የዛሬ ፣ ዘመን ፣ ሰይፎች ፣ የሚገኙት ፣ በገንዘብ ፣ ነው ። የዛሬው ፣ ዘመን ፣ ሰይፎችም ፣ መድፍ ፤ ጠበንጃ ፤ መርከብ ፣ መኪናች ፣ ይባላሉ ። እነሆ ፣ የዛሬ ፣ ዘመን ፣ ሰይፎች ፣ እነዚህ ፣ ናቸው ። እኔ ፣ በምሰበስበው ፣ ሀብት ፣ እነዚህን ፣ ሁሉ ፣ ነገሮች ፣ ልንገዛ ፣ እንችላለን ። አባቶቼ ፣ ሰይፍ ፣ ይታጠቁ ፣ እንደነበረው ፣ እኔም ፣ ሰይፍ ፣ ታጠቅሁ ፣ እንጅ ፣ ሌላ ፣ ምንም ፣ ያደረግሁት ፣ ነገር ፣ የለም ። የተለወጠው ፣ ዓለም ፣ ነው ፣ እንጅ ፣ እኔ ፣ አይደለሁም ። ›

እንዲህ ፣ ሲል ፣ አባቱ ፣ ስለሌላ ፣ ጉዳይ ፣ ልጁን ፣ ይጠቀይዋል ፤ "አሕዝብ ፣ የሆኑትን ፣ የባዕድ ፣ ሰዎች ፣ ለማጥፋት ፣ የምታስብ ፣ ሰው ፣ ሆነህ ፣ ሳለህ ፣ በምን ፣ ምክንያት ፣ ነው ፣ በዚህ ፣ በቤታችን ፣ ውስጥ ፣ በልብህ ፣ ከምትጠላቸውና ፣ ከምትንቃቸው ፣ ዘሮች ፣ ወገን ፣ የሆኑትን ፣ ሰዎች ፣ በእንግድነት ፣ የምትቀበላቸው ? »

ልጁም ፣ እንዲህ ፣ ሲል ፣ ይመልሳል ።

"አባቴ ሆይ ፣ የመዋጋት ፣ ሥራዬን ፣ የምሠራው ፣ እንቅስቅሳቸው ፣ ዘንድ ፣ የተመቹ ፣ ሆነው ፣ ያገኘኋቸውን ፣ መሣሪያዎች ይዤ ነው ። እኔም ፣ ራሴ ፣ በባዕድ ፣ አገር ፣ ሳለሁ ፣ ብዙ ፣ ቤቶች ፣ በዕ

ንግድነት ፡ ተቀብለውኛል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በእንግድነት ፡ የተቀበሉኝ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ከኔ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ፈልገዋል ። አህዛብ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ሥራቸው ፡ እንዲህ ፡ ነው ። በከፈሉኝ ፡ ገንዘብ ፡ መልሼ ፡ እከፍላቸዋለሁ ። ከጥቂት ፡ ወራቶች ፡ በፊት ፡ ያ ፡ ወፍራም ፡ የሆነ ፡ የጀርመን ፡ ሰው ፡ ብሩክነር ፡ የሚባለው ፡ እዚህ ፡ አርፎ ፡ ነበር ። እሱም ፡ ሰካራም ፡ ነው ፤ ሌባ ፡ ነው ፤ አሳማ ፤ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በቢራ ፡ ንግድ ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ባገኘችው ፡ ሙኒክ ፡ በምትባለው ፡ ከተማ ፡ የሚኖር ፡ በቢራ ፡ ሥራ ፡ ከሁሉ ፡ ሰው ፡ የበለጠ ፡ አዋቂ ፡ ነው ። የጌቶቹን ፡ ምሥጢር ፡ ሰርቆ ፡ ይዟል ፡ እኔ ሱም ፡ በዚሁ ፡ ከቤታቸው ፡ አስወጡት ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ቈያልቅ ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ኢቶ ፡ የዚሁኑ ፡ የቡክነርን ፡ ያህል ፡ ቢራ ፡ የመሥራትን ፡ ጥበብ ፡ አጥርቶ ፡ ይማራል ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ይሄዳል ፤ እኔም ፡ በሱ ፡ በኩል ፡ ያሉኝን ፡ እውነተኞች ፡ የሆኑት ፡ አሳቦቹን ፡ ስለሰ ወርኩት ፡ ለራሳችን ፡ የቢራ ፡ ፋብሪካዎች ፡ አቁመን ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ዓይነት ፡ የሆነ ፡ ቢራ ፡ እንሠራለን ። ካውሮፓ ፡ ከሚመጣው ፡ ቢራ ፡ ግማሽ ፡ በግማሽ ፡ ባነሰ ፡ ዋጋ ፡ ወደ ፡ ሺና ፡ አገር ፡ ጠረፎች ፡ ላይ ፡ እየወሰድን ፡ እንሸጠዋለን ። እንደዚህ ፡ አድርገን ፡ በምናገ ኘው ፡ ገንዘብ ፡ መድፎች ፤ መርከቦችና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መኪናዎች ፡ ገዝተን ፡ ከአሕዛቦች ፡ እጅ ፡ ነፃ ፡ ለመውጣት ፡ እንችላለን ። አባቴ ፡ ሆይ ፡ እንደፈቃድህ ፡ ለመሥራት ፡ የምትችል ፡ ብትሆን ፡ ኖሮ ፡ ብሩክነር ፡ የተባለውን ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ጠባዩ ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ አሳማ ፡ አድርገን ፡ እንመለከተው ፡ ነበር ። እኔ ፡ ግን ፡ ከአሕዛቦች ፡ የሚገኙትን ፡ አንዳንድ ፡ ሙያዎች ፡ እንድጠቀምባቸው ፤ የመንግሥታችንም ፡ ደህንነት ፡ እንዲጠበቅ ፡ ለማድረግ ፡ ከሚያስች ሉን ፡ መሣሪያዎች ፡ አንዱን ፡ ለመሥራት ፡ ስል ፡ ይህን ፡ ሌባ ፡ ሰካራም ፡ እንዲረዳኝ ፡ አደረግሁ ።

እንደዚሁ ፡ ሁሉ ፡ ባለጌ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ እንግሊዝ ፡ በቤታ ችን ፡ አርፎ ፡ ነበር ። እሱንም ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ እን ግዳ ፡ አድርገን ፡ ተቀብለነዋል ። ስለምን ? ቢባል ፡ ምክንያቱ ፡ ውብ ፡ የሆኑ ፡ መርከቦች ፡ ለመሥራት ፡ ቀይ ፡ በሆነ ፡ ራሱ ፡ ውስጥ ፡

በዓለም ፡ ላይ ፡ ከሚገኝ ፡ ከማነኛውም ፡ ሰው ፡ የበለጠ ፡ ዕውቀት ፡ ስላለው ፡ ነው ። ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ምንም ፡ ችግር ፡ ሳያገኘው ፡ ለመኖር ፡ የሚችልበት ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ተመልሶ ፡ ገብቷል ። ነገር ፡ ግን ፡ በወንድሜ ፡ በሾገር ፡ መሪነት ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ ውቦች ፡ ከሆኑት ፡ መርከቦች ፡ ሁሉ ፡ የበለጡ ፡ ውቦች ፡ መርከቦች ፡ ለመሥራት ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፡ ትቶልን ፡ ሂዷል ። ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ብልግናውን ፡ ችለን ፡ መኖራችን ፡ የሚገባ ፡ ነገር ፡ አይዶለምን ? ሊቪሴ ፡ የሚባል ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ እንግሊዝ ፡ ነበር ። እሱም ፡ ሲመለከቱት ፡ መልኩ ፡ እንደዚያ ፡ ነው ። መልካም ፡ አስተዳደግ ፡ የሌለው ፡ ተራ ፡ የቀን ፡ ሠራተኛ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሲነጋገር ፡ ሳለ ፡ ባለማቋረጥ ፡ በሚያኮከው ፡ ጭንቅላቱ ፡ ውስጥ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እያልን ፡ እኛ ፡ በመቀማት ፡ ላይ ፡ ያለነው ። ብዙ ፡ ዕውቀቶች ፡ ይገኙበታል ። እሱም ፡ ገንዘብ ፡ ፈላጊ ፡ ነው ። ብዙ ፡ ሰጥቼዋለሁ ። አሁንም ፡ ደግሞ ፡ የበለጠ ፡ እሰጠዋለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ለዚሁ ፡ ለውጥ ፡ ዛሬ ፡ እኛ ፡ ከቀድሞ ፡ ጌቶቹ ፡ ላይ ፡ የምንገዛቸውን ፡ ውብ ፡ የሆኑትን ፡ ጨርቆች ፡ እንዴት ፡ አድርገን ፡ በመኪና ፡ ለመሥራት ፡ እንደምንችል ፡ ምሥጢሩን ፡ ያስተምረናል ። እኛም ፡ ከሌላ ፡ ዘንድ ፡ ጨርቅ ፡ መግዛት ፡ የማያስፈልገን ፡ መሆኑ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሊወዳደረን ፡ እንደማይችል ፡ አድርገን ፡ በጣም ፡ ዝቅተኛ ፡ በሆነ ፡ ዋጋ ፡ ለቀረው ፡ ዓለም ፡ እንሸጣለን ።»

ሰው ፡ ገንዘብን ፡ ለአገር ፡ ጠቃሚዎች ፡ ለሆኑት ፡ ለታላላቅ ፡ ጉዳዮች ፡ ቢያደርገው ፡ የሚያስመሰግን ፡ እንጂ ፡ ቅር ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ስለሌለበት ፡ አባትዬው ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ልጁን ፡ ሊወቅሰው ፡ ወይም ፡ ሊከራከረው ፡ አልፈለገም ። ነገር ፡ ግን ፡ የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ በሰው ፡ መንፈስ ፡ ውስጥ ፡ ስር ፡ ሰዶ ፡ ኃይል ፡ ሲያገኝ ፡ ጠባዩን ፡ ሁሉ ፡ እንደሚያበላሸው ፡ የታወቀ ፡ በመሆኑ ፡ በሚወዳቸው ፡ ልጆቹ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ አደጋ ፡ እንዳይደርስባቸው ፡ ፈርቶ ፡ ፉሬኖ ፡ የቤተ ፡ ሰቡ ፡ ምሳሌ ፡ በሆኑት ፡ "በሦስቱ ፡ ሸንበቆች" ፡ ለሚመስላቸው ፡ ለሦስቱ ፡ ልጆቹ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ የመጨረሻ ፡ ምክሩን ፡ ሰጥቶ ፡ ያሰናብታቸዋል ።

«. . . ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ለናንተ ፡ መናገሬ ፡ ስለ
ፈራሁላችሁ ፡ ነው ። ለቤተ ፡ ሰባችን ፡ ስም ፡ ለፉሬኖ ፡ እሰጋለሁ ።
ለተቀደሰችው ፡ አገራችንም ፡ እፈራላታለሁ ። ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ መጥፎ ፡
ምክሮች ፡ ሰጥቻችሁ ፡ ይሆናል ። አድርጌው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዓይኖቼ ፡
እንደ ፡ አሁን ፡ ተገልጠው ፡ ስላላዩልኝ ፡ ነው ። ሳልዘገይ ፡ ሂጄ ፡
ከያቶቼና ፡ ከእናንተም ፡ አያቶች ፡ ይቅርታን ፡ እለምናለሁ ። ነገር ፡
ግን ፡ ልነግራችሁ ፡ የምፈልገው ፡ ነገር ፡ እነሆ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

ይኸውም ፡ የመጨረሻ ፡ ቃሌ ፡ ይሆናል ። የውርደት ፡ ሥራ ፡
መሥራት ፤ ማታለል ፤ መሸፈጥ ፤ ገንዘብን ፡ አለመጠን ፡ መውደድ ፤
ለናንተም ፡ ሆነ ፡ ላገራችሁ ፡ ከመጉዳት ፡ በቀር ፡ አይጠቅማችሁም ።
አሕዛቦች ፡ የሆኑት ፡ የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ ቢበረታባቸው ፡ ዝቅተኞች ፡
ሕዝቦች ፡ በመሆናቸው ፡ የወረሱት ፡ የግል ፡ ባህርይ ፡ ሆኖባቸው ፡
ነው ። የሚያስከትለውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ለማየት ፡ ረጅም ፡ ዕድሜ ፡
አታገኙም ፡ ይሆናል ። ምናልባት ፡ ልጆቻችሁም ፡ አያዩትም ፡ ይሆ
ናል ።

አሁን ፡ ሦስቱ ፡ ሸንበቆች ፡ ቀጥ ፡ ብለው ፡ ቆመዋል ። ከማፎ
ቻችው ፡ ላይ ፡ የሚገኙትን ፡ ቅጠሎቻቸውን ፡ ነፋስ ፡ ያውለበልባቸ
ዋል ። ማንኛውም ፡ ማዕበል ፡ ቢነሣ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ሊጥላቸው ፡
አይችልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ጠባይን ፡ የሚያበላሸው ፡ ትል ፡ (ነቀዝ ፡)
ስሮቻቸውን ፡ እየበላ ፡ መንግሎ ፡ ሊጥላቸው ፡ ይችላል ። ልጆቼ ፡
ሆይ ፤ ጠባይን ፡ የሚያበላሸው ፡ ነቀዝ ፡ በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡
ነው ፡ ሥራውን ፡ የሚሠራው ። አያቶቻችን ፡ ባሉበት ፡ በተከበረው ፡
ቦታ ፡ መጥታችሁ ፡ በተገናኛችሁኝ ፡ ጊዜ ፡ ሦስቱ ፡ ሸንበቆች ፡ ራሳ
ቸውን ፡ ሁልጊዜ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ቀጥ ፡ አድርገው ፡ እንደቆሙ ፡
ናቸው ፤ ማንኛውም ፡ የውርደት ፡ ሥራ ፡ አላበላሻቸውም ፡ ብላችሁ ፡
እንድትነግሩኝ ፡ እፈልጋለሁ ። የበኵር ፡ ልጄ ፡ ታንገ ፡ ሆይ ፤
በልቤ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ቂም ፡ የለም ፤ በናንተም ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡
ቂም ፡ እንዳይኖር ፡ አድርጉ ። እንግዲህ ፡ በጣም ፡ ደክሞኛልና ፡
ሂጄ ፡ ልተኛ ።»

ይህ ፡ ደራሲ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በዚህ ፡ በጻፈው ፡ የልብ ፡
ወለድ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚጠራቸውን ፡ ሰዎች ፡ ስማቸውን ፡

እየለወጠ ፡ ቢያቀርብልን ፡ ወደፊት ፡ በዚህ ፡ በጃፓን ፡ ታሪክ ፡
ውስጥ ፡ እንደምናገኘው ፡ ሁሉ ፡ ፉሬኖ ፡ በተባለው ፡ ሰው ፡ ስም ፡
ተሠይሞ ፡ የሚገኘው ፡ የታላቁ ፡ የጃፓን ፡ የንግድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡
የሆኑት ፡ የእነ ፡ ሚትሱኢ ፡ ታሪክ ፡ መሆኑ ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ።

## የኢንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡ ስለመስፋፋቱ ፡
## ሚትሱኢና ፡ ሚትሱቢሺ ።

ካ፲፪ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ላይ ፡ ማለት ፡ ሞንጎሎች ፡ የጃፓ
ንን ፡ አገር ፡ ሊወሩት ፡ አስፈርቶ ፡ በነበረበት ፡ ዘመን ፡ የጦር ፡ ዲክ
ታተሮች ፡ ( አባይ ፡ ገነኖች ፡ ) የመንግሥቱ ፡ ዋና ፡ ባለሥልጣኖች ፡
ሆኑ ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ ለስሙ ፡ ብቻ ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ሲቀመጥ ፡
የአገር ፡ አስተዳዳሪነቱን ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ ለእነዚሁ ፡ መሳፍንቶች ፡
ለቀቀላቸው ።

ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ‹ ሾጉኖች › የተባሉት ፡ እነዚህ ፡ ዓባይ ፡
ገነኖች ፡ ( መሳፍንቱ ) ሰባት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ያህል ፡ የበላይነቱን ፡
ሥልጣን ፡ ይዘው ፡ ኖሩ ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ አውሮፓ ፡ አቆጣጠር ፡
እስከ ፡ 1868 ዓ. ም. ድረስ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። በዚሁ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡
የነበሩት ፡ ‹ ዳይሚዎ › የሚባሉት ፡ የጃፓን ፡ መኳንንቶች ፡ ( አገረ ፡
ገዦዎች ፡ ) ቁጥራቸው ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ይሆን ፡ ነበር ። የቀ
ረው ፡ ሕዝብ ፡ ገበሬዎች ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩና ፡
ነጋዴዎች ፡ እየሆኑ ፡ ለእነዚሁ ፡ መኳንንቶች ፡ በመታዘዝና ፡ በመገ
ዛት ፡ ከመኖር ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ መብት ፡ አልነበራቸውም ። ይኸ
ውም ፡ በጭሩ ፡ ባውሮፓ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ‹ ፊዎዳሊቴ ፡ › የመሳፍ
ንት ፡ ግዛት ፡ የሚባለውን ፡ የመሰለ ፡ ነው ።

የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እንዳይገቡ ፡ ተከልክሎ ፡ ተዘግተው ፡
የነበሩትን ፡ የጃፓንን ፡ አገር ፡ በሮች ፡ አውሮፓውያን ፡ በጦር ፡ ጉልበት ፡
ሰብረው ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ ጃፓኖች ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡
ተቀላቅለው ፡ መኖር ፡ ግዴታ ፡ ሆነባቸው ። ሆኖም ፡ ልዩ ፡ ጠባይ ፡
ያላቸው ፡ ሕዝብ ፡ መሆናቸውን ፡ የሚገልጥ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አሳይተ
ዋል ። ለምሳሌ ፡ አገራቸው ፡ የገቡት ፡ አሜሪካኖች ፤ እንግሊዞችና ፡



ሙ ት ሱ ሂ ቶ ፡ « ሜ ይ ጊ »

የተባለው ፡ ጃፓንን ፡ ያሠለጠነ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ።

( ማሴና ፡ ይስሐቅ ፡ ከጻፉት - የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የተቀዳ ፡ ስዕል ።

ፈረንሣዮች ፡ እንደ ፡ መተያያና ፡ እንደ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ እያደረጉ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በያይነቱ ፡ ዕቃና ፡ ጌጥ ፡ ሰጥተውት ፡ ነበር ።

ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግን ፡ እንኳንስ ፡ ሊሠራበትና ፡ ሊያጌጥበት ፡ ይቅርና ፡ በእጁ ፡ እንኳ ፡ ሳይነካው ፡ የተባለው ፡ ጌጥና ፡ ዕቃ ፡ ከ፴ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ባንድ ፡ አሮጌ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ወድቆ ፤ ዝጎ ፤ ቆሽሾና ፡ ተበላሽቶ ፡ ተገኘ ፡ ይባላል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ከ1855 ዓ ም (እ. ኤ. አ.) ጀምሮ ፡ ጃፓኖች ፡ ያውሮፓን ፡ ጥበብ ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችን ፤ የቴክኒክን ፤ የመኪናዎችን ፤ የሲያንስንና ፡ የንግድን ፡ ዕውቀቶች ፡ የሚገኙበትን ፡ ድርጅቶች ፡ አቋቋሙ ።

ጃፓን ፡ የሥልጣኔን ፡ ጥበብ ፡ መቀበል ፡ ወዲያው ፡ እንደ ፡ ጀመረች ፡ ከሁሉ ፡ ነገር ፡ ይልቅ ፡ የሚያስፈልጋት ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ማቋቋም ፡ መሆኑን ፡ በቶሎ ፡ ተረዳችው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ብረት ፤ ወርቅና ፡ ሌላም ፡ አስፈላጊዎች ፡ የሆኑት ፡ ማዕድኖች ፡ የሌሏት ፡ ደሀ ፡ አገር ፡ ሆና ፡ ሳለች ፡ ባለ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ለመሆን ፡ ያደረበትን ፡ ምኞት ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ አስደናቂ ፡ ትጋትና ፡ አስተዋይነት ፡ ልትፈጽመው ፡ እንደቻለች ፡ ታሪኳን ፡ የመረመሩት ፡ ሰዎች ፡ ሊረዱት ፡ አልቻሉም ። እንደዚሁም ፡ አሣ ፡ አጥማጅና ፡ ከብት ፡ አርቢ ፡ ሆኖ ፡ በድህነት ፡ ይኖር ፡ የነበረው ፡ ሕዝቧ ፡ ከእንቅልፉ ፡ ተነሥቶ ፡ አምሳ ፡ ዓመት ፡ በማይሞላ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ባደረገው ፡ እርምጃ ፡ ከተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ ጋር ፡ በሥልጣኔ ፡ ለመወዳደር ፡ ከሚችልበት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ ደረሰ ? ከየፋብሪካው ፡ እየሠራ ፡ በሚያወጣውም ፡ ከጥጥ ፡ በተሠራ ፡ ጨርቃጨርቅ ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ጋር ፡ ሊፎካከርና ፡ ሊበልጥም ፡ ቻለ ? በ1854 ዓ ም ፡ ሃያ ፡ ስድስት ፡ ሚሊዮን ፡ የነበረው ፡ የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ ቁጥር ፡ በዓመት ፡ በዓመቱ ፡ እየጨመረ ፡ ሄዶ ፡ በ1934 ዓ ም እንደምን ፡ ሰባ ፡ ሚሊዮን ፡ ሆነ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ የጃፓንን ፡ ሕዝብ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የተደነቀ ፡ ትንግርተኛ ፡ አደረገው ።

ይልቁንም ፡ ደግሞ ፡ በ1905 ዓ ም ጃፓን ፡ መስኮብን ፡ በጦርነት ፡ ድል ፡ በማድረጓ ፡ አውሮፓና ፡ አሜሪካ ፡ የመደነቅ ፤ የሥጋትና ፡ የፍራቻ ፡ ስሜት ፡ ተቀላቅሎ ፡ አደረባቸው ።

እንግዲህ ፡ ጃፓን ፡ ከዚህ ፡ አስደናቂ ፡ ከሆነው ፡ ዓላማ ፡ እን ዴት ፡ አድርጋ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለመድረስ ፡ እንደቻለች ፡ ለመረዳት ፡ ሲፈለግ ፡ የተከተለችውን ፡ መንገድ ፡ የመረመሩት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ መግለጫ ፡ ይሰ ጡናል ።

ያውሮፓ ፡ አገሮች ፡ ሊሠለጥኑ ፡ የቻሉት ፡ አንዳንድ ፡ የግል ፡ ሰዎች ፡ እየወጡ ፡ ባከናወኑት ፡ የጥበብና ፡ የዕውቀት ፡ ሥራ ፡ ተመር ተው ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ሲያደርጉ ፡ እርምጃቸው ፡ በዝግታ ፡ እየ ተከናወነ ፡ በመሄዱ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አስፈልጓቸዋል ። ጃፓን ፡ ግን ፡ እርምጃዋ ፡ የተከናወነው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቷና ፡ በመንግሥቷ ፡ መሪ ነትና ተጠባባቂነት ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ ነው ። መሪዎቿ ፡ ጉልበቷ ፡ እን ዳይባክን ፡ ለማድረግ ፡ ሲሉ ፡ ማነኛውም ፡ ሥራ ፡ ከመወጠኑ ፡ በፊት ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጥንቃቄና ፡ አስተዋይነት ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲጠና ፡ አደ ረጉ ። ባንድ ፡ ሰው ፡ አካል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ሕዋሳቶች ፡ ሁሉ ፡ የሚያንቀሳቅሱት ፡ አንድ ፡ ልብና ፡ አንድ ፡ አንጎል ፡ ብቻ ፡ እንደሆኑ ፡ ሁሉ ፡ በጃፓንም ፡ አገር ፡ እንደዚሁ ፡ ባንኮችን ፤ ኢን ዱስትሪዎችን ፤ ባለሥልጣኖችን ፤ የቀን ፡ ሠራተኞችን ፤ ዲፕሎማቶችን ፤ ነጋዴዎችን ፤ የሚያንቀሳቅሷቸው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቷና ፡ መንግሥቷ ፡ ናቸው ። ባውሮፓ ፡ ላንድ ፡ መንግሥት ፡ ያካላቱ ፡ ሕዋሳቶች ፡ የሆ ኑት ፡ የሥራ ፡ ድርጅቶች ፡ ሁሉ ፡ በግል ፡ ባለቤቶች ፡ የተቋቋሙና ፡ የሚካሄዱ ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በመከራከርና ፡ በመሮካከር ፡ ጉልበታቸውን ፡ ሲያባክኑ ፡ ይታያሉ ። በጃፓን ፡ አገር ፡ ግን ፡ እነዚህን ፡ የሥራ ፡ ሕዋሳቶች ፡ እየፈጠረ ፡ ካቋቋማቸው ፡ በኋላ ፡ የሚያካሄዳቸው ፡ መንግሥቱ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ኢንዱስትሪዎቿንም ፡ ዋኖች ፡ ሆነው ፡ የሚቆጣጠርዋቸውና ፡ የሚመር ዋቸው ፡ "ሚትሱኢ ፡ "ና" ሚትሱቢሺ ፡ " የሚባሉት ፡ ሁለት ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

አንድነትን ፡ የሰጣቸው ፡ ይህ ፡ የኅብረት ፡ መሣሪያ ፡ የተቋቋ መው ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ ነው ? የሚከናወነ ውስ ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ ነው ? ቢባል ፡ መግለጫው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተዘረዘረው ፡ ነው ።

ከ1871. ዓ. ም. ፡ በፊት ፡ (እ. አ. አ.) በጃፓን ፡ አገር ፡ የነበረው ፡
ሀብት ፡ ሁሉ ፡ የሚገኘው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡
በሚሆኑት ፡ ‹ዳይሚዎስ› በሚባሉት ፡ መኳንንቶች ፡ እጅ ፡ ነበር ።
ሀብታሞቹም ፡ የመሳፍንትና ፡ የመኳንንት ፡ ወገኖች ፡ ብቻ ፡
ነበሩ ። ከእነዚሁም ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ መካከል ፡ የፋብሪካ ፡
መኪናዎች ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ለማስመጣትና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ስፔ
ሲያሊስቶች ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ለመቅጠር ፡ የሚችሉበት ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡
ገንዘብ ፡ (ካፒታል ፡) ያላቸው ፡ ከመሳፍንትና ፡ ከመኳንንት ፡ ወገን ፡
የሆኑ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ስምንት ፡ ወይም ፡ አሥር ፡ ብቻ ፡ ይሆኑ ፡ ነበር ፡
መጀመሪያ ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ በ1862 ዓ. ም. ፳ ፡ ሺህ ፡ ማዳ
ወሪያ ፡ (broches) ያለው ፡ የፈትል ፡ ፋብሪካ ፡ የተከለ ፡ ሳታውማ ፡
የሚባል ፡ መስፍን ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ በ1870 ዓ. ም. የመጀመ
ሪያውን ፡ የሐር ፡ ፋብሪካ ፡ ያቋቋመ ፡ ማኤበሺ ፡ የሚባለው ፡ መስ
ፍን ፡ ነው ። ብረት ፡ እያቀለጠ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በቧምቧ ፡ ቅርጽ ፡
የሚበጁትን ፡ የብረት ፡ ዕቃዎች ፡ የሚሠራውን ፡ ፋብሪካ ፡ በጃፓን ፡
አገር ፡ መጀመሪያ ፡ የተከሉት ፡ "ሚትሱኢ" ፡ የተባሉት ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡
ናቸው ። ከቀሩት ፡ የጃፓን ፡ የመሳፍንትና ፡ የመኳንንት ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡
ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ገንዘብና ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ልማድ ፡ ያላቸው ፡
እነዚሁ ፡ "ሚትሱኢ" ፡ የተባሉት ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ናቸው ። የቀሩት ፡
መሳፍንቶችና ፡ መኳንንቶች ፡ ልጆቻቸው ፡ ወታደሮችና ፡ የመንግሥት ፡
ሠራተኞች ፡ ሲሆኑ ፡ ሚትሱኢ ፡ የሚባለው ፡ መስፍን ፡ ብቻ ፡ ተወ
ላጆቹ ፡ ወደ ፡ ንግድ ፡ ሥራ ፡ ተመርተው ፡ በዚሁ ፡ ጥበብ ፡ እየሠ
ለጠኑበት ፡ ሄዱ ። ሙትሱሂቶ ፡ የተባለው ፡ የጃፓን ፡ ንጉሠ ፡ ነገ
ሥት ፡ በ1868 ዓ. ም. አገሩን ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመ
ምራት ፡ ቆርጦ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ የሚትሱኢ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ በገን
ዘብ ፡ ከቀሩት ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ የበለጡ ፡ ከመሆናቸው ፡
በላይ ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ አስቀ
ድሞ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ እየሠሩ ፡ የኖሩ ፡ በመሆናቸው ፡ የበለጠ ፡
"ኤክስፔሪያንስ" ፡ ማለት ፡ የሥራ ፡ ልማድ ፡ ነበራቸው ።
ነገር ፡ ግን ፡ እነ ፡ ሚትሱኢም ፡ ሆኑ ፡ ወይም ፡ ሌሎቹ ፡ ማነ
ኞቹም ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ከጃፓን ፡ አገር ፡

ወጥተው ፡ የማያውቁ ፡ በመሆናቸው ፡ በኢንዱስትሪ ፡ በኩልም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፤ በጠቅላላው ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ረገድ ፡ የቴክኒክ ፡ ዕውቀት ፡ አልነበራቸውም ።

በዘመናዊው ፡ የሥልጣኔ ፡ መንገድ ፡ እየተመሩ ፡ አገሪቱን ፡ ባለ ኢንዱስትሪ ፡ ለማድረግ ፡ ስፔሲያሊስቶች ፤ መሐንዲሶችና ፡ የሥራን ፡ ድርጅት ፡ ለማካሔድ ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፡ (ኦርጋኒዛተሮች ፡ ) ማግኘት ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነበር ። እነዚህንም ፡ የሥራ ፡ ሊቃውንት ፡ ለማሠልጠን ፡ እነ ፡ ሚትሱኢ ፤ እነ ፡ ሳትሱማ ፤ እነ ፡ ማዩባሺ ፤ የተባሉት ፡ የጃፓን ፡ ሀብታሞች ፡ ችሎታ ፡ አልነበራቸውም ። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ መንግሥት ፡ እጁን ፡ ያገባ ፡ ዘንድ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ።

መጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ጃፓኖች ፡ ራሳቸውን ፡ እስቲችሉ ፡ ድረስ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጆች ፡ የሆኑ ፡ ሠራተኞች ፡ መቅጠር ፡ ግዴታ ፡ ስለሆነባቸው ፤ የጦር ፡ መሪዎቻቸውን ፡ ባዲሱ ፡ የጦር ፡ ትምህርት ፡ እንዲያሠለጥኑላቸው ፡ ፈረንሣዮችን ፡ ቀጠሩ ። በመርከብ ፡ ሥራ ፡ ውሥጥ ፡ ደግሞ ፡ እንግሊዞችን ፤ በትምህርት ፡ ቤቶች ፡ አሜሪካኖችን ፡ አደረጉ ። በየፋብሪካው ፡ ውሥጥም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቴክኒሲያኖችና ፡ ስፔሲያሊስቶች ፡ አድርገዋል ። እኛ ፡ ግን ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውሥጥ ፡ በሰፊው ፡ የምንመለከተው ፡ ጥበብን ፡ ራሳቸው ፡ ሲማሩ ፡ የተከተሉትን ፡ መንገድ ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ ሲያደርግ ፡ ከሁሉ ፡ ነገር ፡ አስቀድሞ ፡ አንድ ፡ የተዘጋጀ ፡ ፕላን ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ መንግሥቱ ፡ በቶሎ ፡ ተረዳው ። ስለዚህ ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ እየሄዱ ፡ የሚማሩትን ፡ ልጆች ፡ የሚልካቸው ፡ መንግሥት ፡ እንጂ ፡ ሀብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ገንዘብ ፡ ካለን ፡ ማ. ይከለክለናል ፡ እያሉ ፡ ልጆቻቸውን ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ይልኳቸው ፡ ዘንድ ፡ አልተፈቀደላቸውም ። መንግሥቱ ፡ ለዋናዋናዎቹ ፡ ጉዳዮች ፡ የሚያቀርባቸውን ፡ ጥያቄዎች ፡ እየመረመሩ ፡ መልሱን ፡ የሚያዘጋጁለት ፡ በዕውቀታቸውና ፡ በችሎታቸው ፡ የተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ አባሎች ፡ ሆነው ፡ የሚሠሩበት ፡ የትምህርት ፡ ከሚሲዮኖች ፡ የሚባሉ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ አቋቋመ ። እነሱም ፡ ለሚቀርቡላቸው ፡ ጥያቄዎች ፡ መልሱን ፡ እያዘጋጁ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ያቀርባሉ ።

የእነሱም ፡ ተግባር ፡ መንግሥቱን ፡ የሚገጥሙትን ፡ ጉዳዮች ፡ መመርመር ፤ መንገዱን ፡ መፈለግና ፡ ማጥናት ፡ ነው ።

ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ሥራ ፡ መንግሥቱ ፡ አደራ ፡ አድርጎ ፡ የጣለባቸው ፡ ሰዎች ፡ በአስተዋይነታቸውና ፡ በገንዘብ ፡ የማይደለሉ ፡ በመሆናቸው ፡ ተፈትነው ፡ ከሺ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ተመርጠው ፡ የተገኙ ፡ ነበሩ ። እነሱም ፡ የአውሮፓን ፡ አገሮች ፡ እየዞሩ ፡ ሲመረምሩና ፡ የታዘዙትን ፡ አሳብ ፡ ለማቅረብ ፡ ጉዳዩን ፡ ሲያጠኑ ፡ ለመንገዳቸው ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ወጭ ፡ ገንዘብ ፡ የሚሰጣቸው ፡ መንግሥት ፡ ነው ።

ከተመለከቱትና ፡ ካደረጉት ፡ ምርመራ ፡ የሚገኘውን ፡ ፍሬ ፡ መጀመሪያ ፡ የሚጠቀምበት ፡ መንግሥት ፡ ነው ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ያውሮፓ ፡ አገሮች ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ረገድ ፡ በየበኩላቸው ፡ ሁሉም ፡ የግል ፡ ዕውቀታቸውን ፡ ብቻ ፡ ይዘው ፡ በጠባብ ፡ መንገድ ፡ ተወስነው ፡ ሲኖሩ ፡ ጃፓን ፡ ግን ፡ በመልክተኞቿ ፡ አማካይነት ፡ የሁሉንም ፡ ዕውቀት ፡ ተመልክታ ፡ እየቀዳች ፡ ከሁሉም ፡ በኩል ፡ አዋጥታ ፡ ያስማማችውንና ፡ የቀሰመችውን ፡ ምሳሌ ፡ መዝገብ ፡ አድርጋ ፡ ሷለሠራችበት ፡ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከሁሉም ፡ የበለጠ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ቻለች ።

በዚህም ፡ አኳኋን ፡ የቴክኒክን ፡ ዕውቀቶች ፡ ሰብስበው ፡ የያዙት ፤ መንግሥት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ልኮ ፡ ያስተማራቸው ፡ ስፔሲያሊስቶች ፡ በመሆናቸው ፡ አገሪቱ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ የምታገኝበትን ፡ መንገድ ፡ ተከትሎ ፡ የማሠራቱን ፡ አደራ ፡ የተቀበለ ፡ እሱው ፡ ራሱ ፡ መንግሥቱ ፡ ሆነ ። የኢንዱስትሪን ፡ ሥራ ፡ ከኢምንት ፡ አንሥቶ ፡ አሳቡን ፡ እየፈጠረ ፡ የሚያቋቁመውና ፡ የሚያካሂደው ፡ የኮሙኒካሲዮንንም ፡ ሥራ ፡ የሚያከናውነው ፡ መንግሥቱ ፡ ወይም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ነበር ።

ጃፓን ፡ አንድነትን ፡ አግኝታ ፡ ኢንዱስትሪን ፡ እንድታቋቁም ፡ ከሁሉ ፡ ነገር ፡ አስቀድሞ ፡ አስፈላጊው ፡ ነገር ፡ የፊውዳል ፡ አገዛዝ ፡ እንዲቀር ፡ ማድረግ ፡ ስለነበረ ፡ "ዳዪሚዎ" የተባሉት ፡ መኳንንቶች ፡ በ1871 ፡ ዓ. ም. ( እ. አ. አ. ) ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡

የመጣውን ፡ የመሳፍንትነት ፡ መብታቸውን ፡ በፈቃዳቸው ፡ ለቀቀው ፡ ግዛታቸውንና ፡ ጉልታቸውን ፡ በፈቃዳቸው ፡ ለመንግሥት ፡ አስረከቡ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መንግሥቱ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ የሚገኙትን ፡ ርስቶች ፡ ሁሉ ፡ ጠቅልሎ ፡ በእጁ ፡ ያዘና ፡ ለሕዝቡ ፡ እያከፋፈለ ፡ በመስጠት ፡ እንዲለሙና ፡ እንዲሠራባቸው ፡ አደረገ ። ወዲያውም ፡ ከእነዚሁ ፡ ርስቶች ፡ አስይዞ ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ አምስት ፡ ሚሊዎን ፡ ዶላር ፡ ተበድሮ ፡ አዲሶችና ፡ ዘመናዊ ፡ የሆኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የፋብሪካ ፡ መኪናዎች ፡ ገዛ ።

የንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ አማካሪዎች ፡ "ፕላን ፡ የሚያዘጋጅ ፡ ኮሚሲዮን ፡" ተብሎ ፡ የሚጠራውን ፡ በሶቢዬት ፡ መስኮብ ፡ አገር ፡ የሚገኘውን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በመሰለ ፡ መንገድ ፡ ይሠሩ ፡ ጀመር ።

ጃፓን ፡ ያላት ፡ ገንዘብ ፡ የተወሰነ ፡ ጥቂት ፡ በመሆኑ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊና ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ፋብሪካ ፡ ብቻ ፡ እየታየ ፡ እንዲገዛ ፡ ተደረገ ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ማነኛውም ፡ ፕላን ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ከመድረሱ ፡ አስቀድሞ ፡ በብዙ ፡ ጥንቃቄ ፡ እየተመረመረ ፡ ይመከር በታል ።

የጃፓን ፡ መንግሥት ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ያቋቋማቸው ፡ የጥጥ ፡ ፈትል ፣ የጨርቃጨርቅ ፣ የመርከብ ፣ የብርጭቆ ፣ የሸክላ ፡ የክብሪት ፣ የጋዝ ፣ የኤሌክትሪሲቲ ፣ መኪኖችና ፡ ፋብሪካዎች ፡ ናቸው ። ነጋዴዎች ፡ የሆኑት ፡ ታላላቆች ፡ መሳፍንቶች ፡ እነ ፡ ሚትሱኢ ፣ ሳትሱማ ፣ ማኤባሺ ፣ ያቋቋሚቸውን ፡ የግል ፡ ፋብሪካዎች ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡ ስፔሲያሊስቶች ፡ እየሾመና ፡ የብድር ፡ ገንዘብ ፡ እየሰጠ ፡ ሥራውን ፡ የሚያስኬድላቸው ፡ መንግሥት ፡ ነበር ። የድን ጋይ ፡ ከሰል ፣ ነሐስ ፣ ብረት ፡ ሌላም ፡ እነዚህን ፡ የመሰለውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ማዕድን ፡ የሚያወጣ ፡ መንግሥት ፡ ነው ። ሥራውንም ፡ የሚያካሄዱት ፡ ሰዎች ፡ መንግሥት ፡ በገንዘቡ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እየላከ ፡ ያስተማራቸው ፡ ስፔሲያሊስቶች ፡ ናቸው ። ይሁን ፡ እንጅ ፡ እነዚሁም ፡ ስፔሲያሊስቶች ፡ ለፋብሪካዎቹ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ መሐንዲሶች ፣ ዲሬክተሮችና ፡ ፕሮፌሰሮች ፡ ካስተማሩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ 1884 ዓ ም ላይ ፡ የጃፓን ፡ መንግሥት ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እያለ ፡ ገን

ዘብነቱ ፡ የባለ ፡ ግል ፡ ሀብታሞች ፡ ከሆነው ፡ ፋብሪካ ፡ ውስጥ ፡ ሁሉ ፡ እጁን ፡ አወጣ ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ምንግሥቱ ፡ የኤኮኖሚክን ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ እንዳይጣናቸው ፤ የግል ፡ ጥቅም ፡ ውድድር ፡ የሚፈጥረውን ፡ ትጋት ፡ እንዳያሰናክልና ፡ ለእሱም ፡ ለራሱ ፡ የአድሚኒስትራሲዮኑ ፡ ሥራ ፡ አለመጠን ፡ ሲበዛበት ፡ እንዳያስቸግረው ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ አመዛዝኖ ፡ እጁን ፡ ከፋብሪካዎች ፡ ውስጥ ፡ ቢያወጣም ፡ የተጠበበ ቂነቱን ፡ ሥራ ፡ አጥብቆ ፡ ማሠራቱን ፡ አላቋረጠም ።

ይህንንም ፡ የተጠባባቂነት ፡ ሥራውን ፡ የፈጸመው ፡ ገንዘብ ፡ እያበደረ ፡ የቴክኒክንና ፡ የገንዘብን ፡ ሥራ ፡ እየተቈጣጠረ ፡ የተፈ ጥሮ ፡ ሀብቶች ፡ (ማቲየር ፡ ፕረሚዬር ፡) የሆኑትን ፡ የሚገዙ ፡ መሥ ሪያ ፡ ቤቶች ፡ እያቋቋመ ፤ ታናናሾች ፡ የሆኑት ፡ የንግድ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በኅብረትና ፡ በማኅበር ፡ እየተባበሩ ፡ እንዲሠሩና ፡ በዚሁም ፤ ኃይል ፡ እንዲያገኙ ፡ እያስገደደ ፡ ነው ።

እንደዚሁም ፡ በያውራጃው ፡ የኢንዱስትሪን ፡ ሥራ ፡ ለመደገ ፍና ፡ ለማስፋፋት ፡ ሲል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በአዲሱ ፡ የመጨረሻ ፡ ጥበብ ፡ የተሠሩትን ፡ ዋጋቸው ፡ ውድ ፡ የሆነውን ፡ የፋብሪካ ፡ መኪኖች ፤ የወርቅ ፡ ቀለም ፡ መንከሪያ ፤ ለፈትልና ፡ ለሌላም ፡ ይህን ፡ ለመሰለው ፡ ሥራ ፡ የሚያገለግሉትን ፡ ከእንግሊዝም ፡ ሆነ ፡ ከሌላ ፡ አገር ፡ እያስገዛ ፡ በያገሩ ፡ ክፍል ፡ ላሉት ፡ ባለፋብሪካዎች ፡ አከፋ ፈላቸው ።

በ ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. አቅራቢያ ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ መንግሥት ፡ ይዟቸው ፡ የነበረውን ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ ለግል ፡ ባለጥቅሞች ፡ እያስተላለፈ ፡ ራሳቸውን ፡ እንዲችሉ ፡ የማድረግ ፡ ሥራውን ፡ አፋ ጠነ ። ሆኖም ፡ እነዚሁኑ ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ እየተረከቡ ፡ ራሳቸ ውን ፡ ችለው ፡ ለመሥራት ፡ የሚችሉ ፡ ስፔሲያሊስቶችና ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ ያላቸው ፡ ሀብታሞች ፡ ቁጥራቸው ፡ ጥቂት ፡ በመሆኑ ፡ ችግር ፡ ሳይፈጥርበት ፡ አልቀረም ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ልማድ ፡ የሌለውና ፡ የሚንቅ ፡ በመሆኑ ፡ በሚሊ ያርድ ፡ የሚቆጠር ፡ ገንዘብ ፡ ካለው ፡ ሀብታም ፡ ከሆነ ፡ ነጋዴ ፡

ይልቅ ፡ ደሀ ፡ የሆነ ፡ ካህን ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ባለእጅ ፡ ወይም ፡ ከብት ፡ አርቢ ፡ የበለጠ ፡ ክብር ፡ ነበረው ።

የሆነው ፡ ሆኖ ፡ መንግሥቱ ፡ እጁን ፡ ከኢንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ባወጣ ፡ ጊዜ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ሥራውን ፡ ያካሄዱ ፡ የነበሩት ፡ ሀብታሞች ፡ የሆኑ ፡ አንዳንድ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ኢንዱስ ትሪውን ፡ ተረከቡት ። ከዚህ ፡ ወዲላ ፡ መንግሥት ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ በወሰደባቸው ፡ ጊዜ ፡ ስማቸው ፡ መጠራቱ ፡ ቀርቶ ፡ የነበረው ፡ እንደ ፡ ሚትሱኢ ፣ ሳትሱማ ፣ ሚትሱቢሺ ፣ አኩራ ፣ የመሰሉት ፡ ሀብታሞች ፡ ስማቸው ፡ ተመልሶ ፡ ተነሣ ።

እነሱም ፡ ይጎድላቸው ፡ የነበረውን ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ፒታል ፣ የሥራ ፡ ልማድና ፡ የቴክኒክ ፡ ዕውቀት ፡ በመንግሥት ፡ መሪነት ፡ አብ ረው ፡ ይሠሩ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ አገኙ ።

በመጨረሻም ፡ ገንዘባቸው ፡ አለመጠን ፡ እየበረከተ ፡ ከመሄዱ ፡ የተነሣ ፡ ትልቅ ፡ ካፒታል ፡ ያላቸው ፡ በመሆናቸውና ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ በመሠልጠናቸው ፡ ሚትሱኢና ፡ ሚትሱቢሺ ፡ (Mitsui et Mitsubishi) የሚባሉ ፡ ሁለት ፡ የንግድ ፡ ቤቶች ፡ የሆኑ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ከሁሉም ፡ የላቁና ፡ የበለጡ ፡ ሆኑ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ እነ ዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ በቀረው ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ፡ ባውሮፓም ፡ ሆነ ፡ ባሜሪካ ፡ እንደሚገኙት ፡ ነጋዴዎች ፡ ሁሉ ፡ ዋናው ፡ ድካማቸ ውና ፡ ጥረታቸው ፡ ገንዘብ ፡ ለመሰብሰብና ፡ እየበለጸጉ ፡ ለመሄድ ፡ ነው ፡ ቢባል ፡ ጃፓንነታቸውን ፡ ያልረሱ ፡ መሆናቸውን ፡ የሚመሰክሩላቸ ውን ከሌላው ፡ አገር ፡ ሀብታሞች ፡ የሚለዩባቸውን ፡ አንዳንድ ፡ ጠባ ዮች ፡ ሳይለቁ ፡ ኖረዋል ። ይኸውም ፡ ያገራቸውን ፡ መንግሥት ፡ እያከሰሩ ፡ ለመበልጸግ ፡ ሲፈልጉ ፡ አለመታየታቸው ፣ ለገንዘብ ፡ ሲሉ ፡ ከጠላት ፡ ጋር ፡ ሲሻረኩ ፡ አለመገኘታቸውና ፡ ገንዘባቸውን ፡ ለማይ ረባ ፡ ነገር ፡ አለማባከናቸው ፡ ነው ።


መንግሥት ፡ ኢንዱስትሪን ፡ በሚመራበት ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ኢንዱስትሪ ፡ መንግሥቱን ፡ በሚመራበት ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱም ፡ እየተረዳዱ ፡ ተባብረው ፡ በመሥራታቸው ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ሆነው ፡ ይቀጠራሉ ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ለጦር ፡ ሠራዊት ፡ ስንቅና ፡ አስፈላጊውን ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሚያቀርቡ ፡ አኩራ ፡ የሚባሉ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ቢኖሩ ፡ ወይም ፡
በኮቤ ፡ ከተማ ፡ ታላላቅ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ያሏቸው ፡ አካዛኪ ፡ የሚ
ባሉት ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በኦዛካ ፡ ባንኮችና ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ ያሏ
ቸው ፡ ሱሚሞቶ ፡ የሚባሉት ፡ ሀብታሞች ፡ መኖራቸው ፡ የታወቀ ፡
ቢሆንም ፡ ማንኞቹም ፡ ቢሆኑ ፡ ሚትሱኢ ፡ ከሚባሉት ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡
ጋር ፡ ሊወዳደሩ ፡ አይችሉም ። ሚትሱኢ ፡ የተባሉት ፡ በ፲፱፻፴፩ ፡
ዓ. ም. ላይ ፡ ሰባት ፡ ሚሊያርድ ፡ ፍራንክ ፡ ነበራቸው ።
ይኸውም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ከአንድ ፡ ሚሊያርድ ፡
በላይ ፡ ይሆናል ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ታናናሾቹ ፡ ሳይቆጠሩ ፡ ሁለት ፡
መቶ ፡ ሀያ ፡ አራት ፡ የሚሆኑ ፡ ዋና ፡ ዋኖቹ ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡
በእነሱ ፡ ተቆጣጣሪነት ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ ይከሄዱ ፡ ነበር ። በእነዚሁም ፡
በተባሉት ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ወይም ፡ ማኅበሮች ፡ ውስጥ ፡ የሚ
ትሱኢ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ያስቀመጡት ፡ ካፒታል ፡ ወደ ፡ ሀያ ፡ ስድ
ስት ፡ ሚሊያርድ ፡ ፍራንክ ፡ ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ ተገምቷል ። ( ይህን ፡
ጽሑፍ ፡ የቀዳነው ፡ ከፈረንሣይ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ ከጦርነት ፡
በፊት ፡ በነበረው ፡ የፈረንሣይ ፡ ፍራንክ ፡ የምንናገር ፡ መሆናችንን ፡
ላንባቢ ፡ እናሳስባለን ። ) ባጭሩ ፡ የሚትሱኢ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ በጃ
ፓን ፡ የንግድ ፡ ሕይወት ፡ ውስጥ ፡ የያዙት ፡ ደረጃ ፡ ምን ፡ ያህል ፡
ከፍ ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ ለመግለጥ ፡ ያህል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡
ግምት ፡ እንሰጣለን ። በ1933 ዓ. ም. በተደረገው ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡
በጃፓን ፡ አገር ፡ በጠቅላላው ፡ ከሚሠራው ፡ የጥጥ ፡ ጨርቃጨርቅ ፡
ከሆነው ፡ ከመቶ ፡ ሰማኒያ ፡ አምስቱ ፡ 85% በእህል ፡ ከመቶ ፡ አር
ባው ፡ 40% በድንጊያ ፡ ከሰል ፡ ከመቶ ፡ አምሳ ፡ ሰባቱ ፡ 57% ከውጭ ፡
አገር ፡ እየተሠሩ ፡ ወደ ፡ ጃፓን ፡ አገር ፡ በሚገቡት ፡ ወይም ፡ በጃ
ፓን ፡ አገር ፡ ተሠርተው ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እየተሸጡ ፡ በሚወጡት ፡
የኢንዱስትሪ ፡ መኪናዎች ፡ ከመቶ ፡ አርባ ፡ 40% ትርፍ ፡ የሚያገኙ
ባቸው ፡ የሚትሱኢ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ናቸው ። የሚትሱኢ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡
ከዚህም ፡ በቀር ፡ በመርከብ ፤ በማዕድን ፤ በድንጊያ ፡ ከሰልና ፡ ሌሎ
ችም ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉትን ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ በሚሠሩ ፡
ማኅበሮች ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ካፒታል ፡ እያስቀመጡ ፡ ይሠራሉ ።

ስለዚህ ፡ በንግዱ ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ "M.B.K." የተጻፈባቸው ፡ ፊደሎች ፡ ስናገኝ ፡ "Mitsui Bussan Kaisha" ማለት ፡ ነው ። ትርጉሙም ፡ « የሚትሱኢ ፡ ንግድ ፡ ድርጅት ፡ » ማለት ፡ ነው ። በፈረንሣይና ፡ በጀርመን ፡ አገሮችም ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ አሏቸው ።

የነሱ ፡ መለያ ፡ የሆኑት ፡ እነዚሁ ፡ "M.B.K." ፊደሎች ፡ በብዙ ፡ መርከቦች ፤ በፈትል ፡ ፋብሪካዎች ፣ ስኳር ፡ በሚያነጥሩ ፡ መኪናዎች ፤ በባንኮች ፡ በታላላቅ ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ቤቶች ፡ ላይ ፡ ተጽፈው ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሺና ፤ በኮሬና ፡ በማንድሹሪ ፡ አገሮች ፡ ይገኛሉ ። በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ለዚሁ ፡ በጣም ፡ ታላቅ ፡ ለሆነው ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ ዋና ፡ ባለቤት ፡ የሆነው ፡ ባሮን ፡ ሃቹሮኤሞን ፡ ሚትሱኢ ፡ ይባላል ። እሱም ፡ በ1930 ዓ ም በቶኪዮ ፡ ከተማ ፡ በዋናው ፡ የንግድ ፡ ሰፈር ፡ የታላላቆቹን ፡ ያሜሪካ ፡ ባንኮች ፡ ፕላን ፡ መዝገብ ፡ አድርጎ ፡ እሳት ፡ የማያቃጥለው ፤ የመሬት ፡ መናወጥ ፡ የማይደፍረውና ፡ የጦር ፡ አኤሮፕላኖች ፡ በትር ፡ የማያፈርሰው ፡ በጣም ፡ የሚያስደንቅ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሕንፃ ፡ አሠርቷል ። ይህም ፡ ሕንጻ ፡ ስድሳ ፡ ሚሊዮን ፡ ዬን ፡ ፈጅቶበታል ።

በምክር ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚቀመጡት ፡ የሕዝብ ፡ ወኪሎች ፡ የሚመረጡት ፡ በሕዝብ ፡ ድምፅ ፡ ስለሆነ ፡ ሚትሱኢና ፡ ሚትሱቢሺ ፡ የሚባሉት ፡ ሁለቱ ፡ ታላላቆች ፡ የንግድ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ለሕዝቡ ፡ ገንዘባቸውን ፡ እያፈሰሱ ፣ ለመንግሥቱ ፡ ፖሊቲካ ፡ የሚስማሙትን ፡ ሰዎች ፡ እንዲመረጡ ፡ ያደርጉለታል ። ይህንንም ፡ የሚፈጽሙት ፡ «ኢንጋይዳን ፡ » የሚባሉ ፡ መልክተኞች ፡ በያገሩ ፡ እየላኩ ፡ ለሕዝቡ ፡ ገንዘብ ፡ በመስጠት ፡ በማስፈራራትና ፡ በማሸበር ፡ ነው ። ለያንዳንዱ ፡ ድምፅ ፡ የሚከፍሉት ፡ ገንዘብ ፡ ደሆች ፡ በሆኑት ፡ አውራጃዎች ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ዬን ፤ በከተማም ፡ ውስጥ ፡ ስምንት ፡ ወይም ፡ አሥር ፡ ዬን ፡ ስለሆነ ፡ የሕዝብ ፡ ወኪሎች ፡ በሚመረጡበት ፡ ጊዜ ፡ ተመራጮቹ ፡ ለመመረጥ ፡ ወጪ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ገንዘብ ፡ የሚከፍሉላቸው ፡ ሚትሱኢና ፡ ሚትሱቢሺ ፡ የሚባሉት ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ቤቶች ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ የንጉሡ ፡ ነገሥቱን ፡ ፖሊቲካ ፡ የሚደግፉት ፡ የፖሊቲካ ፡ ወገኖች ፡ ሁልጊዜ ፡ ኃይል ፡ እንዲያገኙ ፡ ለማድረግ ፡ ሚትሱኢና ፡



በኦዛካ ፡ ከተማ ፡ የሚገኙት ፡ ብረት ፡ እያቀለጡ ፡ የሚሠሩ ፡ የጃፓን ፡ ከባድ ፡ ኢንዱስትሪዎች ።

( አንቷን ፡ ዚሽካ ፡ ከጻፈው ፡ ከጃፓን ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተቀዳ ፡ ስዕል ። )

ሚትሱቢሺ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ገንዘብ ፡ ወጭ ፡ ያደርጋሉ ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ይልቁንም ፡ ሚትሱኢ ፡ የተባለው ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ ለመንግሥቱ ፡ የሰጠው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሌላም ፡ አገልግሎት ፡ አለ ።

ይኸውም ፡ የገንዘብን ፡ ኃይል ፡ መሣሪያ ፡ እያደረገ ፡ የጃፓን ፡ መንግሥት ፡ የቅኝ ፡ አገር ፡ እንዲያገኝ ፡ በማድረጉ ፡ ነው ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ የጃፓን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ከሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ይልቅ ፡ የገንዘብን ፡ ኃይል ፡ መሣሪያ ፡ አድርጎ ፡ የበለጠ ፡ ሥራ ፡ በመሠራቱ ፡ ብዙ ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ ለመንግሥቱ ፡ ሰጥቷል ። ፎርሞዝና ፡ ሳክሃሊን ፡ የተባሉት ፡ አገሮች ፡ የጃፓን ፡ ቅኝ ፡ አገሮች ፡ ለመሆን ፡ የበቁት ፡ በሚትሱኢ ፡ ብርታት ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ የጃፓን ፡ መንግሥት ፡ ማንድሹኩዎ ፡ የምትባለውን ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ያህል ፡ አድርጎ ፡ ሊይዛት ፡ የቻለው ፡ ሚትሱኢ ፡ ባደረገለት ፡ እርዳታ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ሲያደርጉ ፡ ከመስኮብና ፡ ከቻይና ፡ ጋር ፡ የገጠማቸውን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ትግል ፡ እያሸነፉ ፡ ነው ። እነ ሚትሱኢ ፡ የማይሠሩት ፡ ሥራ ፡ የለም ። ለሰው ፡ ሕይወት ፡ (አሱራንስ ፡) ያደርጋሉ ፤ የጃፓንን ፡ ሕዝብ ፡ ያለብሳሉ ፤ በሠሩዋቸው ፡ መርከቦች ፡ ከአሜሪካና ፡ ከኦሴያኒ ፡ ጋር ፡ የማመላለሻን ፡ ሥራ ፡ ይሠራሉ ። አራት ፡ ሚሊዮን ፡ ኮፒ ፡ በሚያወጡት ፡ ጋዜጦቻቸው ፡ የሕዝቡን ፡ አሳብ ፡ ይመሩታል ፤ ያቋቋሟቸው ፡ ኤሌክትሪኮች ፡ ላገሪቱ ፡ ብርሃንና ፡ ጉልበትን ፡ ይሰጧታል ። የሺሚክ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶቻቸውም ፡ ላገሩ ፡ መሬት ፡ ማዳበሪያ ፡ ፍግ ፡ የሚሆኗትንና ፡ ለመንግሥቱም ፡ ለጦር ፡ መሣሪያ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ነገሮች ፡ ሠርተው ፡ ያቀርባሉ ።

ሚትሱቢሺ ፡ የተባሉት ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ዳግም ፡ ደረጃቸው ፡ ከሚትሱኢ ፡ ቀጥሎ ፡ ይመጣል ። በሚትሱቢሺ ፡ ተቆጣጣሪነት ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ የሚካሄዱት ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ቁጥራቸው ፡ ዘጠና ፡ ሁለት ፡ ነው ። በእነዚህ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ያስቀመጡት ፡ ካፒታላቸው ፡ አሥራ ፡ አራት ፡ ሚሊያርድ ፡ ፍራንክ ፡ ይሆናል ። የግል ፡ ተቀማጭ ፡ ገንዘባቸው ፡ ግን ፡ በ1934 ዓ. ም. ላይ ፡ አራት ፡

ሚሊያርድ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ተገምቷል ። አሁን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ ስለ ፡ ጦር ፡ መሣሪያ ፡ ጉዳይ ፡ እንናገራለን ።

ከአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ (ዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡) ጋር ፡ በደረ ጉት ፡ የንግድ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ጃፓኖች ፡ ከሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ የጦር ፡ መርከብ ፡ እንዲገዙ ፡ ተፈቅዶላ ቸዋል ፡ የሚል ፡ አንቀጽ ፡ ነበር ።

ወደ ፡ 1880 ዓ. ም. አቅራቢያ ፡ የጃፓን ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የጦር ፡ መኰንን ፡ ማዦር ፡ ሙራታ ፡ ትሱኔዮሺ ፡ የሚባል ፡ የጠበንጃን ፡ አሠራር ፡ ማወቅ ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ አስቦ ፡ አንድ ፡ ጠበንጃ ፡ ሠራ ፤ ይኸ ውም ፡ በፈረንሣይም ፡ ሆነ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ከሚሠሩት ፡ ጠበንጆች ፡ ጋር ፡ የሚተክከል ፡ ጥሩ ፡ መሣሪያ ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሱ ፡ መዝገብ ፡ የሚሠራ ፡ አንድ ፡ የጠበንጃ ፡ ፋብሪካ ፡ ተቋቋመ ። ይኸውም ፡ (Made in Japan) በጃፓን ፡ አገር ፡ ተሠራ ፡) በሚለው ፡ ምልክት ፡ ይታወቃል ። የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የሚሠሩት ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ የጃ ፓን ፡ ፋብሪካዎች ፡ የሚከሄዱት ፡ በመንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ ነበር ። የሚያስኬዱቸውም ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶች ፡ ነበሩ ። ይኸውም ፡ እስከ ፡ 1905 ዓ. ም. ድረስ ፡ ቆየ ።

በኋላ ፡ ግን ፡ በ1905 ዓ. ም. (Japan Steel Works) (የጃፓን ፡ የጥሩ ፡ ብረት ፡ ሥራ ፡) የሚል ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ሚሊዮን ፡ ዩን ፡ ካፒታል ፡ ያለው ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ተቋቋመ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ፋብሪካን ፡ ማስኬድ ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶች ፡ ተግባር ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ሆነና ፡ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ የግል ፡ ባለገንዘቦችና ፡ የውጭም ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ያስኬዱት ፡ ጀመር ። በመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ ያሉት ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ፋብሪካዎች ፡ አለመጠን ፡ ብዙ ፡ መሣሪያ ፡ እየሠሩ ፡ ስለሸጡ ፡ ፋብሪካዎቻቸው ፡ በጣም ፡ እየተስፋፉ ፡ በመሄዳቸው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ከሚገኙት ፡ ከዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ፋብሪካዎች ፡ ጋር ፡ የሚተካከሉ ፡ ሆኑ ። ጦርነቱ ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ በእነዚሁ ፡ ፋብሪ ካዎች ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ ሆኖባቸው ፡ ስለነበረ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የሚገዛ ፡ ሲጠፋ ፡ ከችግር ፡ ላይ ፡ ወደቁ ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ በሺና ፡ አገር ፡ የርስ ፡ በርስና ፡



ባሁን ፡ ጊዜ ፡ ለጃፓን ፡ ታላላቅ ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ ባለቤት ፡ የሆነው ፡ ወጣቱ ፡ ባሮን ፡ ሚትሱኢ ፡ ከባለቤቱ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ አውሮፓን ፡ ሲጎበኙ ፤ ፀቤርሊን ፡ ከተማ ።

(ከእንቷን ፡ ዚሽካ ፡ መጽሐፍ ፡ ውሥጥ ፡ የተቀዳ ፡ ስዕል ።)

የሸፍትነት ፡ ውጊያ ፡ ስለተፈጠረ ፡ ፋብሪኮቹ ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸውን ፡
ወደዚያ ፡ እየላኩ ፡ ይሸጡ ፡ ጀመር ። በኋላም ፡ ሺናውያን ፡ በእነዚህ ፡
የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ መልሰው ፡ ጃፓኖችን ፡ ወግተዋቸዋል ።

እነዚህም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ፋብሪኮች ፡ ጃፓን ፡ በ1895 ዓ. ም.
ከሺና ፡ ጋር ፤ በ1905 ዓ. ም. ከመስኮብ ፡ ጋር ፤ ተዋግታ ፡ ላገኘ
ቻቸው ፡ ድሎች ፡ በጣም ፡ ረድተዋታል ።

ሚትሱኢ ፡ የተባሉት ፡ ቤተሰቦች ፡ ከ1849 ዓ. ም. ጀምሮ ፡
ብረት ፡ የሚያቀልጥ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ነበራቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ መንግ
ሥት ፡ ይህ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ዘመናዊ ፡ የሆነ ፡ መኪና ፡ እንደሚነድ
ለው ፡ ተመልክቶ ፡ ከዲሱ ፡ ሥልጣኔ ፡ የቴክኒክ ፡ ዕውቀት ፡ የተገ
ኙትን ፡ መኪናዎች ፡ እንዲያገኙ ፡ አደረገላቸው ። በኋላም ፡ የድን
ጋይ ፡ ከሰል ፡ በብዙ ፡ ወደ ፡ ሚገኝበት ፡ ከሺናና ፡ ከኮሬ ፡ አገሮች ፡ አን
ጻር ፡ ወደሚገኘው ፡ ያዋታ ፡ ወደሚባለው ፡ አገር ፡ ፋብሪካቸውን ፡
አዛወሩት ። ከተዛወረም ፡ በኋላ ፡ በ1901 ዓ. ም. ፋብሪካው ፡ ሥራ
ውን ፡ መሥራት ፡ ጀመረ ። በመስኮብና ፡ በጃፓን ፡ መካከል ፡ ጦር
ነት ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ፋብሪካ ፡ በያይነቱ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡
ስለሠራ ፡ ሥራውን ፡ በጣም ፡ እያስፋፋው ፡ ሄደ ። በ1912 ዓ. ም. ይህ ፡
ፋብሪካ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሺ ፡ ቶን ፡ ብረት ፡ እያቀለጠ ፡
ይሠራ ፡ ጀመር ።

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሚትሱኢና ፡ ሚትሱቢሺ ፡ የተባሉት ፡ ቤተሰ
ቦች ፡ ብረት ፡ እያቀለጠ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራውን ፡ ፋብ
ሪካቸውን ፡ በጣም ፡ የተስፋፋ ፡ አደረጉት ። በሁኑ ፡ ዘመን ፡ ከሁ
ሉም ፡ የሚበልጠው ፡ የኤኮኖሚ ፡ ጉዳይ ፡ መሆኑን ፡ ስለተረዱት ፡
ጃፓኖች ፡ ማኅበራዊ ፡ ሕይወታቸው ፡ ሚትሱኢና ፡ ሚትሱቢሺ ፡ በሚ
ባሉት ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ እንዲመራ ፡ ፈቀዱ ። በሕዝቡ ፡ ማኅ
በራዊ ፡ ሕይወትና ፡ በእነዚሁ ፡ በሁለቱ ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ ሆኖ ፡
ሚዛኑ ፡ እንዳይዛነፍ ፡ ነቅቶ ፡ የሚጠባበቅ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ «ሜይጊ ፡»
ብቻ ፡ ነበር ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ በዕውቀታቸውና ፡ በአስተዋይነታ
ቸው ፡ የተመረጡት ፡ ሰዎች ፡ አባሎች ፡ ሆነው ፡ የሚገኙበት ፡ የግል ፡
ምክር ፡ ቤት ፡ አለው ። ይኸውም ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ « ፕላን ፡ የሚያ
ዘጋጅ ፡ ኮሚሲዮን ፡ » ብለን ፡ የጠራነው ፡ ነው ። ይህ ፡ የንጉሠ ፡

ነገሥቱ ፡ የግል ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሚኒስትሮችና ፡ ታላላቅ ፡ የመንግ ሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የሚከተሉትን ፡ መንገድ ፡ እያዘጋጀ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ያቀርባል ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ስሙና ፡ ሰዎቹም ፡ በየጊዜው ፡ ቢለዋወጡ ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ የሚመለከተው ፡ ዓላማና ፡ ሊደርስ ፡ የሚፈልግበት ፡ ግብ ፡ ሁልጊዜ ፡ የማይለወጥ ፡ አንድ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ጃፓን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ከሚገኙት ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ የበለጠችና ፡ የተሻለች ፡ እንድትሆን ፡ ለማድረግ ፡ መጣጣርና ፡ መንገዱን ፡ ማግኘት ፡ ነው ።

## የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ ቊጥር ።

የጃፓን ፡ የኤኮኖሚክ ፡ ሕይወት ፡ የሚመራበትን ፡ መንገድ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ አስተዋይነት ፡ ያዘጋጁት ፡ ሰዎች ፡ የተከተሉትን ፡ አስ ተያየት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ተመለከትነው ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ ጃፓን ፡ ትልቅ ፡ የኢንዱስትሪ ፡ አገር ፡ ለመሆን ፡ የቻለችበት ፡ አንዱ ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እናስተውል ። ለምሳሌ ፡ የፈረንሣይ ፡ አገር ፡ ስፋት ፡ 550.000 ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ካሬ ፡ ሲሆን ፡ የጃፓን ፡ 380.000 ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ካሬ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ከዚሁ ፡ ለርሻ ፡ የማያገለግል ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ ያገር ፡ ክፍል ፡ ስለሚገኝ ፡ እሱ ፡ ተቀናሽ ፡ ሲሆን ፡ የሚታረሰው ፡ መሬት ፡ ከመቶ ፡ አሥራ ፡ ሰባቱ ፡ እጅ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ተገምቷል ። የቀረው ፡ ጫካ ፤ ረግረግ ፤ ሐይቅ ፤ ተራራና ፡ አሸዋ ፡ ነው ። እንግዴህ ፡ ለምሳሌ ፡ የፈረንሳይ ፡ ሕዝብ ፡ ቊጥር ፡ አርባ ፡ አምስት ፡ ሚሊዮን ፡ ሲሆን ፤ የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ ከገሩ ፡ ውጭ ፡ ያለውን ፡ ጨምሮ ፡ መቶ ፡ ሀያ ፡ ሚሊዮን ፡ ሆኗል ። ነገር ፡ ግን ፡ የጃፓን ፡ አገር ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ መከ ተል ፡ በጀመረችበት ፡ ዘመን ፡ ማለት ፡ በ1868 ዓ. ም. የሕዝቧ ፡ ቊጥር ፡ ሀያ ፡ ሚሊዮን ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ታምር ፡ የተፈጸመው ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ እንደሆነ ፡ እናስተውል ።

የጃፓን ፡ መሰፍንት ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ ማለት ፡ ጃፓን ፡ ያው ሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ መከተል ፡ ከመጀመርዋ ፡ በፊት ፤ የሕዝቡን ፡ ቊጥር ፡ ማወቅና ፡ ~~ከኢኮኖሚ ፡ ሕይወቷ ፡ ጋር ፡~~ እየተመዛዘነ ፡ እን

የአ.አ ከተማ ሕዝብ ቤተ መጻሕፍት
A.A. Public Library

ዲሂድ ፡ መጠንቀቅ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ አልዘነጉ ትም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ጃፓን ፡ ያገርዋ ፡ ሰዎች ፡ ከገራቸው ፡ እን ዳይወጡና ፡ ባዕድ ፡ የሆነ ፡ ሕዝብም ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ እንዳይገባ ፡ ከልክለው ፡ ወደቦቻቸውንና ፡ የባሕር ፡ በሮቻቸውን ፡ ዘግተው ፡ ከዓ ለም ፡ ጋር ፡ ተለያይተው ፡ በኖሩበት ፡ ዘመን ፡ የሕዝባቸው ፡ ቊጥር ፡ ከሀያ ፡ አምስት ፡ ሚሊዮን ፡ እንዳይበልጥ ፡ የተወሰነ ፡ አድርገውት ፡ ነበር ።

ምክንያቱም ፡ ያገሪቱ ፡ ሀብት ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ሕዝብ ፡ መግቦ ፡ ለማኖር ፡ የማይችል ፡ መሆኑ ፡ ስለታወቀ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ እንደ ሆነ ፡ የውስጥ ፡ ሁከት ፡ የሚፈጥር ፡ ወይም ፡ ሕዝቡ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ እንዲሰደድ ፡ የሚያስገድደው ፡ ሁኔታ ፡ ያስከትልብናል ፡ ብለው ፡ ስለተረዱትና ፡ ስለፈሩ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ማነኛውም ፡ የጃ ፓን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ከተወሰነው ፡ ቊጥር ፡ በላይ ፡ ልጆች ፡ እንዳይ ኖሩት ፡ ተከልክሎ ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ የሚፀነሱትን ፡ ልጆች ፡ ሴቶቹ ፡ የሚያስወርዱበትን ፡ ዘዴ ፡ እንዲፈጽሙ ፡ በሕግ ፡ የተገደዱ ፡ ሆነው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። በየአውራጃው ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የተወሰነው ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ አገሩ ፡ ልማትና ፡ ሀብት ፡ የተለያየ ፡ ነበር ። በንዳንዱ ፡ አው ራጃ ፡ አንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ከሦስት ፡ ልጆች ፡ በላይ ፡ እንዳይኖሩት ፡ ሲከለከል ፡ በንዳንዱ ፡ አውራጃ ፡ ደግሞ ፡ ለማሳደግ ፡ የተፈቀደው ፡ አንድ ፡ ወንድና ፡ አንድ ፡ ሴት ፡ ልጆች ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ሂውጋ ፡ በሚባለው ፡ አውራጃ ፡ ደግሞ ፡ ለማደግ ፡ የተፈቀደለት ፡ ወንድም ፡ ቢሆን ፡ ሴትም ፡ ብትሆን ፡ መጀመሪያ ፡ የተወለደው ፡ ሕፃን ፡ ብቻ ፡ ነበር ። የቀሩት ፡ ግን ፡ ሳይወለዱ ፡ በዕንስ ፡ እንዳሉ ፡ በማስወረድ ፡ ወይም ፡ ከተወለዱ ፡ በኋላ ፡ በመግደል ፡ ከሕይወት ፡ መዝገብ ፡ እን ዲሰረዙ ፡ በሕግ ፡ ታዟል ። ይህ ፡ የማስወረድና ፡ ሕፃናት ፡ የመግ ደል ፡ ሥራ ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ በጣም ፡ የተለመደ ፡ ከመሆኑ ፡ የተ ነሣ ፡ በንዳንድ ፡ ዘመን ፡ በመሬት ፡ መናወጥና ፡ በሌላም ፡ እሱን ፡ በመሰሉ ፡ መቅሰፍቶች ፡ ምክንያት ፡ የቀን ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ተዋጊ ፡ ወታደር ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ እያነሰ ፡ ሲቸገሩ ፡ የሕዝቡን ፡ ቊጥር ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ አስበው ፡ መሳፍንቶቹ ፡ ሕፃናትን ፡ የማ ስወረድና ፡ የመግደል ፡ ልማድ ፡ ለጊዜው ፡ እንዲቀር ፡ ለመከል

ከል ፡ ፈቅደው ፡ ሕጉን ፡ ለመለወጥ ፡ ባሰቡ ፡ ጊዜ ፡ አዲሱን ፡ ሕግ ማስፈጸም ፡ ሳይቻላቸው ፡ ቀርቷል ።

በኋላ ፡ ግን ፡ የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ ዝና ፡ እየሰማ ፡ ዕውቀት ፡ ለማግኘት ፡ መጓጓት ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ወጣቶች ፡ እየጠፉ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ወይም ፡ ከአሜሪካ ፡ መርከቦች ፡ ውስጥ ፡ እየገቡ ፡ ተደብቀው ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ እየሄዱ ፡ ትምህርት ፡ ይማሩ ፡ ጀመር ። እነዚህም ፡ ወጣ ቶች ፡ ወደ ፡ አገሬቸው ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ አልቀበልም ፡ ብላ ፡ ጃፓን ፡ ያገርዋን ፡ በሮች ፡ ዘግታ ፡ ለመኖር ፡ አሰባ ፡ ያወጣችው ፡ አዋጅ ፡ ትልቅ ፡ጉዳት ፡ እንደሚያስከትልባትና ፡ ከዴጋ ፡ ላይ ፡ እንደሚጥላት ፡ ላገሬቸው ፡ ሰዎች ፡ ስላስረዱቸው ፡ በፊት ፡ መሳፍንቶቹ ፡ ቀጥሎም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይሰሟቸው ፡ ጀመር ። እንደዚሁም ፡ እነዚሁ ፡ ወጣቶች ፡ የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ ቁጥሩ ፡ ያነሰ ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፡ ለማድረግ ፡ የተለመደው ፡ ሕግ ፡ የሚጎዳ ፡ መሆኑን ፡ እያስረዱ ፡ ቁጥሩ ፡ እየጨመረ ፡ እንዲሄድ ፡ ቢደረግ ፡ ግን ፡ ለብዙ ፡ ነገር ፡ እንደሚበጅ ፡ አስረዱ ። ማናቸውም ፡ መንግ ሥት ፡ በዓለም ፡ መንግሥታት ፡ መካከል ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ እንዲታይ የሕዝቡ ፡ ቁጥር ፡ ብዙ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ነገርዋቸው ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ባውሮፓም ፡ ሆነ ፡ ባሜሪካ ፡ በሠ ለጠኑት ፡ አገሮች ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ ጉዳዮች ፡ እንዲ ያጠኑ ፡ የላኳቸውን ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ የጠራናቸውን ፡ የግል ፡ አማካ ሪዎቹን ፡ ማለት ፡ "ፕላን ፡ የሚያዘጋጅ ፡ ኮሚሲዮን' ተብለው ፡ የሚ ጠሩትን ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ አሳባቸውን ፡ እንዲገልጡ ፡ በጠየቃቸው ፡ ጊዜ ፡ ይህንኑ ፡ አስተያየት ፡ ደግፈው ፡ ተናገሩ ። ስለዚህ ፡ የጃፓን ፡ መንግሥት ፡ በፈረንሣይ ፡ አገር ፡ የጸና ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘውን ፡ ሕግ ተከትሎ ፡ የሕዝቡን ፡ ትውልድ ፡ የሚቀንስ ፡ ማናቸውም ፡ አድራረግ ፡ ብልሃት ፡ ወይም ፡ ዘዴ ፡ እንዳይሠራ ፡ ተከልክሏል ፡ የሚል ፡ አዋጅ በ1870 ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ የጸና ፡ አደ አውጥቶ ፡ ይህንኑ ፡ አዋጅ ፡ በጥብቅ ፡ እየተጠባበቀ ፡ ስላስፈጸመው ረገው ። ይህንንም ፡ አዋጅ ፡ በጥብቅ ፡ እየተጠባበቀ ፡ ስላስፈጸመው ሕዝቡ ፡ የጥንት ፡ ልማዱን ፡ እየረሳና ፡ አዲሱን ፡ ሕግ ፡ እያለመደ ፡ ሄደ ።

ይህም ፡ ሕግ ፡ ለሁለት ፡ ዋና ፡ ነገሮች ፡ ጠቀመ ። እንደኛ ፡ ጃፓን ፡ የኢንዱስትሪ ፡ አገር ፡ ለመሆን ፡ ስለፈቀደች ፡ የሕዝቡ ፡ ቁጥር ፡ እየበዛ ፡ ሲሄድ ፡ በድህነት ፡ የሚኖረው ፡ ሕዝባቸው ፡ በአነስተኛ ፡ ዋጋ ፡ እየተቀጠረ ፡ በየፋብሪካው ፡ እንዲሠራ ፡ ለማድረግ ፡ ተቻለ ። ሁለተኛ ፡ መንግሥት ፡ የሚፈልገውን ፡ ያህል ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ አገኘ ። ሶስተኛው ፡ ጥቅም ፡ ደግሞ ፡ ለራሷ ፡ ለጃፓን ፡ ከሁሉም ፡ የበለጠ ፡ ሲሆን ፡ ለጎረቤቶቿ ፡ ግን ፡ የከፋ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ። ይኸውም ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ቁጥሩ ፡ አለመጠን ፡ እየበዛ ፡ ሲሄድና ፡ ያገሩ ፡ ሀብት ፡ ለኑሮው ፡ አልበቃ ፡ ሲለው ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ እየገነፈለ ፡ በመፍሰስ ፡ የሌሎቹን ፡ የደከሞቹን ፡ ሕዝቦች ፡ አገር ፡ እየወረረ ፡ መያዝና ፡ ማጥለቅለቅ ፡ ግዴታ ፡ ስለሚሆንበት ፡ ነው ። እነሆ ፡ የጃፓን ፡ አስተዋዮች ፡ ሰዎች ፡ የቀድሞውን ፡ ሕግ ፡ ሽረው ፡ የሕዝባቸው ፡ ቁጥር ፡ እየጨመረ ፡ እንዲሄድ ፡ ያደረጉበት ፡ ምክንያቶች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። የቀድሞውም ፡ ሆነ ፡ የኋለኛው ፡ ሕግ ፡ የተሠራው ፡ እንደዘመኑ ፡ ሁኔታ ፡ ለሚጠቅም ፡ ዓላማ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ እንዲያው ፡ ያለምክንያት ፡ አይደለም ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ በ፲፰፻፵፮ ፡ ዓ. ም. ሀያ ፡ ስድስት ፡ ሚሊዮን ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ስምንት ፡ ሺ ፡ (26.208.000) የነበረው ፡ የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ በ፲፱፻፵፮ ፡ ዓ. ም. ማለት ፡ ከመቶ ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡ ሚሊዮን ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ስምንት ፡ ሺ ፡ (75.758.000) ሆነ ።

በሌላ ፡ አገር ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የቀን ፡ ሠራተኛ ፡ የሆነ ፡ የሚቀበለው ፡ የዕለት ፡ ቀለቡ ፡ ወይም ፡ ደሞዙ ፡ የማይበቃው ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ሥራ ፡ አጥቶ ፡ ጦም ፡ ሲያድር ፡ አገሩን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እየተሰደደ ፤ የተሻለ ፡ ኑሮ ፡ በሚያገኝበት ፡ አገር ፡ ተቀጥሮ ፡ እየሠራ ፡ ይኖራል ። ጃፓኖች ፡ ግን ፡ እንደኛ ፡ አገራቸውን ፡ ለቅቀው ፡ ለመሄድ ፡ የማይወዱ ፡ በመሆናቸው ፤ ሁለተኛም ፡ መንግሥት ፡ የመውጫ ፡ ፈቃድ ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ ስለማይሰጣቸው ፡ ተርበውና ፡ ተቸግረውም ፡ ቢሆን ፡ ከገራቸው ፡ ሳይወጡ ፡ ይኖራሉ ። ስለዚህ ፡ የጃፓን ፡ ባለ ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ በዚህ ፡ ጸኩል ፡ ችግር ፡ ሳያገኛቸው ፡ የሚፈልጉትን ፡ ያህል ፡ የቀን ፡ ሠራተኞች ፡ እያገኙ ፡ ኢንዱስትሪያቸውን ፡ ሲያስኬዱ ፡ ኖረዋል ።

በኋላ ፡ ግን ፡ ጃፓኖች ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እየሄዱ ፡ መሥራትን ፡ በለመዱ ፡ ጊዜ ፡ መንግሥታቸውም ፡ የሕዝቡ ፡ ቍጥር ፡ ሁልጊዜ ፡ እየጨመረ ፡ የሚሄድ ፡ መሆኑን ፡ አስተውሎ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እንዲሄዱ ፡ ለማድረግ ፡ ስላበረታታቸው ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ አቅራቢያ ፡ ያሉትን ፡ የተባበሩትን ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥታት ፤ ሺናና ፡ አስትራሊን ፡ የመሰሉትን ፡ አገሮች ፡ ስላሰጋቸው ፡ እነዚሁ ፡ አገሮች ፡ ጃፓኖች ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ እንዳይገቡባቸው ፡ ይቃወሙ ፡ ጀመር ። የጃፓን ፡ መንግሥት ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ ለማሻሻል ፡ ሲል ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ እንዲሠሩት ፡ አድርጓል ። ለምሳሌ ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ በከተማው ፡ መንገዶች ፡ እየዞሩ ፡ ጋዜጦች ፡ የሚሸጡ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፤ አንዱ ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ የጋዜጣውን ፡ ስም ፡ እየጠራ ፡ ለሕዝብ ፡ ሲያሰማ ፡ ሁለተኛው ፡ ሠራተኛ ፡ እየጠቀለለ ፡ ጋዜጣውን ፡ ለገዢ ፡ ይሸጣል ። የታክሲ ፡ አቶሞቢል ፡ የሚያከራዩ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፤ አንዱ ፡ አቶሞቢሉን ፡ ሲነዳ ሁለተኛው ፡ ተከራይ ፡ ሲመጣ ፡ በሩን ፡ ከፍቶ ፡ ያስገባል ፡ (ያስተናግዳል ።) በባቡር ፡ ላይ ፡ የተቆጣጣሪነት ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ አራት ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ያራቱ ፡ ሰዎች ፡ ደመወዝ ፡ አንድነት ፡ ተደምሮ ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ አንድ ፡ የባቡር ፡ ተቆጣጣሪ ፡ ከሚያገኘው ፡ ቀለብ ፡ ያንሳል ። እነሆ ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ዘዴ ፡ ጃፓን ፡ በዓመት ፡ በዓመቱ ፡ ቍጥሩ ፡ እየጨረ ፡ የሚሄደው ፡ ሕዝቧ ፡ በራብና ፡ በችግር ፡ እንዳይፈታ ፡ በማለት ፡ ያላትን ፡ ሀብት ፡ ለሁሉም ፡ እንዲዳረስ ፡ ለማድረግ ፡ ትጣጣራለች ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ዘዴ ፡ የገጠማትን ፡ ችግር ፡ በሙሉ ፡ ለማስወገድ ፡ በቂ ፡ አለመሆኑ ፡ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ሕዝቧ ፡ ሁልጊዜ ፡ ቍጥሩ ፡ እየበዛ ፡ በመሄዱ ፡ ምክንያት ፡ የሚያስከትልባት ፡ ችግር ፡ አልበቃ ፡ ብሎ ፡ የመሬት ፡ መናወጥና ፡ ሌላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መቅሰፍት ፡ በአገርዋ ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ሆኖ ፡ በየጊዜው ፡ ይደርስባታል ። በ1923 ዓ ም በመስከረም ፡ ወር ፡ በሆነው ፡ መሬት ፡ መናወጥ ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ከተሞች ፡ ፈርሰው ፡ ብዙ ፡

ፋብሪካዎች ፣ ጠፉ ። በዚሁ ፣ ምክንያት ፣ ብዙ ፣ አገሮች ፣ ለጃፓን ፣ ሕዝብ ፣ እርዳታ ፣ ሲያደርጉ ፣ ኢትዮጵያም ፣ ፲ሺ ፣ ፓውንድ ፣ ሰጥታለች ።

በዚህ ፣ መቅሰፍት ፣ የበለጠ ፣ ጉዳት ፣ ያገኛት ፣ የቶኪዮ ፣ ከተማ ፣ ናት ። ስለዚህ ፣ ከሞት ፣ የተረፉት ፣ የቀን ፣ ሠራተኞች ፣ ሥራ ፣ አጥተው ፣ ጦም ፣ አዳሪዎች ፣ ሆኑ ። ታላላቆች ፣ የእንዱስትሪ ፣ ማኅበሮች ፣ የሆኑት ፣ ሚትሱኢ ፤ ሚትሱቢሺና ፣ ሱሚሞቶ ፣ የሚባሉት ፣ ብቻ ፣ በፈረሰውና ፣ በጠፋው ፣ ፋብሪካቸው ፣ ምትክ ፣ አዲሶች ፣ መኪኖች ፣ እያስመጡ ፣ አዲስ ፣ ፋብሪካ ፣ ለማቋቋም ፣ የሚችሉበት ፣ በቂ ፣ የሆነ ፣ ተቀማጭ ፣ ገንዘብ ፣ ሲያገኙ ፣ የቀሩት ፣ ታናናሾች ፣ የፋብሪካ ፣ ባለቤቶች ፣ እንደ ፣ ከሰሩ ፣ ቀርተዋል ። ከፍ ፣ ብለን ፣ የጠራናቸው ፣ ታላላቆች ፣ የፋብሪካ ፣ ባለቤቶች ፣ ደግሞ ፣ አዲስ ፣ የገዟቸው ፣ የፋብሪካ ፣ መኪናዎች ፣ አዲሱ ፣ የቴክኒክ ፣ ዕውቀት ፣ ባስገኛቸው ፣ ዘዴዎች ፣ ተሻሽለው ፣ የተሠሩ ፣ በመሆናቸው ፣ ቁጥ ጥራቸው ፣ ከቀድሞው ፣ ያነሰ ፣ የቀን ፣ ሠራተኞች ፣ እየቀጠሩ ፣ የበለጠ ፣ የሥራ ፣ ፍሬ ፣ ያገኙበት ፣ ጀመር ። ይህ ፣ ሁሉ ፣ ነገር ፣ ያስከተለው ፣ ሥራ ፣ ፈት ፣ የሆኑት ፣ የቀን ፣ ሠራተኞች ፣ እየበረከቱ ፣ እንዲሄዱ ፣ ማድረግ ፣ ሆነ ። በዚህ ፣ ምክንያት ፣ ሥራ ፣ ፈቶችን ፣ ለመርዳት ፣ መንግሥቱ ፣ ብዙ ፣ ሚሊዮን ፣ ገንዘብ ፣ ወጭ ፣ ማድረግ ግዴታ ፣ ሆነበት ። ለምሳሌ ፣ ያህል ፣ በ1929 ዓ. ም. በጃፓን ፣ አገር ፣ የነበሩ ፣ ሥራ ፣ ፈቶች ፣ የሆኑ ፣ የቀን ፣ ሠራተኞች ፣ ቁጥራቸው ፣ ሁለት ፣ ሚሊዮን ፣ ሰባት ፣ መቶ ፣ ዘጠና ፣ ሺ ፣ (2.790.000) በ1930 ዓ. ም. አንድ ፣ ሚሊዮን ፣ ተኩል ፣ እንደነበረ ፣ በስታቲስቲክ ፣ ተጽፎ ፣ ተገልጧል ። ከዚህም ፣ በቀር ፣ በሥራ ፣ ላይ ፣ ያሉት ፣ ሠራተኞች ፣ ደግሞ ፣ አንደኛ ፣ ደሞዛችን ፣ ተቀነሰብን ፣ (ወይም ፣ አነሰን ፣ ) ሁለተኛ ፣ የሥራ ፣ ሰዓት ፣ ተጨመረብን ፤ ሦስተኛ ፣ ኑሮዋችን ፣ የሚሻሻልበት ፣ አስፈላጊዎቹ ፣ ነገሮች ፣ ይደረጉልን ፣ በማለት ፣ አቤቱታ ፣ እያቀረቡ ፣ በየጊዜው ፣ ሁከት ፣ አንስተዋል ። ሆኖም ፣ የጃፓን ፣ አገር ፣ ሠራተኞች ፣ ከግል ፣ ኑሮዋቸው ፣ በላይ ፣ አድርገው ፣ የሚመለከቱት ፣ የመንግሥታቸውን ፣ ጥቅምና ፣ እድገት ፣ ስለሆነ ፣ አገር ፣ የሚያናውጥ ፣ ያድማ ፣ ሥራ ፣ ሠርተው ፣ አያውቁም ።

ከ1917 ፡ ዓ. ም. (እ. አ. አ.) ጀምሮ ፡ የጃፓን ፡ መንግሥት ፡ ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እየሄዱ ፡ እንዳይሠሩ ፡ ቀድሞ የነበረውን ፡ የመከልከል ፡ አሳብ ፡ ትቶ ፡ እንዲያውም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴ ፡ እያበረታታ ፡ አስፈላጊውን ፡ እርዳታ ፡ ሁሉ ፡ የሚሰጣቸው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አቆመ ።

ይህ ፡ ነገር ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ አቅራቢያ ፡ ያሉትን ፡ መንግሥታት ፡ ስላሰጋቸው ፡ ሁሉም ፡ በየበኩላቸው ፡ መከላከያ ፡ የሚሆናቸውን ፡ ብልሃት ፡ ይፈልጉ ፡ ጀመር ። የተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ በግዛታቸው ፡ ውስጥ ፡ የጃፓን ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ መሬት ፡ ለመግዛት ፡ እንዳይችል ፡ የሚከለክለውን ፡ አዋጅ ፡ በ1920 ዓ. ም. አወጡ ። እንደዚሁም ፡ ቀጥለው ፡ በ1924 ፡ ዓ. ም. የብጫ ፡ ዘር ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ እንዳይገባ ፡ በአዋጅ ፡ ከልክለው ፡ በራቸውን ፡ ዘጉ ። በ1928 ፡ ዓ. ም. ካናዳም ፡ እንደዚሁ ፡ አደረገች ። የፊሊፒን ፡ አገሮችም ፡ በገራቸው ፡ ገብተው የነበሩትን ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ሺ ፡ የሚሆኑትን ፡ የጃፓን ፡ ተወላጆች ፡ ለማስወጣት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴ ፡ ፈጠሩ ።

በጃፓን ፡ አገር ፡ በየፈትል ፡ ፋብሪካው ፡ የሚበልጡት ፡ ሠራተኞች ፡ ሴቶች ፡ ናቸው ። ምክንያቱም ፡ በእነሱ ፡ አገር ፡ ሴቶች ፡ መብት ፡ የሌላቸው ፡ በመሆናቸው ፡ አነስተኛ ፡ ቀለብ ፡ እየሰጡ ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ብዙ ፡ ሰዓቶች ፡ ቢያሠሩዋቸው ፡ ለመከራከር ፡ የማይችሉ ፡ በመሆናቸው ፡ ነው ። በጃፓን ፡ አገር ፡ ወንድም ፡ ለእኅቱ ፤ ልጅ ፡ ለእናቱ ፤ ባል ፡ ለሚስቱ ፤ ጌታዋ ፡ ስለሆነ ፡ ለኢንዱስትሪ ፡ ባለቤቶች ፡ ወይም ፡ "የሴት ፡ አዳሪዎች ፡ ቤት" ለሚከፍቱ ፡ ነጋዴ ባለቤቶች ፡ ወይም ፡ "የሴት ፡ አዳሪዎች ፡ ቤት" ለሚከፍቱ ፡ ነጋዴዎች ፡ እንደ ፡ ባርያ ፡ አድርጎ ፡ ሊሸጣት ፡ ይችላል ። በ1931 ፡ ና ፡ በ1932 ፡ ዓ. ም. መንግሥት ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ ያዘዛቸው ፡ ሰዎች ፡ ደሆች ፡ የሆኑ ፡ ሕዝቦች ፡ በሚኖሩባቸው ፡ መንደሮች ፡ እየተዘዋወሩ ፡ አርባ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ወጣቶች ፡ ሴቶች ፡ ገዝተው ፡ ለሴት ፡ አዳሪነት ፡ ወደ ፡ ማንድሹሪ ፡ ልከዋቸዋል ። ይህን ፡ እንደ ፡ ነውርነት ፡ ወደ ፡ ማንድሹሪ ፡ ልከዋቸዋል ። ይህን ፡ እንደ ፡ ነውር ፡ ሆኖ ፡ የሚቆጠረውን ፡ ልማድ ፡ ጃፓን ፡ ከሠለጠነችም ፡ በኋላ ፡ አልተወችውም ፡ ማለት ፡ ነው ።

በዚሁ ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ ባለኢንዱስትሪዎች ፡ ከዘመዶቻ
ቸው ፡ ላይ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ በኮንትራት ፡ እየገዙ ፡ እንደ ፡ ፈቀዱ ፡
አድርገው ፡ በፋብሪካቸው ፡ ውስጥ ፡ ያሠርዋቸዋል ።

በጃፓን ፡ አገር ፡ ሴት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ስትሄድ ፡ ወዳጆቿ ፡ ከሆ
ኑት ፡ ከሌሎች ፡ ሴቶች ፡ ጋር ፡ ትሄዳለች ፡ እንጂ ፡ ከባሏ ፡ ጋር ፡
ለመሄድ ፡ ያገርዋ ፡ ልማድ ፡ አይፈቅድላትም ። ከሠለጠኑ ፡ በኋላም ፡
ቢሆን ፡ ከዩኒቬርሲቴ ፡ ትምህርቷን ፡ ጨርሳ ፡ የወጣች ፡ ሴት ፡ ብት
ሆንም ፡ እንኳ ፡ ይህን ፡ የጥንት ፡ ልማድ ፡ ለመጣስ ፡ ባልዋ ፡ የሚፈ
ቅድላት ፡ ሴት ፡ ክስንት ፡ አንድ ፡ ነች ። ስለዚህ ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡
ሴት ፡ ልጅ ፡ ምንም ፡ መብት ፡ የሌላት ፡ ፍጹም ፡ ባርያ ፡ ነች ፡ ለማ
ለት ፡ ይቻላል ። የፋብሪካ ፡ ቤቶች ፡ በውስጣቸው ፡ የሚሠሩት ፡
ሴቶች ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ እየሄዱ ፡ ሕዝብ ፡ አነሳሽ ፡ በሆኑ ፡ የፖሊ
ቲካ ፡ ሰዎች ፡ እንዳይሰበኩባቸው ፡ ሲሉ ፡ በዚያው ፡ በፋብሪካው ፡
ግቢ ፡ ውስጥ ፡ በተሠሩላቸው ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ እየተመገቡና ፡ እየተኙ ፡
እንዲኖሩ ፡ አድርገዋል ። በታላላቆቹ ፡ ፋብሪኮች ፡ ውስጥ ፡ እስከ ፡
ሠላሳ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ሴቶች ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ይኖራሉ ። የፋብ
ሪካ ፡ ባለቤት ፡ የሆነውም ፡ ሰው ፡ ላንዲት ፡ ሴት ፡ በቀን ፡ አንድ ፡
ኩባያ ፡ ሩዝና ፡ የምትተኛበት ፡ ቤት ፡ ከሰጣት ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ትርፍ ፡
ነገር ፡ ስለማትፈልግ ፡ እንደ ፡ እስረኛ ፡ አድርጎ ፡ ከግቢው ፡ ውስጥ ፡
እንዳትወጣ ፡ ከልክሎ ፡ የፈቀደውን ፡ ያህል ፡ ተቆጣጣሪ ፡ የሆነ ፡ ባለ
ሥልጣን ፡ ሳይገባበት ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ እያሠራት ፡ ሀብቱን ፡ ክፍ ፡
ከፍ ፡ ለማድረግና ፡ አዲስ ፡ መኪናዎች ፡ እየገዛ ፡ ኢንዱስትሪውን ፡
ሲያስፋፋ ፡ ይኖራል ።

ከፍ ፡ ብለን ፡ ተናገረነው ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡
በጃፓን ፡ አገር ፡ መሬቱን ፡ ሁሉ ፡ ርስት ፡ አድርገው ፡ የያዙት ፡
ዳይሚዮ ፡ የሚባሉት ፡ መሳፍንቶች ፡ ነበሩ ። በ1871 ዓ. ም. መሳፍ
ንቶች ፡ ርስታቸውን ፡ ለቅቀው ፡ ለመንግሥት ፡ ስላስረከቡና ፡ እሱም ፡
በእጁ ፡ ይዞት ፡ የነበረውን ፡ ለም ፡ መሬት ፡ አስይዞ ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡
ተበደረበት ፡ ሸጠው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ እርሻ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ሆነና ፡ መሬት ፡
ለማረስ ፡ ወይም ፡ ከብት ፡ ለማርባት ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ለባለር

ስቱ ፡ ኪራይ ፡ እየከፈለ ፡ ከዚህም ፡ በቀር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግብር ፡ ለመንግሥት ፡ ያገባበት ፡ ጀመር ።

## የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በሲቪል ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ስለመነሣቱ ።

በጃፓን ፡ አገር ፡ የሜይጂ ፡ ዘመን ፡ በተጀመረበት ፡ በመጀመሪያዎቹ ፡ ዓመታት ፡ መንግሥቱ ፡ የጥንቱን ፡ ልማድ ፡ ተከትሎ ፡ በጣም ፡ ያቀረባቸው ፡ የጦር ፡ ወገኖችን ፡ ነበር ። በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችም ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ የያዙት ፡ እነሱ ፡ ነበሩ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ እንዳመለከትነው ፡ ጃፓን ፡ ያዲሱን ፡ ሥልጣኔ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ መልክ ፡ ይዛ ፡ ለመታየት ፡ በተጣጣረች ፡ ጊዜ ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ የተናቁና ፡ የተዋረዱ ፡ ሆነው ፡ ይቆጠሩ ፡ የነበሩት ፡ የሕዝብ ፡ ደረጃዎች ፡ ማለት ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤቶችና ፡ ነጋዴዎች ፡ የባንክ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆችም ፡ የበለጡ ፡ ሆነው ፡ መታየት ፡ ጀመሩ ። የንግድ ፡ ሥራም ፡ መጀመሪያ ፡ በእርሻ ፡ ቀጥሎም ፡ በጦር ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ጣለ ። ወታደሮች ፡ እንደ ፡ ቀድሞዎቹ ፡ አባቶቻቸው ፡ በጀግንነት ፡ እየተዋጉ ፡ ድል ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ አነስተኛ ፡ የነበረው ፡ ደመወዛቸው ፡ ከፍ ፡ ይላልናል ፡ በማለት ፡ ሲመኙ ፡ ከቀድሞው ፡ ምንም ፡ ሳይሻሻል ፡ ቀረ ። ከፍ ፡ ያለ ፡ የመሥዋዕትነት ፡ ሥራ ፡ እየሠሩ ፡ በብዙ ፡ ችግር ፡ ድል ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ የሚፈቅዱትን ፡ ለማድረግ ፡ የሚችሉ ፡ መሰላቸው ። ያገራቸው ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ሰዎች ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ፖሊቲካ ፡ ውስጥ ፡ ከጦርነት ፡ የበለጠ ፡ ትልቅ ፡ ችግር ፡ እንደገጠማቸው ፡ ሊረዱትና ፡ ሊገባቸው ፡ አልቻለም ። ስለዚህ ፡ ወደፊት ፡ እንደምናገኘው ፡ የጃፓን ፡ ጉዳይ ፡ በኢንቴርናሲዮናል ፡ ፖሊቲካ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ክርክርና ፡ ጭቅጭቅ ፡ ከተደረገበት ፡ በኋላ ፡ የጃፓን ፡ ጦር ፡ የያዘውን ፡ አንዳንድ ፡ አገሮች ፡ እንዲለቅና ፡ ክብሩን ፡ ዝቅ ፡ የሚያደርግ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ እንዲፈጽም ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ሰዎች ፡ የጦር ፡ አለቆቹን ፡ ባስታወቋቸው ፡ ጊዜ ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ወገኖች ፡ የክህደት ፡ ሥራ ፡ የሠሩባቸው ፡ መሰላቸው ።

ስለዚህ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወገኖች ፡ በሲቢል ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ተነሡባቸው ።

በሌሎቹ ፡ በሠለጠኑት ፡ ያውሮፓ ፡ አገሮች ፡ ቢሆን ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶች ፡ ይህን ፡ ለማድረግ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አይፈቅድላቸውም ። ነገር ፡ ግን ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሚይጂ ፡ በ፲፰፻፹፱ ፡ ዓ. ም. ወስኖ ፡ ለሕዝቡ ፡ በሰጠው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በሌሎቹ ፡ አገሮች ፡ ያልተለመደውን ፡ መብት ፡ ለጃፓን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሰጥቶታል ። የመንግሥቱን ፡ ፖሊቲካ ፡ በሚመሩት ፡ በሚለዋወጡት ፡ ሚኒስትሮች ፡ ሥልጣን ፡ የሚታዘዝ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ልዩ ፡ መብቶች ፡ ያሉት ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ አካል ፡ ወይም ፡ አባል ፡ አድርጎት ፡ ነበር ። በጃፓን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በ፲፩ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ጦርነትን ፡ ለማንሣት ፡ ወይም ፡ ሰላም ፡ ለማድረግ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሚካዶ ፡ ንጉሡ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ሲፈጽም ፡ በሌላው ፡ አገር ፡ እንደሚደረገው ፡ ሁሉ ፡ ፓርለማው ፡ ወይም ፡ ሚኒስትሮቹ ፡ በአሳቡ ፡ የሚስማሙበት ፡ ወይም ፡ የሚቃወሙት ፡ መሆናቸውን ፡ መጠየቅ ፡ የለበትም ። በ፲፰፻፺፯ ፡ ዓ. ም. በወጣው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የጦር ፡ ሚኒስቴርና ፡ የመርከብ ፡ ሚኒስቴር ፡ የሚማሩት ፡ ቋሚ ፡ በሆነው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሹማምንቶች ፡ ነው ። የጃፖን ፡ ኤታ ፡ ማዦርም ፡ የኢንቴርናሲዮናል ፡ ፖሊቲካ ፡ ስለሚነኩት ፡ የጦር ፡ ጉዳዮች ፡ በውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ አማካይነት ፡ ሳይሆን ፡ ራሱ ፡ በቀጥታ ፡ ሊነጋገርባቸው ፡ መብት ፡ ተሰጥቶታል ። እንደዚሁም ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ በመንግሥቱ ፡ በኩል ፡ አላፊነት ፡ የለበትም ፤ የሚታዘዘው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ እነ ፡ ሚትሱኢና ፡ እነ ፡ ሚትሱቢሺ ፡ የተባሉት ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤቶች ፡ ካፒታላቸው ፡ እያደገና ፡ መኪኖቻቸው ፡ እየበዙ ፡ በሄዱበት ፡ መጠን ፡ የእጅ ፡ ጥበብ ፡ ሥራ ፡ እየሠሩና ፡ ታናናሽ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ እያቋቋሙ ፡ የሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ ትልልቅ ፡ ዓሣዎች ፡ ታናናሽ ፡ ዓሣዎችን ፡ እየዋጧቸው ፡ እንደሚያጠፉዋቸው ፡ ሁሉ ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ የተጠሩት ፡ ታላላቆቹ ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤቶች ፡ የታናናሾቹን ፡ ጥቅም ፡ እየዋጡ ፡ ስላጠፉዋቸው ፡ የሕዝቡ ፡ መንፈስ ፡ በነ ፡ ሚትሱኢና ፡ በነ ፡ ሚትሱቢሺ ፡ ላይ ፡ ተነሣባቸው ።

የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ክፍሎችም ፡ የድሆቹን ፡ አሳብ ፡ ደጋፊ ፡
ሆነው ፡ በታላላቆቹ ፡ ባለኢንዱስትሪዎች ፡ ላይ ፡ ተባብረው ፡ ተነሡ ።
ይኸውም ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ሲደጋገም ፡ የሚኖረው ፡
በሀብታሞችና ፡ በድሆች ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ ሀብት ፡ አከፋፈል ፡ ጉዳይ ፡
በየዘመኑ ፡ የሚፈጠረው ፡ ጠብ ፡ ነው ።

የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ክፍሎች ፡ ይህንን ፡ ሲያደርጉ ፡ የተመረከዙት ፡
አሳብ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ነበር ። በጥንት ፡ ዘመን ፡ ማለት ፡
በ፲ኛውና ፡ በ፲፰ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ላይ ፡ ማለት ፡ መሳፍ
ንቶች ፡ (ሾጉኖች ፡) የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ ከመውሰ
ዳቸው ፡ በፊት ፡ በነበረው ፡ ዘመን ፡ አስተዳደር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡
ከጦር ፡ ሠራዊትና ፡ ከመንግሥት ፡ የሲቪል ፡ ሹማምንቶች ፡ መካከል ፡
በዕውቀታቸውና ፡ በአስተዋይነታቸው ፡ ሶስት ፡ ወይም ፡ አራት ፡ ሰዎች ፡
መርጠ ፡ በእነሱ ፡ አማካይነትና ፡ ረዳትነት ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡
ሆኖ ፡ አገሩን ፡ ይገዛል ። ይህን ፡ በመሰለው ፡ የአስተዳደር ፡ ዘመን ፡
መሳፍንትም ፡ ሆኑ ፡ ነጋዴዎች ፡ በሕዝብ ፡ ኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ውስጥ ፡
አይገኙም ፡ ነበር ። ርስት ፡ ሁሉ ፡ የሚገኘው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡
እጅ ፡ ሆኖ ፡ ነው ፤ እሱም ፡ ለዜጎቹ ፡ እንደሚበቃቸው ፡ መጠን ፡ እያየ ፡
ለሁሉም ፡ ያከፋፍላቸዋል ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሙያውና ፡ እንደችሎ
ታው ፡ የተሰጠውን ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ መኖር ፡ ግዴታ ፡ ነበረበት ።
መንግሥት ፡ ደግሞ ፡ ሕዝቡ ፡ እንዳይበደልና ፡ እንዳይጎዳ ፡ አስቦ ፡
አስፈላጊውን ፡ ሁሉ ፡ ያደርጋል ። ስለዚህ ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶ
ችና ፡ በጠቅላላውም ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ይህን ፡ ወደ ፡ መሰለው ፡
ወደ ፡ ቀድሞው ፡ አስተዳደር ፡ እንመለስ ፡ ባዮች ፡ ሆኑ ።
ይህንንም ፡ አሳብ ፡ ሲያቀርቡ ፡ ስለ ፡ አፈጻጸሙ ፡ ጉዳይ ፡ ርስት ፤
ኢንዱስትሪዎች ፤ ባንኮች ፤ በጠቅላላው ፡ ያገሩ ፡ ሀብቶች ፡ ሁሉ ፡
በመንግሥት ፡ እጅ ፡ ሆነው ፡ የቀን ፡ ሠራተኞች ፡ የሆኑትም ፡ ከሚሠ
ሩባቸው ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ የሚገኘውን ፡ ጥቅምና ፡ ትርፍ ፡ ይካ
ፈሉ ፤ መንግሥትም ፡ ሕፃናቶችን ፡ ሁሉ ፡ እኩል ፡ እያስተማረ ፡ ያሳ
ድጋቸው ፤ ለሕዝብ ፡ ኑሮ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ እርዳታ
ዎችና ፡ ላረጁትም ፡ ሰዎች ፡ የሚሰጠውን ፡ የመጦሪያ ፡ ገንዘብ ፡ መን
ግሥት ፡ ይቻል ፡ ሲሉ ፡ ፕሮግራማቸውን ፡ ነደፉ ። ይኸውም ፡ ከኮ

ሙኒስት ፡ መንፈስ ፡ ጋር ፡ የሚቀራረብ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ መንፈስ ፡ ከሲቪል ፡ አንጕል ፡ የመነጨ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ከጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወገኖች ፡ የመጣ ፡ መሆኑን ፡ ሲያስረዱ ፡ የጃፓንን ፡ ኢም ፔሪያሊስት ፡ መንግሥት ፡ ለማስፋፋት ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ አቅድ ፡ እንመራ ፡ ሲሉ ፡ በፕሮግራሙ ፡ ውስጥ ፡ ጨምረው ፡ አቀረቡ ። ቃሉም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

"ስላገሩ ፡ መከላከያ ፡ ጉዳይ ፡ ሲል ፡ መንግሥት ፡ ጦርነት ፡ ለማ ድረግ ፡ መብት ፡ አለው ። ጦርነት ፡ የሚደረገውም ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ሰፊ ፡ ግዛት ፡ በያዙት ፡ መንግሥታት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በጭ ከኔ ፡ አስተዳደር ፡ በላቸው ፡ መንግሥታት ፡ ላይ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ላይ ፡ አስትራሊን ፤ ምሥራቃዊ ፡ ጫፍ ፡ የሆነውንም ፡ የሲ ቤሪን ፡ አገር ፡ ከመስኮብ ፡ ላይ ፡ መቀማት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። እን ደዚሁም ፡ ለምሳሌ ፡ ህንድን ፡ ከእንግሊዝ ፡ ቀንበር ፤ ሺናንም ፡ ከባ ዕድ ፡ ግፍ ፡ ነፃ ፡ ለማውጣት ፡ ጦርነት ፡ ማድረግ ፡ ነው" ።

ስለዚህ ፡ አስተዳደር ፡ ጉዳይ ፡ የተዘጋጀውን ፡ መጽሐፍ ፡ አሰ ናድቶ ፡ ያቀረበ ፡ ቲኪ ፤ ኪታ ፡ የሚባለው ፡ ሰው ፡ ነው ። ይህን ንም ፡ መጽሐፍ ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶችና ፡ ወታደሮች ፡ ከእጃቸው ፡ አይለዩትም ፡ ነበር ። ከተራው ፡ ወታደር ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዤኔራል ፡ ድረስ ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ አሳብ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያገኛል ፡ ሲሉ ፡ በሙሉ ፡ ልብ ፡ አመኑ ።

ዤኔራል ፡ ሳቶ ፡ የሚባለው ፡ ደግሞ ፡ በመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ አንዳንድ ፡ ያውሮፓ ፡ አገሮች ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ የላ ኩት ፡ የወታደር ፡ ቁጥር ፡ ቢገመት ፤ ከሕዝባቸው ፡ ጠቅላላ ፡ ቁጥር ፡ ከመቶ ፡ አሥራ ፡ ሰባት ፡ እጅ ፡ 17% ይሆናል ፡ የተባለውን ፡ ተመ ርኩዞ ፡ ጃፓን ፡ በጠቅላላው ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሺ ፡ ወታደሮች ፡ አስከትታ ፡ ከዚሁ ፡ ሦስት ፡ ሚሊዮን ፡ ስም ንት ፡ መቶ ፡ ሺ ፡ ወታደሮች ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ለመላክ ፡ ትች ላለች ፡ ሲል ፡ አሳብ ፡ አቀረበ ። ይህንንም ፡ ስንል ፡ ጃፓን ፡ በ1913 ዓ. ም. (የመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በተነሣበት ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ ማለት ፡ ነው ።) ለጦር ፡ ሠራዊት ፡ የምታወጣው ፡ ገንዘብ ፡ ከጠቅ ላላው ፡ የመንግሥቱ ፡ ቡድዤ ፡ ከመቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ 33% በኋ

ላም ፡ በ1933 ዓ. ም. ከመቶ ፡ አርባ ፡ አራት ፡ 44% ሆኖ ፡ ይኸውም ፡ ለጦር ፡ ሠራዊት ፡ ፩፻፶፯ ፡ ሚሊዮን ፡ ዬን ፤ ለመርከብ ፡ ፩፻፳ ፡ ሚሊዮን ፡ ነበር ። በመጨረሻም ፡ በ1934 ዓ. ም. እስከ ፡ ፱፻፴፯ ፡ ሚሊዮን ፡ የመርቀ ፡ ዬን ላይ ፡ ደረሰ ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወገኖች ፡ ኃይላቸው ፡ በጣም ፡ እየበረታ ፡ ስለሄደ ፡ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ በፖሊቲካ ፡ በኩል ፡ የእነሱ ፡ አሳብ ፡ ብቻ ፡ ተፈጻሚነት እንዲያገኝ ፡ ለማድረግ ፡ አሰቡ ። የመንግሥቱን ፡ ፖሊቲካ ፡ የሚመሩትን ሰዎች ፡ አስቸግረዋቸው ። ይህም ፡ ሁኔታ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ነገሮች ፡ እንዳስከተለ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ መጨረሻ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ ወደፊት ፡ በሰፊው ፡ እናገኘዋለን ።

የጃፓን ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ በየቦታው ፡ እየተዋጋ ፡ ድል ፡ አድራጊነትን ባገኘ ፡ ቁጥር ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወገኖች ፡ ትዕቢታቸው ፡ እየገነነ ፡ ይሄድ ፡ ጀመር ። ጃፓን ፡ ማንድሹሪን ፡ ድል ፡ ባደረገች ፡ ጊዜ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወገኖች ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተጠቀሰውን ፡ አሳባቸውን ፡ እናስፈጽማለን ፡ ብለው ፡ በግልጥ ፡ ተነሡና ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ ሁከት ፡ ፈጠሩ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ጀኔራል ፡ አራኪ ፡ የሚባለው ፡ የመንግሥቱን ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ በእጁ ፡ ጨበጠ ። ባጭሩ ፡ ጃፓኖች ፡ ባሁኑ ፡ የሥልጣኔ ፡ ዘመን ፡ የፖሊቲካና ፡ የጦር ፡ ጉዳዮች ፡ ሁለት ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ መሆናቸውን ፡ ለማወቅ ፡ አልፈለጉም ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በፈጠረው ፡ ሁከት ፡ በፖሊቲካ ፡ ጉዳይ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተገደሉ ። ባጭሩ ፡ የመንግሥቱ ፡ አስተዳደር ፡ በጦር ፡ ዲክታተር ፡ የሚመራ ፡ መልክ ፡ የያዘ ፡ ሆነ ። በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትር ፡ የነበረው ፡ ከሚትሱኢ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ኢኑዩ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ነበር ። የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወገኖች ፡ በሀብታሞች ፡ ላይ ፡ ስለተነሡባቸው ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ የጠራነው ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትርና ፡ የሚትሱኢ ፡ ባንክ ፡ ዲሬክተር ፡ የነበረው ፡ ባሮን ፡ ዳን ፡ ተገደሉ ። እንደዚሁም ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ የነበረውም ፡ ኢኑካዩ ፡ የሚባለው ፡ ሰላምን ፡ ፈላጊ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ስለተከሰሰና ፡ ይኸውም ፡ ጦርነትን ፡ ፈላጊዎች ፡ በነበሩት ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወገኖች ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ኃጢአት ፡ ሆኖ ፡ ስለተቆጠረበት ፡ እሱም ፡ ተገደለ ። የውጭ ፡ ጉዳይ ፡

ሚኒስትር ፡ የነበረውም ፡ ባሮን ፡ ሺዴሃራ ፡ የሚባለው ፡ ለሚትሱ ቢሺ ፡ ቤተሰብ ፡ ዋና ፡ ከነበረው ፡ ጋር ፡ ተጋብቶ ፡ አማቹ ፡ ሆኖ ፡ ነበርና ፡ እሱንም ፡ እንደዚሁ ፡ ሊገድሉት ፡ አቁስለውት ፡ በታምር፡ ከሞት ፡ አመለጠ ።

የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ገዳይ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ በተያዘ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ተናገረ ፤ "ፖሊቲካውና ፡ አገሩም ፡ ጭምር ፡ በሀብታሞች ፡ ገዥነት ፡ (አሊጋርሺ ፡) ውሥጥ ፡ ሆነው ፡ በገን ዘብ ፡ ኃይል ፡ ተበላሽተዋል ። እነሱን ፡ ንጹሕ ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻ ልበት ፡ ዘዴ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ እናት ፡ እናቱን ፡ መምታት ፤ የሚያስተጋባ ፡ ምሳሌ ፡ መስጠት ። ይህን ፡ የመሰ ለው ፡ አመፅ ፡ ያሰቀቅናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። . . . . . . . . . ስለአገሩ ፡ ደህንነት ፡ ሲባል ።»

ይህን ፡ አመጽ ፡ የሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ከፍርድ ፡ ላይ ፡ ቀርበው ፡ ቢፈረድባቸው ፡ ፍርዱ ፡ አልተፈጸመባቸውም ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የሁከት ፡ አንሺዎቹ ፡ ወገኖች ፡ እየበረከቱ ፡ ሄዱ ፡ እንጂ አልጠፉም ። የሚሠሩትም ፡ ያመፅ ፡ ሥራ ፡ እየተጨመረና ፡ እየበዛ ፡ መሄዱን ፡ በመመልከት ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤቶች ፡ የባ ንክ ፡ አስኪያጆችና ፡ ታላላቆች ፡ ነጋዴዎች ፡ ይልቁንም ፡ የሚትሱ ኢና ፡ የሚትሱቢሺ ፡ ወገኖች ፡ በልብሳቸው ፡ ውስጥ ፡ ለአካላታቸው ፡ የሚመክትላቸው ፡ የብረት ፡ ሹራብ ፡ እየለበሱ ፡ ይወጡ ፡ ጀመር ።

እንደዚሁም ፡ የሚጠብቋቸው ፡ (የዴቴክቲቭ) ሥራ ፡ የሚያ ውቁ ፤ አመፀኞችን ፡ የሚከታተሉ ፡ ሰዎች ፡ እየቀጠሩ ፡ በነሱ ፡ ይጠ በቁ ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ በጦር ፡ ሠራዊትና ፡ በሀብታሞች ፡ መከከል ፡ የተነሣው ፡ የውስጥ ፡ ውጊያ ፡ እየቀጠለ ፡ ሄደ ። ይኸውም ፡ የሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ሊነሣ ፡ የተቃረበበት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ።

የሀብታሞች ፡ ወገኖች ፡ ቢቸግራቸው ፡ ለጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወገ ኖች ፡ በያይነቱ ፡ ገጸ ፡ በረከትና ፡ የገንዘብም ፡ ጉርሻ ፡ ወይም ፡ እርዳታ ፡ ይሰጡ ፡ ጀመር ። ይኸውም ፡ ለጦር ፡ ሠራዊት ፡ የሰጡት ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ሚሊዮን ፡ ዬን ፡ ደረሰ ።

የሆነው ፡ ሆኖ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ የፈጠረው ፡ ይህ ፡ ፖሊቲካ ፡ የጃ ፓንን ፡ አገሬ ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ከጥፋት ፡ ላይ ፡ እንደጣላት ፡ ወደ ፊት ፡ እናገኘዋለን ።

## ጃፓን ፡ በመርከብ ፡ ሥራ ።

ጃፓን ፡ በደሴቶች ፡ ላይ ፡ የምትገኝ ፡ አገር ፡ በመሆኗ ፡ ጃፓ ኖች ፡ ከውጭ ፡ ዓለም ፡ ጋር ፡ ለመገናኘት ፡ ሲሉ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ መርከብ ፡ መሥራት ፡ ግዴታ ፡ ሆኖባቸዋል ። ስለዚህ ፡ እስከ ፡ ፲፮ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ድረስ ፡ በዙሪያቸው ፡ በሚገኙት ፡ ባሕሮች ፡ ላይ ፡ እየተዘዋወሩ ፡ እስከ ፡ ህንድ ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ። ከፍ ፡ ብለን ፡ እንደተመለከትነው ፡ ፖርቱጌዞች ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ገብተው ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ጃፓኖች ፡ ስለ ፡ ነጻነታቸው ፡ ፈርተው ፡ ባስወጧቸውና ፡ ነጮች ፡ ዳግመኛ ፡ በንግድም ፡ ሆነ ፡ በማነኛም ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ አገ ራቸው ፡ እዳይገቡ ፡ ባዋጅ ፡ በከለከሉ ፡ ጊዜ ፡ የጃፓን ፡ ሕዝብም ፡ ትልልቅ ፡ መርከቦች ፡ እንዳይሠሩ ፡ ተከለከሉ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የመርከብ ፡ ሥራ ፡ ጥበብ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከመስፋፋቱ ፡ ተቋረጠ ። በኋላም ፡ የሚይገዢ ፡ ዘመን ፡ ሲጀመር ፡ ጃፓኖች ፡ በመርከብ ፡ ሥራ ፡ እየበረቱ ፡ ሄዱ ።

የንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ አማካሪዎች ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ኃይለኛ ፡ ለመሆንና ፡ በጠቅላላውም ፡ ከታላላቅ ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ ለመተ ካከል ፡ ለሚፈልግ ፡ ለማነኛውም ፡ መንግሥት ከሚያስፈልጉት ፡ ዋኖች ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ መርከቦች ፡ ማግኘት ፡ መሆኑን ፡ ገለጡ ለት ። ስለዚህ ፡ ከ1870 ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ በየጊዜው ፡ የመርከብን ፡ ሥራ ፡ የሚያስፋፋ ፡ ብዙ ፡ አዋጅ ፡ ወጣ ።

ለሥልጣኔ ፡ መሠረት ፡ የሚያገግሉትን ፡ ነገሮች ፡ ለማቋቋምና ፡ ለማደራጀት ፡ እንዳደረገው ፡ ሁሉ ፡ መንግሥቱ ፡ በመርከብ ፡ በኩልም እንደዚሁ ፡ መርከብ ፡ የሚሠሩባቸውን ፡ የመጀመሪያዎቹን ፡ በታ ዎች ፡ ( ሻንቲዬ ፡ ) አቋቋመ ። የመርከብን ፡ አሠራር ፡ የሚያጠኑ ፡ ከሚሲዮኖች ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ላከ ፤ በታላላቆቹም ፡ ውቅ ያኖሶች ፡ ላይ ፡ የማመላለሻን ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ መርከቦች ፡ እንዲ መሠረቱ ፡ አስፈላጊውን ፡ ገንዘብ ፡ ሰጠ ። በ1875 ፡ ዓ. ም መንግ

ሥቱ ፡ በእጁ ፡ የነበሩትን ፡ መርከቦች ፡ ሚትሱቢሺ ፡ ለሚባለው ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ አስተላልፎ ፡ ለቀቀለት ። ከዚሁም ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ መርከብ ፡ ለመሥሪያ ፡ ሩብ ፡ ሚሊዮን ፡ ዬን ፤ እንደዚሁም ፡ መርከ በኞች ፡ ለማስተማሪያ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ ዬን ፡ በመት ፡ በመቱ ፡ ከመንግሥት ፡ ይሰጣቸው ፡ ጀመር ።

ጃፓኖች ፡ በመርከብ ፡ በኩል ፡ ያደረጉትን ፡ የሚያስደንቅ ፡ እርምጃ ፡ ለማወቅ ፡ ያህል ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ማስተዋል ፡ ይበቃል ። እነ ፡ ሚትሱቢሺ ፡ የመርከብን ፡ ሥራ ፡ ከመንግሥት ፡ ሲረከቡ ፡ የጃፓን ፡ መርከቦች ፡ ፀድምሩ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ዘጠኝ ፡ ነበሩ ፤ ጠቅላላ ፡ ክብደታቸውም ፡ አርባ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ (42.000 ፡) ቶን ፡ ነበር ። ከምሳ ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ የመርከቦቻቸው ፡ ጠቅላላ ፡ ክብ ደት ፡ መቶ ፡ ጊዜ ፡ እጥፍ ፡ ሆኖ ፡ ከራት ፡ ሚሊዮን ፡ ቶን ፡ ደረሰ ፡ በ1893 ፡ ዓ. ም. ፡ 680 ፡ ይሆኑ ፡ የነበሩት ፡ መርከከቦቻቸው ፡ ከሶስት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ማለት ፡ በ1896 ፡ ዓ. ም. 899 ፡ መርከቦች ፡ ሆኑ ።

ከሺንና ፡ ከመስኮብ ፡ ጋር ፡ ባደረጓቸው ፡ ጦርነቶች ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ በመርከብ ፡ በኩል ፡ ያላቸው ፡ ኃይል ፡ እያደገና ፡ እየበረታ ፡ ሄደ ። በ1903 ዓ. ም. የመርከቦቻቸው ፡ ጠቅላላ ፡ ክብደት ፡ ካንድ ፡ ሚሊዮን ፡ በላይ ፡ ደረሰ ። በኋላም ፡ ደግሞ ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፤ በመርከብ ፡ በኩል ፡ ጠቃሚ ፡ ውሎች ፡ እየተፈራ ረሙ ፡ ከእንግሊዝና ፡ ከፈረንሣይ ፡ በኩል ፡ ለመርከብ ፡ መሥ ሪያ ፡ የሚሆን ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አገኙ ። በመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ጃፓን ፡ በያይነቱ ፡ የትራንስፖር ፡ ሥራ ፡ እየሠራች ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ስላገኘች ፡ ጦርነቱ ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ የመርከቦቿ ፡ ክብደት ፡ በጠቅላላው ፡ ከሦስት ፡ ሚሊዮን ፡ በላይ ፡ ሆነ ።

ያገርዋ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ መሆናቸው ፡ ቀርተው ፡ የውጭ ፡ አገ ሮችም ፡ መርከቦቿን ፡ ይገዟት ፡ ጀመር ። በመርከብ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ካፒታል ፡ አግብተው ፡ ጥቅም ፡ ተካፋዮች ፡ (አክሲዮኔር ፡) የሆኑት ፡ ሰዎችም ፡ የሚቀበሉት ፡ የትርፍ ፡ ድርሻ ፡ አለመጠን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ገን ዘብ ፡ ሆነ ። በመጨረሻም ፡ ጊዜ ፡ የመርከቦቻቸው ፡ ብዛትና ፡ ጠንካ ራነት ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡ ከመገኘቱ ፡ የተነሣ ፡ ጃፓኖች ፡

በመርከብ ፡ በኩል ከተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥታትና ፡ ከእንግሊዝ ፡ ጋር ፡ ተወዳዳሪዎች ፡ ከመሆናቸው ፡ አልፈው ፡ ለነዚህ ፡ ለሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ የሚያሰጓቸው ፡ ሆኑ ። የደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ መንግሥታትም ፡ አጠገባቸው ፡ ካሉት ፡ ከተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ አልፈው ፡ መርከቦቻቸውን ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ ለማሠራት ፡ መርጠው ፡ ያሠሩ ፡ ጀመር ። እንደዚሁ ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ የጦር ፡ መርከቦች ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ አሠራ ። ስለ ፡ መርከብ ፡ ጉዳይ ፡ ስንናገር ፡ ያሚራል ፡ ቶጎን ፡ ታሪክ ፡ሳንጠቅስ ፡ ልናልፈው ፡ አንችልም ።

ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሜይጊ ፡ በ1868 ዓ. ም. የመርከብ ፡ ትምህርት ፡ እንዲማሩ ፡ ብዙ ፡ ወጣቶች ፡ በላከ ፡ ጊዜ ፡ በእነሱ ፡ መካከል ፡ ሰውነቱ ፡ ከሲታ ፡ የሆነ ፡ ሃዩሃቺሮ ፡ ቶጎ ፡ የሚባል ፡ ልጅ ፡ ነበር ።

ይህ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ሲሄድ ፡ የመርከብንና ፡ የቴክኒኩን ፡ የትምህርት ፡ ቅርንጫፎች ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ እንዲማር ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጥቶት ፡ ነበር ። በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ተቀምጦ ፡ በ1875 ዓ ም ተመልሶ ፡ አገሩ ፡ ገባ ። ይኸ ፡ ሰው ፡ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ መላው ፡ ዓለም ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ የተደነቀበትን ፡ የመርከብ ፡ ውጊያ ፡ አድርጎ ፡ መስኮብን ፡ በባህር ፡ ላይ ፡ ድል ፡ መታት ። በዚሁ ፡ የመርከብ ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ከመስኮብ ፡ በኩል ፡ አራት ፡ ሺ ፡ ሰዎች ፡ ሞተው ፡ ሰባት ፡ ሺ ፡ ሰዎች ፡ ሲማረኩ ፡ ከጃፓን ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ አሥራ ፡ ስድስት ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ሞተውባቸው ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ቆስለውባቸዋል ። ይህን ፡ ጉዳይ ፡ የመረመሩ ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ ዋጋ ፡ ያን ፡ ያህል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ ያለበትን ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ ያገኘች ፡ ጃፓን ፡ ብቻ ፡ ነች ፡ ሲሉ ፡ መስክረዋል ።

ይሁን ፡ እንጅ ፡ ለመስኮብ ፡ የጦር ፡ መርከቦች ፡ መሪ ፡ የነበረው ፡ አሚራል ፡ ዚኒሪ ፡ ፒትሮቪች ፡ ሮዤትስቬንስኪ ፡ የሚባለው ፡ ሰው ፡ በጀግንነቱ ፤ በችሎታውና ፡ በብልህነቱ ፡ በጣም ፡ የታወቀና ፡ የተመሰገነ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በቂ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ሳይሰጡት ፤ እንደዚሁም ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ሳያገኝ ፤ ከመስኮብ ፡ አገር ፡ ተልኮ ፡ ወደ ፡ ጃፓን ፡ አገር ፡ ሲሄድ ፡ የመን

ገዱ ፡ ሩቅነት ፡ ደግሞ ፡ ያንኑ ፡ አነስተኛ ፡ የሆነ ፡ ጉልበቱን ፡ አድ ክሞበት ፡ ነበር ። የመስኮብ ፡ መንግሥት ፡ ፖርት ፡ አርቱር ፡ በሚ ባለው ፡ ወደብ ፡ ላይ ፡ በገኔራል ፡ ቶጎ ፡ መሪነት ፡ የሚዋጉት ፡ የጃፓን ፡ መርከቦች ፡ አደጋ ፡ ጥለው ፡ ያደረጉበትን ፡ ጉዳት ፡ እንደ ፡ ውርደት ፡ ስለቆጠረው ፡ አሚራል ፡ ሮገርስትቬንስኪን ፡ የላከው ፡ ይህ ንኑ ፡ ውርደት ፡ እንዲበቀልለት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በሚገባ ፡ ተጠንቶ ፡ የተዘጋጀ ፡ ጦር ፡ በመስጠት ፡ ፈንታ ፡ የተሰጠው ፡ ጦር ፡ በችኮላ ፡ የተሰበሰበ ፡ ነበር ። ይህ ፡ የመስኮብ ፡ ጦር ፡ ከውጊያ ፡ ቦታ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ፴፫ ፡ ሺ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ መጓዝ ፡ ነበረበት ። በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ እንግሊዝ ፡ የጃፓን ፡ የጦር ፡ ጓደኛ ፡ ስለ ነበረች ፡ በየመንገዱ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ እንደሚያገኘው ፡ ያውቅ ፡ ነበር ።

የሚበልጡትም ፡ መርከበኞች ፡ በየመንገዱ ፡ ወባና ፡ ተቅማጥ ፡ እየታመሙ ፡ ብዙዎች ፡ ሲሞቱ ፡ ብዙዎች ፡ ደግሞ ፡ ተኝተው ፡ ነበር ። እንደዚሁም ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ትልቅ ፡ ማዕበል ፡ ተነሥቶ ፡ ብዙዎቹ ፡ መርከቦች ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ ደረሰባቸው ። ሰባት ፡ ወር ፡ ከተጓዙ ፡ በኋላ ፡ የመስኮብ ፡ መርከቦች ፡ ውጊያው ፡ ከተደረገበት ፡ ቦታ ፡ ደረሱ ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ በማመዛዘን ፡ ድል ፡ የተመታው ፡ የመስኮቡ ፡ አሚራል ፡ ከመንግሥቱ ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀብሎ ፡ ድል ፡ እንደሚሆን ፡ እያወቀው ፡ ሳይከራከርና ፡ ሳያጉረመርም ፡ ተግባሩን ፡ ለመፈጸም ፡ ይህን ፡ መስዋዕትነት ፡ መቀ በሉ ፡ ክብሩ ፡ ድል ፡ ካደረገው ፡ ጠላቱ ፡ ክብር ፡ ጋር ፡ የሚመዛ ዘን ፡ መሆኑን ፡ ታሪክ ፡ መስክሮለታል ። ውጊያው ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ የመስኮቡ ፡ አሚራል ፡ ቆስሎና ፡ ተማርኮ ፡ ከሆስፒታል ፡ ተኝቶ ፡ ስለነበረ ፡ አሚራል ፡ ቶጎ ፡ ሊጠይቀው ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለ ውን ፡ ቃል ፡ ተናግሮታል ፤ «ስለ ፡ እርስዎ ፡ ያለኝን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ልገልጥልዎ ፡ እወዳለሁ ። ድል ፡ መመታት ፡ በያንዳንዳችን ፡ ላይ ፡ ሊደርስብን ፡ የሚችል ፡ ዕድል ፡ ነው ። ከማንኛውም ፡ ነገር ፡ የሚበልጠው ፡ ተግባርን ፡ ፈጽሞ ፡ መገኘት ፡ ብቻ ፡ ነው ። እርስ ዎና ፡ ሰዎችዎ ፡ በጣም ፡ የሚያስደንቅ ፡ የጀግና ፡ ሥራ ፡ ሠርታ ችኋል ። አሁን ፡ የሚቀረኝ ፡ በቶሎ ፡ ድነው ፡ እንዲነሡ ፡ ያለኝን ፡ ምኞት ፡ መግለጥ ፡ ብቻ ፡ ነው ።»

ባጭሩ ፡ ጃፓን ፡ በመርከብ ፡ በኩል ፡ የሠራችውን ፡ የሚያስደ ንቅ ፡ ሥራ ፡ ለመረዳት ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ መገንዘብ ፡ ያስፈልጋል ። የመርከብን ፡ ሥራ ፡ እንዲማር ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ተልኮ ፡ የነበረው ፡ አሚራል ፡ ቶጎ ፡ ትምህርቱን ፡ ጨርሶ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ ሰላሳ ፡ ዓመት ፡ ቆይቶ ፡ መስከብን ፡ ድል ፡ አደረጋት ። ከስ ድሳ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ማለት ፡ በ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ. ም. የጃ ፓን ፡ የመርከብ ፡ ሚኒስትር ፡ የሆነው ፡ አሚራል ፡ ኦሱሚ ፡ « የጃ ፓን ፡ የጦር ፡ መርከብ ፡ ሠራዊት ፡ በምሥራቅ ፡ በሮች ፡ ላይ ፡ ከማ ነኛውም ፡ መንግሥት ፡ የመርከብ ፡ ሠራዊት ፡ ጋር ፡ ለመወዳደር ፡ ስለሚችልና ፡ ማንንም ፡ ስለማይፈራ ፡ ከተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግ ሥታትና ፡ ከእንግሊዝ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ለኩል ፡ ሆኖ ፡ ያላንድ ፡ ልዩነት ፡ እንዲቆጠር ፡ ይጠይቃል ፡» ሲል ፡ ለመላው ፡ ዓለም ፡ አስታወቀ ።

የመርከብ ፡ ሹማምንቶች ፡ የሆኑት ፡ ደሞዛቸው ፡ በሌላ ፡ አገር ፡ እነሱን ፡ የመሰሉት ፡ ሠራተኞች ፡ ከሚያገኙት ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ነው ። ከዚያው ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ለመርከብ ፡ ሥራ ፡ እር ዳታ ፡ እያሉ ፡ ከቀለባቸው ፡ ቀንሰው ፡ ይሰጣሉ ። ሦስት ፡ ጋሎን ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ የጃፓን ፡ የመርከብ ፡ ሹም ፡ የጃፓንን ፡ መርከቦች ፡ ለጎበኘ ፡ ላንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ ይባላል ፤ » እርግጥ ፡ ነው ፡ የምንቀበለው ፡ ቀለብ ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ቤተ ፡ ሰባችንን ፡ ለመመገብ ፡ እንኳ ፡ ያንሰናል ። ነገር ፡ ግን ፡ እኛ ፡ እንዲህ ፡ እየተቸገርን ፡ በምናደርገው ፡ እርዳታ ፡ ለምሳሌ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ አገራችን ፡ ሦስት ፡ አዲስ ፡ መርከቦች ፡ ለመሥራት ፡ ችላለች ። »

እነሆ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ጃፓን ፡ ከታላላቆቹ ፡ የዓለም ፡ መንግ ሥታት ፡ እኩል ፡ የሚሆን ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ባገርዋ ፡ አቋቁማ ፡ በያይነቱ ፤ ለዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ዕቃ ፡ እየሠራችና ፡ በመ ርከቦቿ ፡ ጭና ፡ ባራቱ ፡ ማዕዘን ፡ በሚገኙት ፡ በዓለም ፡ ገበያዎች ፡ ላይ ፡ ወስዳ ፡ እየሸጠች ፡ ኃይሏና ፡ ሀብቷ ፡ በጣም ፡ እያደገ ፡ በመሄዱ ፡ ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ላሜሪካም ፡ ሆነ ፡ ላውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ አስግታቸዋለች ፡ ቢባል ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ ሕዝቧ ፡ የግል ፡ ጥቅማቸውን ፡ ለመንግሥታቸው ፡ ጥቅም ፡ ሲሉ ፡ መስዋዕት ፡ ማድረግን ፡ የሚያውቁበት ፡ በመሆናቸው ፡ ነው ።

## ጃፓን ፡ በማንድሹሪ ።

ጃፓን ፡ መስከብን ፡ ድል ፡ ከመታች ፡ በኋላ ፡ ማንድሹሪን ፡ እጅ ፡ አደረገች ። ይህንንም ፡ አገር ፡ በመያዟ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ አገኘችበት ። በእርሻና ፡ ባታክልት ፡ ሥራ ፡ ያገኘችውን ፡ ጥቅም ፡ ለብቻው ፡ ትተን ፡ በማዕድን ፡ ረገድ ፡ ያገኘችውን ፡ እና ስተውል ። በመጀመሪያው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደተመለከተው ፡ ጃፓን ፡ አገርዋ ፡ ሀብት ፡ የሌለውና ፡ ማዕድን ፡ የማይገኝበት ፡ ነው ።

ማንድሹሪን ፡ በያዘች ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ይህቺ ፡ አገር ፡ በማዕ ድን ፡ ሀብታም ፡ በመሆኗ ፡ ብረት ፡ የድንጊያ ፡ ከሰል ፡ ወርቅ ፡ ቤንዚንና ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አገኘች ። እንደ ዚሁም ፡ ስንዴ ፡ የሱፍ ፡ ጨርቅ ፡ ለመሥሪያ ፡ የሚሆን ፡ የበግ ፡ ጠጉር ፡ ጥጥ ፡ ትንባሆ ፡ ቀይ ፡ ስር ፡ ለክብሪትና ፡ ለወረቀት ፡ መሥ ሪያ ፡ የሚሆን ፡ በያይነቱ ፡ እንጨት ፡ ስላገኘች ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ ለማሠራት ፡ ሥራ ፡ አጥተው ፡ የነበሩትን ፡ ያገርዋን ፡ ሰዎች ፡ ወደ ዚያ ፡ እየወሰደች ፡ እንዲሠሩና ፡ እንጀራ ፡ እንዲያገኙ ፡ አደረገች ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሀብት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ስላፈራላት ፡ ወዲያው ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰላሳ ፡ አንድ ፡ የሚሆን ፡ ፋብሪካ ፡ አቋቋመች ። በማንድ ሹሪ ፡ የሚገኙት ፡ ለፋብሪካዎቿ ፡ የሚሆኑት ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶች ፡ የድንጊያ ፡ ከሰልን ፡ ብረትን ፡ እንጨትንና ፡ ቤንዚንን ፡ የመሰሉት ፡ በእሷ ፡ ተቆጣጣሪነት ፡ ውስጥ ፡ ሆኑ ። የማንድሹሪ ፡ተወላጆች ፡ የሆ ኑት ፡ የቀን ፡ ሠራተኞች ፡ ደግሞ ፡ ከጃፓን ፡ ተወላጆች ፡ ባነሰ ፡ ዋጋ ፡ የሚሠሩ ፡ በመሆናቸው ፡ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ለጃፓን ፡ ተጨ ማሪ ፡ ጥቅም ፡ ሆነላት ።

የጃፓን ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ፡ የሆነው ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ አሳቡን ፡ ሲገልጥ ፡ "ማንድሹሪና ፡ ሞንጎሊ ፡ የተፈጥሮ ሀብቶችን ፡ የምናገኝባቸው ፡ ጠቃሚዎች ፡ የሆኑ ፡ ምንጮች ፡ ሆነው የተገኙልን ፡ ለኛ ፡ ቅርብ ፡ በመሆናቸው ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ የት ራንስፖሩን ፡ ጥበቃ ፡ የተረጋገጠ ፡ ስለሚያደርግልን ፡ ነው ። ቀድሞ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶችን ፡ ሁሉ ፡ የምናመጣቸው ፡ ከሩቅ ፡ አገሮች በመሆኑ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ የማይመች ፡ መሆኑ ፡ ብቻ

ሳይሆን ፡ ይልቁንም ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ለትራንፖርቱ ፡ ሥራ ፡ እጅግ ፡ የሚያሠጋ ፡ አደጋ ፡ ነበረበት ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ አሳብ ፡ ጃፓን ፡ ፈቷን ፡ ወደ ፡ ማንድሹሪና ፡ ወደ ፡ ሞንጎሊ ፡ መመለስ ፡ ግዴታ ፡ የሆነባትን ፡ ምክንያት ፡ ሰው ፡ እንዲረዳው ፡ ያደርጋል ። » ብሎ ፡ ተናገረ ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ጃፓን ፡ በተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ በኩል ፡ የነበረባትን ፡ ችግር ፡ ማንድሹሪን ፡ በመያዟ ፡ ያስወገደችው ፡ መስሎ ፡ ቢታያት ፡ ይህን ፡ አገር ፡ በመያዟ ፡ የሚከራከርዋትና ፡ የሚቃወሟት ፡ መስኮብና ፡ ሺና ፡ አሉ ። በመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ጃፓን ፡ ከጦር ፡ ጓደኞች ፡ ጋር ፡ አብራ ፡ ስለተሰለፈች ፡ በሺና ፡ ላይ ፡ በያይነቱ ፡ የጭቆና ፡ ሥራ ፡ እየሠራች ፡ በማንድሹሪና ፡ በምሥራቃዊው ፡ የሞንጎሊ ፡ አገር ፡ ጥቅሟን ፡ ለማስፋፋት ፡ ችላለች ። በፖለቲካ ፣ በገንዘብና ፡ በጦር ፡ ሥራ ፡ ክፍሎች ፡ ሺና ፡ በእነዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ በቂ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ የጃፓን ፡ ተወላጆች ፡ የሆኑ ፡ አማካሪዎች ፡ ትቀበላለች ። „ “ ዋና ፡ ዋኖች ፡ በሆኑት ፡ አገሮች ፡ ወይም ፡ በታዎች ፡ ሺናውያንና ፡ ጃፓኖች ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ የፖሊስ ፡ ሥራ ፡ ይሠራሉ ። „ “ ሺና ፡ ከመቶ ፡ አምሳ ፡ 50% የሚሆነውን ፡ የሚያስፈልጋትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ከጃፓን ፡ ላይ ፡ ትገዛለች ፣ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ሁለቱ ፡ አገሮች ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ ባዋጡት ፡ ገንዘብ ፡ ጃፓን ፡ በሺና ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ፋብሪካ ፡ አቋቁማ ፡ የጃፓን ፡ ተወላጆች ፡ የሆኑ ፡ የቴክኒክ ፡ ኤክስፔርቶች ፡ እንዲያካሂዱት ፡ ታደርጋለች ፤ ለፋብሪካው ፡ የሚያስፈልገውም ፡ ማዕድን ፡ ከጃፓን ፡ አገር ፡ ይገዛል ። „ የሚሉ ፡ ቃሎች ፡ በ፩ኛ ፣ በ፫ኛና ፡ በ፬ኛ ፡ አንቀጾች ፡ የሚገኙበት ፡ ውል ፡ በ1915 ፡ ዓ. ም. ጃፓን ፡ አቅርባ ፡ ሺናን ፡ በግድ ፡ አስፈረመቻት ። ያውሮፓ ፡ መንግሥታትም ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ አስፈሪ ፡ በሆነው ፡ ጦርነት ፡ አሳባቸው ፡ ተጠምዶ ፡ ስለነበረ ፤ በሌላም ፡ በኩል ፡ ጃፓን ፡ የጦር ፡ ጓደኛቸው ፡ ስለሆነች ፡ ሊቃወሟት ፡ ባለመቻላቸው ፡ ለጊዜው ፡ ምንም ፡ ሊያደርጉ ፡ አልቻሉም ። ሺና ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ጭቆና ፡ የሞላበት ፡ ውል ፡ ስላስፈረመቻት ፡ በጃፓን ፡ ላይ ፡ የጠላትነት ፡ መንፈስ ፡ አድሮባት ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ጃፓን ፡ በማንድሹሪ ፡ ያለውን ፡ ሀብት ፡

እንዳትጠቀምበት ፡ ለመከላከል ፡ የተቃዋሚነትና ፡ የወንበዴነት ፡ ሥራ ፡
እየሠራች ፡ ታስቸግራት ፡ ጀመር ። ይህንንም ፡ ማድረጓ ፡ ምንም ፡
እንኳ ፡ ጃፓን ፡ በማንድሹሪ ፡ የሚገኘው ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ እን
ዲሠራበት ፡ ለማድረግ ፡ ብዙ ፡ ሚሊያርድ ፡ ገንዘብ ፡ ወጭ ፡ ብታደርግ ፡
የሚበልጠውን ፡ ጥቅም ፡ ለመውሰድ ፡ አስባ ፡ መሆኑን ፡ ስላወ
ቀች ፡ ነው ።

ሺናውያን ፡ ደግሞ ፡ በበኩላቸው ፡ የሚያስቡት ፡ ለመጭው ፡ ትውልድ ፡
ነው ። ሀብቱን ፡ ጃፓን ፡ ወስዳ ፡ ብትጨርሰው ፡ አገሩ ፡ ባዶ ፡ ቀለህ ፡
ሆኖ ፡ ስለሚቀር ፡ ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ ችሎታ ፡ አግኝተው ፡ ራሳቸው ፡
የሚጠቀሙበት ፡ ዘመን ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ እየተከላከሉ ፡ ጠብቆ ፡
መኖር ፡ የሚገባቸው ፡ መሆኑን ፡ በማስተዋል ፡ ደረሱበት ። ከዚህም ፡
የተነሣ ፡ ማዕድን ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ከሺና ፡ መንግሥት ፡ በቀር ፡
ሌላ ፡ ማነኛውም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡
የንግድ ፡ ማኅበር ፡ እንዳይጠቀምበት ፡ ተከለከለ ። እንደዚሁም ፡ መሬ
ቱን ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጆች ፡ የሸጠ ፡ ወይም ፡ ለረጅም ፡ ዘመን ፡
ያከራየ ፡ ሰው ፡ ከአምስት ፡ እስከ ፡ ሀያ ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ እሥ
ራት ፡ አለዚያም ፡ በሞት ፡ እንደ ፡ ጥፋቱ ፡ ትልቅነት ፡ ይቀጣል ፡
ብለው ፡ ባዋጅ ፡ ከለከሉ ። የጃፓንን ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ የማንድሹሪ ፡
ሕዝብ ፡ እንዳይገዛ ፤ የጃፓንን ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ እየጫነ ፡ እንዳያመ
ላልስ ፤ በጃፓን ፡ ገንዘብ ፡ እንዳይገበያይ ፤ በጃፓን ፡ ባንክ ፡ ገንዘ
ቡን ፡ እንዳያስቀምጥ ፤ ከጃፓን ፡ ተወላጆች ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ እንዳ
ያደርግ ፤ ለጃፓን ፡ ተቀጥሮ ፡ እንዳይሠራና ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመ
ሰለ ፡ የጃፓንን ፡ ጥቅም ፡ የሚያበላሽ ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጸም ፡ ሕዝብ ፡
የሚያሰድሙ ፡ ማኅበሮች ፡ ሺናውያን ፡ በ1931 ዓ. ም. አቋቋሙ ። በመካከ
ላቸው ፡ ያለው ፡ ጠብ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ እየከረረ ፡ ስለሄደ ፡ በመጨረሻ ፡
በዚሁ ፡ በ1931 ዓ. ም. በመካከላቸው ፡ ጦርነት ፡ ፈነዳ ።

በሌሎቹ ፡ በሠለጠኑት ፡ አገሮች ፡ ቢሆን ፡ የመንግሥቱ ፡ ፖሊ
ቲካ ፡ የሚመራው ፡ በውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ በኩል ፡ ስለሆነ ፡
የፖሊቲካው ፡ አላፊዎች ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ በጉዳዩ ፡ ተከራክረው
በት ፡ ከቃታቸው ፡ በኋላ ፡ የጦርነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ሰጥተው ፡ ግን
ኙነታቸውን ፡ ጠላት ፡ ከሆነው ፡ አገር ፡ ጋር ፡ እንዲያቋርጡና ፡

ውጊያ ፡ እንዲጀመር ፡ እስቲፈቅዱ ፡ ድረስ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ጦር ነት ፡ ሊያነሣ ፡ አይችልም ።

በጃፓን ፡ አገር ፡ ግን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወገኖች ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ ስለዚሁ ፡ በተጻፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ የማንንም ፡ አሳብ ፡ አንቀበልም ፡ እያሉ ፡ እንደ ፡ ፈቀዱ ፡ መሥራት ፡ ከጀመሩ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖ ፡ ነበርና ፡ በማንድሹሪ ፡ ምክንያት ፡ ከሺና ፡ ጋር ፡ ጦርነትን ፡ ያነሡት ፡ በራሳቸው ፡ አሳብና ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

የማንድሹሪ ፡ ጦርነት ፡ በኤንተርናሲዮናል ፡ ፖሊቲካ ፡ በኩል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳይ ፡ መሆኑን ፡ እናስታውሳለን ። ጃፓንና ፡ ሺና ፡ በዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ አባሎች ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ጃፓን ፡ የአጥቂነትን ፡ ሥራ ፡ በሺና ፡ ላይ ፡ ስትሠራበት ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ግፈኛውን ፡ መንግሥት ፡ ቀጥቶ ፡ ጦርነቱን ፡ ማቆም ፡ ግዴታ ፡ ነበረበት ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሳያደርግ ፡ ቀረ ። ጃፓንም ፡ የማንድሹሪን ፡ አገር ፡ ለመውረር ፡ ስትል ፡ ከዓለም ፡ መን ግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ወጣች ። ስለዚህ ፡ በሙሶሊኒ ፡ መሪነት ፡ የኢ ጣሊያ ፡ ፋሺስት ፡ መንግሥት ፡ ይህንኑ ፡ የመሰለ ፡ የግፍ ፡ ወረራ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ሠርቶ ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ የመ ሠረተውን ፡ የሰላም ፡ መድኅን ፡ ጨርሶ ፡ እስቲያጠፋው ፡ ድረስ ፡ ግፈኞች ፡ መንግሥታት ፡ የተመሩበትን ፡ የጥጋብ ፡ መንፈስ ፡ ፈጥራ ፡ ጀርመንና ፡ ኢጣሊያ ፡ ከዓለም ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ እንዲወጡ ፡ በሩን ፡ የከፈተችላቸው ፡ ጃፓን ፡ ነች ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሺናውያን ፡ ደግሞ ፡ በበኩላቸው ፡ ጃፓን ፡ የእነሱን ፡ ሀብትና ፡ የእነሱን ፡ ጉልበት ፡ መሣ ርያ ፡ አድርጋ ፡ የመጨረሻ ፡ ዓላማዋን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ለመፈጸም ፡ የተነሣች ፡ መሆንዋን ፡ በተረዱት ፡ ጊዜ ፡ ጃፓን ፡ ያልጠረጠረችው ፡ የተቃዋሚነት ፡ መንፈስ ፡ አድሮባቸው ፡ ላገራቸው ፡ ጥቅም ፡ ተከላ ካዮች ፡ ሆነው ፡ ተነሡበት ። በ1927 ዓ. ም. የጃፓን ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒ ስትር ፡ የነበረው ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ለሚካዶ ፡ ባቀረበው ፡ የም ሥጢር ፡ ራፖር ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ።

"ሺናን ፡ ድል ፡ አድርገን ፡ ለመያዝ ፡ ስንፈልግ ፡ አስቀድሞ ፡ ማንድሹሪንና ፡ ሞንጎሊን ፡ ድል ፡ አድርገን ፡ መያዝ ፡ ይገባናል ።

ዓለምን ፡ ድል ፡ አድርገን ፡ ለመያዝ ፡ ስንመኝ ፡ ደግሞ ፡ አስቀድ
መን ፡ ሺናን ፡ ድል ፡ አድርገን ፡ መያዝ ፡ ይገባናል ፡፡

የጃፓን ፡ ፕላን ፡ ይህ ፡ ሲሆን ፡ ሺና ፡ በተከላካይነቷ ፡ ለጃፓን ፡
ወረራ ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆና ፡ በመገኘቷ ፡ አቅዷን ፡ ሁሉ ፡ ያበላሸችብ
ትና ፡ ያስናከለችባት ፡ መሆኗ ፡ ግልጥ ፡ ነገር ፡ ነው ፡፡ ይሁን ፡ እንጅ ፡
በመጨረሻ ፡ ጃፓን ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ኃይል ፡ ተዋግታ ፡ የማትገ
ፋው ፡ ነገር ፡ ስለሆነባት ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ አገሩን ፡ ለመያዝ ፡
የምትችልበት ፡ ዘዴ ፡ ፈልጋ ፡ ከንግቲሀ ፡ ፑ. ዒ. የሚባል ፡ ንጉሥ ፡
በማንድሹሪ ፡ አነገሠች ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ ለጃፓን ፡ መሣ
ሪያ ፡ ሆኖ ፡ ከማገልገል ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ እንደማይሠራ ፡ ማንም ፡
ሰው ፡ ቢሆን ፡ አልሰተውም ፡፡

## ጃፓንና ፡ መስኮብ ፡ በሲቤሪ ፡፡

ጃፓን ፡ በገርዋ ፡ ውስጥ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ የሆኑት ፡ ለፋብ
ሪካዎቿ ፡ የሚያስፈልጉዋት ፡ ዋና ፡ ዋናች ፡ ነገሮች ፡ ባለመገኘታቸው ፡
የኢንዱስትሪም ፡ ሥራዋ ፡ እያደገ ፡ በመሔዱ ፡ ከደረሰችበት ፡ ከፍተኛ ፡
ደረጃ ፡ ጋር ፡ የሚመዛዘን ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ ለማግኘት ፤ የምት
ችልበትን ፡ መንገድ ፡ ከመፈለግ ፡ አላቋረጠችም ፡፡ ሲቤሪ ፡ የሚባለው ፡
አገር ፡ ስፋቱ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ መላው ፡ አውሮፓን ፡ የሚያህል ፡ ሆኖ ፡
በውስጡ ፡ በያይነቱ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶች ፡ የሚገኙበት ፡ ባለጸጋ ፡
አገር ፡ ነው ፡፡

ይህ ፡ አገር ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የሚገኘው ፡ በመ
ስኮብ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ቢሆን ፡ በገዦግራፊ ፡ አቀማመጥ ፡ ከጃፓን ፡
ጋር ፡ የሚቀራረብ ፡ ትይዩ ፡ በመሆኑ ፡ ጃፓን ፡ ዓይኖቿን ፡ ሳትጥል
በት ፡ አልቀረችም ፡፡ በ1905 ፡ ዓ. ም. በመስኮብና ፡ በጃፓን ፡ መከ
ከል ፡ በሆነው ፡ ጦርነት ፡ ጃፓን ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ ስትሆን ፡ ማን
ድሹሪን ፡ እጅ ፡ አድርጋ ፡ የመስኮብ ፡ ንግድ ፡ ወደ ፡ እስያ ፡ እንዳ
ይተላለፍ ፡ በሩን ፡ ዘጋችው ፡፡ በሲቤሪ ፡ የሚገኙትም ፡ ሀብቶች ፡ ልዩ ፡
ልዩ ፡ እንጨት ፤ ዓሣ ፡ ቤንዚን ፡ በያይነቱ ፡ የብረት ፡ ማዕድንና የደ
ንጊያ ፡ ከሰል ፡ ናቸው ፡፡ ከዚህም ፡ በቀር ፡ ይልቁንም ፡ በማነኛውም ፡

ጊዜ ፡ በመስኮብና ፡ በጃፓን ፡ መካከል ፡ ጦርነት ፡ ቢነሣ ፡ መስኮብ ይህን ፡ አገር ፡ የጦር ፡ ሠፈር ፡ አድርጋ ፡ አኤሮፕላኖቿንና ፡ መርከቦቿን ፡ ከዚያ ፡ እያስነሣች ፡ የጃፓንን ፡ አገር ፡ ለመደብደብ ፡ ይመቻታል ።

ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ በማመዛዘን ፡ ጃፓን ፡ ይህን ፡ አገር ፡ ከመስኮብ ፡ ላይ ፡ ቀምታ ፡ ለመያዝ ፡ አሰበች ።

በመስኮብ ፡ አገር ፡ በ1917 ዓ. ም. ሬቮሊሲዮን ፡ ሆኖ ፡ የንጉሡ ፡ መንግሥት ፡ ወድቆ ፡ የኮሚኒስም ፡ መንግሥት ፡ በተቋቋመ ፡ ጊዜ ፡ ጃፓን ፡ የመስኮብ ፡ መንግሥት ፡ ባገሩ ፡ ውስጥ ፡ በሆነው ፡ ውጊያና ፡ ብጥብጥ ፡ እንደ ፡ ደከመ ፡ አስተውላ ፡ ይህን ፡ ምኞቷን ፡ ለመፈጸም ፡ የምትችልበት ፡ ጊዜ ፡ የደረሰ ፡ መስሎ ፡ ታያት ። መስኮብ ፡ ደግሞ ፡ በበኬሏ ፡ ይህንኑ ፡ ተረድታው ፡ መንግሥቷ ፡ እስቲጠናና ፡ ኃይል ፡ እስከታገኝ ፡ ድረስ ፡ ከጃፓን ፡ ጋር ፡ ግጭት ፡ ማድረግ ፡ ጉዳት ፡ እንደሚያስከትልባት ፡ ስላወቀችው ፡ ጃፓንን ፡ ማባበልና ፡ የስምምነት ፡ ውል ፡ እናድርግ ፡ እያለች ፡ መለማመጥ ፡ ግድ ፡ ሆነባት ። ጃፓን ፡ ግን ፡ በውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትርዋ ፡ በሙሴ ፡ ኮኪ ፡ ሂሮታ ፡ አማካይነት ፤ « እጃችንን ፡ ወደፈለግነው ፡ ቦታ ፡ ለመሰንዘር ፡ እንድንችል ፡ ነፃ ፡ ልናደርገው ፡ እንፈልጋለን ። » ብላ ፡ ማነኛውንም ፡ ውል ፡ እምቢ ፡ በማለት ፡ መልስ ፡ ሰጠች ። ይኸውም ፡ እጃችን ፡ በውል ፡ እንዲታሰር ፡ አንፈልግም ፡ ማለት ፡ ነው ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ የጃፓኖች ፡ ምኞት ፡ በማንድሹሪ ፤ በሞንጎሊና ፡ በሲቤሪ ፡ ላይ ፡ የተሰነዘረ ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ታየ ።

ነገር ፡ ግን ፡ መስኮብ ፡ በሬት ፡ በሌኒን ፤ ቀጥሎም ፡ በስታሊን ፡ መሬነት ፡ ኃይል ፡ እያገኘች ፡ ስለሄደች ፡ ለጃፓን ፡ ትልቅ ፡ ተወዳዳሪ ፡ ሆና ፡ መታየት ፡ ጀመረች ። ይልቁንም ፡ በ1928 ዓ. ም. ስታሊን ፡ የሲቤሪን ፡ አውራጃ ፡ በኢንዱስትሪ ፡ የጠነከረ ፡ ለማድረግ ፡ አቅዶ ፡ ብፈጸመው ፡ ፕሮግራም ፡ ይህ ፡ አውራጃ ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ የእስረኞች ፡ ማኖሪያ ፡ አገር ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ማዕድኑና ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቱ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ሆነ ። ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ደግሞ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘው ፡ ነገር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ፡

በሲቤሪ ፡ አውራጃ ፡ የሚገኙት ፡ የመስኮብ ፡ ፋብሪካዎች ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ ባያይነቱ ፡ ለንግድ ፡ የሚሆኑና ፡ ለኑሮ ፡ የሚያገለግሉ ፡ ነገሮች ፡ እየሠሩ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ በሀያ ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ ተለውጠው ፡ በያይነቱ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እንዲሠሩ ፡ ይደረጋሉ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ በ1933 ዓ ም የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እንዲሠሩ ፡ ስለታዘዘ ፡ ለሰላም ፡ ኑሮ ፡ የሚያገለግሉ ፡ ዕቃዎች ፡ መሥራታቸው ፡ ቀርቶ ፡ በያይነቱ ፡ ታንኮች ፤ አኤሮፕላኖች ፡ ትራክተሮችና ፡ ጥይትም ፡ ይሠሩ ፡ ጀመር ። በሰላም ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ከእነዚሁ ፡ ፋብሪካዎች ፡ እየተሠሩ ፡ የሚወጡት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ሺናን ፡ አፍጋኒስታንን ፤ ሞንጎሊንና ፡ ህንድንም ፡ ሳይቀር ፡ እንዳያጥለቀልቋቸው ፡ ለማድረግ ፡ በመስኮብ ፡ ስሌች ፡ ውስጥ ፡ የታቀደ ፡ ነገር ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ። ጃፓን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ኢንዱስትሪዋን ፡ በጣም ፡ ብታስፋፋው ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ ስለሌላት ፡ ይህን ፡ ጉድለት ፡ ለማሻሻል ፡ የምትችለው ፡ የጎረቤቶቿን ፡ ደካማነት ፡ በመደገፍ ፡ ነበር ። አሁን ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ባገርዋ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኘው ፡ ሀብት ፡ የምትበልጣት ፡ መስኮብ ፡ ከእንቅልፋዋ ፡ ነቅታ ፡ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ኢንዱስትሪዋን ፡ ስላስፋፋችና ፡ ስለጠነከረች ፡ ለጃፓን ፡ ትልቅ ፡ አደጋ ፡ እንደፈጠረችባት ፡ ከማንም ፡ ይልቅ ፡ ጃፓኖች ፡ አውቀውታል ። ጃፓን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ በማስተዋል ፡ የመስኮብን ፡ ኃይል ፡ ለማድከም ፡ ስትል ፡ ጠላቷ ፡ ከሆነችው ፡ ከቱርክ ፡ ጋር ፡ መስማማት ፡ የተሻለ ፡ ነገር ፡ ስለመሰላት ፡ ከቱርክ ፡ የሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳን ፡ ከኬማል ፡ ፓሻ ፡ ጋር ፡ በ1934 ዓ ም ንግግር ፡ ጀመረች ። በዓለም ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እንደምንመለከተው ፡ ሁሉ ፡ በምስኮብና ፡ በቱርክ ፡ መካከል ፡ በየዘመኑ ፡ ግጭትና ፡ ጦርነት ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነውና ፡ ቱርክ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ጠላቷ ፡ የሆነችውን ፡ መስኮብን ፡ ለማጥቃት ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ባትችል ፡ እንኳ ፡ ራሷን ፡ ለመጠበቅና ፡ ለመከላከል ፡ ስትል ፡ የጃፓን ፡ እርዳታ ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ አስተውላ ፡ የንግድ ፡ ግንኙነት ፡ አድርጋ ፡ የሚያስፈልጓትንም ፡ መርከቦች ፡ ከጃፓን ፡ ትገዛ ፡ ጀመር ።

ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ስንጽፍ ፡ ዋና ፡ የተነሣንበት ፡ አሳብ ፡ ጃፓን ፡ በጥቂት ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ የፈጸመችውን ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡

ለመግለጥ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በዚህ ፡ ባለንበት ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ከመ
ስከብ ፡ ጋር ፡ የገጠማትን ፡ ትግል ፡ በሰፊው ፡ መናገር ፡ ግዴታ ፡
ሆነብን ። አንድ ፡ መንግሥት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ጠንክሮ ፡ ሀብታምና ፡
ኃይለኛ ፡ ለመሆን ፡ ቢሠራ ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ እንቅፋትና ፡ ችግር ፡
የሚገጥመው ፡ መሆኑን ፡ መዘንጋት ፡ አይገባንም ። የትግል ፡ ቦታ ፡
በሆነችው ፡ በዚህች ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ የሕዝቦች ፡ ትልቅነት ፡ የሚገ
መተው ፡ የሚገጥማቸውን ፡ እንቅፋት ፡ አሸንፈው ፡ ለመኖር ፡ በሚያ
ሳዩት ፡ ብርታትና ፡ በሚፈጥሩት ፡ ዘዴ ፡ ነው ። ይህንኑ ፡ ለመግለጥ ፡
ያህል ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ጃፓን ፡ የገጠማትን ፡ ትግል ፡ ባጭሩ ፡
ካስተዋልነው ፡ በኋላ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ አሳባችን ፡ ተመልሰን ፡
በተለየ ፡ ስለጃፓን ፡ ጉዳይ ፡ እንናገራለን ።

ጃፓኖች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ እጅግ ፡ የሚያስደንቅና ፡ የሚያስመ
ሰግን ፡ እርምጃ ፡ አድርገው ፡ በኢንዱስትሪም ፡ ሆነ ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ ከታ
ላላቆቹ ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ጋር ፡ በጥቂት ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡
ለመፎካከር ፡ ቢችሉ ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ እየቀዱና ፡ እየገለበጡ ፡
ነው ፡ እንጅ ፡ ከራሳቸው ፡ አመንጭተው ፡ የሠሩት ፡ ምንም ፡ ነገር ፡
አይገኝም ፡ እየተባሉ ፡ ታምተዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ዘለፋ ፡
የሚያስተባብል ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ ጃፓኖች ፡ ያሳዩ ፡ መሆናቸውን ፡
ለመግለጥ ፡ ያህል ፡ አንድ ፡ ማስረጃ ፡ እንሰጣለን ። በ1933 ዓ. ም.
በማንቸስተር ፡ የሚገኙት ፡ የእንግሊዝ ፡ የጨርቅ ፡ ፋብሪካ ፡ ባለቤቶች ፡
የጃፓን ፡ ፋብሪካዎች ፡ አዲስ ፡ መኪናዎች ፡ ሠርተው ፡ በጥቂት ፡
ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በብዛቱም ፡ ሆነ ፡ በጥራቱ ፡ ከእንግሊዝ ፡ የበለጠ ፡
ጨርቅ ፡ እየሠሩ ፡ የእነሱን ፡ ንግድ ፡ ሊገድሉባቸው ፡ እንደተነሡ ፡
አውቀውት ፡ በዚህም ፡ ከጃፓኖች ፡ ጋር ፡ ለመወዳደርና ፡ ለመፎካከር ፡
ተጣጥረው ፡ ሳይቻላቸው ፡ በመቅረቱ ፡ እነዚህ ፡ አዲሶቹ ፡ የጃፓን ፡ መኪ
ናዎች ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ ጥበብ ፡ የተሠሩ ፡ መሆናቸውን ፡ ለማወቅ ፡
አስበው ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ የሚሆኑ ፡ የፈትል ፡ መኪናዎች ፡ ለፋብሪ
ካቸው ፡ ሊገዙ ፡ ከጃፓን ፡ አገር ፡ ጠየቁ ።

እነዚሁም ፡ መኪናዎች ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ሊላኩ ፡ አዛካ ፡
በሚባለው ፡ ወደብ ፡ ላይ ፡ በሣጥን ፡ ሆነው ፡ ቀርበው ፡ ሳሉ ፡ የጃ
ፓን ፡ የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ እንዳይላኩ ፡ ከልክሎ ፡ እንዲመለሱ ፡

አዘዘ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የእነዚህን ፡ የአዲሶቹን ፡ መኪናዎች ፡ አሠራር ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ አይተው ፡ ጥበቡን ፡ እንዳያገኙባቸው ፡ ለማድረግ ፡ ጃፓኖች ፡ መኪናዎቹን ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ እንዳይሸጡ ፡ በሕግ ፡ ከለከሉ ። ጃፓኖች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የሠለጠኑት ፡ ያውሮፓን ፡ ጥበብ ፡ ቀድተው ፡ በኋላ ፡ ጊዜ ፡ ከራሳቸው ፡ እያመነጩ ፡ መምህራኖቻቸው ፡ የሆኑትን ፡ አውሮፓውያንን ፡ ለመተካከልና ፡ ለመብለጥም ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ለመግለጥ ፡ ያህል ፡ ይህን ፡ ምሳሌ ፡ ስንሰጥ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ራሳቸው ፡ ከሰው ፡ እየቀዱ ፡ እንዲሠለጥኑ ፡ ዓለም ፡ እንደፈቀደላቸው ፡ ዘንግተውት ፡ በበኩላቸው ፡ ያገኙትን ፡ ጥበብ ፡ ዓለም ፡ እንዳያውቅባቸው ፡ መከልከላቸው ፡ የሚያስወቅሳቸው ፡ መሆኑን ፡ ሳናሳስብ ፡ ልናልፈው ፡ አይገባንም ።

ጃፖኖች ፡ እንደዚህ ፡ አድርገው ፡ ስድሳ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ጠንክረው ፡ በመሥራት ፡ ከሠለጠኑ ፡ በኋላ ፡ በልባቸው ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የትዕቢት ፡ መንፈስ ፡ አደረባቸው ። በመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ማለቂያ ፡ ላይ ፡ ማለት ፡ በ1918 ዓ. ም. ዤኔራል ፡ ርርካ ፡ የሚባለው ፡ የጃፖን ፡ የጦር ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ የተናገረው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ የምንጠቅሰው ፡ ንግግር ፡ በጃፓኖች ፡ ዘንድ ፡ የሚገኘውን ፡ የትዕቢት ፡ መንፈስ ፡ በትክክል ፡ አድርጎ ፡ ይገልጣል ።

«እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የሚመኛት ፡ ሰላም ፡ ዓለም ፡ በአንድ ፡ ዋና ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ እስከምትታዘዝበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ አትገኝም ። ከዚህ ፡ ካሁኑ ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ ሁለት ፡ አዲሶች ፡ ዝንባሌዎች ፡ ይፈጠራሉ ። አንደኛው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ለመሥራት ፡ የሚደረግ ፡ እሽቅድድም ፡ ነው ።

ሁለተኛው ፡ ብርቱ ፡ የሆነ ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ክስ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ያሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ ሰላም ፡ እንዳትገኝ ፡ ተቃራኒዎች ፡ ሆነው ፡ ሲታዩ ፡ የዓለም ፡ ሰላም በምን ፡ አኳኋን ፡ ልትገኝ ፡ ትችላለች ? ውሳኔውን ፡ ለማስፈጸም ፡ የሚችልበት ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ጉልበት ፡ የሌለው ፡ ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ የማይረባ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንግሥታት ፡ ዘንድ ፡ የሚገኙት ፡ የፍርድ ፡ ሚዛንና ፡ የክብር ፡ መጠበ

ቂያ፡ሕግ የተለዋወጡና፡የተለያዩ፡ናቸው ። የጦር፡መሣሪያ፡እንዲቀነስ፡ለማድረግ፡የተሰጠው፡አሳብ፡ፍጻሜ፡ሊያገኝ፡የማይቻል፡ነው ።

ሰላም፡የምትመጣው፡መላው፡ዓለም፡ባንድ፡መንግሥት፡በሚተዳደርበት፡ጊዜ፡ነው ። ዓለም፡አሁን፡የሚመራው፡ይህን ወደ፡መሰለው፡ጊዜ፡ነው ። አሁን፡ያለው፡እያንዳንዱ፡መንግሥት፡የተቋቋመው፡ብዙ፡ጎሣዎች፡ባደረጉት፡የድል፡አድራጊነት፡ሥራ፡ነው ። እሱም፡ጠንካራ፡ኃይል፡ሲያገኝ፡ሰላም፡ይቋቋማል ። ይህም፡በጃፓን፡አገር፡እውነተኛ፡ነገር፡ሆኖ፡ታይቷል ። የፖሊቲካ፡መጨረሻ፡ዓላማው፡የበላይ፡ጠቅላይ፡ገዥ፡በሚሆን፡ባንድ፡ትልቅ፡መንግሥት፡የዓለም፡ድል፡መደረግ፡ነው ። ዓለምን፡ድል፡ለማድረግ፡የሚችል፡ይትኛው፡ሕዝብ፡ይሆን ? ጥብቅ፡በሆነ፡አኳኋን፡ባገር፡ፍቅር፡አንድ፡የሆነ፡የማይደመሰስ፡የድል፡አድራጊነት፡ሞኆት፡ያደረበትና፡ለመጨረሻው፡ዋና፡ዓላማ፡ማነኛውንም፡መሥዋዕትነት፡ለመፈጸም፡የተዘጋጀ፡ሆኖ፡የሚገኘው፡ነው ። በዓለም፡ላይ፡የበላይ፡ኃያል፡መንግሥት፡ሆኖ፡ለመገኘት፡ለሚደረገው፡ትግል፡ጃፓን፡አላፊዎች፡በሆኑት፡የሲሳይ፡ምኞቶች፡ተወስና፡የምትቀር፡አይደለችም ። ጃፓን፡ክብር፡የሞላበት፡ታሪኳንና፡አቀማመጧንም፡በማስተዋል፡የታጨችለትን፡ተግባር፡ለመፈጸም፡መጣጣር፡ይገባታል ። » እንግዲህ፡ወደፊት፡ይህ፡የትዕቢት፡መንፈስ፡ከምን፡እንዳደረሳቸው፡እንመለከተዋለን ። ይህ፡የናፓሊዎንን፡ንግግር፡የመሰለው፡ቃል፡ጃፓን፡የዓለም፡ገዥ፡ለመሆን፡የጋለ፡ምኞት፡አድሮባት፡እንደነበረ፡በትክክል፡ይገልጣል ።

## የ ጃ ፓ ን ፡ ታ ላ ላ ቅ ፡ ሰ ዎ ች ።

ከዚህ፡በላይ፡ጃፓኖች፡ያውሮፓን፡ሥልጣኔ፡ለመቅዳት፡በመ አሰበው፡በተነሡ፡ጊዜ፡የተከተሉትን፡መንገድና፡ተግተው፡በመሥራታቸውም፡የደረሱበትን፡ደረጃ፡ባጭሩ፡ተመልክተነዋል ። አሁን፡ደግሞ፡ጃፓን፡ይህን፡አስደናቂ፡የሆነ፡ትጋት፡አሳይታ፡ይህን፡ሁሉ፡ሥራ፡ለመሥራት፡እንድትችል፡ያደረጓት፡ባገሩዋ፡

ውስጥ ፡ የተፈጠሩ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ በማግኘቷ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከእነዚሁ ፡ ያንዳንዶቹን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ በጭሩ ፡ እንናገራለን ። ወደፊት ፡ እንደምናገኘው ፡ ጃፓን ፡ በጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ወዲያው ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ ከተቀበለችበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ብዙ ፡ ትልልቅ ፡ ሰዎች ፡ የማፍራት ፡ ዕድል ፡ ማግኘቷ ፡ በጣም ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ እንዘነጋው ።

ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ በዓለም ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ስንመለከት ፡ አንድ ፡ አገር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ ከትልቅ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ የሚደርሰው ፡ የመንግሥቱ ፡ መሪ ፡ የሆነው ፡ እንደነ ፡ ትልቁ ፡ ፍሬድሪክ ፡ በሰፊ ፡ መንፈስ ፡ ተነሥቶ ፡ ታላላቅ ፡ ሥራ ፡ ሲፈጽምላት ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ እንደነ ፡ ሪሸሊየና ፡ ለሉዊ ፡ ፲፬ኛ ፡ የፈረንሳይ ፡ ንጉሥ ፡ የሥራ ፡ረዳቶቹ ፡ የሆኑ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሥራ ፡ ችሎታና ፡ የዕውቀት ፡ ስጦታ ፡ ያላቸው ፡ ሚኒስትሮች ፡ ተገኝተው ፡ ብዙ ፡ ጠቃሚ ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩላት ፡ ነው ። ጃፓን ፡ አውሮፓውያን ፡ ወዲያው ፡ አገርዋ ፡ እንደ ፡ ገቡ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የተዘጋጀ ፡ እንደ ፡ ሙትሱሂቶ ፡ ያለ ፡ እስታዋይነቱ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ንጉሥና ፡ ለሱም ፡ የሥራ ፡ ረዳቶች ፡ የሆኑት ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ በማግኘቷ ፡ ከትልቅ ፡ ዕድል ፡ ይቆጠርላታል ። የሁሉንም ፡ ታሪክ ፡ ለመጻፍ ፡ ሰፊ ፡ ሥራ ፡ በመሆኑ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ የስማቸውን ፡ ዝርዝር ፡ ከሰጠን ፡ በኋላ ፡ ሊመሠገኑና ፡ ሊደነቁ ፡ የቻሉበትን ፡ ጠባይ ፡ እየገለጥን ፡ አገራቸውን ፡ ለመጥቀም ፡ የቻሉበትን ፡ አኳኋን ፡ ለማስረዳት ፡ ያህል ፡ ከመካከላቸው ፡ አንዳንዶቹ ፡ የፈጸሙትን ፡ ተግባር ፡ ከሕይወት ፡ ታሪካቸው ፡ ጋር ፡ ጨምረን ፡ ባጭሩ ፡ እናቀርባለን ።

አንዳንድ ፡ አገሮች ፡ በስንት ፡ ዘመን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ሲያገኙ ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ብርቅ ፡ ነገር ፡ ይቆጠርላቸዋል ። ለዚሁም ፡ በቱርክ ፡ አገር ፡ ኬማል ፡ ፓሻ ፡ በህንድ ፡ አገር ፡ ጋንዲ ፡ በሺና ፡ ሰን ፡ ያት ፡ ሴን ፡ ምሳሌ ፡ ሆነው ፡ ሊጠቀሱ ፡ ይቻላል ። ጃፓን ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ወዲያው ፡ ከሥልጣኔ ፡ ጋር ፡ እንደተዋወቀች ፡ ከአሥር ፡ የሚበልጡ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ አፈለቀች ። እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡

ረገድ ፡ ላንዳንዶቹ ፡ ቸር ፤ ላንዳንዶቹ ፡ ግን ፡ ንፉግ ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፡ የማይመረመር ፡ ምሥጢር ፡ ነው ።

ከጃፓን ፣ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ዋና ፣ ዋኖቹ ፣ ኪዶ ፤ አኩቦ ፤ ታከሃሺ ፤ ኢታጋኪ ፤ ሳይጎ ፤ ፉኩዛዋ ፤ ያማጋታ ፤ ኢቶ ፤ ካትሱ ፤ አኩማ ፤ ኖጊ ፤ ቶጎ ፤ ይባላሉ ። ስለ ፣ ቶጎ ፣ የሕይወት ፣ ታሪክ ፣ ባለፉት ፣ ገጾች ፣ ስንናገር ፣ ይህ ፣ ሰው ፣ በእንግሊዝ ፣ አገር ፣ የመርከብ ፣ ትምህርት ፣ ተምሮ ፣ ላገሩ ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ አገልግሎት ፣ መሥራቱንና ፣ የመስከብን ፣ የጦር ፣ መርከብ ፣ በባሕር ፣ ውጊያ ፣ ድል ፣ አድርጎ ፣ ስሙ ፣ በዓለም ፣ ታሪክ ፣ ውስጥ ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ ደረጃ ፣ መያዙን ፣ ተመልክተነዋል ። ወደፊት ፣ ደግሞ ፡ እንደገና ፡ ተመልሰን ፡ ስለ ፡ እሱ ፣ እንናገራለን ። አሁን ፣ ካትሱ ፣ ስለሚባለው ፣ ሰው ፣ ታሪኩን ፣ እናስተውለው ።

ካትሱ ፣ አያቱ ፣ ዐይነ ፣ ስውርና ፣ ለማኝ ፣ ሰው ፣ ነበር ። ጃፓኖች ፣ በሃይማኖት ፣ ጉዳይ ፣ ከፖርቱጌዞች ፣ ጋር ፣ ተጣልተው ፣ የክርስቲያንን ፣ ሃይማኖት ፣ ካገራቸው ፣ ካጠፉና ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ሰዎች ፣ ወደ ፣ አገራቸው ፣ እንዳይገቡ ፣ ያገራቸውም ፣ ሰዎች ፣ ወደ ፣ ውጭ ፣ አገር ፣ እንዳይሄዱ ፣ ከከለከሉ ፣ በኋላ ፣ ሁለት ፣ መቶ ፣ አምሳ ፣ ዓመታት ፣ የሚሆን ፣ ዘመን ፣ ከዓለም ፣ ጋር ፣ ተለያይተው ፣ ሲኖሩ ፣ በመጨረሻ ፣ ጊዜ ፣ አሜሪካኖች ፤ ፈረንሳዮችና ፣ እንግሊዞች ፣ በጦር ፣ ኃይል ፣ ጥሰው ፣ ብጃፓን ፣ አገር ፣ ውስጥ ፣ ከመግባታቸው ፣ በፊት ፣ ቀደም ፤ ብሎ ፡ አንዳንድ ፣ የጃፓን ፣ ወጣቶች ፣ አገራቸው ፣ የተከተለችው ፣ ከዓለም ፣ ጋር ተለያይቶ ፣ የመኖር ፣ ፖሊቲካ ፣ የሚጎዳት ፣ እንጂ ፣ የማይጠቅማት ፣ መሆኑን ፣ ማስተዋል ፣ ጀምረው ፣ ነበር ። ይህም ፣ የሆነበት ፣ ምክንያት ፣ በጃፓን ፣ አገር ፣ የንግድ ፣ ሥራ ፣ እንዲሠሩ ፣ ተፈቅዶላቸው ፣ የነበሩት ፣ የሆላንድ ፣ ተወላጆች ፣ የሆኑት ፣ ሰዎች ፣ የሠለጠኑት ፣ ያውሮፓ ፣ መንግሥታት ፣ ታላላቅ ፣ የሆኑ ፣ መርከቦችና ፣ ኃይለኛ ፣ የሆነ ፣ የጦር ፣ መሣሪያ ፣ እንደሚሠሩ ፣ ይነግሩዋቸው ፣ ስለ ፡ ነበረ ፣ ነው ። ስለዚህ ፣ ነጮች ፣ ይህን ፣ የመሰለ ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ ኃይል ፣ ያገኙበትን ፣ መርከብና ፣ የጦር ፣ መሣሪያ ፣ ለመሥራት ፣ የቻሉት ፣ በምን ፣ ዓይነት ፣ ጥበብ ፣ ይሆን ? ሲሉ ፣ አንዳንድ ፣ የጃፓን ፣ ወጣቶች ፣ መመራመር ፣ ጀመሩ ። ከእነዚሁም ፣ አንዱ ፣ ካትሱ ፣ የሚባለው ፣ ነው ።

ከትሱ ፡ በዝና ፡ ብቻ ፡ ያወቀው ፡ ይህ ፡ ያውሮፓ ፡ ሥልጣኔ ፡ ምሥጢሩ ፡
ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለመረዳት ፡ ስለፈለገ ፡ ቋንቋቸውን ፡ ሊማር ፡ ቁርጥ ፡ አሳብ ፡
አድርጎ ፡ ተነሣ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ ያሉ ፡ ነጮች ፡ ሆላንዶች ፡
ብቻ ፡ ስለሆኑ ፡ የሆላንድን ፡ ቋንቋ ፡ መማር ፡ ግዴታ ፡ ሆነበት ። በጃ
ፓን ፡ አገር ፡ የነበሩትም ፡ የሆላንድ ፡ ተወላጆች ፡ የሆኑት ፡ ነጋዴ
ዎች ፡ ሁሉም ፡ የነበራቸው ፡ ትምህርት ፡ ዝቅተኛ ፡ በመሆኑ ፡ ለሆ
ላንድ ፡ ቋንቋ ፡ መማሪያ ፡ የሚሆነው ፡ አንድ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡
(ዲክሲዮኔር) ማግኘት ፡ አፅበና ፡ ፈልጎ ፡ ሳያገኝ ፡ ቀረ ። ስለዚህ ፡
የመምህሩን ፡ የዲክሲዮኔር ፡ መጽሐፍ ፡ ለምኖ ፡ በእጁ ፡ እየጻፈ ፡ በሁ
ለት ፡ ቅጅ ፡ ገለበጠውና ፡ አንዱን ፡ ለራሱ ፡ አስቀርቶ ፡ ሁለተኛውን ፡
በውድ ፡ ዋጋ ፡ ሸጠ ፡ ባገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ሌላ ፡ መጻሕፍት ፡ ገዛበት ።
እንግዲህ ፡ አንድ ፡ የዲክሲዮኔር ፡ መጽሐፍ ፡ ለመገልበጥ ፡ ምን ፡
ያህል ፡ አድካሚ ፡ ሥራ ፡ መሆኑን ፡ አንባቢ ፡ ሊገነዘበው ፡ ይችላል ።
ነገር ፡ ግን ፡ ከትሱ ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ አልተወሰነም ። ዕውቀትን ፡ ለማ
ግኘት ፡ ሲል ፡ ዕድሜውን ፡ ሙሉ ፡ የመጽሐፍ ፡ አዳኝ ፡ ሆኖ ፡ ኖረ ።


መጀመሪያ ፡ ከገዛቸው ፡ መጻሕፍቶች ፡ አንዱ ፡ ስለጦር ፡ አቅድ ፡
ትምህርት ፡ የሚናገር ፡ መጽሐፍ ፡ ነበር ። ይህንኑ ፡ መጽሐፍ ፡ ለመ
ግዛት ፡ የሚበቃ ፡ ገንዘብ ፡ ሰላላገኘ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ለማንበብ ፡
ብቻ ፡ ሲል ፡ ያለውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ከፍሎ ፡ ላንድ ፡ ዓመት ፡ ተከ
ራየውና ፡ በእጁ ፡ እየጻፈ ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ገለበጠው ። በብዙ ፡
ድካም ፡ ገልብጦ ፡ ከጨረሰው ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ቆይቶ ፡ ባንድ ፡
የመጽሐፍ ፡ መደብር ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ጦር ፡ አቅድ ፡ ጉዳይ ፡ የተጻፈ ፡
ዳግም ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ መጽሐፍ ፡ ድንገት ፡ አገኘ ። ነገር ፡ ግን ፡
ለመግዛት ፡ ቢጠይቅ ፡ ዋጋው ፡ ውድ ፡ ስለሆነበት ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡
ለመግዛት ፡ ሲል ፡ ከወዳጅ ፡ ከዘመድ ፡ ገንዘብ ፡ እየለመነ ፡ ሲያጠራ
ቅም ፡ ቆየና ፡ ለመግዛት ፡ የሚችልበት ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ ሲያገኝ ፡ ወደ ፡
መደብር ፡ ሔደ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ከመደብሩ ፡ ገብቶ ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ የሚፈልገውን ፡
መጽሐፍ ፡ ከጥቂት ፡ ሰዓት ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ገዝቶ ፡
እንደወሰደው ፡ ነገሩት ።

ካትሱ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ተናድዶ ፡ ያ ፡ እንደ ፡ እሱ ፡ ዕውቀት ፡ የተጠማው ፡ ሰው ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ፈልጎ ፡ ስሙን ፡ ካልነገርከኝ ፡ እገድልሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ነጋዴውን ፡ በታጠቀው ፡ ሰይፍ ፡ አስፈራራውና ፡ ስሙን ፡ እንዲገልጥለት ፡ አስገደደው ። ነጋዴውም ፡ ደንግጦ ፡ የሚፈልገውን ፡ መጽሐፍ ፡ የገዛው ፡ ሀብታም ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የጃፓን ፡ መኰንን ፡ ( ሳሙራዪ ) መሆኑን ፡ ስለነገረው ፡ ካትሱ ፡ ቤቱን ፡ እየጠየቀ ፡ ከተማውን ፡ ሙሉ ፡ ከዞረ ፡ በኋላ ፡ ደረሰበት ። ከቤቱም ፡ ሰተት ፡ ብሎ ፡ ገብቶ ፤ « ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ በጣም ፡ እፈልገዋለሁና ፡ ለኔ ፡ ሽጥልኝ ፡ » ብሎ ፡ ጠየቀው ። ያም ፡ መኰንን ፡ « አልሽጥም » ብሎ ፡ መለሰለት ። « እንግዲያው ፡ አከራየኝ ፡ » አለው ። « አላከራይም ፡ » ሲል ፡ መለሰ ። « ሁልቱንም ፡ ልመናዬን ፡ እምቢ ፡ ካልከኝ ፡ እንግዲያው ፡ አውሰኝ ፡ » አለው ። « መጽሐፉ ፡ ሁልጊዜ ፡ ስለሚያስፈልገኝ ፡ ላውስህ ፡ አልችልም ፤ » ሲል ፡ ሦስተኛ ፡ መለሰለት ። ካትሱ ፡ አሁንም ፡ መለሰና ፡ « እንቅልፍ ፡ አትተኛም ፡ ወይ ? » ብሎ ፡ መኰንኑን ፡ ጠየቀው ። መኰንኑም ፡ « ሌሊት ፡ እተኛለሁ ። » ብሎ ፡ መለሰለት ። « እንግዲያውስ ፡ እኔ ፡ እንቅልፍ ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ አላውቅምና ፡ ሁልጊዜ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ከቤትህ ፡ እየመጣሁ ፡ አንተ ፡ ስትተኛ ፡ መጽሐፉን ፡ ወስጄ ፡ ጧት ፡ በማለዳ ፡ እንድመልስልህ ፡ ፍቀድልኝ ፤ ለዚሁም ፡ መያዣ ፡ እንዲሆንህ ፡ ይህን ፡ ገንዘብ ፡ እንካ ። » ብሎ ፡ መጽሐፉን ፡ ለመግዛት ፡ የሰበሰበውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ሰጠው ። ልመና ፡ ታክቶት ፡ ግልፍ ፡ ስላለው ፡ « መጽሐፌ ፡ ከቤቴ ፡ እንዲወጣ ፡ ጨርሼ ፡ አልፈቅድም ። » ሲል ፡ ደረቅ ፡ የሆነ ፡ መልስ ፡ መለሰለት ። ካትሱ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እሱም ፡ በበኩሉ ፡ በጣም ፡ ተቆጣና ፡ ሰይፉን ፡ ጨብጦ ፡ ነቀነቀው ።

የመጽሐፉ ፡ ባለቤት ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ችክ ፡ ባለ ፡ ልመና ፡ ታክ

ጃፓኖች ፡ ከብራቸውን ፡ የሚነካ ፡ ነገር ፡ ሲደርስባቸው ፡ ወይም ፡ መሞት ፡ (ሃራ ጠላታቸውን ፡ መግደል ፡ ወይም ፡ በገዛ ፡ እጃቸው ፡ ኪሪ ፡ ) ማድረግ ፡ ልማዳቸው ፡ ስለሆነ ፡ ሁለቱ ፡ መኰንኖች ፡ ተፋጠጡ ። አሁንም ፡ ደግሞ ፡ ካትሱ ፡ መለሰና ፡ « እንግዲያው ፡ አንተ ፡ ስትተኛ ፡ እዚሁ ፡ አቤትህ ፡ ሆኜ ፡ ሌሊት ፡ መጽሐፉን ፡ እንዳነበው ፡ የመጽሐፉ ፡ ባለቤት ፡ ትፈቅድልኛለህ ፡ ወይ ? » ሲል ፡ ጠየቀው ።



ጃፓንን ፡ ትልቅ ፡ መንግሥት ፡ ካደረጓት ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ የሆነው ፡ ካትሱ ።

አቢሲኒያ ባንክ
Bank of Abyssinia

(THE WESTERN WORLD AND JAPAN ከተባለው ፡ G. B. SANSOM የሚባል ፡ ደረሰ[illegible] ፡ መጽሐፍ ፡ የተቀዳ ፡ ሰዕል ፡)

ይህ ፡ የገጠመው ፡ ሰው ፡ የለመነውን ፡ ነገር ፡ ሳያገኝ ፡ በደኅና ፡ እንደማይለቀው ፡ አውቆ ፡ ፈቀደለት ። ካትሱ ፡ ቤቱ ፡ ሩቅ ፡ ስለሆነ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ እየመጣ ፡ መጽሐፉን ፡ ሲያነብ ፡ እያደረ ፡ ጧት ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ እየተመለሰ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ሲሠራ ፡ ከቆየ ፡ ከኋላ ፡ በ፲ ፡ ጥራዞች ፡ (ቮሉም ፡) ይከፈል ፡ የነበረውን ፡ ያን ፡ የሚፈልገውን ፡ መጽሐፍ ፡ ጨርሶ ፡ አንብቦ ፤ ከዚህም ፡ በላይ ፡ በእጁ ፡ አንድ ፡ ግልባጭ ፡ በሙሉ ፡ ጽፎ ፡ ወሰደ ። ሀብታሙ ፡ መኰንን ፡ ካትሱ ፡ ይህን ፡ አስደናቂ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ በትጋቱ ፡ እጅግ ፡ ተደንቆ ፡ መጽሐፉንም ፡ ጨምረሀ ፡ እንድትወስደው ፡ ፈቅጄልሃለሁ ! የሚገባህ ፡ ሰው ፡ ነህና ፡ ብሎ ፡ መረቀለት ። ያገራችን ፡ ሊቅ ፡ አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ በግጥሞቻቸው ፡ ውሥጥ ፡ «መጽሐፍ ፡ የሚበላ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቀበኛ ፡» ብለው ፡ ያወጡት ፡ ስያሜ ፡ ሊሰጥ ፡ የሚገባው ፡ እንደ ፡ ካትሱ ፡ ለመሰሉት ፡ ሰዎች ፡ ነው ። እነሆ ፡ ጃፓንን ፡ ታላቅ ፡ መንግሥት ፡ ለመሆን ፡ ካበቋት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ የሆነው ፡ ካትሱ ፡ የለማኝ ፡ ልጅ ፡ ነው !

በኋላም ፡ ጃፓን ፡ በንጉሡ ፡ ነገሥቷ ፡ በሙትሱሂቶ ፡ መሪነት ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ መቀበል ፡ በጀመረች ፡ ጊዜ ፡ ካትሱ ፡ በመረመረው ፡ ዕውቀትና ፡ በተከታተለው ፡ ጥበብ ፡ በመርከብና ፡ በመድፈኛ ፡ ጦር ፡ ክፍል ፡ አገሩን ፡ ለማገልገል ፡ ትልቅ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ። ብረት ፡ እያቀለጡ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ለሚሠሩ ፡ ባለኢንዱስትሪ ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ መዝገብ ፡ የሚሆናቸው ፡ የመድፍ ፡ ስዕል ፡ እየሳለ ፡ ስለሰጣቸው ፡ እነሱም ፡ መድፉን ፡ ሠርተው ፡ እየሸጡ ፡ ካገኙት ፡ ገንዘብ ፡ የሚገባውን ፡ ድርሻ ፡ ለካትሱ ፡ ላኩለት ። ካትሱ ፡ ግን ፡ የበለጠና ፡ የተሻለ ፡ ዓይነት ፡ መድፍ ፡ ለመሥሬያ ፡ እርዳታ ፡ ይሁናችሁ ፡ ብሎ ፡ ገንዘቡን ፡ መልሶ ፡ ስለላከላቸው ፡ የፋብሪካው ፡ ባለቤቶች ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ በጣም ፡ አደነቁት ።

ቀጥሎ ፡ የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ ግማሾቹ ፡ ነጮች ፡ አገራችን ፡ እንዲገቡ ፡ አንፈልግም ፡ በማለት ፡ ግማሾቹም ፡ እንዲገቡ ፡ አድርገን ፡ ጥበባቸውን ፡ እንማር ፡ በማለት ፡ ከሁለት ፡ ተከፍለው ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ውጊያና ፡ ብጥብጥ ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፡ ካትሱ ፡ ባስታራቂነት ፡ ከመካከ

ላቸው ፡ ገብቶ ፡ የገላጋይነት ፡ ሥራውን ፡ ባስተዋይነትና ፡ በዘዴ ፡
ከመሥራቱ ፡ የተነሣ ፡ ሁለቱን ፡ ወገኖች ፡ አስማምቶ ፡ አስታረቃቸውና ፡
የሾጉኖች ፡ (የመሳፍንት ፡) ሥልጣን ፡ እንዲሻር ፤ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡
ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ተመልሶ ፡ ተቋቁሞ ፡ የሜይዢ ፡ ዘመን ፡ እንዲ
ከፈት ፡ ለማድረግ ፡ ረዳ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ የመሳፍ
ንትን ፡ ወገኖች ፡ ፖሊቲካ ፡ ደጋፊ ፡ ቢሆን ፡ ላገር ፡ የሚጠቅመ
ውን ፡ ነገር ፡ በማመዛዘን ፡ ዘመን ፡ የሻረውን ፡ ሥልጣን ፡ ይዞ ፡ ለመ
ኖር ፡ ማሰብ ፡ ትልቅ ፡ ሞኝነት ፡ መሆኑን ፡ በብልሃትና ፡ በምክር ፡
ለመሳፍንት ፡ ወገኖች ፡ አስረድቶ ፡ ሥልጣናቸውን ፡ በፈቃዳቸው ፡
እንዲያስረክቡ ፡ አደረጋቸው ። በመጨረሻም ፡ ካትሱ ፡ መጀመሪያ ፡
አሚራል ፤ ቀጥሎ ፡ የመርከብ ፡ ሚኒስትር ፤ ከዚያም ፡ የመሳፍንት ፡
ምክር ፡ ቤት ፡ አባል ፤ በመጨረሻ ፡ ከምት ፡ ተብሎ ፡ ከማዕርግ ፡
ወደ ፡ ማዕርግ ፡ ከሹመት ፡ ወደ ፡ ሹመት ፡ እየተዘዋወረ ፡ ከፍ ፡
ካለ ፡ ትልቅ ፡ ደረጃ ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ በ1900 ዓ. ም. ሞተ ።

ከጃፓን ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ የሆነው ፡ ፉኩዛዋ ፡ የሚ
ባለው ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ተቀብሎ
ተጠምቋል ። ሚትሱኢ ፡ የሚባለው ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ በሰጠው ፡
ገንዘብ ፡ ፉኩዛዋ ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ ዑኒቬርስቲን ፡ አቋቋመ ።
ጃፓን ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ ጥበብና ፡ ዕውቀት ፡ አግኝታ ፡ ትልቅ ፡
መንግሥት ፡ እንድትሆን ፡ ከደከሙላት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ፉኩዛዋ ፡
ነው ። በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ እኛ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አባቶቻችን ፡
የጉግስ ፡ ጨዋታ ፡ ይወዱ ፡ እንደነበረ ፡ ሁሉ ፡ ጃፓኖችም ፡ እንደ
ዚሁ ፡ የሰይፍ ፡ ውጊያ ፡ የሚባል ፡ ጨዋታ ፡ ነበራቸው ። ፉኩዛዋ ፡
ይህን ፡ የአሮጌውን ፡ ዘመን ፡ ጨዋታ ፡ ትተው ፡ ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ የፈረ
ንጆችን ፡ የስፖር ፡ ጨዋታዎች ፡ እንዲለምዱ ፡ አደረገ ።

እንደዚሁም ፡ ትልቁን ፡ የጃፓን ፡ ጋዜጣ ፡ አቋቁሞ ፡ ሥራውን ፡
አስፋፋው ። በያይነቱ ፡ ኢንዱስትሪዎችና ፡ በወሀ ፡ ኃይል ፡ የሚ
ሠሩ ፡ የኤሌትሪክ ፡ መኪናዎች ፡ በየቦታው ፡ እንዲቋቋሙ ፡ ለማድ
ረግ ፡ ከደከሙት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ፉኩዛዋ ፡ ነው ። በፓርለማ ፡
ውስጥ ፡ የሕዝብን ፡ መንፈስ ፡ ለመማረክና ፡ ለማሳመን ፡ ሰሚዎቹም ፡
መንግሥቱ ፡ የሚከተለውን ፡ ፖሊቲካ ፡ እንዲረዱት ፡ ለማድረግ ፡

የሚቻልበትን ፡ ንግግር ፡ የማወቅን ፡ ዘዴ ፡ የጃፓን ፡ ፓርለማ ፡ አባሎች ፡ እንዲማሩትና ፡ እንዲሠለጥኑበት ፡ ያደረገ ፡ ፉኩዛዋ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ገንዘብ ፡ ማግኘትን ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ነውር ፡ ይቈጥረው ፡ ነበር ። ይልቁንም ፡ የመሳፍንትና ፡ የመኳንንት ፡ ወገኖች ፡ የሆኑት ፡ ሁልጊዜ ፡ ንግድን ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ውርደት ፡ ቈጥረውታል ። ካውሮፓ ፡ ሥልጣኔ ፡ ጋራ ፡ ተገናኝተው ፡ መኖር ፡ በጀመሩ ፡ ጊዜ ፡ የተማሩትና ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ የንግድን ፡ ሥራ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ይዘው ፡ ቢኖሩ ፡ ያገሪቱ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሕይወት ፡ በባዕድ ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ የተጨበጠ ፡ ሆኖ ፡ ይገኝና ፡ ለመንግሥቱ ፡ ፖሊቲካና ፡ ለሕዝቡም ፡ አስተዳደር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ እንደሚያመጣ ፤ ላገሩ ፡ ነፃነትም ፡ እንደሚያሰጋ ፡ ስለተረዱት ፡ ያገራቸው ፡ ሰዎች ፡ የንግድን ፤ የኢንዱስትሪንና ፡ የባንክን ፡ ሥራዎች ፡ እንዲማሩ ፡ ለማድረግ ፡ ምክር ፡ በመስጠት ፡ ደከሙበት ። ከእነሱም ፡ አንዱ ፡ ፉኩዛዋ ስለሆነ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ለሕዝብ ፡ ባደረገው ፡ ንግግር ፡ ውስጥ ፡ ተናገረ ፤ "ያገሬ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፤ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ስትሉ ፡ በላችሁ ፡ ጉልበት ፡ ሁሉ ፡ ተጣጣሩበት ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ የመንግሥቱ ፡ ኃይል ፡ እየበረታ ፡ የሚሄድበትን ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ትችላላችሁ ። »

ፉኩዛዋ ፡ ይህንን ፡ ሲናገር ፡ ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ በአእምሮዋቸውና ፡ በእጃቸው ፡ እየሠሩ ፡ ንጹህ ፡ የሆነ ፡ የድካማቸውን ፡ ዋጋ ፡ እንዲያገኙ ፡ እንጂ ፡ በማይገባ ፡ መንገድ ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ እንዲጣጣሩ ፡ አለመሆኑን ፡ ማሰብ ፡ ያስፈልጋል ። የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ባገራችን ፡ እየገቡ ፡ ሠርተው ፡ ሲከብሩ ፡ እናንተ ፡ ሥራን ፡ ባለማወቅ ፡ ወይም ፡ በስንፍና ፡ ደሆች ፡ አትሁኑ ፡ ለማለት ፡ ነው ። በኤኮኖሚም ፡ በኩል ፡ የሕዝቡ ፡ ድህነት ፡ ለመንግሥቱ ፡ የሚጎዳ ፡ የሕዝቡ ፡ ብልጽግና ፡ ደግሞ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ኃይል ፡ እንደሚሰጠው ፡ ለመግለጥ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ነው ።

አሁን ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ አሚራል ፡ ቶጎ ፡ ጥቂት ፡ እንናገራለን ። ቶጎ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የመርከብ ፡ ትምህርት ፡ የተማረበት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ (THAMES NAUTICALCOLLEGE) ይባላል ።

ይህ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ እንደሠራ ፡ በመስኮብና ፡ በጃፓን ፡ መካከል ፡ ስለሆነው ፡ ጦርነት ፡ ጉዳይ ፡ በተናገርንበት ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ገልጠነዋል ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ በሕይወቱ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ያገኘውን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የክብር ፡ ደረጃ ፡ ለማሳወቅ ፡ ያህል ፡ አንዳንድ ፡ መግለጫ ፡ እንሰጣለን ፡

ቶጎ ፡ የመስኮብን ፡ የጦር ፡ መርከብ ፡ ድል ፡ ባደረገበት ፡ ውጊያ ፡ ላይ ፡ ያሳየው ፡ ሰፊ ፡ አስተዋይነትና ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ዕውቀት ፡ ያደረበት ፡ የጦር ፡ አቅድ ፡ በማናኛውም ፡ የመርከብ ፡ ውጊያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ታይቶ ፡ ያልታወቀ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ በመርከብ ፡ ጦርነት ፡ ወደ ላይ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ መስክረዋል ። ቶጎ ፡ ወደ ዚህ ፡ ጦርነት ፡ ታዞ ፡ ለውጊያ ፡ ሲሔድ ፡ ከመንግሥቱ ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ የጦር ፡ መርከቦቹን ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ አሰልፎ ፡ ትልቅ ፡ ውጊያ ፡ ከማድረግ ፡ እንዲጠነቀቅና ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ መርከቦቹን ፡ እየበታተነ ፡ የጠላትን ፡ ኃይል ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እያለ ፡ እንዲያደክም ፡ ነበር ። እሱ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ የማይበጅ ፡ ሆኖ ፡ ስለታየው ፡ ትልቅ ፡ ውጊያ ፡ አድርጎ ፡ ድል ፡ አድራጊነትን ፡ ማግኘት ፡ አለዚያም ፡ መጥፋት ፡ ከእነዚህ ፡ ከሁለቱ ፡ ዕድሎች ፡ አንዱን ፡ ማግኘት ፡ የተሻለ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ስላሰበ ፡ በራሱ ፡ አሳብ ፡ ብቻ ፡ ተመርቶ ፡ ሊዋጋ ፡ ቁርጥ ፡ አሳብ ፡ አደረገና ፡ በሱ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩትን ፡ የመርከብ ፡ ሹማምንቶች ፡ ሰብስቦ ፡ ከውጊያው ፡ በፊት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ንግግር ፡ አደረገላቸው ።

«ያለኝን ፡ ኃይል ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቤ ፡ ልዋጋ ፡ ቆርጫለሁ ። የኔን ፡ አሳብ ፡ የምትቀበሉ ፡ እንደሆናችሁ ፡ በኋላ ፡ አሳቤ ፡ ስሕተት ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፡ ሁላችንም ፡ ሃራኪሪ ፡ እንድናደርግ ፡ እንማማላለን ። አሳቤ ፡ ትክክል ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቶ ፡ የመስኮብን ፡ የመርከብ ፡ ሠራዊት ፡ ድል ፡ የመታነው ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ሕይወታችንን ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ሰጥተን ፡ እንደሚወዱ ፡ አድርገው ፡ ቢፈቅዱ ፡ ይቀጡናል ፤ ወይም ፡ ይሸልሙናል ። »



ከጃፓን ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡
አሚራል ፡ ቶጎ ።

ሊፕተን ፡ ክሎግ ፡ ከጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ ውሥጥ ፡ የተቀዳ ፡ ስዕል ።)

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቶጎ ፡ ውጊያ ፡ ገጥሞ ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ ስለ ሆነ ፡ ባገሩ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የመጨረሻ ፡ ክብር ፡ ተደረገለት ። ቶጎ ፡ በ 1911 ዓ. ም. ዓለምን ፡ እየዞረ ፡ ጎበኘ ። እንግሊዝ ፡ አገር ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ በታላቅ ፡ ደስታና ፡ ክብር ፡ በሞላበት ፡ አቀባበል ፡ ተቀበሉት ። የእንግሊዝም ፡ ጋዜጠኞች ፡ በኛ ፡ አገር ፡ የመርከብ ፡ ትምህርት ፡ የተማረው ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ በመሥራቱ ፡ እኛም ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ የክ ብር ፡ ተከፋይነት ፡ ስሜት ፡ ይሰማናል ፡ ሲሉ ፡ አርእስቶቻቸውን ፡ በታላላቅ ፡ ፊደሎች ፡ ጻፉ ። እሱም ፡ የተማረበትን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሂዶ ፡ ጎበኝና ፡ ንግግር ፡ (ዲስኩር ፡ ) አደረገ ።

ከዚያም ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ አገር ፡ ሄደ ። በአሜሪካንም ፡ አገር ፡ እንደዚሁ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ የታየበት ፡ አቀባበል ፡ ተደረገለት ። በሴና ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ እንዲገባና ፡ የምክር ፡ ቤቱ ፡ አባሎች ፡ በክብር ፡ እንዲቀበሉት ፡ ተፈቀደለት ። የኰንግሬስ ፡ ምክር ፡ ቤትም ፡ ስለ ፡ ቶጎ ፡ እንግድነት ፡ ወጪ ፡ የሚሆነውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ያሜ ሪካ ፡ መንግሥት ፡ ፈቅዷል ፡ ሲል ፡ ጉዳዩ ፡ በጉባኤው ፡ ላይ ፡ ቀርቦ ፡ እንዲወሰን ፡ አደረገ ። ይህም ፡ አደራረግ ፡ እንደ ፡ ዤኔራል ፡ ላፋዬት ፡ ላሉ ፡ ላንዳንድ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ለሆኑ ፡ እንግዶች ፡ ብቻ ፡ የተደረገ ፡ ነው ። በመጨረሻም ፡ ቶጎ ፡ ወደ ፡ ቴዎዶር ፡ ሩዝ ቬልት ፡ ዘንድ ፡ ሂዶ ፤ በመኖሪያ ፡ ቤታቸው ፡ ተገናኛቸው ። ቴዎ ዶር ፡ ሩዝቬልትም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሳጋሞር ፡ በሚባለው ፡ አገር ፡ በሚገኘው ፡ በግል ፡ መኖሪያ ፡ ቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ ይኖሩ ፡ ነበርና ፡ ቶጎን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ “ሳጋሞር ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አሚራል ፡ ቶጎን ፡ የሚያህል ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ተቀብላ ፡ አታውቅም ፤ ወደፊትም ፡ አት ቀበልም ። » የሚል ፡ ቃል ፡ ተናገረው ፡ ቶጎን ፡ ተቀበሉት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቶጎ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ተመልሶ ፡ የድህነት ፡ እንጂ ፡ የጌትነት ፡ መልክ ፡ በማይታይበት ፡ባንዲት ፡ አነስተኛ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይኖር ፡ ጀመር ።

ባንድ ፡ በኩል ፡ ኩላሊቱ ፡ ጠጠር ፡ ሠርቶ ፤ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የጉሮሮ ፡ ነቀርሳ ፡ ይዞት ፡ ጤንነቱ ፡ ተበላሽቶ ፡ ስለነበረ ፡ ከዚህ በኋላ ፡ ቶጎ ፡ ሕመምተኛ ፡ ስለሆነ ፡ የእርጅና ፡ ዓመታቱን ፡

በሽታውን ፡ በማስታመም ፡ ያሳልፍ ፡ ጀመር ። ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ደግሞ ፡ ቶጎ ፡ ባገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የተወደደና ፡ የተከበረ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀው ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ በተደረገለት ፡ የክብር ፡ ፍታትና ፡ አቀባበር ፡ ነው ፡ ይባላል ። ባገሩ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ቶጎ ፡ በሞተበት ፡ ቀን ፡ በማነኛውም ፡ ባህር ፡ ላይ ፡ የሚገኙት ፡ የጃፓን ፤ ያሜሪካ ፤ የእንግሊዝ ፡ የፈረንሣይና ፡ የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ መርከቦች ፡ ስለ ፡ ቶጎ ፡ የኀዘን ፡ ክብር ፡ ሁሉም ፡ ሀያ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መድፎቻቸውን ፡ ተኰሱ ። የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ኀዘኑ ፡ የአበባ ፡ ዘውድ ፡ ላኩ ።

አሁን ፡ ደግሞ ፡ ታካሃሺ ፡ የሚባለውን ፡ ሰው ፡ ታሪክ ፡ በጥቂቱ ፡ እንመልከተው ። ታካሃሺ ፡ ችሎታውና ፡ ዝንባሌው ፡ ወደ ፡ ባንክ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ሳበው ፡ በባንክ ፡ ውስጥ ፡ በተራ ፡ ሠራተኛነት ፡ ተቀጥሮ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ካገለገለ ፡ በኋላ ፡ በችሎታው ፡ ተመርጦ ፡ የጃፓን ፡ ባንክ ፡ ዲሬክተር ፡ ሆነ ። ቀጥሎ ፡ ወደ ፡ ገንዘብ ፡ ምንዛሬ ፡ ክፍል ፡ ተዛውሮ ፡ ምክትል ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ሆነ ። በመስኮብና ፡ በጃፓን ፡ መካከል ፡ ጦርነት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ታካሃሺ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ ካሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የገንዘብ ፡ ብድር ፡ ጠይቆ ፡ በዚሁ ፡ በተላከበት ፡ ጉዳይ ፡ ቀንቶት ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ተመለሰ ። ጃፓንም ፡ ይህን ፡ የገንዘብ ፡ ብድር ፡ በማግኘቷ ፡ መስኮብን ፡ ድል ፡ ለማድረግ ፡ ቻለች ። ታካሃሺ ፡ መጀመሪያ ፡ የጃፓን ፡ የባንክ አገረ ፡ ገዥ ፡ ቀጥሎ ፡ ባሮን ፤ በመጨረሻም ፡ ቪኮምት ፡ ተብሎ ፡ እሱም ፡ ከሹመት ፡ ወደ ፡ ሹመት ፡ ከማዕርግ ፡ ወደ ፡ ማዕርግ ፡ ተዛውሯል ። ጃፓንን ፡ ትልቅ ፡ መንግሥት ፡ ካደረጓት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ታካሃሺ ፡ ነው ።

በሕክምና ፡ ዕውቀት ፡ ጃፓን ፡ በጣም ፡ የታወቁና ፡ ዝናቸው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የገነነ ፡ ብዙ ፡ ትልልቅ ፡ ሰዎች ፡ አፍርታለች ። ከእነዚሁም ፡ አንዱ ፡ ታካሚን ፡ የሚባለው ፡ ለሱካር ፡ በሽታ ፡ መከላከያ ፡ የሚሆነውን ፡ ኢንሱሊን ፡ የሚባለውን ፡ መድኀኒት ፡ ያገኘ እሱ ፡ ነው ፡ ይባላል ።

በሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ከቀሩት ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ አንዷ ፡ የነበረችው ፡ ጃፓን ፡ ባዲሱ ፡ የዕውቀት ፡ መንፈስ ፡ እየተመራች ፡

እነበረችበት ፡ ከታናናሾች ፡ መንግሥታት ፡ ደረጃ ፡ ተነሥታ ፡ በጥ ቂት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ተወርውራ ፡ በቅጽበት ፡ ታላላቅ ፡ መንግ ሥታት ፡ ከያዙት ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ለመድረስ ፡ የበቃችው ፡ ባገርዋ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ መንፈሳቸው ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያሉትን ፡ ታላ ላቅ ፡ ዓላማዎች ፡ ለማስተዋልና ፡ ለመከታተል ፡ የቻለ ፡ አስተዋይነት ፡ ያደረባቸው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በማግኘቷ ፡ ነው ። ኢቶ ፡ የሚባለው ፡ ሰው ፡ የፕሩስን ፡ (የጀርመንን ፡) ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መዝገብ ፡ አድ ርጎ ፡ ለጃፓን ፡ የሚስማማትን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አዘጋጀ ። ያማ ጋታ ፡ የሚባለው ፡ የጃፓንን ፡ የጦር ሠራዊት ፡ ባዲሱ ፡ ዘመን ፡ አስተዳደር ፡ ላይ ፡ እንዲቋቋም ፡ አደረገ ። ኢኑዬ የሚባለው ፡ የጃ ፓንን ፡ የገንዘብ ፡ አስተዳደርና ፡ ሥራት ፡ በዘመናዊው ፡ ሥልጣኔ ፡ ሕግ ፡ እንዲመሩ ፡ አደረገ ። ሌሎችም ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ታላላቅ ፡ ሥራዎች ፡ የፈጸሙ ፡ ባስተዋይነታቸውና ፡ በብልህነታቸው ፡ መላው ፡ ዓለም ፡ ያደነቃቸው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

ስለ ፡ ጃፓን ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ታሪክ ፡ "LE PERIL JAPONAIS" በሚል ፡ አርእስት ፡ ከ "UPTON CLOSE" የተጻፈውን ፡ መጽሐፍ ፡ መመልከት ፡ ነው ።

ጃፓኖች ፡ ታላላቆችን ፡ መርከቦች ፡ ባዲሱ ፡ ሥልጣኔ ፡ ጥበብ ፡ መሥራትን ፡ የተማሩት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ዘዴ ፡ ተከትለው ፡ ነው ። ዋጋቸውን ፡ ከፍለው ፡ በኤኮስ ፡ አገር ፡ አዲሶች ፡ መርከቦች ፡ እንዲሠሩላቸው ፡ አዘዙና ፡ በኮንትራቱ ፡ ውስጥ ፡ እነዚሁ ፡ መርከ ቦች ፡ ሲሠሩ ፡ የጃፓን ፡ መሐንዲሶች ፡ ሥራውን ፡ እየተጠባበቁ ፡ ይከታተላሉ ፡ የሚል ፡ አንቀጽ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገባ ፡ አደረጉ ።

ከሰማኒያ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ በሥልጣኔ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ያህል ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀረች ፡ ሆና ፡ ትናቅ ፡ የነበረችው ፡ የጃፓን ፡ አገር ፡ ዛሬ ፡ በሥልጣኔ ፡ የደረሰችበትን ፡ ቦታ ፡ አንባቢ ፡ ሊገምተው ፡ ይችል ዘንድ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ መግለጫ ፡ እንሰጠዋለን ።

ከሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በፊት ፡ በነበረው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕውቀቶችና ፡ ጥበቦች ፡ በየዓመቱ ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ በጠቅላላው ፡ ሠላሳ ፡ ሺ ፡ መጻሕፍት ፡ ይታተሙ ፡ እንደ ነበረ ፡ ማሳሰብ ፡ ይበቃ ፡ ይመስለናል ። ኖማ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡

ጋዜጠኛ ፡ የሚያሳትመው ፡ ባለ ፡ ሥዕል ፡ የሆነ ፡ ( ማጋዚን ፡ ) ጋዜጣ ፡
በሁለት ፡ ሚሊዮን ፡ ቅጅ ፡ እየሆነ ፡ ይወጣ ፡ ነበር ። የጃፓን ፡
ባለጸጎች ፡ እንደነ ፡ ሚትሱኢ ፡ ያሉት ፡ ገንዘባቸውን ፡ እንዴት ፡
አድርገው ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ እንደሚያውሉት ፡ ለማወቅ ፡ ብን
ፈልግ ፡ ታላላቆቹን ፡ ዩኒቬርሲቲዎች ፡ ያቋቋሟቸው ፡ እነሱ ፡ መሆ
ናቸውን ፡ ማሰብ ፡ ይገባናል ።

## ንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ ሕዝቡ ።

ጃፓኖች ፡ በሃይማኖታቸው ፡ ሺንቶ ፡ በሚባለው ፡ እንደሚያስ
ተምሩዋቸው ፡ የቀሩት ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ሥነ ፡ ፍጥረታ
ቸው ፡ ከዝቅተኛ ፡ ምንጭ ፡ የመጣ ፡ ሲሆን ፡ እነሱ ፡ ጃፓኖች ፡
ብቻ ፡ ከሰማይ ፡ አማልክት ፡ የተወለድን ፡ ነን ፡ ስለሚሉ ፡ ዘራቸ
ውን ፡ የተቀደሰ ፡ አድርገው ፡ ይመለከቱታል ። አንድ ፡ ቀን ፡ የዓ
ለም ፡ ገዥዎች ፡ እንሆናለን ፡ የማለት ፡ አሳብ ፡ በመንፈሳቸው
ውስጥ ፡ የተፀነሰበት ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ በዚሁ ፡ ማለት ፡ ራሳቸ
ውን ፡ ከቀሩት ፡ ሁሉ ፡ ሰዎች ፡ በላይ ፡ አድርገው ፡ በመቍጠራቸው ፡
ነው ። ንጉሠ ፡ ነገሥታቸውንም ፡ "የእግዜር ፡ ልጅ ፡ " ነው ፡ ብለው ፡
እየጠሩት ፡ የአማልክት ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፤ የሕዝቡ ፡ አባት ፤ አድርገው ፡ ስለሚ
መለኩት ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ክብር ፡ ይሰጡታል ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡
ስላገራቸውና ፡ ስለ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ ያላቸውን ፡ ፍቅር ፡
እንደ ፡ ብረት ፡ የጠነከረ ፡ አድርጎት ፡ ይኖራል ። ራሳቸውን ፡ የአ
ማልክት ፤ ተወላጆች ፡ አድርገው ፡ ስለሚቆጥሩት ፡ በጠባያቸውና ፡
በባርያዊው ፡ ከሰው ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ የበለጡና ፡ የተለዩ ፡ ሆነው ፡
ለመገኘት ፡ የማይዛባ ፡ ምኞት ፡ በልባቸው ፡ አሳድሮባቸዋል ። አንድ ፡
የጃፓን ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ አሜ
ሪካ ፡ ሂዶ ፡ በታላላቆቹ ፡ ዩኒቬርሲቲዎች ፡ ገብቶ ፡ ከተማረ ፡ ከኋላ ፡
የተማረው ፡ ማንኛውም ፡ ትምህርት ፡ ታሪክም ፡ ሆነ ፡ ፍልስፍና ፡
ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆኖ ፡ ቢጠመቅም ፡ እንኳ ፡ እኛ ፡
ጃፓኖች ፡ በሥነ ፡ ፍጥረታችን ፡ ከሌሎች ፡ ሁሉ ፡ ሕዝቦች ፡ የላ
ቅን ፡ የአማልክት ፡ ልጆች ፡ ነን ፡ እያሉ ፡ ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ በልቡ ፡

ውስጥ ፡ ያሳደሩበትን ፡ እምነት ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ከመንፈሱ ፡ ውስጥ ፡ ሊፍቀው ፡ አይችልም ።

ለምሳሌ የሳሙራዪ ፡ (የመኳንንት ፡ ) ልጅ ፡ የሆነ ፡ በወታደርነት ሲዋጋ በጠላት ፡ እጅ ፡ ሊማረክ ፡ አይገባውም ፤ ይህንን ፡ አድርጎ ቢገኝ ፡ የጃፓንን ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ክብር ፡ ያዋርዳል ፡ እያሉ ፡ ስለ ፡ ሚያስተምሩዋቸው ፡ ጃፓኖች ፡ ይህንን ፡ የትምክህት ፡ ስሜታቸውን ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ጠብቀውት ፡ ይኖራሉ ። አሁን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በሻንጋይ ፡ አገር ፡ ጦርነት ፡ ሆኖ ፡ ጃፓኖች ፡ ከቺናውያን ፡ ጋር ፡ ሲዋጉ ፡ አንድ ፡ የጃፓን ፡ ወታደር ፡ ብቻ ፡ ቆስሎ ፡ ስለነበረ ፡ ተማረከ ፡ ይባላል ። በኋላም ፡ ታክሞ ፡ ሲድን ፡ እንደገና ፡ ወደ ፤ ወገኖቹ ፡ ወደ ፡ ጀፓኖች ፡ የጦር ፡ ሠፈር ፡ ተመልሶ ፡ በገዛ ሽጉጡ ፡ ራሱን ፡ ገደለ ።

በጃፓኖች ፡ ጠባይ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ከፍተኛ ፡ ባህርይ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠርላቸው ፡ ይህ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ ያላቸው ፡ ታማኝነት ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ ከመቀበላቸው ፡ በፊት ፡ ሆነም ፡ ወይም ፡ አሁን ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ ሳይለወጥና ፡ ሳይቀዘቅዝ ፡ ባዲሱ ፡ ሥልጣኔ ፡ የተገኘውም ፡ መጥፎ ፡ መንፈስ ፡ ሳያበላሸው ፡ ሁልጊዜ ፡ የጋለ ፡ ሆኖ ፡ መኖሩ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ላንድነታቸውና ፡ ላገራቸው ፡ ፍቅር ፡ ጥብቅ ፡ የሆነ ፡ ማሰሪያ ፡ ሆኖ ፡ አገልግሏቸዋል ።

ለምሳሌ ፡ አንቷን ፡ ዚሽካ ፡ የሚባል ፡ የጃፓንን ፡ ታሪክ ፡ የጻፈ ፡ አንድ ፡ ይራሲ ፡ አሁን ፡ ብቅርብ ፡ ዘመን ፡ በ1932 ዓ. ም. ቶኪዮ ፡ ከተማ ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ ወጣት ፡ የጃፓን ፡ አኤሮፕላን ፡ ነጂ ፡ አኤሮፕላን ፡ ሲነዳ ፡ ሰማዩን ፡ ደመና ፡ ሸፍኖት ፡ ስለነበረ ፡ ባለማወቅ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ አንዣብቦ ፡ አለፈ ። መሬት ፡ ከረፈ ፡ በኋላ ፡ ይህንኑ ፡ አውቆ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ክብር ፡ የመድፈር ፡ ሥራ ፡ አድርጎ ፡ ስለቆጠረው ፡ ሃራኪሪ ፡ አድርጎ ፡ ሞተ ።

በጃፓኖች ፡ ልማድ ፡ ንጉሣቸውን ፡ ከከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ መመልከት ፡ የማይገባ ፡ በመሆኑ ፡ ለምሳሌ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ሲያልፍ ፡ በፎቅ ፡ ላይ ፡ የሚ

ኖሩ ፡ ሰዎች ፡ በሮቻቸውንና ፡ መስኮቶቻቸውን ፡ ዘግተው ፡ በቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣሉ ፡ እንጂ ፡ ከሰገነቱ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ንጉሡን ፡ ቍልቍል ፡ አይመለከቱትም ።

ከማንዳ ፡ ኩጋ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ የጃፓን ፡ የጦር ፡ ሹም ፡ ከሺናውያን ፡ ጋር ፡ በጦርነት ፡ ውስጥ ፡ ሲዋጋ ፡ በብርቱ ፡ አኳኋን ፡ ቆስሎ ፡ አእምሮውን ፡ በማያውቅበት ፡ ጊዜ ፡ ሺናውያን ፡ ማረኩት ። በኋላም ፡ ጦርነቱ ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ ነፃ ፡ ለቀቁት ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ የጃፓን ፡ የጦር ፡ ሹም ፡ የሆነ ፡ ሕሊናውን ፡ በሳተበት ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ተማርኮ ፡ ሊገኝ ፡ አይገባውም ፡ በማለት ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ሞተ ።

አሁን ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ ያለው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከብዙ ፡ ሺ ፡ ዓመታት ፡ ጀምሮ ፡ ባለማቋረጥ ፡ ከንድ ፡ ንጉሣዊ ፡ ትውልድ ፡ ተያይዞ ፡ የመጣ ፡ መቶ ፡ ሃያ ፡ አራተኛው ፡ ነው ። የጃፓን ፡ ነገሥታት ፡ የሚደረግላቸው ፡ ክብር ፡ ከማልከቶቻቸው ፡ እኩል ፡ ነው ።

የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ትጋት ፡ የሞላበት ፡ መጣጣር ፡ አሳይቶ ፡ በጥበብና ፡ በዕውቀት ፡ እየተራመደ ፡ ባውሮፓ ፡ ሥልጣኔ ፡ ከታላላቆቹ ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ የአንድነቱ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ያለውን ፡ የአክብሮትና ፡ የፍቅር ፡ መንፈስ ፡ ማነኛውም ፡ የባዕድ ፡ ስብከት ፡ ወልቡ ፡ ውስጥ ፡ ሊያቀዘቅዘው ፡ አልቻለም ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ መላው ፡ ዓለም ፡ የተደነቀበትን ፡ የጃፓኖችን ፡ መልክም ፡ ጠባይ ፡ ለመግለጥ ፡ ያህል ፡ አንዳንድ ፡ ምሳሌ ፡ እንጠቅሳለን ።

በጃፓን አገር ፡ የሚኖር ፡ ማነኛውም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥታቸውን ፡ ክብር ፡ ጥቂት ፡ የሚነካ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ በተገኘ ፡ ቍጥር ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ደርሶበታል ።

በጃፓን ፡ አገር ፡ የሚታተሙ ፡ አንዳንድ ፡ የእንግሊዝ ፡ ጋዜጣዎች ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ስም ፡ ሲጠሩ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በመዘንጋት ፡ በትልልቅ ፡ ፊደሎች ፡ ሳይጽፉት ፡ በቀሩ ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቅጣት ፡ ወድቆባቸዋል ። በኮቤ ፡ ከተማ ፡ በሚታተም ፡ ባንድ ፡ የእንግሊዝ ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ ጋዜጠኛው ፡ አንድ ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ከዚህ ፡ ከሁኑ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት በፊት ፡ የነበረው ፡

ትልቁ ፡ ንጉሥ ፡ ሙትሱሂቶ ፡ የሞተበትን ፡ በሽታ ፡ ጠቅሶ ፡
በጋዜጣው ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ጻፈ ፡ ተይዞ ፡ ይህን ፡ የድፍረት ፡ ሥራ ፡
በመሥራቱ ፡ ተጠየቀበት ። እሱም ፡ አጥፍቻለሁ ፡ ብሎ ፡ ይቅርታ ፡
ለመነ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ወራት ፡ በወህኒ ፡ ታሥሮ ፡
ቅጣቱን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ የጃፓኖችን ፡ ትልቅነት ፡
ለዓለም ፡ ለማሳወቅ ፡ ተገቶ ፡ የፕሮፓጋንድ ፡ ሥራ ፡ ሲሠራላቸው ፡
ኖረ ። በዚሁ ፡ አኳኋን ፡ በፔኪን ፡ ከተማ ፡ የሚታተም ፡ አንድ ፡
የሺና ፡ ጋዜጣ ፡ የዚህኑ ፡ የጃፓን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በሽታ ፡ ምን ፡
እንደነበረ ፡ ለመግለጥ ፡ አርእስቶች ፡ ለመጻፍ ፡ ስለ ፡ ጀመረ ፡ ማነ
ኛውንም ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡
ጥሰን ፡ የጋዜጣውን ፡ ማተሚያ ፡ ቤትና የጽሕፈት ፡ ቤቱንም ፡ በዲ
ናሚት ፡ እናፈርሰዋለን ፡ ብለው ፡ ጃፓኖች ፡ ስላስታወቁት ፡ አርእስ
ቱን ፡ ማቋረጥ ፡ ግዴታ ፡ ሆነበት ።

ይህንንም ፡ ማድረጋቸው ፡ በሕጋቸውና ፡ በልማዳቸው ፡ ንጉሣ
ቸው ፡ የተቀደሰ ፡ ፍጡር ፡ ሆኖ ፡ ስለሚታይ ፡ ማነኛውም ፡ ሰው ፡
ቢሆን ፡ ፍጹም ፡ አክብሮት ፡ እንዲያደርግለት ፡ የታዘዘ ፡ በመሆኑ ፡
ነው ። ምንም ፡ እንኳ ሌሎቹ ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ይህን ፡ የመሰ
ለው ፡ ነገር ፡ በልማዳችን ፡ ውስጥ ፡ የሌለ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ጃፓኖች ፡ በሚቻላ
ቸው ፡ መጠን ፡ ንጉሣቸውን ፡ እንዲያከብሩላቸው ፡ ያስገድዷቸዋል ።
በሃዋዩ ፡ ደሴቶች ፡ በሆኖሉሉ ፡ ከተማ ፡ የሚታተም ፡ አንድ ፡ የአሜ
ሪካ ፡ ጋዜጣ ፡ ጃፓኖች ፡ ለንጉሣቸው ፡ የሚያደርጉለት ፡ ክብር ፡ ለኛ ፡
ላሜሪካኖች ፡ ግራ ፡ ነገር ፡ ሆኖብናል ፡ ብሎ ፡ ቢጽፍ ፡ በዚሁ ፡ ከተማ ፡
የሚኖሩ ፡ ጃፓኖች ፡ አድማ ፡ አድርገውበት ፡ ብዙ ፡ አሳር ፡ ደርሶ
በታል ።

በጃፓን ፡ አገር ፡ የሚኖሩ ፡ ነጮች ፡ ድንገት ፡ ንጉሡ ፡ በመን
ገድ ፡ በአቶሞቢል ፡ ሆኖ ፡ ሲያልፍ ፡ ባዩ ፡ ቁጥር ፡ በዝናብ ፡ ላይ ፡
ጃንጥላቸውን ፡ እያጠፉ ፡ ከጃፓኖች ፡ ጋራ ፡ አብረው ፡ እጅ ፡ ይነሣሉ ።

የጃፓን ፡ ነገሥታት ፡ እናት ፡ ነች ፡ ለምትባለው ፡ ለፀሐይ ፡ ሴት ፡
አምላክ ፡ አማቴራሱ ፡ ለምትባለው ፡ ከተሠራላት ፡ የመቅደስ ፡ ቦታ ፡
ሞሬ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ነጭ ፡ ከዘራውን ፡ ይዞ ፡ ስለገባ ፡ ጃፓኖች ፡
አስገድለውታል ።

የፖለቲካ ፡ ዝንባሌው ፡ ወደ ፡ ከሚኒስቶች ፡ የተጠጋ ፡ አንድ ፡
የጃፓን ፡ የፓርላማ ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፓር
ላማን ፡ በሚጐበኙበት ፡ ቀን ፡ ለበዓሉ ፡ ክብር ፡ የሚገባውን ፡ የማ
ዕርግ ፡ ልብስ ፡ ሳይለብስ ፡ ወደ ፡ ፓርላማ ፡ ስለገባ ፡ አገሩን ፡ አፍ
ቃሪ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የጃፓን ፡ ተወላጅ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ የድፍ
ረት ፡ ሥራ ፡ በመሠራቱ ፡ ወቅሶ ፡ እዚያው ፡ ገድሎታል ። ጃፓኖች ፡
ይህን ፡ በመሰለው ፡ ጉዳይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥታቸውን ፡ ክብር ፡ ለመ
ጠበቅ ፡ የሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ የተለመደና ፡ ብዙም ፡ በመሆኑ ፡
ጠቅሰን ፡ አንጨርሰውም ።

በዚህ ፡ በኩል ፡ ያላቸውን ፡ ባህርይ ፡ ለመግለጥ ፡ ያህል ፡ በመ
ጨረሻ ፡ አንድ ፡ ምሳሌ ፡ እንሰጣለን ።

አሚራል ፡ ቶጎ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ያን ፡ የመሰለ ፡ የጀብዱ ፡
ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ ከጃፓን ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ የሆነው ፡ ጄኔ
ራል ፡ ኖገር ፡ የሚባለው ፡ ደግሞ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ለሚዋ
ጋው ፡ የጃፓን ፡ ጦር ፡ አዝማች ፡ ነበር ። ኖገር ፡ ከዚያን ፡ በፊት ፡
በሺና ፡ አገር ፡ ባደረገው ፡ ውጊያ ፡ በጀግንነቱና ፡ በጦር ፡ መሪነቱ ፡
የታወቀና ፡ የተመሰገነ ፡ ሰው ፡ ነበር ። የኖገር ፡ ጦር ፡ በፖርት ፡
አርቱር ፡ ወደብ ፡ ላይ ፡ በሆነው ፡ ውጊያ ፡ መስኮቦች ፡ የኤሌክት
ሪክ ፡ ኃይል ፡ ባለበት ፡ ሽቦ ፡ አጥረውት ፡ የነበረውን ፡ ምሽግ ፡ እየ
ጣሰ ፡ ወታደሮቹ ፡ በብዙ ፡ ካለቁበት ፡ በኋላ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ምሹ
ጉን ፡ ይዟል ። እንደዚሁም ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ በተንጣለለው ፡ ሜዳ ፡
ላይ ፡ የመስኮብ ፡ መትረየሶች ፡ እያስካኩ ፡ ወታደሮቹን ፡ ሲቆሏቸው ፡
የኖገር ፡ ጦር ፡ ያለቀው ፡ እያለቀ ፡ ሁልጊዜ ፡ ወደፊት ፡ ይገፋ ፡
ነበር ። ከወታደሮቹ ፡ ግማሾቹ ፡ የጠላትን ፡ ምሽጎች ፡ ሲይዙ ፡ የተ
ቀበረው ፡ ዲናሚት ፡ እየፈነዳ ፡ ፈጅቷቸዋል ። ዓለም ፡ በጀግንነቱ ፡
ያደነቀው ፡ የኖገር ፡ ጦር ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ብዙ ፡ ሌሎች ፡ ልዩ ፡
ልዩ ፡ አደጋዎች ፡ ገጥመውት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡
ቢሆን ፡ አግደው ፡ ሳያቆሙት ፡ ሁልጊዜ ፡ ግሥገሣውን ፡ እየቀጠለ ፡
ወደፊት ፡ በመሄዱ ፡ በመጨረሻ ፡ ፖርት ፡ አርቱርና ፡ ሙክደን ፡ ወደ
ሚባሉት ፡ ወደቦች ፡ ገብቶ ፡ ስለ ፡ ያዛቸው ፡ የድል ፡ አድራጊነቱን ፡
አክሊል ፡ ተቀዳጀ ።

ጃፓኖች ፡ ባገራቸውና ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፤ ወይም ፡ በግል ፡ ክብራቸው ፡ በኩል ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ሲደርስባቸውና ፡ ተስፋ ፡ ሲቈርጡ ፡ ሆዳቸውን ፡ በጩቤ ፡ ቀድደው ፡ ይሞታሉ ። ይህንንም ፡ ሲያደርጉ ፡ ከበስተኋላቸው ፡ ሆኖ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በገዛ ፡ ሰይፋቸው ፡ ይጨርሳቸዋል ። ይህም ፡ አሟሟት ፡ ሃራኪሪ ፡ ይባላል ። ይህን ፡ ልማድ ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላም ፡ አልተዉትም ። ስለዚህ ፡ የሚወዱት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ ሜይጂ ፡ የሚባለው ፡ ሙትሱሂቶ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ ታሪኩን ፡ የገለጥነው ፡ ጀግናው ፡ የጦር ፡ መሪ ፡ ገኔራል ፡ ኖጊ ፡ ከደጉ ፡ ገገርዬ ፡ (ንጉሤ ፡ ) በኋላ ፡ የተረፈኝ ፡ ሕይወት ፡ ለምንም ፡ አይጠቅመኝም ፡ ብሎ ፡ ሃራኪሪ ፡ አድርጎ ፡ ሞተ ። ሚስቱም ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ አብራ ፡ ሃራኪሪ ፡ አደረገች ።

ሙትሱሂቶ ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ በጣም ፡ የተወደደ ፡ ንጉሥ ፡ ስለነበረ ፤ "ሜይጂ ፡ ቴኖ ፡ " ተብሎ ፡ ይጠራል ። ትርጕሙም ፡ "ብር ሃናዊው ፡ ንጉሥ ፡ " ማለት ፡ ነው ። ሕዝቡን ፡ በተቻለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለመጥቀም ፡ የተጣጣረና ፡ የደከመ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ። በግል ፡ ኑሮ ውም ፡ ጊዜውን ፡ የሚያሳልፈው ፡ ቅኔ ፡ በመጻፍና ፡ ሥዕል ፡ በመ ሣል ፡ ነበር ። እሱው ፡ ራሱ ፡ የጻፋቸው ፡ ግጥሞች ፡ በሦስት ፡ መጻ ሕፍት ፡ ተጽፈው ፡ ይገኛሉ ። ይህ ፡ ንጉሥ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ ከመሳፍንቱና ፡ ከመኳንንቱ ፡ ከታላላቆቹም ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ የንጉሡን ፡ አስከሬን ፡ አጅቦ ፡ በታላቅ ፡ ኃዘን ፡ ወደ ፡ መቃ ብሩ ፡ በታ ፡ ሲጓዝ ፡ ጀግናው ፡ ኖጊ ፡ ብቻ ፡ ባጀቡ ፡ ውስጥ ፡ አል ተገኘም ። የኖጊ ፡ ነፍስ ፡ ሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ ባላት ፡ ነበልባል ፡ እሳት ፡ ተለውጣ ፡ የንጉሡ ፡ አስከሬን ፡ ይገኝበት ፡ ከነበረው ፡ በበሬዎች ፡ ከሚሳበው ፡ ሰረገላ ፡ በላይ ፡ ሆና ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ እያንዣበበች ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ አብራ ፡ ንጉሡን ፡ ተከትላ ፡ ትጓዝ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ ያምናል ።

በጃፓን ፡ አገር ፡ እንደነ ፡ ሙትሱሂቶ ፡ ያሉት ፡ ነገሥታትና ፡ እንደ ፡ ቶጎና ፡ እንደ ፡ ኖጊ ፡ የመሰሉት ፡ ላገራቸው ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ቅዱሳን ፡ ተቆጥረው ፡ ሕዝቡ ፡ በየጊዜው ፡ ወደ ፡ መቃብራቸው ፡ በታ ፡ እየሄደ ፡ ይሳለማል ።

## ሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ።

ይህቺን ፡ መጽሐፍ ፡ ለማዘጋጀት ፡ አስበን ፡ የተነሣንበት ፡ ዓላማ ፡ ጃፓን ፡ በሥልጣኔ ፡ ረገድ ፡ የፈጸመችውን ፡ የሚያስቀና ፡ ተግባር ፡ ለመግለጥ ፡ ስለሆነ ፡ ይህንኑ ፡ በተቻለ ፡ አኳኋን ፡ አሳጥረን ፡ አቅርበነዋል ። ይህንንም ፡ ስናደርግ ፡ ከጃፓን ፡ ታሪክ ፡ ጋር ፡ የተያያዙ ፡ ሆነው ፡ የሚገኙትን ፡ የኢንቴርናሲዮናል ፡ ጉዳዮች ፡ ጨምረን መናገር ፡ ግዴታ ፡ ሆኖብናል ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ የጀመርነውን ፡ የጃፓንን ፡ ታሪክ ፡ ከመፈጸማችን ፡ በፊት ፡ በዚህ ፡ በመጨረሻው ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ በመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ የደረሱበትን ፡ ነገሮች ፡ ሳንናገር ፡ ብናልፈው ፡ ስለጃፓን ፡ ታሪክ ፡ ያቀረብነው ፡ መግለጫ ፡ ጎደሎ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ስለዚህ ፡ ይህንኑ ፡ አንባቢ ፡ ባጭሩ ፡ እንዲያውቀው ፡ ለማድረግ ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ በመጨረሻዎቹ ፡ ዓመታት ፡ የተደረጉትን ፡ ነገሮች ፡ እንናገራለን ።

በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ጃፓን ፡ ከኢንዱስትሪዎቿ ፡ እየሠራች ፡ የምታወጣቸውን ፡ በያይነቱ ፡ የሆኑ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ በርካሽ ፡ ዋጋ ፡ እየሸጠች ፡ የዓለምን ፡ ገበያ ፡ ሁሉ ፡ ያዘችው ። በእስያ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የጃፓን ፡ ዕቃ ፡ በአውሮፓም ፡ ይሸጥ ፡ ጀመረ ። በጃፓን ፡ አገር ፡ የሚሠሩት ፡ ሰዓቶች ፡ በርካሽ ፡ ዋጋ ፡ መሸጥ ፡ ስለጀመሩ ፡ በሰዓት ፡ ሥራ ፡ የታወቁና ፡ የተመሰገኑ ፡ የነበሩት ፡ ብዙ ፡ የስዊስ ፡ የሰዓት ፡ ፋብሪካዎች ፡ እየከሰሩ ፡ ፋብሪኮቻቸውን ፡ አቆሙ ። ለኤሌክትሪክ ፡ የሚሆን ፡ ብርጭቆ ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ እየተሠራ ፡ በርካሽ ዋጋ ፡ ስለተሸጠ ፡ በጀርመንና ፡ በነምሳ ፡ አገሮች ፡ ይህንኑ ፡ ዕቃ ፡ ይሠሩ ፡ የነበሩ ፡ ፋብሪኮች ፡ እየከሰሩ ፡ ተዘጉ ። ጫማ ፤ ጨርቃ ጨርቅ ፡ ሌሎችም ፡ እነሱን ፡ የመሰሉ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ የሚሠሩ ፡ ብዙ ፡ ፋብሪኮች ፡ በአሜሪካና ፡ በአውሮፓ ፡ በጃፓን ፡ ምክንያት ፡ ከከሣራ ፡ ላይ ፡ ወደቁ ። ጃፓን ፡ በጥራቱና ፡ በብዛቱ ፡ ከሁሉም ፡ የበለጠ ፡ ዕቃ ፡ እየሠራች ፡ ከቀሩት ፡ ሁሉ ፡ ባነስ ፡ ዋጋ ፡ መሸጥን ፡ የንግዱ ፡ ዓላማ ፡ አድርጋ ፡ በሚያስደንቅ ፡ ትጋት ፡ ይህን ፡ መንገድ ፡ ተከትላ ፡ ስለ ፡ ሠራች ፡ የዓለም ፡ ገበያ ፡ ለሷ ፡ ተከፍቶ ፡ የዓለም ፡ ገንዘብ ፡ በእጅዋ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡

ባለ ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ የሆኑ ፡ ሠላሳ ፡ የሚሆኑ ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ እንግሊዝንና ፡ የተባበሩት ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥታትን ፡ ጨምሮ ፡ በጃፓን ፡ ምክንያት ፡ ከትልቅ ፡ ከሣራ ፡ ላይ ፡ እንዳይወድቁ ፡ የሚድኑበትን ፡ መንገድ ፡ ይፈልጉ ፡ ጀመር ። እነሱም ፡ የጃፓን ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ወደ ፡ አገራቸውና ፡ ወደ ፡ ግዛታቸው ፡ እንዳይገባ ፡ ለመከልከል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴ ፡ ፈጠሩ ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ የነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ሁሉ ፡ ተገልብጠ ፡ ታየ ። ቀድሞ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ የሚመጡ ፡ ነጋዴዎቹም ፡ ሆኑ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎቻቸው ፡ ወደ ፡ አገሬ ፡ አይግባብኝ ፡ ብላ ፡ ከልክላ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ዓመታት ፡ ከዓለም ፡ ተለይታ ፡ የኖረች ፡ ጃፓን ፡ ነበረች ። በዚሁም ፡ ታላላቆቹ ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ያገርሽን ፡ ገበያ ፡ ለዓለም ፡ መከፈት ፡ ይገባሻል ፡ ሲሉ ፡ በኃይል ፡ አስገደዷት ። በኋላ ፡ ግን ፡ ጃፓን ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ተራምዳ ፡ ስለደረሰችባቸውና ፡ የዓለምን ፡ ገበያ ፡ በንግድ ፡ ዕቃዎቿ ፡ ስለ ፡ አጥለቀለቀችው ፡ የጃፓን ፡ ንግድ ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ አይግባ ፡ በማለት ፡ እነሱው ፡ መልሰው ፡ በሮቻቸውን ፡ ሲዘጉባት ፡ ተገኙ ።

ጃፓንም ፡ ይህን ፡ አደራረግ ፡ ተቃውማ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ያሜሪካ ፡ ግዛቱን ፡ ለማጣት ፡ የደረሰው ፡ በንግድ ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ ጭቆና ፡ ለማድረግ ፡ ባሰበ ፡ ጊዜ ፡ መሆኑን ፡ እያሳሰበች ፡ አሁንም ፡ ይልቁን ፡ በህንድ ፡ ግዛቶቹ ፡ ውስጥ ፡ የጃፓን ፡ ዕቃ ፡ እንዳይገባ ፡ በመከልከሉ ፡ የህንድ ፡ ሕዝብ ፡ በርካሽ ፡ የሚያገኘውን ፡ ዕቃ ፡ እንዳይገዛ ፡ ተከልክሎ ፡ በውድ ፡ ዋጋ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ላይ ፡ እንዲገዛ ፡ ማስገደድ ፡ ሷለሆነ ፡ ሕዝቡ ፡ የጥቅሙን ፡ መብቶች ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲል ፡ ሁከት ፡ እንዲያነሣ ፡ መገፋፋት ፡ እንደሚሆንበት ፡ ይወቀው ፡ ስትል ፡ ለእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ አስጠነቀቀችው ። የእንግሊዝ ፡ መንግሥትም ፡ ይህ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሥጋት ፡ አሳደረበት ። እውነትም ፡ ጃፓን ፡ እንደተናገረችው ፡ ሁሉ ፡ የህንድ ፡ ሕዝቦች ፡ በዚህ የንግድ ፡ ጭቆና ፡ ተበሳጭተው ፡ መናወጥ ፡ ጀመሩ ። አስትራሊም ፡ የበግ ፡ ጠጉር ፡ ለጃፓን ፡ በብዙ ፡ ትሸጥ ፡ ስለነበረ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ጋር ፡ ተስማምታ ፡ የጃፓንን ፡ ዕቃ ፡ አልገዛም ፡ ስላለች ፡ ጃፓን ፡ ደግሞ ፡ ከአስትራሊ ፡ ላይ ፡ የበግ ፡ ጠጉር ፡ መግዛቷን ፡ ትታ ፡ ከአ

ርዣንቲን ፡ ላይ ፡ ትገዛ ፡ ጀመር ። አውስትራሊያም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ከት ልቅ ፡ ጉዳት ፡ ላይ ፡ እንደሚጥላት ፡ ተረድታው ፡ የእንግሊዝን ፡ ምክር ፡ ጥሳ ፡ ከጃፓን ፡ ጋር ፡ ያላትን ፡ የንግድ ፡ መለዋወጥ ፡ እን ደገና ፡ ቀጠለች ።

ጃፓን ፡ ይህን ፡ በመሰለው ፡ ሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ እንዴት ፡ አድርጋ ፡ የዓለምን ፡ ሕዝቦች ፡ መንፈስ ፡ እንደማረከችው ፡ ለማወቅ ብንፈልግ ፡ አንድ ፡ የህንድ ፡ ተወላጅ ፡ በቶኪዮ ፡ ከተማ ፡ ለሚታ ተም ፡ ላንድ ፡ የጃፓን ፡ ጋዜጣ ፡ የጻፈውን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለ ውን ፡ የደብዳቤ ፡ ቃል ፡ እናስተውለው ፤ «ጃፓን ፡ የንግድ ፡ ዕቃዋን ለደሆች ፡ በርካሽ ፡ ዋጋ ፡ የምትሸጥ ፡ ስለሆነች ፡ የፈጸመችው ፡ የክርስቶስን ፡ ቃል ፡ ነው ። አምሳ ፡ ሣንቲም ፡ ለሚያወጣው ፡ ዕቃ ፡ ደሆች ፡ አንድ ፡ ዶላር ፡ ሲከፍሉ ፡ ስታይ ፡ ጃፓን ፡ ልቧ ፡ በኃዘን ፡ ይመታል ። ጃፓን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ለሚኖሩ ፡ በብዙ ፡ አሥር ፡ ሚሊዮን ፡ ለሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ ቤዛ ፡ ሆናቸዋለች ። ይህ ፡ የፈጸመ ችው ፡ ሥራ ፡ የተቀደሰና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ተግባር ፡ ነው ። ጃፓን ሆይ ፡ አንቺ ፡ ለደሆችና ፡ ለትሁታን ፡ አርዓያ ፡ ነሽ ።»

እንደዚህ ፡ አድርጋ ፡ ጃፓን ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ኃይሏን ፤ እያጠነ ከረች ፡ ስለሄደች ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ ነጮችን ፡ በገዛ ፡ ግዛታቸው ፡ ውስጥ ፡ እየገባች ፡ ገባያቸውን ፡ ነጠቀቻቸው ። ሜይጂ ፡ የተባለው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቷ ፡ ዓርባ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ከ1867 እስከ ፡ 1912 ዓ. ም. በነገሠበት ፡ ዘመን ፡ የትምህርትና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራዎች ፡ ተያይዘው ፡ በጥንቃቄ ፡ በተጠና ፡ መንገድ ፡ እንዲሄዱ ፡ ስለተደረገ ፤ ጃፓን ፡ በጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ለሕዝቧ ፡ ኑሮ ፡ የሚያስፈል ገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ባገርዋ ፡ ውስጥ ፡ ከሠራች ፡ በኋላ ፡ ከራሷ ፡ ተርፎ ፡ ከታላላቆቹ ፡ መንግሥታት ፡ ላይ ፡ የዓለምን ፡ ገበያ ፡ ለመ ውሰድ ፡ ትወዳደራቸው ፡ ጀመር ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ይኸው ፡ ሜይጂ ፡ የተባለው ፡ ንጉሥ ፡ ሲነግሥ ፡ ሠላሳ ፡ ሚሊዮን ፡ የነበረው ፡ የሕዝቧ ፡ ቁጥር ፡ እየጨመረ ፡ እንዲሄድ ፡ በመደረጉ ፡ ከስድሳ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ባሁኑ ፡ ንጉሥ ፡ በሂሮሂቶ ፡ ዘመን ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሃያ ፡ ሚሊዮን ፡ ሆነ ። የአውሮፓ ፡ ሕዝቦች ፡ ቁጥራቸው ፡ እያነሰና ፡ እየ ተቀነሰ ፡ የሚሄድ ፡ መሆኑን ፡ የዓለምን ፡ ሕዝቦች ፡ ቁጥር ፡ መርማ

ሪዎች ፡ የሆኑት ፡ ሊቃውንት ፡ በሚያረጋግጡበት ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ጃፓን ፡ የሕዝቧ ፡ ቁጥር ፡ ባመት ፡ ባመቱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ እየጨመረ ፡ የሚሄድ ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ። የኢኮኖሚ ፡ ኃይሏና ፡ የሕዝቧ ፡ ብዛት ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ አካሄድ ፡ የሚራመድ ፡ መሆኑን ፡ ስናመዛዝነው ፡ ወደፊት ፡ ያውሮፓ ፡ ሕዝቦች ፡ እየወደቁ ፡ ሲሄዱ ፡ የሥልጣኔ ፡ ኃይል ፡ አውሮፓን ፡ ትታ ፡ ወደ ፡ እስያ ፡ በመዛወር ፡ ላይ ፡ ያለች ፡ መስላ ፡ ትታያለች ፡ ሲሉ ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ያጠኑት ፡ ሰዎች ፡ ጨምረው ፡ ገልጠዋል ። ከፍ ፡ ብለን ፡ በምዕራፉ ፡ እንደተመለከትነው ፡ ሁሉ ፡ ከጃፓን ፡ ጋር ፡ ለመወዳደር ፡ የሥራዋ ፡ አካሄድና ፡ የሕዝቧም ፡ ብዛት ፡ የሚፈቅድላት ፡ መስላ ፡ የምትታይ ፡ መስኮብ ፡ ብቻ ፡ ነች ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሁለቱም ፡ ቢሆኑ ፡ የጂኦግራፊ ፡ አቀማመጣቸው ፡ የሚመራው ፡ ወደ ፡ እስያ ፡ ስለሆነ ፡ በዚያም ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ አውሮፓን ፡ የሚገድላት ፡ እንጅ ፡ የሚያድናት ፡ ነገር ፡ ያለ ፡ አይመስልም ።

በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ በመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ መስኮብ ፡ ሬቮሊሲዮን ፡ አድርጋ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መኖር ፡ ጨርሳ ፡ ስለካደች ፡ ጃፓን ፡ በክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ መንፈስ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተው ፡ ያውሮፓ ፡ ሥልጣኔ ፡ በመፍረስና ፡ በመደምሰስ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ መስሎ ፡ ታያት ። ሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በተነሣበት ፡ ጊዜ ፡ ከሂትለርና ፡ ከሙሶሊኒ ፡ ጋር ፡ ሆና ፡ የጦር ፡ ጓደኞችን ፡ የወጋቻቸው ፡ እነዚህን ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ነገሮች ፡ በመመርኰዝ ፡ ነው ።

ተመልካች ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ነገሩን ፡ ሲያመዛዝነው ፡ እነ የተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥታት ፤ እንግሊዝና ፡ መስኮብ ፡ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ታላላቅ ፡ መንግሥታት ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ተሰልፈው ፡ ሲወጓት ፡ ጃፓን ፡ እንደምን ፡ አድርጋ ፡ ለእነሱ ፡ ለመመከትና ፡ በመጨረሻም ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ አገኛለሁ ፡ ብላ ፡ ለመመኘት ፡ ቻለች ፡ ብሎ ፡ ይህንኑ ፡ እንደ ፡ ዕብደት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ አለማስተዋል ፡ አድርጎ ፡ ይቆጠርባታል ። አንዳንዶቹማ ፡ ሰዎች ፡ ጃፓን ፡ ይህንን ፡ በማድረጓ ፡ ዓይኗን ፡ ጨፍና ፡ እሳት ፡ ውሥጥ ፡ እንደ ገባች ፡ ያህል ፡ ስለቆጠሩባት ፡ የጃፓን ፡ መንግሥት ፡ ሃራኪሪ ፡ አደ

ረገ ፡ ብለው ፡ አፈዘዘውበታል ። ነገር ፡ ግን ፡ ጦርነቱ ፡ ከመነ
ሣቱ ፡ በፊት ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ የኖሩ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጆች ፡
የሆኑ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በተለየም ፡ አሜሪካኖችና ፡ እግሊዞች ፡ የሆኑ ፡
ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ መርምረው ፡ አሳባቸውን ፡ የገለጡበትን ፡ ጽሑ
ፎች ፡ ስናነብ ፡ ጃፓኖች ፡ እንደ ፡ ልማዳቸው ፡ ይህንን ፡ ጉዳይ ፡
ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ አስተዋይነትና ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጥንቃቄ ፡ አጥንተውት ፡
ለጊዜው ፡ አሁኑኑ ፡ የዓለም ፡ ገዥዎች ፡ ለመሆን ፡ ባይችሉ ፡ እንኳ ፡
ነጮችን ፡ ከእስያ ፡ ሊያስወጧቸው ፡ የሚችሉበትን ፡ መንገድ ፡ በዘጋጁት ፡
አቅድ ፡ ውስጥ ፡ ደህና ፡ አድርገው ፡ አሰናድተውት ፡ ነበር ። እስ
ያን ፡ ከያዙ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ የዓለም ፡ ገዥዎች ፡ ለመሆን ፡ ያላ
ቸው ፡ አሳብ ፡ በሁለተኛው ፡ እርምጃ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንደሚያገኝ ፡
ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ሊረዳው ፡ የሚችል ፡ ግልጥ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ጃፓኖች ፡ የአውሮፓ ፡ ሥልጣኔ ፡ ገና ፡ መጀመሪያ ፡ ወደ ፡ አገ
ራቸው ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ጥልቅ ፡ ተመልካቾች ፡ በመሆናቸው ፡
ምሥጢሩን ፡ መርምረው ፡ ወዲያው ፡ ስለ ፡ ደረሱበት ፡ የሚያስፈልጋቸ
ውንና ፡ የሚጠቅማቸውን ፡ ብቻ ፡ ለይተው ፡ ከወሰዱ ፡ በኋላ ፡ የሚ
ጎዳቸውንና ፡ የሚያበላሻቸውን ፡ አንቀበልም ፡ ብለው ፡ ወረወሩት ።
እንደዚሁም ፡ በበኩላቸው ፡ ከሚገኘው ፡ ከጥንት ፡ ጀምር ፡ ተያይዞ ፡
ከመጣው ፡ ባህላቸውና ፡ ልማዳቸው ፡ ውስጥ ፡ እየመረጡ ፡ ከዲሱ ፡
ሥልጣኔ ፡ ጋር ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነውን ፡ በማረም ፡ ከጣሉት ፡ በኋላ ፡
ሊጠቅማቸው ፡ የሚችለውን ፡ ግን ፡ የጸና ፡ ሆኖ ፡ እንዲጠበቅ ፡ አደ
ረጉት ።

ኢንዱስትሪ ፡ ዋና ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡
እንደምንም ፡ ብለው ፡ በመጣጣር ፡ በገራቸው ፡ ውስጥ ፡ አስፋፉት ።
እንደዚሁም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ አገራቸው ፡ ደሀ ፡ መሬት ፡ ቢሆን ፡
የሕዝባቸው ፡ ቍጥር ፡ እየበረከተ ፡ እንዲሄድ ፡ አደረጉ ። ሌሎች ፡
ብዙዎች ፡ አገሮች ፡ ግን ፡ የሚጠቅማቸውን ፡ የገል ፡ ልማዳቸውን ፡
የሚተካ ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ባሕሪ ፡ ሳያደርጉበት ፡ እየጣሉት ፡ ከውርፓ ፡
ሥልጣኔ ፡ ደግሞ ፡ የሚጎዳቸውን ፡ መጥፎውን ፡ ብቻ ፡ እየተቀበሉ ፡
የሚጠቅማቸውን ፡ ግን ፡ ሳይወርሱት ፡ በመቅረታቸው ፡ ወደ ፡ ሥል
ጣኔ ፡ የሚያደርጉትን ፡ እርምጃ ፡ ባጉል ፡ መንገድ ፡ በመምራታቸው ፡

ከጉዳት ፡ ላይ ፡ ጥሏቸዋል ። ጃፓኖች ፡ ግን ፡ የሚጠቅማቸውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንዳይጠፋ ፡ ተጠነቀቁበት ።

ለምሳሌ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ተያይዞ ፡ የመጣው ፡ የሃይማኖታቸው ፡ ትምህርት ፡ ራሳቸውን ፡ ያማልክት ፡ ልጆች ፡ አድርገው ፡ እንዲመለከቱ ፡ አስተምሮዋቸዋል ። አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ራሱን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ የሚመካበት ፡ የግል ፡ እምነት ፡ ከሌለው ፡ በዱር ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ጨለመበት ፡ መንገደኛ ፡ የሚቀበዘበዝ ፤ ወይም ፡ በምንም ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ አማኝነት ፡ አጥቶ ፡ የሚናውዝ ፡ እንደሚሆንና ፡ ይህም ፡ ትልቅ ፡ ጉዳት ፡ እንደሚያስከትልበት ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡ ይህ ፡ የሚከሩበት ፡ የግል ፡ እምነታቸው ፡ ሁልጊዜ ፡ በሕዝባቸው ፡ መንፈስ ፡ ውስጥ ፡ ተቀርጾ ፡ እንዲኖር ፡ አስፈላጊውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አደረጉ ።

ሂትለር ፡ የጀርመንን ፡ ሕዝብ ፡ የዓለም ፡ ገዥዎች ፡ ለማድረግ ፡ ባሰበ ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ የሚያግል ፡ ትምህርት ፡ ካልተጨመረ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ማደራጀት ፡ ብቻ ፡ የማይበቃ ፡ መሆኑን ፡ ተረድቶት ፡ መጀመሪያ ፡ ጎቢኖ ፡ ቀጥሎ ፡ ቻምቤርለን ፡ ከተባሉት ፡ ደራስያን ፡ የተገኘውን ፡ የፍልስፍና ፡ አሳብ ፡ ተመርኵዞ ፡ የጀርመን ፡ ሕዝብ ፡ ደም ፡ የሥልጣኔ ፡ ምንጭ ፡ ከሆኑት ፡ ከአርያን ፡ ሕዝቦች ፡ ዘር ፡ የመጣ ፤ ዝቅተኞች ፡ ከሆኑት ፡ ከሌሎች ፡ ሕዝቦች ፡ ደም ፡ ጋር ፡ ሳይቀላቀል ፡ ንጹህ ፡ ሆኖ ፡ የኖረ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለሕዝቡ ፡ በማስተማር ፡ ይህን ፡ የትዕቢት ፡ መንፈስ ፡ በልባቸው ፡ ውስጥ ፡ አሳደረባቸው ። የቀሩት ፡ ያውሮፓ ፡ አገሮች ፡ ሊቃውንት ፡ ግን ፡ በታሪክም ፡ ሆነ በፍልስፍና ፡ መንገድ ፡ ሲመረመር ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ የሚያስቅ ፡ ሆኖ ፡ በሚገኘው ፡ በዚህ ፡ ትምህርት ፡ ላይ ፡ እምነት ፡ ማድረግ ፡ ትልቅ ፡ ሞኝነት ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ጀርመኖችን ፡ ከስህተት ፡ ሊመልሷቸው ፡ ሞከሩ ። የጀርመን ፡ ተወላጆች ፡ ግን ፡ የዓለም ፡ ገዥዎች ፡ ለመሆን ፡ መብት ፡ የሚሰጣቸው ፡ አድርገው ፡ የተመለከቱትን ፡ ይህን ፡ ትምህርት ፡ ዓይናቸውን ፡ ጨፍነው ፡ በሙሉ ፡ ልባቸው ፡ ተቀበሉት ።

እንግዲህ ፡ ሌሎቹ ፡ ሕዝቦች ፡ እንደዚህ ፡ አድርገው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ባገራቸው ፡ ውስጥ ፡ ያልነበረውን ፡ እምነት ፡ እየፈጠሩ ፡ ለሕዝባቸው ፡ ሲያስተምሩት ፡ በሚታዩበት ፡ ጊዜ ፡ ጃፓን ፡ ከብዙ ፡

ሺ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ጀምሮ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣውን ፡ የምትኩራበትን ፡ እምነት ፡ ነቅላ ፡ ለመጣል ፡ አልፈለገችም ። ጀርመኖች ፡ የአርያን ፡ ዘር ፡ ነንና ፡ የዓለም ፡ ገዥዎች ፡ መሆን ፡ ይገባናል ፡ ሲሉ ፡ ጃፓኖች ፡ ደግሞ ፡ እኛ ፡ ያማልክት ፡ ልጆች ፡ ነን ፡ በማለታቸው ፡ በሙግትና ፡ በክርክር ፡ መንገድም ፡ ቢሆን ፡ ነገሩን ፡ ሲያመዛዝኑት ፡ የዓለም ፡ ገዥነትን ፡ ለመመኘትና ፡ ለመፈለግ ፡ የበለጠ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ እነሱ ፡ ሆነው ፡ እንዲታዩ ፡ እንደሚያደርግላቸው ፡ ሳይሰማቸው ፡ አልቀረም ።

ፈረንጆች ፡ (ሰሪዝ ፡ ) የሚሉትን ፡ ፍሬ ፡ የሚያፈራ ፡ አንድ ፡ ዛፍ ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ በብዙ ፡ ይገኛል ። ጃፓኖች ፡ በጠቅላላው ፡ አበባ ፡ በጣም ፡ ይወዳሉ ። በተለየ ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ ዛፍ ፡ የሚያብበውን ፡ ነጭ ፡ አበባ ፡ እጅግ ፡ አድርገው ፡ ያፈቅሩታል ። ይህቺ ፡ አበባ ፡ ባበበች ፡ ጊዜ ፡ እንቡጧ ፡ ሳይጠወልግና ፡ ሳይደርቅ ፡ እንደለመለመች ፡ አበባዋ ፡ በቶሎ ፡ ትረግፋለች ። ጃፓኖች ፡ ይህቺ ፡ አበባ ፡ የሳሙራዩ ፡ (የመኳንንት ፡ ) ተወላጅ ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የነፍሱ ፡ ምሳሌ ፡ ናት ፡ ይላሉ ።

እንቡጧ ፡ መጠውለግና ፡ መድረቅ ፡ ሳይነካው ፡ አበባዪቱ እንደምትረግፍ ፡ ሁሉ ፡ ከአማልክት ፡ ዘር ፡ ተወላጅነት ፡ ያለው ፡ ሳሙራዩም ፡ ሰውነቱን ፡ ውርደት ፡ ሳይነካው ፡ መሞት ፡ (መርገፍ ፡ ) ይገባዋል ፡ ይላሉ ። ሃራኪሪ ፡ በማድረግ ፡ በገዛ ፡ እጃቸው ፡ የሚሞቱበትን ፡ ምክንያት ፡ ሲጠየቁ ፡ ጃፓኖች ፡ ከሃይማኖት ፡ ምሥጢር ፡ ጋር ፡ እያስማሙ ፡ የሚሰጡት ፡ መልስ ፡ ይህ ፡ ነው ። ጀርመኖችስ ፡ ከሂትለር ፡ ጀምሮ ፡ እነ ፡ ገበልስንና ፡ እነ ፡ ሂምለርን ፡ ጨምሮ ፡ ከመዋረድ ፡ መሞት ፡ ይሻላል ፡ በማለት ፡ በገዛ ፡ እጃቸው ፡ ሲሞቱ ፡ አልታዩምን?

ጀርመኖችና ፡ ጃፓኖች ፡ ተመሳሳይነት ፡ ያለው ፡ ትዕቢት ፡ አድሮባቸው ፡ ዓለምን ፡ ለመግዛት ፡ ከመነሣታቸው ፡ በፊት ፡ ታሪካቸውን ፡ ስንመለከተው ፡ በመንፈስ ፡ የሚቀራረቡ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። ጃፓኖች ፡ ሕገ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ሲያዘጋጁ ፡ ምሳሌ ፡ አድርገው ፡ የወሰዱት ፡ የጀርመንን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ነው ። በጦር ፡ አስተዳደርም ፡ በኩል ፡ ጃፓኖች ፡ ከፈረንሣዮችና ፡ ከጀርመኖች ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ቀድተዋል ።

በዚህ ፡ አሁን ፡ በለፈው ፡ በሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ወዳጆች ፡ ሆነው ፡ ሲዋጉ ፡ ሁለቱም ፡ በየበኩላቸው ፡ አንዱ ፡ አንደኛውን ፡ ሊያታልለው ፡ አሳብ ፡ እንደነበራቸው ፡ ግልጥ ፡ ሆኖ ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፡ ነበር ። ሁለቱም ፡ የዓለም ፡ ገዥዎች ፡ ለመሆን ፡ ሲያስቡ ፡ በመጨረሻ ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ ለመስማማት ፡ እንደሚችሉ ፡ ለማወቅ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ ነው ። እውነተኛው ፡ አሳባቸው ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተው ፡ ነበር ። የጀርመን ፡ አሳቧ ፡ አውሮፓን ፡ ከያዘች ፡ በኋላ ፡ ቢሆንላት ፡ ወዲያው ፡ በትኩሱ ፡ ባይሆንላትም ፡ የያዘችውን ፡ አደራጅታ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አረፍት ፡ አድርጋ ፡ እስያን ፡ በሙሉ ፡ ጃፓንን ፡ ጨምራ ፡ ለመያዝ ነበር ። ጃፓን ፡ ደግሞ ፡ በበኩሏ ፡ ሂትለር ፡ ለጊዜው ፡ ቀንቶት ፡ ያውሮፓን ፡ አገሮች ፡ ቢይዝም ፡ እኔን ፡ በእስያ ፡ ሊደፍረኝ ፡ አይችልምና ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ እሱ ፡ የአውሮፓ ፤ እኔ ፡ የእስያ ፡ ገዥዎች ፡ ሆነን ፡ ከቆየን ፡ በኋላ ፡ ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ በምናደርገው ፡ ውጊያ ፡ ቀኙ ፡ ለእኔ ፡ ይሆናል ፡ የማለት ፡ አሳብ ፡ እንደነበራት ፡ አይጠረጠርም ። ጃፓኖች ፡ በጦርነቱ ፡ ሰዓት ፡ ሲናገሩ ፡ እንደዚህ ፡ ይሉ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ በሦስት ፡ ይከፈላሉ ። በአንደኛው ፡ ክፍል ፡ ጠላቶቻችን ፡ ይገኛሉ ። በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ያሉት ፡ ከጦርነቱ ፡ ውሥጥ ፡ ያልገቡ ፡ ጠላቶቻችን ፡ ናቸው ። ሦስተኛውን ፡ ክፍል ፡ ያየዙት ፡ ደግሞ ፡ ወዳጆቻችን ፡ የሆኑት ፡ ጠላቶቻችን ፡ ናቸው ። ጃፓኖች ፡ የሕዝባቸውን ፡ ብዛትና ፡ የወታደሮቻቸውን ፡ ጅግንነት ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎቻቸውንም ፡ ጥራት ፡ አመዛዝነው ፡ የእስያን ፡ ሕዝቦች ፡ ከያዙ ፡ በኋላ ፡ ዓለምን ፡ ለመግዛት ፡ ይሳነናል ፡ ብለው ፡ ጥቂት ፡ እንኳ ፡ አልጠረጠሩም ፡ ነበር ።

ዡን ፡ ሞሪስ ፡ የተባለ ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ የኖረ ፡ አንድ ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጅ ፡ በጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ አስተዳደር ፡ ጉዳይ ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ የተመለከታቸውን ፡ ነገሮች ፡ በተናገረበት ፡ ውስጥ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ገልጧል ። በጃፓን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ ማንኛውም ፡ ወታደር ፡ ሲቀጠር ፡ ከሁሉ ፡ ነገር ፡ አስቀድሞ ፡ የሚያስተምሩትና ፡ የሚያስጠኑት ፤ ከሱ ፡ የሚጠበቀው ፡ ዋናው ፡ ተግባር ፡ ላገሩ ፡ ሲል ፡ እንዲሞት ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡

ነው ። ስለዚህ ፡ የጃፓን ፡ ወታደር ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ባንጎሉ ፡ ውስጥ ፡ ያደረበት ፡ ምኞት ፡ የጀግንነት ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ መሞት ፡ ብቻ ፡ ነው ። በሌሎቹ ፡ አገሮች ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ማናኛውም ፡ ወታደር ፡ ቢሆን ፡ ወደ ፡ ዘመቻ ፡ ሄዶ ፡ ከጦርነቱ ፡ እሳት ፡ ውስጥ ፡ ወጥቶ ፡ ብደኅና ፡ ሲመለስ ፡ በዘመዶቹና ፡ በወዳጆቹ ፡ ዘንድ ፡ ትልቅ ፡ ደስታ ፡ ይሆናል ፤ እሱም ፡ ራሱ ፡ ዕድሉን ፡ ያመሰግናል ። በጃፓኖች ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ጦርነት ፡ ከተዋጋ ፡ በኋላ ፡ ቆስሎ ፤ ወይም ፡ ከማናኛውም ፡ አደጋ ፡ ድኖ ፡ የተመለሰ ፡ ወታደር ፡ ሳይሞት ፡ በመቅረቱ ፡ በሚያውቁት ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ነውር ፡ ይቆጠርበታል ። እሱም ፡ ራሱ ፡ ይህንኑ ፡ ከውርደትና ፡ ከነውር ፡ እየቆጠረው ፡ ሕይወቱን ፡ ሙሉ ፡ ሲያፍርበትና ፡ ሲፀፀትበት ፡ ይኖራል ። የጃፓን ፡ ወታደር ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ከመማረክ ፡ ይልቅ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ መሞትን ፡ የሚመርጥበት ፡ ምክንያት ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። ወታደሮቻቸው ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ መንፈስ ፡ ይዘው ፡ የሚዋጉ ፡ በመሆናቸው ፡ የጃፓን ፡ ጦር ፡ እጅግ ፡ የሚያስፈራ ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ።

ይህ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወታደር ፡ ያለውን ፡ ጠባይ ፡ የሚገልጥ ፡ ሲሆን ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ በጠቅላላው ፡ ከቀሩት ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ የተለየ ፡ ባሕሪ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ የሚታይበትን ፡ እንመልከተው ። የጃፓን ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሁልጊዜ ፡ ሲሠራባቸው ፡ የተገኙ ፡ ሁለት ፡ ጠባዮች ፡ አሉት ። አንደኛ ፡ ጦርነትን ፡ ሲጀምር ፡ ጠላት ፡ ባላሰበበት ፡ በዘነጋበትና ፡ ባልተዘጋጀበት ፡ ጊዜ ፡ ዱብ ፡ ዕዳ ፡ የሆነ ፡ አደጋ ፡ ጥሎ ፡ ሞራሉን ፡ ( መንፈሱን ፡ ) መግደልና ፡ የኃይሉን ፡ ቅስም ፡ መስበር ፡ ይወዳል ።

ሁለተኛው ፡ ጠባዩ ፡ ደግሞ ፡ ይልቁንም ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ መስኮቦች ፡ ሲሠሩበት ፡ ከታየው ፡ ዘዴ ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ጦርነትን ፡ ከመጀመር ፡ በፊት ፡ ጃፓኖች ፡ የሚያዘጋጁትን ፡ መሣሪያ ፡ ሁሉ ፡ እየደበቁ ፡ ጠላት ፡ ጉልበታቸውን ፡ እንዳያውቀው ፡ በማድረግ ፡ ሰውረውት ፡ መኖራቸው ፡ ነው ። ይህም ፡ ዘዴ ፡ ጠላት ፡ መከላከያውን ፡ እንዳይዘጋጅና ፡ ጉልበታቸውንም ፡ ገዘቅ ፡ አድርጎ ፡ በመገመት ፡ ከስህተት ፡ ላይ ፡ እንዲወድቅ ፡ ለማድረግ ፡ እንዲረዳ ፡ ረቂቅ ፡ በሆነ ፡ ብልጠት ፡ ታስቦ ፡ የተሰናዳ ፡ ብልሀት ፡ ነው ። ከዚህ ፡

ግብ ፡ ለመድረስ ፡ በያይነቱ ፡ ብዙ ፡ የማታለል ፡ ሥራ ፡ ሠርተዋል ። ለምሳሌ ፡ ብዙዎቹ ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ አዲስ ፡ የሠሩዋቸውን ፡ የጦር ፡ መሣሪዎች ፡ ለኤክስፖዚሲዮን ፡ እንዲያገለግል ፡ ወደ ፡ ጃፓን፡ አገር ፡ በላኩ ፡ ጊዜ ፡ ጃፓኖች በአኤሮፕላን ፡ በኩል ፡ ሳይቀር ፡ በራሳቸው ፡ በኩል ፡ ያቀረቡት ፡ መናኛውን ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እየ መረጡ ፡ ነው ። ጦርነቱ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ በአኤሮፕላንም ፡ ሆነ ፡ በቀረው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሣሪያ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ብልጫ ፡ ያላ ቸው ፡ ሆነው ፡ ስለተገኙ ፡ አሜሪካኖችና ፡ እንግሊዞች ፡ እስቲደርሱ ባቸው ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አስፈልጓቸዋል ። ደኅና ፡ አድርገው ፡ እንዳታለሏቸው ፡ የተረዱትም ፡ በኋላ ፡ ነው ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ጃፓን ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ እንደተመለከትነው ፡ ሁሉ ፡ በንግድም ፡ ሆነ ፡ በኤኮኖሚ ፡ ጉዳይ ፡ የገጠሟትን ፡ ችግሮች ፡ ለማቃላል ፡ ስትል ፡ ከብዙ ፡ መንግሥታት ፡ ጋር ፡ የሚያጋጩዋት ፡ ነገሮች ፡ በየጊዜው ፡ ቢፈጠሩ ፤ በተቻላት ፡ መጠን ፡ ከታላላቆቹ ፡ መን ግሥታት ፡ ጋር ፡ በሰላም ፡ ለመኖር ፡ ፈቅዳ ፡ ከተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥታት ፤ ከመስኮብ ፤ ከእንግሊዝና ፡ ከፈረንሣይ ፡ ጋር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ውሎችና ፡ ስምምነቶች ፡ ተፈራርማ ፡ ነበር ።

በጃፓን ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ በጋዜጣና ፡ በፕሮፓጋንድ ፡ ክፍል ፡ ሹም ፡ የነበረ ፡ አማው ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ጃፓን ፡ በመጨ ረሻ ፡ ጊዜ ፡ ፖሊቲካ ፡ መለወጧን ፡ ሲገልጥ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ተናገረ ፤

« ዋሺንግቶን ፡ ላይ ፡ በ1922 ዓ. ም. በተደረገው ፡ ጉባኤ ፡ ስለ ፡ ሺና ፡ ነፃነት ፡ ጉዳይ ፡ አሜሪካ ፡ የወሰነችውን ፡ አሳብ ፡ ለማክበር ፡ ተቀብለነው ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ ውል ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በመርከብ ፡ ረገድ ፡ እኩል ፡ ለኩል ፡ መሆንን ፡ እንድንተው ፡ በ1922 ዓ. ም. በዋሺንግቶን ፤ በ1930 ዓ. ም. በሎንዶን ፡ ስላደረግናቸው ፡ ስምምነቶች ፡ የምንሰጣ ቸውን ፡ አስተያየቶች ፡ ለማወቅ ፡ ብትፈልጉ ፡ ጀርመን ፡ በቬርሳይ ፡ ስላደረገችው ፡ ውል ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሠራች ፡ አስቡ ። ዛሬ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ መንግሥቶች ፡ ይገኛሉ ፤ እነሱም ፡ ውሎች ፡ የተደረጉላቸውና ፡ ውሎች ፡ የተደረጉባቸው ፡ መንግሥታት ፡ ናቸው ። ጀርመንና ፡ ጃፓን ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ በተመለከቱት ፡ ውስጥ ፡

ናቸው ። በእውነቱ ፡ አንቃችሁ ፡ ልትገድሏቸው ፡ የምትፈልጉ ፡ ከሆናችሁ ፡ ይህንኑ ፡ በውል ፡ ወረቀት ፡ ልታደርጉት ፡ መሞከራችሁ ፡ ቀርቶ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ብትፈልጉ ፡ ይሻላል ።"

ይህ ፡ ንግግር ፡ ጃፓን ፡ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ የጀርመንን ፡ አሳብ ፡ ተቀብላ ፡ ባለፉት ፡ ጊዜዎች ፡ ከአሜሪካና ፡ ከእንግሊዝ ፡ ጋር ፡ የተፈራረመቻቸውን ፡ ውሎች ፡ ለማፍረስ ፡ መቁረጧንና ፡ በሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ናዚስት ፡ ከሆነችው ፡ ጀርመንና ፡ ፋሺስት ፡ ከሆነችው ፡ ኢጣሊያ ፡ ጋር ፡ ተባብራ ፡ ለመዋጋት ፡ ያደረሳትን ፡ ፖሊቲካ ፡ መከተሏን ፡ ይገልጣል ። በአሜሪካና ፡ በጃፓን ፡ መካከል ፡ ለተፈጠረው ፡ አለመግባባት ፡ ምክንያት ፡ የሆነችው ፡ ሺና ፡ ነች ። የተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ ሺና ፡ ነፃ ፡ አገር ፡ ስለ ፡ ሆነች ፡ የጦር ፡ መሣሪያን ፡ ካሜሪካ ፡ አገር ፡ ብትገዛና ፡ የንግድ ፡ ሥራዋንም ፡ ካሜሪካ ፡ ጋር ፡ ለማከናወን ፡ ብትፈልግ ፡ ነፃ ፡ አገር ፡ በመሆኗ ፡ የሚከለክላት ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ሲሉ ፡ ጃፓን ፡ ግን ፡ የእስያ ፡ ሕዝቦች ፡ እየተረዳዱ ፡ ራሳቸውን ፡ ይችላሉ ፡ እንጅ ፡ የባዕድ ፡ መንግሥት ፡ እንዲገባባቸው ፡ አይፈልጉም ፡ ባይ ፡ ሆነች ። የተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ ደግሞ ፡ ጃፓን ፡ ኃይሏ ፡ እየገነነ ፡ ስለሄደ ፡ ደካሞች ፡ የሆኑት ፡ ሌሎቹ ፡ የእስያ ፡ አገሮች ፡ በጃፓን ፡ ጥፍር ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ እንዲኖሩና ፡ የበለጠ ፡ ኃይል ፡ የምታገኝባቸው ፡ መሣሪያዎቿ ፡ እንዲሆኑ ፡ አልፈለጉም ።

ጃፓን ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ የሕዝቧ ፡ ቁጥር ፡ እየጨመረ ፤ በሁለተኛው ፡ በኩል ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራዋ ፡ በጣም ፡ እየተስፋፋ ፡ በመሄዱ ፡ የኃይሏ ፡ መሠረቶች ፡ የሆኑትን ፡ እነዚህን ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ የምትዘረጋበት ፡ ቦታ ፡ ማግኘት ፡ ግዴታ ፡ ሆኖባት ፡ ነበር ። ባካባቢዋ ፡ የሚገኙትም ፡ አገሮች ፡ ካናዳ ፤ የተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥታት ፤ ኦስትራሊና ፡ ብሬዚል ፡ ብጫ ፡ ሕዝቦችን ፡ አንቀበልም ፡ በማለትና ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎቿም ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ እንዳይገቡ ፡ በመከልከል ፡ በራቸውን ፡ ስለዘጉባት ፡ ችግሩዋ ፡ እየበረታ ፡ ሄደ ።

የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤቶች ፡ የሆኑት ፡ እነ ፡ ሚትሱኢና ፡ ሚትሱቢሺ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እያልን ፡ በዘዴና ፡ በብልሃት ፡ ብንሠራ ፡ በሺና ፡ አገር ፡ ያለውን ፡ ገበያ ፡ ለመውሰድና ፡ የንግድ ፡ ዕቃችንን ፡

ሰፊ ፡ የሆነው ፡ የሺና ፡ አገር ፡ ተቀባይ ፡ እንዲሆንልን ፡ ለማድረግ ፡ እንችላለን ፡ የማለት ፡ አሳብ ፡ አቀረቡ ። ነገር ፡ ግን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወገኖች ፡ ማንድሹሪንና ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ የሺናን ፡ አገር ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ ወርረን ፡ መያዝ ፡ ይሻለናል ፡ ብለው ፡ ተነሡ ። ባስተዋይነትና ፡ በትእግሥት ፡ ብንሠራ ፡ ይሻላል ፡ ሲሉ ፡ ምክር ፡ ያቀረቡትን ፡ ሚኒስትሮች ፡ ሁሉ ፡ አስገደሏቸው ። ትዕቢትን ፡ መሣሪያ ፡ አድርገው ፡ ለተነሱት ፡ ለእነዚህ ፡ የጦር ፡ ወገኖች ፡ ሊያግዳቸው ፡ የሚችል ፡ ምንም ፡ ልጓም ፡ አልተገኘም ። የማንድሹሪን ፡ አገር ፡ የወረሩበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚመረምር ፡ ከሚሲዮን ፡ ከዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ በተላከ ፡ ጊዜ ፡ ጃፓኖች ፡ ተቆጥተው ፡ ከዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ወጡ ።

ቀጥሎ ፡ በ1937 ዓ. ም. ጃፓኖች ፡ በሺና ፡ አገር ፡ ላይ ፡ የወረራ ፡ ጦርነት ፡ ጀመሩ ። መስከብ ፡ እንዳትዋጋቸው ፡ በሂትለር ፡ ይመራ ፡ ከነበረው ፡ ከጀርመን ፡ ናዚስት ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ውል ፡ ተፈራረሙ ። ውጊያውም ፡ እንደተጀመረ ፡ ስለቀናቸው ፡ የፔኪንን ፤ የሻንጋዩን ፡ የናንኪንንና ፡ የሃንኬውን ፡ ከተማዎች ፡ ያዙ ። ነገር ፡ ግን ፡ በቻንጋይ ፡ ሼክ ፡ መሪነት ፡ የገጠማቸው ፡ የሺና ፡ ተከላካይ ፡ ጦር ፡ ያልጠረጠሩትን ፡ አንድነትንና ፡ ጠንካራነትን ፡ ተደግፎ ፡ ስለመከተላቸው ፡ ጦርነቱን ፡ በቶሎ ፡ እንጨርሳለን ፡ ሲሉ ፡ የነበራቸው ፡ ተስፋ ፡ ሳይፈጸምላቸው ፡ ቀረ ። እንግሊዝ ፤ ፈረንሣይና ፡ መስኮብም ፡ ሌሎች ፡ የባሱ ፡ ጉዳዮች ፡ ገጥመዋቸው ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በውጊያው ፡ ውስጥ ፡ ሊገቡ ፡ ባይችሉ ፡ ሺናን ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፤ ስንቅና ፡ አኤሮፕላኖች ፡ እየሰጡ ፡ ረዷት ። በጃፓንና ፡ በሺና ፡ መካከል ፡ የፈነዳው ፡ ይህ ፡ ጦርነት ፡ እስከ ፡ 1945 ዓ. ም. ድረስ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ቆየ ። እነሆ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ በሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ጃፓን ፡ ከሂትለርና ፡ ከሙሶሊኒ ፡ ጋር ፡ ጎን ፡ ለጎን ፡ ተሰልፋ ፡ ተገኘች ። ታኅሣሥ ፡ 7 ቀን ፡ 1941 ዓ. ም. ጃፓን ፡ ፒርል ፤ ሃርበር ፡ በሚባለው ፡ ውቅያኖስ ፡ ላይ ፡ በሚገኘው ፡ ወደብ ፡ ውስጥ ፡ በነበሩት ፡ በተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ መርከቦች ፡ ላይ ፡ ድንገተኛ ፡ አደጋ ፡ ስለጣለችባቸው ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ ደረሰባቸው ።

Bank of Abyssinia No. 1

የተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ ያውሮፓ ፡ ጦርነቱ ፡ ገጥ ሟቸው ፡ ኃይላቸውን ፡ በሌላ ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ ላይ ፡ ይሠሩበት ስለ ፡ ነበረ ፡ ለጊዜው ፡ ጃፓንን ፡ ሊያጠቋት ፡ አልቻሉም ። ነገር ፡ ግን ፡ በኋላ ፡ ፋታ ፡ አግኝተው ፡ ፊታቸውን ፡ ወደ ፡ እሷ ፡ በመለሱ ፡ ጊዜ ፡ ባዳኞች ፡ አኤሮፕላኖች ፡ የታጀቡ ፡ በምብ ፡ ጣይ ፡ አኤሮፕላኖች ፡ እያከታተሉ ፡ በመላክ ፡ ኢንዱስትሪዎቿን ፤ ቤንዚን ፡ የሚያነጥሩ ፡ ፋብሪኮቿን ፤ ወደቦቿንና ፡ መርከቦቿን ፡ እየቀጠቀጡ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ አደረጉባት ።

በመጨረሻም ፡ በምብ ፡ አቶሚክ ፡ የተባለው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ መጀመሪያ ፡ ሂሮሺማ ፤ ቀጥሎ ፡ ናጋሳኪ ፡ በተባሉት ፡ በሁለቱ ፡ የጃፓን ፡ ከተሞች ፡ ላይ ፡ በምብ ፡ አቶሚካቸውን ፡ ጥለው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በማነኛውም ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ታይቶና ፡ ተሰምቶ ፡ ያልታወቀ ፡ ጥፋት ፡ አደረጉባት ። በሂሮሺማ ፡ ከተማ ፡ ብቻ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሀያ ፡ አራት ፡ ሺ ፡ ሰዎች ፡ ሞቱ ። ጃፓኖች ፡ ይህን ፡ እጅግ ፡ የሚያስፈራ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ በቶሎ ፡ እርቅ ፡ ጠይቀው ፡ እጃቸውን ፡ የሰጡ ፡ መሰሉት ፡ አንባቢ ፡ እንዳይታለል ።

ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሂሮሂቶ ፡ አገሩንና ፡ ሕዝቡን ፡ ከጥፋት ፡ ለማ ዳን ፡ ሲል ፡ ሰላም ፡ ለማድረግ ፡ ቆረጠ ። ነገር ፡ ግን ፡ አናሚ ፤ ቶዮ ዳና ፡ ቴሜዙ ፡ የሚባሉት ፡ ብንጉሡ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ለመ ቀመጥ ፡ የተፈቀደላቸው ፡ ሦስቱ ፡ የጦር ፡ መኰንኖች ፡ እርቅ ፡ እና ደርግም ፡ ብለው ፡ አስቸገሩት ። አሜሪካኖችን ፡ ድል ፡ ለማድረግ ፡ በምሥጢር ፡ ያስቀመጥነው ፡ አንድ ፡ የጦር ፡ አቅድ ፡ አለን ፡ እያሉ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እርቅ ፡ እንዳያደርግ ፡ አገሩ ፡ ላይ ፡ ወድቀው ፡ እንደ ፡ ሕፃናት ፡ ልጆች ፡ እንባቸውን ፡ እያፈሰሱ ፡ ይለምኑት ፡ ጀመር ። ለበምብ ፡ አቶሚክ ፡ መመለሻ ፡ የሚሆን ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ሊኖራቸው ፡ ይችል ፡ ኖርዋል ? ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጃፓን ፡ ያማልክት ፡ ልጆች ፡ የሚኖሩበት ፡ የተቀደሰች ፡ አገር ፡ በመሆኗ ፡ ማነኛውም ፡ ሕዝብ ፡ ቢሆን ፡ ድል ፡ ሊያደርጋት ፡ አይችልም ፡ በማ ለት ፡ የሚያምኑበት ፡ ከሃይማኖታቸው ፡ የሠረፀው ፡ እምነት ፡ የሚሆ ነውን ፡ ነገር ፡ ዓይተው ፡ እንዳይፈርዱ ፡ የቷን ፡ ያህል ፡ ዓይናቸውን ፡ እንደ ፡ ሸፍነው ፡ ከመግለጥ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የሚያስረዳው ፡ ነገር ፡

አልነበረም ። በሌላም ፡ በኩል ፡ ጃፓኖች ፡ ጀግንነታቸው ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ ይገልጥልናል ።

ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ ተቆጥቶ ፤ «እኔ ፡ የምፈልገው ፡ የጦር ፡ ጓደኞቼ ፡ ያቀረቡልኝን ፡ የእርቅ ፡ አሳብ ፡ ለመቀበል ፡ ብቻ ፡ ነው ።» ሲል ፡ መለሰላቸው ። ንጉሡ ፡ እርቅ ፡ ለማድረግ ፡ የፋረጠ ፡ መሆኑን ፡ ሲያውቀው ፡ የጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ አናሚ ፡ የሚባለው ፡ እያለቀሰና ፡ እግሩ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ እየተንከባለለ ፡ እርቅ ፡ አታ ድርግ ፡ ሲል ፡ ንጉሡን ፡ ይለምነው ፡ ጀመር ። ንጉሡ ፡ ግን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወገኖች ፡ በገትጋታነት ፡ እርቅን ፡ እምቢ ፡ ብለው ፡ የፈ ጠሩት ፡ ይህ ፡ አስቸጋሪነት ፡ ጥፋትን ፡ ከማስከተል ፡ በቀር ፡ ለምንም ፡ እንደማይጠቅም ፡ ስለተረዳው ፡ የቀረበልኝን ፡ የእርቁን ፡ አሳብ ፡ ተቀ ብያለሁ ፡ ሲል ፡ የላከው ፡ መልስ ፡ ለጦር ፡ ጓደኞቼ ፡ ደረሳቸው ።

በመጨረሻም ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወገኖች ፡ ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ በን ጉሣቸው ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ አይመለሱም ፡ ተብሎ ፡ ተፈርቶ ፡ ስለነበረ ፡ ንጉሡ ፡ እርቁን ፡ በተቀበለበት ፡ ቀን ፡ ሌሊቱን ፡ ተደብቆ ፡ አደረ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የጦር ፡ ወገኖች ፡ በዚህ ፡ በት ልቁ ፡ የሁከት ፡ ሰዓት ፡ እንኳ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸውን ፡ ለመድፈር ፡ አልሞከሩም ። የጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩን ፡ የሱዙኪን ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ግን ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉት ፤ እሱም ፡ ተደብቆ ፡ በመሸሹ ፡ ከሞት ፡ ዳነ ። ንጉሡ ፡ እርቅ ፡ አድርጌያለሁ ፡ ሲል ፡ ላገሩ ፡ ሕዝብ ፡ በማስ ታወቂያ ፡ መግለጡን ፡ የጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ አናሚ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሃራኪሪ ፡ አድርጎ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ሞተ ። ዋና ፡ ዋኖቹም ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶች ፡ እንደዚሁ ፡ በገዛ ፡ እጃቸው ፡ ሞቱ ። ጄኔራል ፡ ታናካ ፡ የሚባለው ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ለጃፓን ፡ ጦር ፡ አዝማች ፡ የነበ ረው ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ እን ዳይሠራ ፡ ሲጠባበቅ ፡ ቆይቶ ፡ ንጉሡ ፡ ደኅና ፡ መሆኑን ፡ ባይኑ ፡ አይቶ ፡ ለንጉሡም ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ከተሰናበተ ፡ በኋላ ፡ እሱም ፡ በመ ጨረሻ ፡ ሃራኪሪ ፡ አድርጎ ፡ ሞተ ።

ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ስንመለከተው ፡ በምብ ፡ አቶሚክ ፡ የተባለው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ባይገኝ ፡ ኖሮ ፡ የጃፓን ፡ ጦርነት ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ ሊያ ልቅ ፡ ኖርዋል ? የሚል ፡ አሳብ ፡ በመንፈሳችን ፡ ውስጥ ፡ ይፈጠራል ።

ጃፓን ፡ በመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ከጦር ፡ ጓደኞች ፡ ጋር ፡
አንድነት ፡ ሆና ፡ ስለተዋጋችና ፡ ስለረዳቻቸው ፡ ደጋፊነታቸውን ፡
አግኝታ ፡ ግዛቷን ፡ እያስፋፋች ፡ ሄዳ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡
በሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ከናዚስቶችና ፡ ከፋሺስቶች ፡ ጋር ፡
ሆና ፡ ስለወጋቻቸው ፡ ድል ፡ በሆነች ፡ ጊዜ ፡ ፈቅደውላትም ፡ ሆነ ፡
ሳይፈቅዱላት ፡ በየጊዜው ፡ የያዘቻቸውንና ፡ የኤኮኖሚ ፡ ጉልበቷን ፡
የዘረጋችባቸውን ፡ ማንዱሹሪ ፣ ኮሪ ፣ ኩዋንቱንግ ፣ ካራፉቶ ፣ ፎር
ሞዝ ፣ ሪውኪው ፣ ካሮሊን ፣ ማርሻል ፣ ማሪያን ፣ ፓሎ ፣ ሌሎችም ፡
እነዚህን ፡ የመሰሉትን ፡ አገሮችና ፡ ደሴቶች ፡ እንድትለቅና ፡ የራሷ ፡
አገሮች ፡ በሆኑት ፡ ደሴቶች ፡ ብቻ ፡ እንድትወሰን ፡ አስገደዷት ።
እነዚህም ፡ የለቀቀቻቸው ፡ አገሮች ፡ በጣም ፡ የሚጠቅሟት ፡ ነበሩ ።
ከማንድሹሪ ፡ የብረታ ፡ ብረት ፡ ማዕድኖች ፣ ከኮሪ ፡ ሩዝ ፡ በብዙ ፣
ከካራፉቶ ፡ ቤንዚን ፣ ከፎርሞዝ ፡ ከምፋር ፣ ታገኝ ፡ ነበር ። ከዚህም ፡
በቀር ፡ አሜሪካኖች ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የምትሠራባቸውን ፡ ኢንዱስት
ሪዎቿን ፡ ነቅለው ፡ ወስደውባታል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጦርነቱ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ በተከተሉት ፡ ዓመ
ታቶች ፡ ውሥጥ ፡ አሜሪካኖች ፡ ከመስኮብ ፡ ጋር ፡ የሚጋጩበት ፡
የፖለቲካ ፡ ሁከት ፡ እያሰጋቸው ፡ ስለሄደ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ቂማቸው ፡ እየ
በረደ ፡ መጩቆናቸውን ፡ ትተው ፡ በጃፓን ፡ በኩል ፡ ያላቸውን ፡
ፖለቲካ ፡ ለውጠውታል ።

የጃፓንን ፡ ሕዝብ ፡ መንፈስ ፡ ወደ ፡ ዴሞክራቲክ ፡ አስተዳደር ፡
ለመለወጥ ፡ ወጥነውት ፡ የነበረው ፡ ሥራ ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡
ስለተረዱት ፡ ችላ ፡ ብለውታል ። እንደዚሁም ፡ ይህቺን ፡ አገር ፡
እንደጠላት ፡ መቍጠራቸውን ፡ እየተዉ ፡ ጃፓን ፡ የንግድ ፡ ሥራዋን ፡
እንደ ፡ ቀድሞው ፡ እንድታስፋፋና ፡ በኤኮኖሚም ፡ በኩል ፡ ከወደቀች
በት ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ እንድትነሣ ፡ በሁሉ ፡ ጊዜ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መን
ገድ ፡ ሲረዷት ፡ ይታያሉ ።

አሜሪካኖች ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ከጃፓን ፡ አገር ፡ ሲገቡ ፡
ጃፓን ፡ ባሁኑ ፡ ጦርነት ፡ የወጋቻቸው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ ሕዝቡ ፡
ትውልዳችን ፡ ካማልክት ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ በማመናቸው ፡
ይህን ፡ የመሰለ ፡ (የፋናቲክነት ፡ ) መንፈስ ፡ በልባቸው ፡ ስላሳደሩ ፡

ነው ፡ ይህንኑም ፡ ከልባቸው ፡ ነቅሎ ፡ መጣል ፡ ያስፈልጋል ፡ ብለው ፡
አሜሪካኖች ፡ አሰቡ ። ስለዚህ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሂሮሂቶ ፡ እኔ ፡
ያምላክ ፡ ልጅ ፡ አይዶለሁም ፤ ወይም ፡ ያምላክነት ፡ ትውልድ ፡
የለኝም ፡ ብሎ ፡ ለሕዝቡ ፡ እንዲያስታውቅ ፡ አሜሪካኖች ፡ አዘዙት ።
እሱም ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ አምላክነቱን ፡ ለሕዝቡ ፡ ባደረገው ፡ ንግግር ፡
ክዶ ፡ የድል ፡ አድራጊዎቹን ፡ አሳብ ፡ ወዲያው ፡ ፈጸመ ። ነገር ፡ ግን ፡
ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ በሚገልጠው ፡
ሁኔታ ፡ ድል ፡ አድራጊዎቹ ፡ የጣሉበት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጭቆና ፡
እየቀለለለት ፡ ሲሄድ ፤ በጠላት ፡ ይዞታ ፡ ውስጥ ፡ በመሆኑ ፡ ከወደ
ቀበት ፡ የጦር ፡ አስተዳደር ፡ እየወጣ ፡ ወደ ፡ ሰላማዊ ፡ ኑሮ ፡ በሚተ
ላለፍበትም ፡ መጠን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ያምላክ ፡
ልጅ ፡ አድርጎ ፡ መቁጠሩን ፡ ያልተወ ፡ መሆኑን ፡ በሚያደርገው ፡
የፍቅርና ፡ የአክብሮት ፡ አገላለጥ ፡ መስክሮዋል ። አሜሪካኖችም ፡
ንጉሠ ፡ ነሥቱም ፡ ሆነ ፡ ሕዝቡ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በኩል ፡ እንዳሸ
ፋብቸው ፡ ተረዱት ። ቦምብ ፡ አቶሚካቸው ፡ የሂሮሺማንና ፡ የናጋሳ
ኪን ፡ ከተማዎች ፡ እንዳልነበሩ ፡ አድርጎ ፡ ሲያፈርሳቸው ፡ ጃፓኖች ፡
ያማልክት ፡ ተወላጆች ፡ ናቸው ፡ የሚለውን ፡ በጃፓኖች ፡ መንፈስ ፡
ውስጥ ፡ ተቀርጾ ፡ የሚኖረውን ፡ እምነት ፡ ግን ፡ ሊያጠፋው ፡ ያል
ቻለ ፡ መሆኑ ፡ ተገለጠ ። ጃፓኖች ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ ያንድነ
ታቸው ፡ ማሰሪያ ፤ የነፃነታቸው ፡ ሕይወትና ፡ የክብራቸው ፡ አክሊል ፡
መሆኑን ፡ ስለሚያውቁ ፡ ይህንን ፡ የኃይላቸው ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡
የባሕሪያቸውን ፡ ሀብት ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ በማናቸውም ፡
ዓይነት ፡ ስብከት ፡ እንዲገፍፋቸው ፡ አልፈቀዱም ።

አሁን ፡ በቅርብ ፡ ቀን ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ ዘመን ፡ በሚለውጥበት ፡
የዓመት ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ ለንግሥቲቱ ፡ እንኳን ፡ ከዘመን ፡
ወደ ፡ ዘመን ፡ ያሸጋገራችሁ ፡ ለማለት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡
ከአራት ፡ መቶ ፡ ሺ ፡ በላይ ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ተሰብስበው ፡ ስለሄዱ ፡
ከሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ አሥራ ፡ ስድስት ፡ ሰዎች ፡ በግፊያው ፡
ውስጥ ፡ እየተረገጡ ፡ እንደሞቱና ፡ አርባ ፡ ሰዎች ፡ እንደቆሰሉ ፡ የዓ
ለም ፡ ጋዜጣዎች ፡ ጽፈውታል ። ይህም ፤ ነገር ፡ የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡
ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ያለው ፡ ፍቅር ፡ ከዚህ ፡ ካሁኑ ፡ ጦርነት ፡ በኋ

ላም ፡ ይበልጥ ፡ እየጋለ ፡ እንጅ ፡ እየቀዘቀዘ ፡ እንዳልሄደ ፡ የሚገ
ልጥ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ። ለንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ ያላቸው ፡ አክብሮትና ፡
ፍቅር ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ በመሆኑ ፡ የኢትዮጵያና ፡ የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡
በዚህም ፡ በኩል ፡ ባህሪያቸው ፡ በጣም ፡ ይመሳሰላል ። የኢትዮጵያ ፡
ሕዝብ ፡ ወደፊትም ፡ በሥልጣኔ ፡ እየተራመደ ፡ በሚሄድበት ፡ መጠን ፡
ይህ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ያለው ፡ ፍቅር ፡ እንደ ፡ ጃፓን ፡ ሕዝብ ፡
ሁል ፡ ጊዜ ፡ እየጋለ ፡ እንዲሄድ ፡ እንመኛለን ።

በዛሬ ፡ ጊዜ ፡ በኢንቴርናሲዮናል ፡ ግንኙነቶች ፡ ውሥጥ ፡ በመ
ንግሥታት ፡ መካከል ፡ ሁከትንና ፡ ጭቅጭቅን ፡ የሚፈጥሩ ፡ ጦርነት
ንም ፡ የሚያስነሡ ፡ ሁለት ፡ ጉዳዮች ፡ ናቸው ። አንደኛ ፡ በኢንዱ
ስትሪ ፡ ብርቱ ፡ የሆኑ ፡ ሕዝቦች ፡ ከፋብሪኮቻቸው ፡ ውሥጥ ፡ እየ
ተሠሩ ፡ የሚወጡትን ፡ ዕቃዎች ፡ የሚሸጡበትን ፡ቦታ ፡ እንዲያገኙ ፡
ይፈልጋሉ ። ሁለተኛ ፡ የሕዝባቸው ፡ ቁጥር ፡ እየበዛ ፡ ሲሄድ ፡ አገ
ራቸው ፡ ግን ፡ ጠባብና ፡ ደሀ ፡ በመሆኗ ፡ ሕዝባቸውን ፡ የሚያፈሱ
በት ፡ መሬት ፡ የሚያገኙበትን ፡ መንገድ ፡ ይፈልጋሉ ። ስለዚህ ፡ ኢት
ዮጵያ ፡ የኃይለኞች ፡ መከራከሪያና ፡ መወዳደሪያ ፡ ሥፍራ ፡ እንዳት
ሆን ፡ በቶሎ ፡ በኢንዱስትሪ ፡ በኩል ፡ ራሷን ፡ የቻለች ፡ ሆና ፡ የሚያስፈልጋ
ትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ባገርዋ ፡ ውሥጥ ፡ የምትሠራ ፡ መሆን ፡ ይገባታል ።

ሂትለር ፡ ሙሶሊኒና ፡ ጃፓን ፡ ጦርነት ፡ ያነሡት ፡ እነዚህን ፡
ሁለት ፡ ችግሮች ፡ ለማሻሻል ፡ ሲሉ ፡ ነው ። አንድ ፡ የፈረንሣይ ፡
ሊቅ ፡ ዦርዥ ፡ ዱሃሜል ፡ የሚባለው ፡ አሁን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የጃ
ፓንን ፡ አገር ፡ ከጎበኘ ፡ በኋላ ፡ በጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ ውሥጥ ፡ ይህ
ንኑ ፡ ጉዳይ ፡ ጠቅሶ ፡ ጃፓን ፡ የሕዝቧ ፡ ቁጥር ፡ በላይ ፡ በላዩ ፡
እየጨመረ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ ያለው ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ትልቅ ፡
ችግር ፡ መፍጠሩን ፡ አሳስቧል ። ችግርዋም ፡ እየበረታ ፡ ከመሄዱ ፡
የተነሣ ፡ ጦርነት ፡ አንስታ ፡ ዓለምን ፡ ለመበጥበጥ ፡ በቃች ፤ በዚ
ሁም ፡ ሳይቀናት ፡ ስለቀረ ፡ አሁን ፡ የምታደርገው ፡ ብታጣ ፡ ወደ
ጥንቱ ፡ ልማዷ ፡ ተመልሳ ፡ ሕፃናት ፡ እንዳይፀነሱ ፡ ወይም ፡ እንዳ
ያድጉ ፡ ለማድረግ ፡ አስባለች ፡ እየተባለ ፡ መወራቱን ፡ እየገለጠ ፡
ይህ ፡ ለሥልጣኔ ፡ መንፈስ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ መጥፎ ፡ ልማድ ፡ በው
ነት ፡ ይደረጋል ፡ ተብሎ ፡ እንደማይታሰብ ፡ ካስገነበዘ ፡ በኋላ ፡ ይል

ቅስ ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ በተባበሩት ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ ቀርቦ ፡ ቢጠና ፡ በጣም ፡ የተሻለ ፡ መሆኑን ፡ አመልክቷል ። ስለ ፡ ጃፓን ፡ ታሪክ ፡ ከዚህ ፡ የተረፈውን ፡ አንባቢ ፡ ወደፊት ፡ በሚታተመው ፡ የዓለም ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ሊያገኘው ፡ ይችላል ።

## ሊቴራቱር ፡ በጃፓን ፡ አገር ።

አሁን ፡ እዚህ ፡ ጣልቃ ፡ አግብተን ፡ ስለ ፡ ሌቴራቱር ፡ ጥቂት ፡ እንናገራለን ።

ጃፓኖች ፡ በሌቴራቱር ፡ በኩል ፡ ባገራቸው ፡ ውስጥ ፡ በያይነቱ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍትና ፡ ጋዜጦች ፡ የሚጽፉ ፡ አያሌ ፡ ደራስያን ፡ ያሏቸው ፡ ከመሆናቸው ፡ በላይ ፡ ባውሮፓም ፡ ሆነ ፡ ባሚሪካ ፡ ጥቅሙና ፡ ዋጋው ፡ የታወቀ ፤ የተመሰከረለት ፡ ማንኛውም ፡ መጽሐፍ ፡ ታትሞ ፡ ወጥቶ ፡ አገራቸው ፡ ውስጥ ፡ ወዲያው ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ በማይሞላ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በጃፓን ፡ ቋንቋ ፡ ተተርጕሞ ፡ ለሕዝቡ ፡ ይደርሰዋል ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሚተረጕሙት ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ተማሪዎች ፡ ካታሚዎቹ ፡ ጋር ፡ እየተስማሙ ፡ ነው ። ብዙዎቹም ፡ ተማሪዎች ፡ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ ሥራ ፡ እየሠሩ ፡ ለኑሮዋቸው ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ገንዘብ ፡ በዩኒቨርሲቲው ፡ ውስጥ ፡ እንዳሉ ፡ ያገኛሉ ።

ጃፓኖች ፡ በየውጭው ፡ አገሮች ፡ የሚታተሙትን ፡ መጻሕፍት ፡ ለሕዝባቸው ፡ እንዲደርሰው ፡ ለማድረግ ፡ ሲሉ ፡ በራሳቸው ፡ ቋንቋ ፡ ሲያስተረጕሙት ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ደራስያን ፡ ለደራሲነታቸው ፡ መብት ፡ የሚታሰብላቸውን ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ ቢከፍሉ ፡ ኖሮ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ወጭ ፡ ማድረግ ፡ እንደሚያስፈልጋቸው ፡ ተረድተውት ፡ ከዚህ ፡ ጉዳት ፡ ለመዳን ፡ ሲሉ ፡ ስለ ፡ "COPYRIGHT" መብት ፡ ማንኛውንም ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ውል ፡ አልተፈራረሙም ። ስለዚህ ፡ ማንኛውም ፡ የጃፓን ፡ ሰው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋዎች ፡ የታተሙትን ፡ መጻሕፍት ፡ ቢተረጕም ፡ ስለ COPYRIGHT ፡ መብት ፡ የሚሰጋበት ፡ ነገር ፡ የለም ።

እኛም ፡ ባገራችን ፡ ይህንኑ ፡ ምሳሌ ፡ ብንከተል ፡ ጥቅማችንን ፡ ይደግፍልናል ። ስለ ፡ "COPYRIGHT" ጉዳይ ፡ እጃችንን ፡ አስሮ ፡

በውጭ ፡ አገሮች ፡ የሚጎርፉትን ፡ የዕውቀትና ፡ የትምህርት ፡ መጻሕፍት ፡ እየተረጐምን ፡ ጥበብ ፡ ለተጠማው ፡ ሕዝባችን ፡ እንዳ ሰንጠው ፡ ከልክሉ ፡ ሊጎዳን ፡ ከሚችል ፡ ከማንኛውም ፡ የኢንቴርና ሲዮናል ፡ ስምምነት ፡ ውስጥ ፡ እንዳንገባ ፡ መጠንቀቅ ፡ ያስፈልገናል ። በኡኔስኮ ፡ (U.N.E.S.C.O.) ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አባል ፡ ሳትሆን ፡ መቅረቷ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ጠቃሚ ፡ ታል ። ለወደፊቱም ፡ በሚ ደረጉት ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ አስፈላጊው ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲደረግ ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሊያስብበት ፡ ይገባል ። ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ "RETOUR DU JAPON" በሚል ፡ አርእስት ፡ ከ JOHN MORRIS የተጻፈውን ፡ መጽሐፍ ፡ መመልከት ፡ ነው ።

በመተርጐም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ጃፓኖች ፡ የውጭ ፡ አገሮችን ፡ መጻሕፍት ፡ ከደራሲው ፡ ሳያስፈቅዱ ፡ በገራቸው ፡ ውሥጥ ፡ እያተሙ ፡ ያወጧቸዋል ።

ከፍ ፡ ብለን ፡ የጠቀስነው ፡ ጸሐፊ ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ምሳሌ ፡ ይሰጣል ። ስመ ፡ ጥሩው ፡ የእንግሊዝ ፡ ደራሲ ፡ ቤርናር ፡ ሾ ፡ የሚባለው ፡ ወደ ፡ ጃፓን ፡ አገር ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ በቶ ኪዮ ፡ የሚገኘውን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ዩኒቬርሲቲ ፡ ሲጎበኝ ፡ ያስ ተናገዱት ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ የታተሙት ፡ የእሱ ፡ መጻሕፍቶች ፡ የተደረደሩበትን ፡ ቦታ ፡ አሳዩት ። እሱም ፡ ይህንኑ ፡ ተመልክቶ ፡ አታሚዎቹ ፡ መጻሕፍቶቹን ፡ ለማሳተም ፡ የፈቀደላቸው ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ስለ ፡ ደራሲውም ፡ መብት ፡ ገንዘቡን ፡ የሚቀበለው ፡ ሰው ፡ ማ. መሆኑን ፡ በጠየቃቸው ፡ ጊዜ ፡ ጃፓኖች ፡ ነገሩ ፡ እንዳ ልገባቸው ፡ ሆነው ፡ መልስ ፡ ሳይሰጡት ፡ ቀሩ ።

## መደምደሚያ ።

እንግዲህ ፡ የጃፓንን ፡ ታሪክ ፡ አንብበን ፡ ከጨረስን ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ በሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርቶ ፡ የነበረው ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ቆራጥ ፡ በሆነ ፡ መንፈስ ፡ ተነሥቶ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሥራ በመሥራቱ ፡ አገሩን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ከትልቅ ፡ ቦታ ፡ አደረሳት ፤ እኛስ ፡ ላገራችን ፡ የሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ምን ፡ ማድ

ረግ ፡ ይገባናል ? የሚል ፡ አሳብ ፡ ከፊታችን ፡ መደቀኑ ፡ የማይቀር ፡ ነገር ፡ ነው ።

ይልቁንም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ከአክሱም ፡ መንግሥት ፡ ጀምሮ ፡ እስካሁን ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ የነበረባቸውን ፡ ችግር ፡ እየተመለከትን ፡ ያገራቸውንና ፡ የሕዝባቸውን ፡ ነፃነትና ፡ ክብር ፡ ጠብቀው ፡ ለመኖር ፡ የገጠማቸውን ፡ ፈተናና ፡ ትግል ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ድካምና ፡ ብርታት ፡ አሸንፈው ፡ ዛሬ ፡ እኛ ፡ የምንከራበትን ፡ መብት ፡ እንዳወረሱን ፡ ስንመረምረው ፡ ጃፓኖች ፡ ለነፃነታቸው ፡ ጥበቃ ፡ በየዘመኑ ፡ ከሠሩት ፡ የጀግንነት ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ ይመሳሰላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የአውሮፓ ፡ ሥልጣኔ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ እየተስፋፋች ፡ ሄዳ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ወደ ፡ ጃፓን ፡ አገሮች ፡ ባንድ ፡ ዘመን ፡ ከገባች ፡ በኋላ ፡ ጃፓኖች ፡ ዘመናችን ፡ የፈጠረውን ፡ አዲስ ፡ የጥበብ ፡ መንፈስ ፡ በሚያስደንቅ ፡ ቅልጥፍና ፡ ተቀብለው ፡ ከባሕሪያቸው ፡ ጋር ፡ ስላዋሀዱት ፡ በቅጽበት ፡ ተወርውረው ፡ ከታላላቆች ፡ መንግሥታት ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ሆኑ ። ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ዳተኛ ፡ ሆና ፡ በመገናኗ ፡ አውሮፓውያን ፡ አገርዋ ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ የሥልኔን ፡ ጥበቦች ፡ ሳትወርስ ፡ ስለዘገየች ፡ ያፄ ቴዎድሮስ ፤ ያፄ ፡ ዮሐንስና ፡ ያፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመናት ፡ በከንቱ ፡ አለፉ ፤ በእነዚህ ፡ ዘመናት ፡ ጠንክራ ፡ ሠርታ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ አሁን ፡ ያለፈው ፡ የፋሺስት ፡ የወረራ ፡ አደጋ ፡ ባልደረሰባት ፡ ነበር ።

አሁንም ፡ አገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከፍ ፡ ወይም ፡ ዝቅ ፡ ለማለት ፡ የምትበቃው ፡ እኛ ፡ ልጆቿ ፡ የምንሰጠው ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ የሚጠቅም ፡ ወይም ፡ የማይረባ ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ መጠን ፡ ነው ። አሳባችንን ፡ የምናውለው ፡ በፍሬ ፡ ቢስ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ አገራችን ፡ ከፍ ፡ ትላለች ፡ ብለን ፡ ለመመኘት ፡ ምንም ፡ መብት ፡ የለንም ። ነገር ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ በዘመናችን ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ደረጃ ፡ የያዙት ፡ ሕዝቦች ፡ አገራቸውን ፡ ለመጥቀም ፡ ሲሉ ፡ የሚሠሩትን ፡ ሥራ ፡ አብነት ፡ በማድረግ ፡ ላንድ ፡ አገርና ፡ ላንድ ፡ ሕዝብ ፡ ዋኖቹ ፡ ጉዳዮች ፡ ምንድናቸው ? ብለን ፡ እነሱን ፡ እየመረመርን ፡ የተሻለውን ፡ መልካም ፡ መንገድ ፡ ይዘን ፡ ለመሥራት ፡ ቆርጠን ፡

ብንነሣ ፡ መጭው ፡ ጊዜ ፡ የክብር ፤ የኃይልና ፡ የሲሳይ ፡ ዘመን ፡
ሆኖ ፡ ይጠብቀናል ።

አባቶቻችን ፡ ይህቺን ፡ የምንከራበትን ፡ አገር ፡ ከነፃነቷና ፡ ከክ
ብርዋ ፡ ጋር ፡ እንዳቆዩን ፡ ሁሉ ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ ባስተዋይነት ፡ ብን
ሠራ ፡ ለልጆቻችን ፡ የሚመኩበትን ፡ ሥራ ፡ ሠርተን ፡ አገራችን ፡
ከፍ ፡ ብላ ፡ የምትታይበትን ፡ ታሪክ ፡ እናወርሳቸዋለን ። ሰው ፡ አላፊ ፤
ጠፊ ፤ ሟች ፡ ነው ። አገርና ፡ ትውልድ ፡ ግን ፡ ዘለዓለም ፡ ይኖራሉ ።

ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ የዓለምን ፡ አካሄድ ፡ ስንመለከተው ፡ በሁለት ፡
ዓይነት ፡ ነገሮች ፡ ይመሰላል ። አንድ ፡ ሰው ፡ በበቅሎ ፡ ተቀምጦ ፡
ጧት ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ከቃቂ ፡ ከአኤሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ተነሥቶ ፡
ወደ ፡ ምዕዋ ፡ ይጓዛል ። በዚያው ፡ ሰዓት ፡ ከዚያው ፡ ቦታ ፡ አንድ ፡
ሌላ ፡ ሰው ፡ በአኤሮፕላን ፡ ተሳፍሮ ፡ ይሄዳል ። በበቅሎ ፡ የሚጓ
ዘው ፡ ሰው ፡ ከሁለት ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ ለገዳዲ ፡ ይደርሳል ፤ በአኤ
ሮፕላን ፡ የሄደው ፡ ሰው ፡ ግን ፡ በዚያው ፡ ሰዓት ፡ አሥመራ ፡
ይገባል ። በበቅሎ ፡ የሚገሠግሠው ፡ መንገደኛ ፡ ማታ ፡ ምስር ፡ ምድር ፡
ሲገባ ፡ በአኤሮፕላን ፡ የሄደው ፡ ሰው ፡ ከይሮ ፡ ይገባል ። በበቅሎ ፡ የሚ
ሄደው ፡ ሰው ፡ ወገቡ ፡ ደቆ ፤ ጭኑ ፡ ጓጉሎ ፡ እግሩ ፡ ዝሎ ፡ ደክሞት ፡ ምስር ፡
ምድር ፡ ሰፍሮ ፡ ከተኛ ፡ በኋላ ፡ ጧት ፡ ጉዞውን ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡
ሊቀጥል ፡ ሲነሣ ፡ በአኤሮፕላን ፡ የተሳፈረው ፡ ሰው ፡ ሲሄድ ፡
ከዋለ ፡ በኋላ ፡ ማታ ፡ ምንም ፡ ድካም ፡ ሳይሰማውና ፡ የመልኩ ፡
ወዝ ፡ ሳይለወጥ ፡ እንቅልፍ ፡ መተኛትም ፡ ምንም ፡ ያሀል ፡ ሳያስ
ፈልገው ፤ ቢያስፈልገውም ፡ ጥቂት ፡ ተኝቶ ፡ ጧት ፡ ዓይኑን ፡ ሲገ
ልጥ ፡ ፓሪስ ፡ ገብቶ ፡ ይገኛል ። ይህ ፡ ነገር ፡ አሁን ፡ ላለንበት ፡
ዘመን ፡ ትልቅ ፡ ትምህርት ፡ የሚገኝበት ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። አገራችን ፡
ኢትዮጵያ ፡ ባመት ፡ ባመቱ ፡ በሥልጣኔ ፡ በኩል ፡ ስለምን ፡ አትራ
መድም ? ብለን ፡ እናስባለን ። ምክንያቱም ፡ ምን ፡ እደሆነ ፡ አይገ
ባንም ።

ነገር ፡ ግን ፡ አስተውለን ፡ ብንመለከተው ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ በሀሳብ ፡
ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሥልጣኔ ፡
ቶሎ ፡ ወደፊት ፡ ለመራመድ ፡ የማትችለው ፡ በገንዘብ ፡ ምክንያት ፡
ነው ፤ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ቢኖራት ፡ ኖሮ ፡ ብዙ ፡ መንገዶች ፡ እየሠራች ፡

ብዙ ፡ ፋብሪካዎች ፡ እያቋቋመችና ፡ ሌላም ፡ አስፈላጊዎች ፡ የሆኑ ትን ፡ ነገሮች ፡ እየገዛች ፡ እርምጃዋን ፡ ለማፋጠን ፡ ትችል ፡ ነበር ፡ ይላሉ ። ይህ ፡ ነገር ፡ በከፊል ፡ እውነትን ፡ የያዘ ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ ገንዘብ ፡ አይደለም ። ገንዘብ ፡ ሰው ፡ የሠራው ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠረው ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ሰው ፡ ደግሞ ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ ለመሥራት ፡ የሚችለው ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰጠው ፡ ጸጋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የራሱ ፡ ሥራ ፡ በሆነው ፡ ገንዘብ ፡ በሚባ ለው ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ሰው ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ ሊሠራ ፡ የሚችልበት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተሰጠው ፡ መሣሪያ ፡ አሳብ ፡ ይባላል ። በዓለም ፡ ላይ ፡ የተሠሩትን ፡ ታላላቅ ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ በታሪክ ፡ ስንመለከታቸው ፡ ተመ ርተው ፡ የተገኙት ፡ በሀሳብ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ በገንዘብ ፡ አይደለም ። ሌላ ውን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ትተን ፡ በሁኑ ፡ ዘመን ፡ ከሰው ፡ ልጅ ፡ የተገኘውን ፡ አስደናቂ ፡ ሥራ ፡ ሆኖ ፡ የተቆጠረውን ፡ በምብ ፡ አቶሚክን ፡ ብን መለከተው ፡ እንደነ ፡ አይንሽታይን ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ፒየር ፡ ኪውሪ ፡ ከመሰሉት ፡ ሊቃውንት ፡ አንጎል ፡ ፈልቆ ፡ ወጣ ፡ እንጅ ፡ እንደነ ፡ ሮክፌለር ፡ የመሰሉት ፡ ሀብታሞች ፡ በገንዘባቸው ፡ ገዝተው ፡ ለዓለም ፡ አላበረከቱትም ። ስለዚህ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ዋና ፡ ሀብቱ ፡ አሳብ ፡ ነው ። ገንዘብንም ፡ የፈጠረው ፡ የሰው ፡ አሳብ ፡ ነው !

ከፍ ፡ ብለን ፡ እንዳመጣነው ፡ ምሳሌ ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ታላ ላቅ ፡ ሕዝቦች ፡ የሆኑት ፡ እንደዚያ ፡ በአኤሮፕላን ፡ እንደተሳፈረው ፡ ሰው ፡ አሳባቸው ፡ በፍጥነት ፡ እየገሰገሰ ፡ ሩቅ ፡ ቦታ ፡ ደርሶ ፡ ዓለ ምን ፡ እየዞረ ፡ ሥራውን ፡ ሲፈጽም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ግን ፡ አሳባቸው ፡ ከሚኖሩበት ፡ አገር ፡ ወይም ፡ አውራጃ ፡ ሳይወጣ ፡ ቀኑ ይመሻል ። ስለዚህ ፡ ባሳብ ፡ የተቀደሙ ፡ በመሆናቸው ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርተው ፡ ይኖራሉ ። ከእነዚህ ፡ ሕዝቦች ፡ አንዱ ፡ እኛ ፡ ነን ።

በንብረታችን ፤ ፀግል ፡ ኑሮአችን ፤ በገዛ ፡ አገራችን ፡ ውስጥ ፡ ባሉ ብን ፡ ጉዳዮች ፡ ብቻ ፡ አሳብችን ፡ ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ እየተጠመደ ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ በመጨቃጨቅ ፤ በመናሸር ፤ በመጣላትና ፡ በመታ ገል ፡ ብዛት ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ያሳባችንን ፡ ጉልበት ፡ ስንጨርስ ፡ እን ውልና ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ በመሸ ፡ ቁጥር ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ድካም ፡ እየ ተሰማን ፡ እንተኛለን ። ሌሎቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ግን ፡ ዕውቀትና ፡ ጥበብ ፡

የተባለውን ፡ ዘመናዊ ፡ ጸጋ ፡ ላሳባቸው ፡ መሳሪያ ፡ አድርገው ፡ ረጅም ፡
በሆነው ፡ አስተያየታቸው ፡ ዓለምን ፡ እየዞሩ ፡ ሰነፎች ፡ የሆኑትን ፡
ሕዝቦች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እያጣሉ ፤ ሀብታቸውን ፡ ወደቤታቸው ፡
እየሰበሰቡ ፡ ያገባሉ ። የሰነፎቹ ፡ ሕዝቦች ፡ ዘር ፡ እየጠፉ ፤ እንዲሄ
ድና ፡ የነሱ ፡ ትውልድ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ከዋክብት ፤ እንደ ፡
ባሕር ፤ አሸዋ ፡ እየበዛ ፡ ሄዶ ፡ ዓለምን ፡ እንዲወርሳት ፡ ለማድረግ ፡
የሚችሉበትን ፡ መንገድ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ተግተው ፡ ይሠራሉ ። እስከ
ዚያም ፡ ድረስ ፡ በሄዱበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ የተከበሩና ፡ የተፈሩ ፡ ናቸው ።
ይህንንም ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ የሚያከናውኑት ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ መንፈስ ፡
እየተመሩ ፡ ስለሆነ ፡ ድካም ፡ አይሰማቸውም ። ሁልጊዜ ፡ የሚታዩት ፡
ሲዘፍኑና ፡ ሲጨፍሩ ፡ ነው ፤ ተመልከች ፡ የሆነ ፡ ሰውም ፡ ምን ፡
ጊዜ ፡ ነው ፡ ሥራቸውን ፡ የሚሠሩ ፡ ብሎ ፡ ያስባል ። በጭሩ ፡ ድካም ፡
ሳይሰማው ፡ ጧት ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ተነሥቶ ፡ እየተጫወተ ፡ ከተጓዘ ፡
በኋላ ፡ በማግሥቱ ፡ ጧት ፡ ፓሪስ ፡ የሚገባውን ፡ መንገደኛ ፡ ሰው ፡
ይመስላሉ ። ያ ፡ በበቅሎ ፡ የሚጓዘው ፡ ምስኪኑ ፡ መንገደኛ ፡ ግን ፡
ካሰበበት ፡ ቦታ ፡ ከምፅዋ ፡ ለመድረስ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ስለሚያስፈል
ገው ፡ በአኤሮፕላን ፡ የሄደው ፡ ሰው ፡ መላ ፡ ዓለምን ፡ ዞሮ ፡ ከዋ
ሽንግቶን ፤ ከቶኪዮ ፡ ከፔኪን ፤ ከኒውዴልሂ ፤ ከሲድኔ ፤ ከሞስኮ ፤
ከካይሮ ፤ ደርሶ ፡ የአሜሪካንን ፤ የጃፓንን ፤ የሺናን ፤ የሕንድን ፤ የአ
ስትራሊን ፤ የግብፅን ፤ አገሮች ፡ ከጎበኘ ፡ በኋላ ፡ ጉዳዩን ፡ ሁሉ ፡
ፈጽሞ ፡ ተመልሶ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ይገባል ።
ስለዚህ እኛ የተቀደምነው በማመላለሻ መሣሪያ ብቻ ሳይሆን
ባሳብም ጭምር ነው:: አገራችን ሀብታም ስለሆነች ብናውቅበት
የምንፈልገውን ያህል ብዙ ገንዘብ ለማግኘት እንችላለን:: ያለንን
ፍቅር ለመግለጥ የምንችለው የዘመናችን ሕዝቦች የሚዋጉበትን
የጦር መሣሪያ ለመሥራት የምንችልበት ዘዴ ፊልገን በማግኘት
መሆኑን ገና አልተረዳነውም::
በምንማረው ፡ ትምህርት ፡ ከዘመናዊው ፡ ሥልጣኔ ፡ ልንፈልገው ፡
የሚገባን ፡ ነገር ፡ የሚጠቅመንን ፡ ብቻ ፡ ለማግኘት ፡ ስለሆነ ፡ ራሳ

ችንን ፡ የቻልን ፡ መሐንዲሶች ፤ የፋብሪካ ፡ መኪና ፡ አስኪያጆች ፤ ሐኪሞች ፤ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ አዋቂዎች ፤ ሆነን ፡ ላገራችን ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ራሳችንን ፡ ችለን ፡ በዕድ ፡ ሳናስገባ ፡ ለመሥራት ፡ የምንችል ፡ ሆነን ፡ እንድንገኝ ፡ ያሻል ። በጭሩ ፡ ላንድ ፡ መንግሥትና ፡ ላንድ ፡ ሕዝብ ፡ ኑሮ ፡ አስፈላጊዎች ፡ የሆኑትን ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ከነርሶች ፡ እኩል ፡ በዘመናዊው ፡ ጥበብ ለማከናወን ፡ የምንችልበትን ፡ መንገድ ፡ መፈለግ ፡ አለብን ። እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ለመፈጸም ፡ የምንችለው ፡ በማሰብ ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ እንወቀው ። እንደርስበታለ ፡ የማለት ፡ እምነት ፡ በልባችን ፡ አሳድረን ፡ ባሳባችን ፡ ኃይለኞች ፡ ከሆንን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ልንፈጽመው ፡ እንችላለን ። አሳባችንን ፡ ኃይለኛ ፡ ልናደርገው ፡ የምንችለው ፡ ደግሞ ፡ ጉልበታችንን ፡ አርበና ፡ ለሌለው ፡ ነገር ፡ ማባከናችንን ፡ ትተን ፡ እነዚህን ፡ ላገራችን ፡ ዋኖች ፡ ጉዳዮች ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ ባሳባችን ፡ ውስጥ ፡ በማውጣትና ፡ በማውረድ ፡ የሚበጀውንም ፡ መንገድ ፡ ለማግኘት ፡ ስንል ፡ ለእነዚሁ ፡ ጉዳዮች ፡ አዲስ ፡ አሳብ ፡ እየሰጡን ፡ ሊረዱን ፡ የሚችሉትን ፡ መጻሕፍት ፡ በማንበብ ፡ ነው ። ስንፍና ፡ ካላሸነፈን ፡ በቀር ፡ የምንፈልገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በመጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ እናገኘዋለን ። ትንኝ ፡ (ቢምቢ ፡ ) ምግቧን ፡ ከአበባ ፡ ላይ ፡ ቀስማ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የወባን ፡ በሽታና ፡ ሞትን ፡ ትሰጠዋለች ። ንብ ፡ ደግሞ ፡ በበኩሏ ፡ ከአበባ ፡ ላይ ፡ ምግቧን ፡ ቀስማ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ጣፋጭ ፡ የሆነውን ፡ ማር ፡ ትሰጠዋለች ። ሰዎችም ፡ እንደዚሁ ፡ በመጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ሊጠፉበት ፡ ወይም ፡ ሊለሙበት ፡ የሚችሉበትን ፡ ትምህርት ፡ ስለሚያገኙበት ፡ የሚጠቅማቸውንና ፡ የሚጎዳቸውን ፡ እየመረጡ ፡ መቅሰም ፡ ይህ ፡ ሕሊናቸውን ፡ ዳኛ ፡ አድርገው ፡ ሊፈጽሙት ፡ የሚገባ ፡ ተግባር ፡ ነው ።

ሰው ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ሊፈጽም ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ምሳሌ ፡ ወይም ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ አብነት ፡ ሆኖ ፡ ሊያገለግለው ፡ የሚችል ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሲያገኝ ፡ ያሰበውን ፡ ሥራ ፡ በቶሎ ፡ ለመፈጸም ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ይሆንለታል ።

አለዚያ ፡ ግን ፡ መንገዱ ፡ ጠፍቶበት ፡ በመደናበር ፡ ጊዜውን ፡ ይፈጃል ። አገራችንን ፡ ልንጠቀማትና ፡ ልናገለግላት ፡ የምንችልበትን ፡

መንገድ ፡ ለማወቅ ፡ ብንፈልግ ፡ የጃፓንን ፡ ታሪክ ፡ ከማንበብ ፡ የተ
ሻለ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አናገኝም ። ወደ ፡ ኋላ ፡ ከቀሩት ፡ አገሮች ፡
ሁሉ ፡ ነፃነቷን ፡ ሳታስደፍር ፡ ለመሠልጠን ፡ የቻለች ፡ እሷ ፡ ብቻ ፡
ነች ። በጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በሥልጣኔ ፡ ራሷን ፡ የምትችል
በትን ፡ አቅድ ፡ (ፕላን ፡ ) እንዴት ፡ አድርጋ ፡ እንዳዘጋጀችውና ፡ በእ
ንደምን ፡ ያለ ፡ ቆራጥነትና ፡ ትጋት ፡ እንደፈጸመችው ፡ ስናስተው
ለው ፡ የምትሰጠን ፡ ምሳሌ ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ በማ
ንኛውም ፡ ዘመን ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ አገር ፡ ተደርጎ ፡ የማይ
ታወቅ ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ ነው ። የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ አገሩ ፡ ደሀ ፡ ነው ።
ሕዝቡ ፡ ግን ፡ አሳቡ ፡ ሩቅ ፡ የሚያስተውል ፡ የመንፈስ ፡ ባለ ፡ ጸጋ ፡
በመሆኑ ፡ ብቻ ፡ ሁልጊዜ ፡ ራሱን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ለማሳየት ፡ ቻለ ።
ስለዚህ ፡ ታሪካቸውን ፡ በማንበብ ፡ ምሳሌ ፡ ሆኖ ፡ ሊያገለግለን ፡ የሚ
ችልና ፡ የመንፈስ ፡ ባለጸጎች ፡ የሚያደርገን ፡ ብዙ ፡ ትምህርት ፡ እና
ገኝበታለን ።

ይህንን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተግባር ፡ ሲፈጽሙ ፡ ጃፓኖች ፡ በለሥል
ጣኖቻቸው ፡ መንግሥታቸው ፡ ሕዝባቸው ፡ ባንድ ፡ አሳብና ፡ ባንድ ፡
ዓይነት ፡ ምኞት ፡ የተቃኙ ፡ ሆነው ፡ በመታየት ፡ የውጭ ፡ ጠላት ፡
በስብከትም ፡ ሆነ ፡ በሌላ ፡ በማንኛውም ፡ ነገር ፡ የሚገባበት ፡ ቀዳዳ ፡
ባለመስጠታቸው ፡ ኅብረታቸው ፡ ብረት ፡ የለበሰ ፡ መሣሪያ ፡ ሆኖ ፡
ተገኝቷል ። ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ደግሞ ፡ የጃፓን ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡
ታሪካቸው ፡ የሰውን ፡ መንፈስ ፡ ወደ ፡ ትልቅ ፡ ዓላማ ፡ የሚመራ ፡
አቅኚነት ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ መድኃኒቱ ፡ ምን
ድነው ? ብለን ፡ ስናስብ ፡ ከኛ ፡ ከሁኖቹ ፡ ሰዎች ፡ ቀጥሎ ፡ አዲስ ፡
ትውልድ ፡ እንዲፈጠር ፡ ማድረግ ፡ ይገባናል ። በዚህ ፡ አዲስ ፡ ትው
ልድ ፡ ውስጥም ፡ ስለ ፡ አገራችን ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምንመኝላት ፡
ከፍ ፡ ያለው ፡ ምኞት ፡ በልባቸው ፡ ውስጥ ፡ አድሮ ፡ ላገር ፡ ጠቃ
ሚዎች ፡ የሆኑትን ፡ ታላላቅ ፡ ሥራዎች ፡ ለመፈጸም ፡ የሚችሉ ፡
ሙሉ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ እንዲፈጠሩ ፡ ማድረግ ፡ የሚ
ቻልበትን ፡ መንገድ ፡ ማዘጋጀት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ከዚህ ፡
ቀጥሎ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ መንገዶች ፡ በመከተል ፡ ልንደርስበት ፡ እን
ችላለን ።

ዛሬ ለኢትዮጵያ ያዲሱ ስልጣኔ መሰረቶች ተጥለውላታል። ወጣቶቿ ባገራቸው ውስጥም በየውጭው አገርም እየሄዱ ይማራሉ። ትምህርትን ለማስፋፋት ከፍ ያለ ወጭ ይደረጋል። ባገራችን ውስጥ ያሉት ተማሪዎች በብዙ አስር ሺ የሚቆጠሩ ሲሆኑ በየውጭው አገር የሚማሩት ደግሞ እንደዚሁ ቁጥራቸው በጣም እየጨመረ ሄዷል። ከነዚሁም ብዙዎች እየተመለሱ መጥተው አገራቸውን በማገልገል ላይ ናቸው ። ይኸውም በጣም ደስ የሚያሰኝ ነው። እንደዚሁም ወደ ኮሬ የተላኩት የኢትዮጵያ ወታደሮች የዓለም ሰላም የተመሰረተበትን የስኩሪቴ ኮልክቲብን አሳብ ለማስከበር ከሚዋጋው የዓለም መንግስታት ድርጅት አባሎች ከላኩት ጦር ጋር ጎን ለጎን ተሰልፈው ሲዋጉ በሰሩት ብዙ የጀብድ ሥራ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጀግንነት ስመ ጥሩነቱን ጠብቆ የኖረ መሆኑን ለዓለም የሚገልጥ ትልቅ ማስረጃ ሆኖ ተገኝተዋል ።

በኤኮኖሚም ፣ በኩል ፣ ኢትዮጵያ ፣ ሀብቷ ፣ እየጨመረና ፣ ገቢ ፣ ገንዘቧ ፣ በያመቱ ፣ እያደገ ፣ ሲሄድ ፣ ይታያል ። ብዙ ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ የሥልጣኔ ፣ ሥራዎች ፣ በቀን ፣ በቀኑ ፣ ሲቋቋሙ ፣ እንመለ ከታለን ። ይህ ፣ ሥራ ፣ ሁሉ ፣ እንደ ፣ ቡቃያ ፣ ወይም ፣ እንደ ፣ አበባ ፣ የሚቆጠር ፣ ሲሆን ፣ መልካም ፣ ፍሬ ፣ ሊሰጥ ፣ የሚችለው ፣ ሁሉም ፣ በየበኩሉ ፣ ተግቶ ፣ እየተረዳዳ ፣ ሲሠራ ፤ እያንዳንዱም ፣ ኢትዮጵያዊ ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ አስተያየት ፣ ኖሮት ፣ የተሰጠውን ፣ ተግ ባር ፣ ሰፊ ፣ በሆነ ፣ መንፈስ ፣ ሲፈጽመው ፣ ነው ። ንጉሠ ፣ ነገሥታ ችን ፣ ኢትዮጵያን ፣ ከፍ ፣ ለማድረግ ፣ የምንችልበትን ፣ መሣሪያ ፣ እን ደዚህ ፣ አድርገው ፣ ሲያስጨብጡን ፣ ዋጋ ፣ ያለው ፣ ሥራ ፣ ልን ሠራበት ፣ የምንችለው ፣ እኛ ፣ ነን ።

ለምሳሌ ፣ ጃፓን ፣ ስማቸውን ፣ የጠራነው ፣ ታላላቅ ፣ ሰዎች ፣ ተገኝተው ፣ እየተረዳዱ ፣ ባይሠሩላት ፣ ኖሮ ፣ ሚይገር ፣ የተባለው ፣ ንጉሠ ፣ ነገሥቷ ፣ የሥልጣኔን ፣ ዘመን ፣ መክፈቱና ፣ ሥራዎቹንም ፣

ማቋቋሙ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ጃፓን ፡ ከዚህ ፡ አሁን ፡ ካለችበት ፡ ደረጃ ፡
ለመድረስ ፡ ትችል ፡ ኖርዋል ፡ ወይ ?

እንግዲህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከፍ ፡ ለማለት ፡ የምትችልበትን ፡ መንገድ ፡ የማ
ዘጋጀቱን ፡ አደራ ፡ ለመፈጸም የትምህርት ፡ ሚኒስቴርና ፡ የኢንዱስትሪ ፡
ሚኒስቴር ፡ ናቸው ። የትምህርትና ፡ የዕውቀት ፡ ቅርንጫፎች ፡ በሁ
ለት ፡ ታላላቅ ፡ ክፍሎች ፡ ይከፈላሉ ። አንዱ ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ ሌቴ
ራቱር ፡ ፍልስፍና ፡ ጥብቅና ፡ ወይም ፡ ሕግ ፡ ዓዋቂ ፡ ፊሎሎገር ፡
የቋንቋ ፡ ዕውቀትና ፡ ሌሎችም ፡ እነሱን ፡ የመሰሉ ፡ በንግግር ፡ ወይም ፡
በቃል ፡ የሚከናወኑ ፡ ትምህርቶች ፡ የተመደቡበት ፡ ናቸው ። ሁለተ
ኛው ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ መሐንዲስነት ፡ ሕክምና ፡ የእርሻ ፡
ትምህርት ፡ በጠቅላላውም ፡ የቴክኒክ ፡ ትምህርቶች ፡ የሚገኙበት ፡
ናቸው ። አገር ፡ ሊለማ ፡ ሕዝብ ፡ ሊበለጽግና ፡ መንግሥቱም ፡ ሊጠ
ነክር ፡ የሚችለው ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ የተጠሩትን ፡ ትምህርቶች ፡
አጥርተው ፡ የተማሩ ፡ ሰዎች ፡ ሲገኙበት ፡ ነው ። የቃል ፡ ወይም ፡
የንግግር ፡ ትምህርቶች ፡ ብለን ፡ የጠራናቸውን ፡ ብቻ ፡ የኢትዮጵያ ፡
ወጣቶች ፡ ቢማሩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የእጅ ፡ ሥራዎች ፡ የሚሠሩ ፡ ከሌ
ሉባቸው ፡ አገሪቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጆች ፡ የሆኑ ፡
ሠራተኞች ፡ አስፈላጊዎቿ ፡ ሆነው ፡ ይኖራሉ ። እነሱም ፡ ለሚያከና
ውኑላት ፡ ሥራዎች ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ውድ ፡ ዋጋ ፡ እየከፈለች ፡ ወር
ቋን ፡ ታፈስላቸዋለች ፤ በዚህም ፡ አኳኋን ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ራሷን ፡
የቻለች ፡ አገር ፡ ለመሆን ፡ አትበቃም ። ለምሳሌ ፡ የክብሪት ፡ ፋብ
ሪካ ፡ ብናቋቁም ፡ እንኳ ፡ እሱን ፡ ለማስኬድ ፡ የሚችሉ ፡ ቴክኒ
ሲያኖች ፡ የሉንም ። ስለዚህ ፡ የትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ የቴ
ክኒክን ፡ ሥራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ በየቅርንጫፉ ፡ እንዲ
ማሩት ፡ ማድረግ ፡ አለበት ። ይህንንም ፡ ሲያደርግ ፡ ባገራችን ፡
ውስጥ ፡ ባቆመው ፡ የቴክኒክ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አስተምሮ ፡
ራሳቸውን ፡ የቻሉ ፡ የሚከኒክንና ፡ የእጅ ፡ ሥራዎችን ፡ አጥርተው ፡
የሚያውቁ ፡ ሠራተኞች ፡ እናገኛለን ፡ ብሎ ፡ ለመመኘት ፡ የሚቻል ፡
ነገር ፡ አይመስለኝም ። ምክንያቱም ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ይህን ፡
የመሰለውን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በደንብ ፡ ለማስኬድ ፡ የሚችሉ ፡

መምህራን ፡ አይገኙም ። ሁለተኛም ፡ እነሱን ፡ እየተቆጣጠሩ ፡ ትም ሀርት ፡ ቤቱን ፡ በደንብ ፡ እንዲከሄድ ፡ ለማድረግ ፡ የሚችሉ ፡ ኢት ዮጵያውያን ፡ አናገኝም ።

ስለዚህ ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ ድረስ ፡ በመት ፡ በመቱ ፡ የቴክኒክን ፡ ትምህርቶች ፡ የሚማሩ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እየተመለመሉ ፡ ችሎታቸውና ፡ ስጦታቸው ፡ ከታየ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አውሮፓና ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ እንዲሄዱ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ገንቢዎችና ፡ አናጢዎች ፡ እንኳ ፡ ለማግኘት ፡ ስንል ፡ ልጆቻችንን ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ መላክ ፡ ያስፈልገናል ።

ዛሬ ፡ ትልልቅ ፡ ሕንፃዎችና ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ የመኖሪያ ፡ ቤቶች ፡ ለመሥራት ፡ ስናስብ ፡ ሁልጊዜ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሠራተኞች ፡ መፈ ለግ ፡ አለብን ። እንደዚሁም ፡ መንግሥት ፡ መንገድ ፡ ሲያሠራ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መሐንዲሶችና ፡ ድልድይ ፡ የሚሠሩ ፡ ገንቢዎች ፡ ይቀጥ ራል ። በመት ፡ በመቱ ፡ ለሕንፃዎችና ፡ ለመኖሪያ ፡ ቤቶች ፡ ለመ ንገድና ፡ ለድልድዮች ፡ የምናወጣው ፡ ገንዘብ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደ ሆነ ፡ አስበነዋልን ? እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ መከፈሉ ፡ ቀርቶ ፡ ላገራችን ፡ ተወላጆች ፡ ብንሰጣቸው ፡ ኖሮ ፡ በኢኮኖሚ ፡ ረገድ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይጠቅመን ፡ እንደነበረ ፡ አስተውለን ፡ ብናስበው ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ የሚቆጭ ፡ ነገር ፡ ይገኛል ፡ ወይ ? አሁን ፡ ባለንበት ፡ ሁኔታ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ግን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ጥሩ ፡ ቤት ፡ ለመሥራት ፡ ሲፈልግ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ገንቢዎችና ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ አናጢዎች ፡ አሠራለሁ ፡ ብሎ ፡ አይሞክርም ፤ ምክ ንያቱም ፡ መልካምና ፡ ጠንካራ ፡ ሥራ ፡ እንደማይሠሩለት ፡ ስለሚያ ውቅ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ሄደው ፡ ከነሞች ፡ ገን ቢዎችና ፡ አናጢዎች ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ በቴክኒክና ፡ በእጅ ፡ ሥራ ፡ መማሪያ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተምረው ፡ የመጡ ፡ ያገሩ ፡ ተወላጆች ፡ የሆኑ ፡ ሠራተኞች ፡ ቢኖሩን ፡ ቤቱን ፡ በነሱ ፡ እጅ ፡ ለማሠራት ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ቅር ፡ ባላለው ፡ ነበር ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ስናመዛዝነው ፡ የትምህ ርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የቴክኒክ ፡ ትምህርት ፡ የሚማሩ ፡ ሃያ ፡ የሚሆኑ ፡ ተማሪዎች ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ልኳል ፤ ወደፊት ፡ ደግሞ ፡ በብዙ ፡ ቢልክ ፡ ለዚህ ፡ የሚወጣው ፡ ገንዘብ ፡ ምንም ፡ ቅር ፡ የሚያሰኝ ፡ ባልሆነ ፡ ነበር ።

እንደዚሁ ፡ ሁሉ ፡ ፋብሪካዎችን ፡ ለማስኬድ ፡ የሚችሉ ፡ የፋብሪካ ፡
መሐንዲሶችና ፡ የሥራ ፡ መሪዎች (contre-maîtres) አገራችን ፡ እንድ
ታገኝ ፡ ማድረግ ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡
ባገራችን ፡ የቃጫ ፤ ያቡጀዲና ፡ የፈትል ፤ የሲሚንቶ ፡ ፋብሪካዎች ፡
የኤሌክትሪክም ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ አሉን ። ያገራችን ፡ ልጆች ፡ ብቻ
ቸውን ፡ ሆነው ፡ እነዚህን ፡ ሥራዎች ፡ ለማስኬድ ፡ እንዲችሉ ፡ ለማ
ድረግ ፡ የምንበቃበትን ፡ መንገድ ፡ መፈለግ ፡ አለብን ።

እንደዚሁም ፡ ነገና ፡ ተነገ ፡ ወዲያ ፡ ልናቆማቸው ፡ ለሚያስፈ
ልጉን ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ አስፈላጊዎች ፡ የሆኑትን ፡ ቴክኒሲያኖች ፡
አስተምረን ፡ ለማውጣት ፡ የምንችለው ፤ ፋብሪካዎቹንስ ፡ የምናቋቁ
ማቸው ፡ እንዴት ፡ አድርገን ፡ ነው ? ብለን ፡ ማሰብ ፤ አለብን ። ስናስ
ብም ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ በጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ማለት ፡ በሥ
ርና ፡ በሥራአምስት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲያገኝ ፡ ለማድ
ረግ ፡ የሚያስፈልገን ፡ ነገር ፡ ምንድነው ? ብለን ፡ ማሰብ ፡ ይገባ
ናል ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሊያስቡበት ፡ የሚገባቸው ፡ የትምህርት ፡
ሚኒስቴር ፤ የኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴርና ፤ የሥራ ፡ ሚኒስቴር ፡ ናቸው ። ጊዜው ፡
ሲደርስ ፡ ዐውቆ ፡ ይፈጸማል ፡ ብለን ፡ ያሰብን ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ለመ
ቼም ፡ አንደርስም ። ዋና ፡ ዋናውም ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡ በውጭ ፡
አገር ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ ገብቶ ፡ ያልቃል ። የቴክኒክን ፡ ሥራ ፡ የሚ
ማሩ ፡ ልጆች ፡ አሁኑኑ ፡ መርጠን ፡ ብንልክ ፡ ግን ፡ መጀመሪያ ፡ ላሁኑ ፡
ችግራችን ፡ ይደርሱልናል ። ሁለተኛ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጮች ፡ የሆኑ ፡
ያገራችን ፡ መሐንዲሶችና ፡ ሠራተኞች ፡ እየተፈጠሩ ፡ ይደረጃሉ ።
ሦስተኛ ፡ ለምናቆማቸው ፡ የቴክኒክ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ መሪዎችና ፡
አስተማሪዎች ፡ ሆነው ፡ ባውሮፓ ፡ በተማሩትና ፡ በተመለከቱት ፡
አኳኋን ፡ ያደራጁታል ።

የትምህርታቸውን ፡ አቅድ ፡ በመልክም ፡ መንገድ ፡ ሳይመሩ ፡
እየቀሩ ፡ ባገራቸው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ዋና ፡ ዋናች ፡ ሥራዎች ፡
ለማስኬድ ፡ ሁልጊዜ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጆች ፡ የሆኑ ፡ ቴክኒ
ሲያኖች ፡ የሚያስፈልጓቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ዘወትር ፡ ባገራቸው ፡
ውስጥ ፡ ሁከትና ፡ ብጥብጥ ፡ ሲፈጠር ፡ ይታያል ። ለዚሁም ፡ ምሳሌ ፡
ግብፅንና ፡ ኢራንን ፡ ልንጠቅሳቸው ፡ እንችላለን ።

ባጭሩ ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ በሁለት ፡ ደረጃ
ዎች ፡ ይከፈላሉ ። እነዚሁም ፡ ቴክኒሲያኖች ፡ ካገር ፡ ተወላጆቻቸው ፡
መካከል ፡ ለማውጣት ፡ የሚችሉና ፡ የማይችሉ ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡
አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ትልቅ ፡ ሊሆን ፡ የሚችለው ፡ ከሁለተኛው ፡ ደረጃ ፡
ወጥቶ ፡ ወደ ፡ አንደኛው ፡ ደረጃ ፡ ለመተላለፍ ፡ አስፈላጊውን ፡
ሲፈጽም ፡ ይህም ፡ ማለት ፡ ቴክኒሲያኖችን ፡ ከሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ለማ
ግኘት ፡ ሲችል ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ይልቁንም ፡ የኢንዱስትሪን ፡ ሥራዎች ፡ ለመምራትና ፡ ለማስ
ኬድ ፡ የሚችሉ ፡ ልጆች ፡ ማግኘት ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ዋና ፡
ነገር ፡ ነው ። በዚህ ፡ በኩል ፡ በጃፓን ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እንደተ
መለከትነው ፡ ሁሉ ፡ ኢንዱስትሪና ፡ ንግድ ፡ ባሁኑ ፡ የሥልጣኔ ፡ ዘመን ፡
ላንድ ፡ መንግሥትና ፡ ላንድ ፡ ሕዝብ ፡ የሀብቱና ፡ የጉልበቱ ፡ ምንጭ ፡ ናቸው ።
ያገሩን ፡ ኢንዱስትሪ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ቢይዙት ፡ የመንግ
ሥቱም ፡ ሆነ ፡ ያሕዝቡ ፡ ሀብትና ፡ ጉልበት ፡ በባዕድ ፡ እጅ ፡ ተያዘ ፡
ማለት ፡ ስለሆነ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ጉዳትና ፡ አደጋ ፡ የለም ። አንድ ፡
ሕዝብ ፡ ለኑሮው ፡ የሚያስፈልጉትን ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎችና ፡
የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ የሚያገኘው ፡ ከኢንዱስትሪ ፡ ስለሆነ ፡ ሕዝቡ
የኢንዱስትሪን ፡ ሥራ ፡ እንዲለምድና ፡ እንዲማር ፡ ማድረግ ፡ ከማ
ነኛውም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ ይህ ፡ ነው ። ለም
ሳሌ ፡ ያገራችን ፡ ነጋዴዎችና ፡ ሀብታሞች ፡ ገንዘባቸውን ፡ በርስት ፡
ላይ ፡ ብቻ ፡ ማስቀመጥ ፡ ይወዳሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሀብታቸውን ፡
በኢንዱስትሪ ፡ ላይ ፡ ቢያደርጉት ፡ ኖሮ ፡ የበለጠ ፡ ትርፍና ፡ ጥቅም ፡
አግኝተውበት ፡ ለአገረቸውም ፡ የሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ ሊሠሩ ፡ ይች
ላሉ ። ቤት ፡ አይሥሩ ፡ ለማለት ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡
ሰው ፡ ሀብታም ፡ ሲሆን ፡ ከጠቅላላ ፡ ሀብቱ ፡ ከሦስት ፡ እጅ ፡
አንዱን ፡ ቤት ፡ ሲሠራበት ፡ ሁለቱን ፡ እጅ ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ላይ ፡
ማድረግ ፡ ይገባዋል ። አቶሞቢል ፤ መድፍ ፤ ታንክ ፤ አኤሮፕላን ፤
ባቡር ፤ መርከብ ፤ ባጭሩ ፡ ላንድ ፡ ዘመናዊ ፡ መንግሥት ፡ ኀይሉና ፡
ግርማው ፡ የሆኑት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ የሚገኙት ፡ ከኢንዱስትሪ ፡ ነው ፡

ስለዚህ ፡ ሕዝቡ ፡ ጥቅሙን ፡ እንዲያውቀው ፡ ለማድረግ ፡ መም
ከር ፤ ማስተማርና ፡ መምራት ፡ ያስፈልጋል ። ይህንንም ፡ ማድረግ ፡
የሚገባቸው ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ የጠራናቸው ፡ ሚኒስቴሮች ፡ ናቸው ።

እንግዲህ ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በግል ፡ ጉልበ
ቱና ፡ በግል ፡ ትጋቱ ፡ ምን ፡ መሥራት ፡ እንደሚገባው ፡ እናስብ ።
ለምሳሌ ፡ የትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ አንዱን ፡ ወጣት ፡ ወደ ፡ አው
ሮፓ ፡ ይልከውና ፡ ገንዘብ ፡ እየከፈለ ፡ ያስተምረዋል ። ያ ፡ ወጣት ፡
የያዘውን ፡ ትምህርት ፡ አጥርቶ ፡ ካንድ ፡ ነጭ ፡ ጋር ፡ ለመተካከል ፡
ማሰብና ፡ ከዚህ ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ ተግቶ ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ መማር ፡
የሱ ፡ ፈንታ ፡ ነው ። ገንዘቡን ፡ የሚከፍሉት ፡ መንግሥትም ፡ ሆነ ፡
ወይም ፡ ዘመዶቹ ፡ ቢሆኑ ፡ አስፈሊጊው ፡ ነገር ፡ እንዳይጎድለው ፡
ከማድረግ ፡ በቀር ፡ ትምህርቱን ፡ በትጋት ፡ አጥርቶ ፡ እንዲማር ፡ የሚቆጣጠ
ሩበት ፡ መንገድ ፡ የላቸውም ። እሱ ፡ ግን ፡ አገሩ ፡ ያለችበትን ፡
ችግርና ፡ የተማሩ ፡ ሰዎች ፡ የሚያስፈልጓት ፡ መሆኗን ፡ በማሰብ ፡
ጥበብንና ፡ ዕውቀትን ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ በሰፊ ፡ መንፈስ ፡ እጥፍ ፡
በሆነ ፡ ትጋትና ፡ ድካም ፡ መሥራት ፡ አለበት ።

ሰው ፡ ትምህርት ፡ ሲማር ፡ አሳቡ ፡ ሰፊ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ፡
ስላልነው ፡ ጉዳይ ፡ ትርጉሙ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለመግለጥ ፡ ያህል ፡
አንድ ፡ ምሳሌ ፡ እንሰጣለን ። የጃፓን ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡
ሆኩዛኢ ፡ የሚባለው ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ሥዕል ፡ ሠዓሊ ፡
ሲናገር ፡ እንደዚህ ፡ ብሏል ፡ “የእንስሳት ፤ የዕፅዋት ፤ የዛፎች ፤
የአዕዋፍ ፤ የዓሣዎችና ፡ የትሎች ፡ እውነተኛው ፡ የሥነ ፡ ፍጥረታ
ቸው ፡ አሠራር ፡ የተገለጠልኝ ፡ በሰባ ፡ ሦስት ፡ ዓመቴ ፡ ነው ።
ወደፊት ፡ ደግሞ ፡ ሰማንያ ፡ ዓመት ፡ ሲሞላኝ ፡ የበለጠ ፡ እርምጃ ፡
አደርጋለሁ ። የዘጠና ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ሲኖረኝ ፡ ደግሞ ፡ በነገሮች ፡ ውስጥ ፡
ተሸፍኖ ፡ የሚገኘው ፡ ምሥጢር ፡ ይገለጥልኛል ። መቶ ፡ ዓመት ፡
ሲሆነኝ ፡ ድንቅ ፡ ከሆነ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ አደርሳለሁ ። መቶ ፡ ዓሥር ፡
ዓመት ፡ ሲኖረኝ ፡ ግን ፡ አንዲት ፡ ነጥብ ፤ ወይም ፡ አንዲት ፡ መስ
መር ፤ ማንኛውም ፡ ነገር ፤ በኔ ፡ ዘንድ ፡ ሕይወት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡
ይገኛል ።” ሆኩዛኢ ፡ ይህን ፡ ሲናገር ፡ የሰባ ፡ ሦስት ፡ ዓምት ፡
ሽማግሌ ፡ ነበር ። ይህን ፡ ማለቱ ፡ ሰው ፡ በሥዕል ፡ ሠዓሊነትም ፡
ቢሆን ፡ ከመጨረሻው ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ ሲያስብ ፡
ያንድ ፡ ሰው ፡ ዕድሜ ፡ አይበቃውም ፡ ለማለት ፡ ነው ።

ሆኩዛኢ ፡ በሥዕል ፡ ሠዓሊነቱ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ የሠራና ፡ በዓ
ለም ፡ ላይ ፡ የታወቀ ፡ በመሆኑ ፡ ማንኛውንም ፡ አነስተኛ ፡ ዲክሲዮ
ኔር ፡ ስንገልጥ ፡ ስሙን ፡ የዓለም ፡ ታሪክ ፡ ከሚያስታውሳቸው ፡ ታላ
ላቅ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ተጽፎ ፡ እናገኘዋለን ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሆኩ
ዛኢ ፡ አሳበ ፡ ሰፊ ፡ ሰው ፡ ስለነበረ ፡ በሕይወቱ ፡ የፈጸመው ፡ ሥራ ፡
አላጠገበውም ። በምዕራፉ ፡ እንደተመለከትነው ፡ የጃፓን ፡ ታላላቅ ፡
ሰዎች ፡ እነ ፡ ካትሱ ፤ ቶጎ ፤ ኖጊ ፡ ፉኩዛዋ ፤ ሁሉም ፡ የትልቁ ፡
እስክንድርንና ፡ የናፖሌዎንን ፡ ታሪክ ፡ ማንበብ ፡ የሚወዱ ፡ ሰዎች ፡
ስለነበሩ ፡ አሳባቸው ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ የሚያስተውለው ፡ በሰፊ ፡
አስተያየት ፡ ነበር ። ብዙ ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የቻሉትም ፡
አሳባቸው ፡ ባለጸጋ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በየትምህርት ፡
ቤቱና ፡ በውጭም ፡ አገር ፡ የሚማሩት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ የጃ
ፓንን ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ታሪክ ፡ ምሳሌ ፡ በልባቸው ፡ አሳድረው ፡
የእነሱን ፡ የመሰለ ፡ ባህርይ ፡ በመውረስ ፡ በትጋትና ፡ በጋለ ፡ መን
ፈስ ፡ እየሠሩ ፡ ላገራቸው ፡ ያገለግላሉ ፡ ብለን ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡
እናደርጋለን ።

ገንዘብ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ ዕድሜያቸው ፡ የሚፈቅድ
ላቸው ፡ ሲሆኑ ፡ እነሱው ፡ ራሳቸው ፡ መማር ፡ ይገባቸዋል ። ቢችሉ ፡
ባገራቸው ፡ ውስጥ ፡ አለዚያም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ሄደው ፡
መማር ፡ አለባቸው ። ዕድሜያቸው ፡ የማይፈቅድላቸው ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡
ልጆቻቸውን ፡ ማስተማር ፡ ያስፈልጋቸዋል ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ባሁኑ ፡
ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ እየላኩ ፡ ሲያ
ስተምሩ ፡ ስለምናይ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ነው ። ነገር ፡
ግን ፡ ብዙዎቹ ፡ ይህን ፡ ቢያደርጉ ፡ ሊያደርጉት ፡ ሲችሉ ፡ የማያደ
ርጉት ፡ ብዙዎች ፡ ደግሞ ፡ ሞልተዋል ።

በሕክምናም ፡ በኩል ፡ እንደዚሁ ፡ ብዙ ፡ ሐኪሞች ፡ በቅርብ ፡
ጊዜ ፡ ማስተማር ፡ የሚቻልበትን ፡ መንገድ ፡ የትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡
መፈለግ ፡ አለበት ። ብዙ ፡ ሐኪሞች ፡ ብናገኝ ፡ የሕዝቡ ፡ ጤንነት ፡
በሚገባ ፡ እየተጠበቀ ፤ የሕዝቡ ፡ ቁጥር ፡ እየጨመረና ፡ እያደገ ፡ ይሄ
ዳል ። ለምሳሌ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ ከጃፓን ፡ አገር ፡ ስፋት ፡ ሦስት ፡
ጊዜ ፡ ተኩል ፡ ይበልጣል ። ጠባብ ፡ በሆነው ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ ሰባ ፡

አምስት ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ ሲኖርበት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ተኩል ፡ በሚበልጠው ፡ ሰፊ ፡ ብሆነው ፡ በኛ ፡ አገር ፡ የሚኖረው ፡ የሕዝብ ችን ፡ ቁጥር ፡ ከአሥር ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ሚሊዮን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እየተባለ ፡ ይገመታል ። ሕዝቡ ፡ የሕክምናን ፡ እርዳታ ፡ በሚገባ ፡ ሲያገኝ ፡ ግን ፡ የሚወለዱት ፡ ሕፃናት ፡ እያደጉ ፡ በመሔዳ ቸው ፡ ትውልዳችን ፡ የሚበዛ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

እንደዚሁም ፡ ለምሳሌ ፡ ቆላ ፡ የሆኑት ፡ የኢትዮጵያ ፡ አውራ ጆች ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አይኖርባቸውም ። ምክንያ ቱም ፡ ወባና ፡ ሌላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሽታ ፡ ስለሚገኝባቸው ፡ በሽ ታውን በመፍራታችን ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ጥጥ ፡ ሸንኮራ ፡ አገዳና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አታክልት ፡ በብዙ ፡ ሊገኝባቸው ፡ የሚችሉ ፡ የሀብት ፡ ምንጭ ፡ የሆኑ ፡ መሬቶች ፡ ሞልተውባቸዋል ። ሐኪሞች ፡ መሐንዲሶችና ፡ የእርሻ ፡ ትምህርት ፡ የሚያጠኑ ፡ ሰዎች ፡ ቢኖሩን ፡ ግን ፡ በሽታውን ፡ እያጠፋን ፡ አገሩን ፡ ለማልማት ፡ እንችላለን ። በጭሩ ፡ በቴክኒክ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የተማሩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ዎች ፡ የሚያውቁ ፡ ሰዎች ፡ ቢኖሩን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ኃይለኛና ፡ ሀብ ታም ፡ መንግሥት ፡ ለማድረግ ፡ የምንችልበት ፡ ተቆጥሮ ፡ የማያልቅ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ እንችላለን ። የአናጢነትን ፡ ሥራ ፡ አሳምረው ፡ የሚያውቁ ፡ ሠራተኞች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቢኖርዋት ፡ ኖሮ ፡ ብእንጨት ፡ ሀብታም ፡ አገር ፡ ስለሆነች ፡ በእንጨት ፡ የሚሠሩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃዎች ፡ እየሠራች ፡ ለጐረቤቶቿ ፡ ለነ ፡ ግብፅ ፡ እየሸጠች ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ ለማግኘት ፡ ትችል ፡ ነበረ ። አሁን ፡ ግን ፡ እንኳንስ ፡ ይህን ፡ ልታደርግ ፡ ወርቅዋን ፡ እያፈሰሰች ፡ ለራሷ ፡ እንኳ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ እንጨትና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ የተሠሩ ፡ የቤት ፡ ዕቃ ዎች ፡ ስትገዛ ፡ ትታያለች ።

ባገራችን ፡ ውስጥ ፡ በምናቆማቸው ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ተምረው ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ለማከናወንና ፡ የባንክንም ፡ ሥራ ፡ ለማከሄድ ፡ የሚችሉ ፡ ልጆች ፡ ለማግኘት ፡ አንችልም ። እነዚህን ፡ ሁለት ፡ ሥራዎች ፡ በት ክክል ፡ ሊያስኬዱ ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፡ ከሌሉን ፡ ደግሞ ፡ የመንግሥታ ችንና ፡ ያገራችን ፡ የሕዝቡም ፡ የጉልበታችው ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡

የንግድ ፡ ሥራ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ ለማውጣት ፡ የማይቻል ፡ ነገር ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያገራችን ፡ ነጋዴዎች ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ እያቋቋሙ ፤ ከፍ ፡ ብለን ፡ የጠራናቸው ፡ የንግድን ፡ ሥራ ፡ ተምረው ፡ የመጡት ፡ ልጆች ፡ ሥራውን ፡ እያስኬዱላቸው ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ኃይል ፡ እንዲያገኙ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ። ለምሳሌ ፡ በየጊዜው ፡ ያገራችን ፡ ሰዎች ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ አቋቁመው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሥራቸውን ፡ የሚመሩላቸው ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ እውቀት ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ በመሆናቸው ፡ ሁል ጊዜ ፡ እየከሰሩ ፡ ማኅበራቸው ፡ ሲፈርስ ፡ ታይቷል ።

በዚህም ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብታውቅበት ፡ ከጃፓን ፡ የተሻለ ፡ መንገድ ፡ ለመከተል ፡ ዕድል ፡ አግኝታለች ። ዛሬ ፡ በገራችን ፡ እንደነ ፡ ሚትሱኢ ፡ ወይም ፡ እንደነ ፡ ሚትሱቢሺ ፡ የመሰሉ ፡ ብቻቸውን ፡ ሆነው ፡ ፋብሪካ ፡ ለማቆም ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፡ አይገኙም ። በጃፓን ፡ አገር ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ የጠራናቸው ፡ ሰዎች ፡ የንግዱን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ጠቅልለው ፡ ስለ ፡ ያዙት ፡ ያገሩ ፡ ገንዘብና ፡ ሀብት ፡ በጥቂት ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ ገብቷል ። ይህም ፡ አሁን ፡ ለጊዜው ፡ መልካም ፡ መስሎ ፡ ቢታይ ፡ ወደፊት ፡ ሁከት ፡ እንደሚያመጣባቸው ፡ አይጠረጠርም ። ባገራችን ፡ ግን ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ እየተፈጠሩ ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ እንዲያቋቁሙ ፡ ሲደረግ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በንግድ ፡ የሚገኘውን ፡ ሀብት ፡ ባለ ፡ አክሲዮኖች ፡ እየሆኑ ፡ ሊካፈሉ ፡ ይችላሉ ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ ብልጽግና ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ እንዲዳረስ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻለው ፡ ሕዝቡ ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ጥቅሙን ፡ ለማወቅ ፡ የሚችልበት ፡ ዕውቀት ፡ ስለሌለው ፡ የትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ የንግድና ፡ የባንክ ፡ ሥራ ፡ የሚያውቁ ፡ ተማሪዎች ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እየላከ ፡ በማስተማር ፡ የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴርም ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ እንዲፈጠሩ ፤ ሕዝቡም ፡ የኢንዱስትሪን ፡ ሥራ ፡ እንዲለምዱ ፡ በመምከር ፡ ሁለቱ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ እየተስማሙና ፡ እየተረዳዱ ፡ ሕዝቡን ፡ ሲመሩት ፡ ነው ።

እንዲያውም ፡ የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ላገር ፡ የሚ
ጠቅም ፡ ሆኖ ፡ የተገኘውን ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ሁሉ ፡ ግማሹን ፡ ገንዘብ ፡
ከመንግሥት ፡ እያስፈቀደ ፡ የተረፈውን ፡ አክሲዮን ፡ በመሸጥ ፡ እየሰ
በሰበ ፡ ካቋቋመው ፡ በኋላ ፡ ቴክኒሲያኖቹን ፡ እየመረጠ ፡ ሰጥቶ ፡
ሥራው ፡ በደንብ ፡ እንዲካሄድና ፡ ሰውም ፡ በዚሁ ፡ ኢንዱስትሪ ፡
ሥራ ፡ ላይ ፡ እምነት ፡ እንዲጥልበት ፡ አስፈላጊውን ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡
ይገባዋል ። ሥራው ፡ በደንብ ፡ ከተቋቋመ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ አክሲዮኑን ፡
ለባለ ፡ ጥቅሞች ፡ ሸጦ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ያቋቁማል ። ይህም ፡
ሕዝቡን ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ መምራት ፤ መምከርና ፡ ማሳደግ ፡ ይባላል ።
ይኸውም ፡ በጃፓን ፡ አገር ፡ መደረጉን ፡ ተመልክተነዋል ።

ያገራችን ፡ ሕዝብ ፡ በንግድና ፡ በኢንዱስትሪ ፡ እያደገ ፡ሲሄድ ፡
ለመንግሥቱ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ጥቅም ፡ ሊሰጥ ፡ እንደሚችልና ፡
እንደሚገባው ፡ ለማስረዳት ፡ ያሀል ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ የተደረጉ ፡
አንዳንድ ፡ ምሳሌዎች ፡ እንሰጣለን ።

የፈረንሣይ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነው ፡ ትልቁ ፡ ዓዋቂ ፡ ፌርዲናንድ ፡
ደ ፡ ሌሴፕስ ፡ የሚባለው ፡ ጥልቅ ፡ በሆነው ፡ ጥበቡ ፤ ማነኛውም ፡
እንቅፋት ፡ ሊያሰናክለው ፡ ባልቻለው ፡ ትእግሥቱና ፡ ትጋቱ ፡ የሱዌ
ዝን ፡ የባሕር ፡ በር ፡ ከግብፅ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ተስማምቶ ፡
ራሱ ፡ ሥራውን ፡ እያሠራ ፡ ከከፈተው ፡ በኋላ ፡ እንግሊዝ ፡ ወደ ፡
ህንድ ፡ አገር ፡ ግዛቷ ፡ ለምትመላለስበት ፡ መንገድ ፡ ይህ ፡ በር ፡ ዋና ፡ ኬላ ፡
መሆኑን ፡ አስተውላ ፡ በዚህ ፡ በር ፡ ላይ ፡ እጅዋን ፡ ለመጣን ፡ ተግታ ፡
ትጣጣር ፡ ጀመር ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ በር ፡ የተከፈተውና ፡ የተሠ
ራው ፡ በግብፅ ፡ መሬትና ፡ በፈረንሳዩ ፡ ሊቅ ፡ ጥበብ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡
የሚበልጠውን ፡ አክሲዮን ፡ የያዙት ፡ ሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ነበሩ ።

የግብፅ ፡ ኬዲቭ ፡ (ንጉሥ ፡) ገንዘብ ፡ የማይበቃው ፡ አባካኝ ፡
ስለ ፡ ነበረ ፤ በ1875 ዓ. ም. (እ. ኤ. አ.) በሱዌዝ ፡ የባሕር ፡ በር ፡
ኩባንያ ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ሰባት ፡ አክሲ
ዮን ፡ ሊሸጥ ፡ ማሰቡ ፡ ተወራ ። ይህንኑም ፡ ለመግዛት ፡ ከማንም ፡
ይልቅ ፡ መብት ፡ ያላት ፡ ፈረንሣይ ፡ ነበረች ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚያን ፡
ጊዜ ፡ ፈረንሣይ ፡ ጀርመን ፡ ድል ፡ ካደረገቻት ፡ በኋላ ፡ ቢስማርክ ፡

የሚባለው ፡ የጀርመን ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ አስጨንቆ ፡ ይዟት ፡ ስለነበረ ፡ የእንግሊዝን ፡ ደጋፊነት ፡ ለማግኘት ፡ ስትል ፡ እነዚህን ፡ አክሲዮኖች ፡ ከግብፅ ፡ ላይ ፡ እንድትገዛ ፡ ለእንግሊዝ ፡ ፈቀደችላት ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የእንግሊዝ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፡ ዲስራኤሊ ፡ የሚባለው ፡ ነበር ።

ባንድ ፡ በኩል ፡ የእንግሊዝ ፡ ፓርለማ ፡ በዕረፍት ፡ ምክንያት ፡ ተዘግቶ ፡ ስለነበረ ፡ የግብፅን ፡ አክሲዮን ፡ ለመግዣ ፡ የሚሆነውን ፡ ገንዘብ ፡ ከፓርለማ ፡ ለማስፈቀድ ፡ አልተቻለም ። በሌላም ፡ በኩል ፡ ለጊዜው ፡ በመንግሥቱ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ የግብፅ ፡ ኬዲቭ ፡ ስለ ፡ አክሲዮኑ ፡ ዋጋ ፡ ጠይቆት ፡ የነበረው ፡ አራት ፡ ሚሊዮን ፡ ፓውንድ ፡ አልተገኘም ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ኬዲቩ ፡ ይህንኑ ፡ ገንዘብ ፡ በፍጥነት ፡ ለችግሩ ፡ እንዲደርስለት ፡ ስለፈለገ ፡ አስቀድሞ ፡ ለሚከፍለው ፡ ገዥ ፡ ሊሸጥ ፡ የተዘጋጀ ፡ መሆኑን ፡ አስታውቆ ፡ ነበርና ፡ የእንግሊዝ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ዲስራኤሊ ፡ ሮትቻይልድ ፡ ከሚባለው ፡ ባለ ፡ ባንክ ፡ ከሆነው ፡ ባለጸጋ ፡ ዘንድ ፡ መልክተኛ ፡ ልኮ ፡ በፍጥነት ፡ አራት ፡ ሚሊዮን ፡ ፓውንድ ፡ አበድረን ፡ ሲል ፡ ለመነው ። ሮትቻይልድም ፡ ስሌ ፡ ዋስትና ፡ ምን ፡ ትሰጡኛላችሁ ? ሲል ፡ ጠየቀ ። ዲስራኤሊም ፡ ዋስ ፡ የሚሆንህ ፡ ራሱ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ነው ፤ ብሎ ፡ መለሰለት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሮትቻይልድ ፡ ወዲያው ፡ የተፈለገውን ፡ ገንዘብ ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ ወለድ ፡ ለእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ስላበደረው ፡ የግብፅን ፡ አክሲዮን ፡ ለመግዛትና ፡ እጁን ፡ በሱዌዝ ፡ የባሕር ፡ በር ፡ ላይ ፡ ለመጫን ፡ ቻለ ። *

ጃፓን ፡ በ1905 ዓ. ም. መስኮብን ፡ ለመውጋት ፡ ባሰበች ፡ ጊዜ ፡ የጦርነቱ ፡ ከሳራ ፡ የፈጀባት ፡ ገንዘብ ፡ አንድ ፡ ሚሊያርድ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሃያ ፡ ሚሊዮን ፡ ዬን ፡ ነው ። ከዚሁ ፡ የሚበልጠውን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ብትበደር ፡ እነ ፡ ሚትሱኢና ፡ ሚትሱቢሺ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እየሠሩ ፡ ከማቅረባቸው ፡ በላይ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ በመዋጮ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሚሊዮን ፡ ዬን ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታ ፡ ሰጥተውታል ። እነ ፡ ፉኩዛዋ ፡ ሕዝቡን ፡ እየሠራ ፡ እንዲበለጽግ ፡ መምከራቸው ፡ ብልጽግናው ፡ ይህን ፡ ለመሰለው ፡ ከፍ ፡ ላለ ፡ ላገር ፡ ጉዳይ ፡ እንዲያገለግል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡

* ANDRE MAUROIS የጻፈውን ፡ የዲስራኤሊን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ተመልከት ።

ባገራችን ፡ ትልልቅ ፥ የንግድ ፡ ቤቶች ፡ እንዲፈጠሩ ፡ ሲደረግ ፥ ዋናው ፥ አሳብ ፡ ሀብታቸው ፥ መርከብ ፡ ለመሥራትና ፥ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የሚሠሩ ፡ ኢንዱስትሪዎችና ፡ ዩኒቬርሲቲዎችም ፡ ለማቋቋም ፥ መንግሥቱንም ፡ በልዩ ፥ ልዩ ፥ ጉዳዮች ፥ ለመርዳት ፥ እንዲችሉ ፥ ለማድረግ ፥ ነው ።

ለምሳሌ ፡ የጀርመን ፡ ጦር ፥ በዓለም ፥ ላይ ፡ በጣም ፥ የተፈራ ፥ ለመኃይለኛ ፡ መሆኑን ፥ እናውቃለን ። ይህን ፥ ያህል ፥ የተፈራ ፥ ለመሆን ፡ ያበቃው ፡ ማነው ? ክሩፕ ፡ የሚባለው ፥ ነጋዴ ፡ አይደለምን ? ክሩፕ ፡ ብረት ፡ የሚያቀልጡ ፡ ከባድ ፡ ኢንዱስትሪዎች ፥ አቁሞ ፥ በያይነቱ ፥ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፥ እየሠራ ፥ ለጀርመን ፥ ጦር ፡ ሠራዊት ፥ ባይሰጠው ፡ ኖሮ ፡ የጀርመን ፡ ወታደር ፥ በጀግንነቱ ፡ ብቻ ፡ ምን ፥ ሊያደርግ ፡ ይችል ፥ ኖርዋል ? በጃፓንም ፥ አገር ፥ እነ ፥ ሚትሱኢና ፡ ሚትሱቢሺ ፡ ዘመናዊ ፥ የሆነ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እየሠሩ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ባይሸጡለት ፡ ኖሮ ፡ የጃፓን ፡ ጦር ፥ ምትየማይፈራ ፡ ጀግና ፡ መሆኑ ፡ ብቻ ፡ ምንም ፥ ዋጋ ፡ ባልኖረው ፥ ነበር ። በጀግንነቱ ፡ ከጀርመኖችና ፡ ከጃፓኖች ፥ የማያንሰውን ፡ የኢትዮጵያን ፥ ሕዝብ ፡ የፋሺስት ፡ ጦር ፥ ድል ፡ ያደረገው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፥ ስለጐደለው ፡ ብቻ ፥ አይደለም ፡ ወይ ?

ለምሳሌ ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚኖሩ ፡ የውጭ ፥ አገር ፡ ነጋዴዎች ፡ ከኢትዮጵያ ፥ የሚገኘውን ፥ እንደ ፡ ቡና ፥ እንደ ፥ ቆዳና ፡ እንደ ፡ ሰም ፡ የመሰሉትን ፡ የንግድ ፥ ዕቃዎች ፥ ወደ ፡ ውጭ ፥ አገር ፡ እየላኩ ፤ ላገራችን ፡ የሚያስፈልጉትንም ፥ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፥ ከውጭ ፥ አገር ፥ እያስመጡ ፡ በመሸጥና ፡ በመለወጥ ፥ የሚያተርፉት ፡ ገንዘብ ፥ ምን ፥ ያህል ፡ እንደሆነ ፥ አውቀነዋልን ? ይህም ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፥ ገቢ ፥ የሚሆነው ፡ ላገራችን ፥ ነጋዴዎች ፡ ሆኖ ፥ እነሱም ፥ ላገር ፡ የሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ ቢሠሩበት ፡ ኖሮ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ አገራችን ፡ ትለማ ፥ እንደነበረ ፥ አስበነዋልን ? አሁን ፡ ግን ፡ ከገራችን ፥ በንግድ ፥ ሥራ ፥ የሚገኘው ፡ ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ የሚገባው ፥ በውጭ ፥ አገር ፥ ሰዎች ፥ እጅ ፥ ስለሆነ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፥ አገር ፡ እየሄደ ፡ የሌሎቹን ፡ አገሮች ፥ ያለማል ፥ እንጅ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አልተጠቀመችበትም ።

ይህንንም ፡ ስንል ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ነጋዴዎችን ፡ ለመመቅኘት ፡
አይደለም ። እንዲያውም ፡ እነሱ ፡ ገንዘባቸውንና ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡
በኩልም ፡ ያላቸውን ፡ ዕውቀት ፡ እያመጡ ፡ በመሥራታቸው ፡ የመ
ንግሥቱ ፡ ቀረጥ ፡ እየተጨመረ ፡ ገቢ ፡ ገንዘቡ ፡ እንዲያድግ ፡ ያገራች
ንም ፡ ሰዎች ፡ ሥራ ፡ እንዲያገኙና ፡ አገራችንም ፡ በሥራ ፡ እንድትን
ቀሳቀስ ፡ በማድረጋቸው ፡ በጣም ፡ የረዱን ፡ መሆናቸውን ፡ መዘ
ንጋት ፡ አይገባንም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ ያለት ፡ አገራችን ፡ ላይ ፡ ነው ፡
በሙሉ ፡ ነቅተን ፡ አስፈላጊውን ፡ ሳናደርግ ፡ ብንቀር ፡ ግን ፡
በኋላ ፡ ጉሮሮዎችንን ፡ የታነቅን ፡ ሆነን ፡ እንገኛለን ። ስለ ፡ ዘለቄ
ታው ፡ ጉዳይ ፡ ስናስብ ፡ ያገራችን ፡ ብልጽግና ፡ ላገራችን ፡ ግል
ሚያ ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋል ። ከዚህም ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ የም
ንችለው ፡ አጉል ፡ ምቀኝነት ፡ በልባችን ፡ በማሳደር ፡ ሳይሆን ፡ ዕው
ቀትንና ፡ ሠራተኛነትን ፡ መሣሪያ ፡ አድርገን ፡ ተግተን ፡ በመሥራት ፡
ነው ። ከፍ ፡ ብለን ፡ እንደገለጥነው ፡ ልጆቻችንን ፡ ወደ ፡ አውሮፓና ፡
ወደ ፡ አሜሪካ ፡ እየላክን ፡ በታላላቆቹ ፡ የንግድ ፡ ትምህርት ፡
ቤቶች ፡ ከተማሩ ፡ በኋላ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ገንዘብ ፡ ለተቋቋሙት ፡
የንግድ ፡ ቤቶች ፡ ዲሬክተሮች ፡ ሆነው ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ በዕውቀትና ፡
በጥበብ ፡ በታማኝነትም ፡ እየሠሩ ፡ በሌላም ፡ በኩል ፡ መንግሥት ፡ እየደገፉ
ቸው ፡ የንግዱን ፡ ማኅበር ፡ ሲያስኬዱት ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የንግድን ፡
ሥራ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እያልን ፡ አው
ጥተን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እጅ ፡ ለማዛወር ፡ የምንመኘው ፡
ምኞት ፡ አውቶ ፡ ይፈጸማል ። ተግተን ፡ እንደዚህ ፡ የምናገኘውንም ፡
ገንዘብ ፡ ለከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ማድረጋችን ፡ ቀርቶ ፡ ላገር ፡ ለሚጠ
ቅም ፡ ሥራ ፡ ልናውለው ፡ የሚገባን ፡ መሆኑን ፡ ያገራችን ፡ ባለፀ
ጎች ፡ ሊያውቁት ፡ ይገባቸዋል ።

ራሳችንን ፡ እስክንችል ፡ ድረስ ፡ ግን ፡ ከሁሉም ፡ የሚሻለው ፡
ዘዴ ፡ ባገራችን ፡ የሚጠቀሙት ፡ ነጋዴዎችና ፡ ባለኢንዱስትሪዎች ፡
ከኢትዮጵያውያን ፡ ጋር ፡ ካፒታላቸውን ፡ እኩል ፡ ለኩል ፡ እያደረጉ ፡
አብረው ፡ በባለአክሲዮንነት ፡ እንዲሠሩ ፡ ማስገደድ ፡ ነው ።

እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነ ፡ በሥልጣኑ ፡ ባለጸጋ ፡
የሆነ ፡ በገንዘቡ ፡ ትምህርት ፡ ያለው ፡ በዕውቀቱ ፡ እየተረዳዱ ፡ ቢሠሩ ፡

አገራችን ፡ ትልቅ ፡ የምትሆንበትን ፡ የማያጠራጥረውን ፡ መንገድ ፡ ተከትለናል ፥ ለማለት ፡ እንችላለን ። ሥልጣን ፤ ገንዘብና ፡ ጥበብ ፡ ካልተራዳዱ ፡ ደግሞ ፡ ባሁኑ ፡ ሥልጣኔ ፡ ዘመን ፡ ፍሬ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ አይቻልም ። ይህንንም ፡ ስናደርግ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ማሰብ ፡ አለብን ። ለሰው ፡ ልጅ ፡ የሕይወቱና ፡ የኑሮው ፡ ዓላማዎች ፡ ሁለት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። አንደኛ ፡ በነፍሱ ፡ በኩል ፡ መንግሥተ ፡ ሰማ ያትን ፡ ለማግኘት ፡ መጣጣር ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፡ ግብ ፡ ደግሞ ፡ የተወለደባትን ፡ አገር ፡ በመንግሥታት ፡ መካከል ፡ ስትቀመጥ ፡ ልጆቿ ፡ በፈጸሙት ፡ ሥራ ፡ ለመመካት ፡ ችላ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ እንድት ይዝ ፡ ለማድረግ ፡ መሥራትና ፡ መድከም ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልገዋል ።

ጃፓን ፡ አንደኛ ፡ ባገርዋ ፡ ውስጥ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ እንዲስፋፋ ፤
ሁለተኛ ፡ ያገርዋ ፡ ተወላጆች ፡ ቴክኒሲያኖች ፡ እንዲሆኑ ፤
ሦስተኛ ፡ ያገርዋ ፡ ነጋዴዎች ፡ እንዲበለጽጉ ፤ እነዚህን ፡ ሦስት ፡ መሠረታዊ ፡ ነገሮች ፡ ተደግፋ ፡ በማይናወጥ ፡ ቆራጥነትና ፡ ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ አስተዋይነት ፡ ፕሮግራሟን ፡ ተከትላ ፡ ስለሠራች ፡ ያገኘችው ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፤ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አንባቢ ፡ ጉልህ ፡ በሆነ ፡ ማስ ረጃ ፡ ሊያውቀው ፡ ቢፈልግ ፡ አሁንም ፡ ጨምረን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ መግለጫ ፡ እንሰጣዋለን ።

የሜይጊ ፡ ዘመን ፡ ተከፍቶ ፡ ጃፓን ፡ ያውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡
መቀበል ፡ ከጀመረች ፡ በኋላ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ማለት ፡ በ1872
ዓ. ም. ላይ ፡ የመንግሥቱ ፡ ያመት ፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ፡ 58 (አምሳ ፡
ስምንት ፡) ሚሊዮን ፡ ዬን ፡ ብቻ ፡ ነበር ። በመጀመሪያው ፡ የዓለም ፡
ጦርነት ፡ ላይ ፡ ጃፓን ፡ ደኅና ፡ አድርጋ ፡ ኢንዱስትሪዎቿን ፡ እያሠ
ራች ፡ ስለ ፡ ነገደች ፡ በጦርነቱ ፡ ማለቂያ ፡ ላይ ፡ ማለት ፡ በ1918 ዓ. ም
የመንግሥቱ ፡ ያመት ፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ፡ እያደገ ፡ ሄዶ ፡ ከ714 (ሰባት ፡
መቶ ፡ አሥራ ፡ አራት ፡) ሚሊዮን ፡ ዬን ፡ ደረሰ ። በእነዚህ ፡ ኢንዱስትሪ
ዎች ፡ ከመጠቀሟ ፡ በፊት ፡ ጃፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ ከተቀበለችበት ፡ ከ1868 ዓ ም
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ 1898 ዓ ም ድረስ ፡ ማለት ፡ በሠላሳ ፡ ዓመታት ፡
ውስጥ ፡ 2910 ሁለት ፡ ሺ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ አሥር ፡) ኢንዱስት
ሪዎች ፡ አቋቁማለች ። የጃፓን ፡ መንግሥት ፡ ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ በነ

በሩት ፡ ዓመታት ፡ የሒሳቡን ፡ ሚዛን ፡ ለማስተካከል ፡ ሲል ፡ ባመት ፡ ባመቱ ፡ 90 (ዘጠና ፡ ሚሊዎን ፡ ዬን ፡ ይበደር ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ የጃፓን ፡ መንግሥት ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ ኢንዱስትሪን ፡ ማስፋፋት ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ አምስት ፡ ሚሊዎን ፡ ፓውንድ ፡ ከእ ንግሊዝ ፡ ላይ ፡ መበደሩን ፡ ተመልክተነዋል ። ይህም ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ተበድሮ ፡ መሠረት ፡ ላለው ፡ ሥራ ፡ ሲያው ለው ፡ በመጨረሻ ፡ አሥር ፡ ጊዜ ፡ እጥፍ ፡ አድርጎ ፡ ሰብሉን ፡ እንደ ሚሰበስብ ፡ ያስተምረናል ።

ልዩ ፡ ልዩ ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ የሚያውቁ ፡ ሠራተኞች ፤ መሐን ዲሶች ፤ ሐኪሞች ፤ የንግድንና ፡ የባንክን ፡ ሥራ ፡ የሚመሩ ፡ ሰዎች ፡ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለማግኘትሳ ፡ እንደምን ፡ ያለ ፡ መንገድ ፡ መከተል ፡ ይገባናል ዋናው ፡ ነገር ፡ በተለየ ፡ እነዚህን ፡ ዕውቀ ቶች ፡ ለመማር ፡ የሚችሉ ፡ ልጆች ፡ የሚዘጋጁበት ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ማቋቋም ፡ ያስፈልጋል ። በእነዚህም ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሊገቡ ፡ የሚችሉ ፤ በሒሳብ ፤ በማቴማቲክ ፤ ልዩ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ልጆች ፡ እየተመረጡ ፡ ነው ።

እነሱም ፡ በእነዚሁ ፡ ትምሀርት ፡ ቤቶች ፡ ሊገፉ ፡ የሚችሉ ፡ መሆናቸው ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ እየተላኩ ፡ በቴክ ኒክ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲገቡ ፡ ቢደረግ ፡ በያይነቱ ፡ መሐንዲ ሶች ፡ ለማግኘት ፡ እንችላለን ። አለዚያ ፡ ግን ፡ ችሎታቸው ፡ ሳይረ ጋገጥ ፡ ቢሄዱ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ከተከፈለላቸው ፡ በኋላ ፡ በፈተና ፡ ይወድቁና ፡ ከታሰበው ፡ ግብ ፡ ሳይደርሱ ፡ ይመለሳሉ ። ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ አንድ ፡ ምሳሌ ፡ ልሰጥ ፡ እፈቅዳለሁ ። በአለፈው ፡ ዓመት ፡ ፓሪስ ፡ በነበርኩ ፡ ጊዜ ፡ መኰንን ፡ ሙላት ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወጣት ፡ በኢትዮጵያ ፡ አምባሳድ ፡ አግኝቼው ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ እንደሄደ ፡ አጫወተኝ ። ይህ ፡ ወጣት ፡ በማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ በመሐንዲስ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከተማረ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ፈረ ንሣይ ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ ትምህርቱን ፡ ሊቀጥል ፡ ፈቀደ ። የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ያገሩን ፡ የኑሮ ፡ ውድነት ፡ ባለማወቁ ፡ የቆረጠለት ፡ ገንዘብ ፡ የማይበቃው ፡ መሆኑንና ፡ እንደዚሁም ፡ ለመርከብ ፡ አባቱ ፡ እንደከፈ ሉለት ፡ ነገረኝ ። እኔም ፡ ይህንኑ ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ ነግሬለት ፡ ግር

ማዊነታቸውም ፡ በተለመደው ፡ ቍርነታቸው ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ገንዘብ ፡ በየወሩ ፡ እንዲከፈለው ፡ አዘዙ ። አሁን ፡ የገብረ ፡ ማርያም ፡ ትም ህርት ፡ ቤት ፡ ዲሬክተር ፡ ሙሴ ፡ ቤርላ ፡ እንደ ፡ አረጋገጡልኝ ፡ ይህ ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሳይሞላው ፤ ፈተና ፡ አልፎ ፡ ስለቀ ናው ፡ አሁን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሲቪል ፡ መሐንዲስነት ፡ ትምህርት ፡ በመ ማር ፡ ላይ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ትምህርት ፡ ተምረው ፡ የተሰናዱት ፡ ልጆች ፡ ትምህርታቸው ፡ በቡቃያ ፡ እንዳይቀር ፡ እየተ መረጡ ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ሊላኩ ፡ ያስፈልጋል ። ይህ ፡ ወጣት ፡ ራሱ ፡ ተጣጥሮ ፡ መሄዱ ፡ ያስመሠግነዋል ።

እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ እንደዚህ ፡ ልጅ ፡ ችሎታቸው ፡ የታወቀ ፡ ወጣቶች ፡ በልዩ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እየተዘጋጁ ፡ ቢሄዱ ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ የሚሆኑ ፡ መሐንዲሶች ፡ ለማግኘት ፡ ይቻላል ። የኢንዱስትሪን ፡ ጉልበት ፡ የሚያንቀሳቅሰውን ፡ የኤሌክትሪክ ፡ ኃይል ፡ በየቦታው ፡ ሊያቋቁሙ ፡ የሚችሉት ፡ መሐንዲሶች ፡ ናቸው ። የዓለ ምን ፡ ዡግራፊ ፡ ገልጠን ፡ የእያንዳንዱን ፡ አገር ፡ ታሪክ ፡ እየመረ መርን ፡ ስንመለከተው ፡ በየዓለሙ ፡ ክፍል ፡ በሚገኙት ፡ ብዙ ፡ አገሮች ፡ በቅርብ ፡ ዘመን ፡ በድንቁርና ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩ ፡ ስንት ፡ ሕዝቦች ፡ ዛሬ አውራጆቻቸውን ፡ የሚያገናኟቸው ፡ ብዙ ፡ መንገዶችና ፡ የባቡር ሐዲዶች ፡ እየዘረጉ ፤ ትምህርት ፡ ቤቶችና ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ እያቋቋሙ ፤ የእርሻንና ፡ ያታክልትን ፡ ሥራዎች ፡ በሰፊው ፡ እየሠሩ ፡ አገራቸውን ፡ በማልማትና ፡ በማበልጸግ ፡ የሕዝቡ ፡ ቍጥር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ እንዲሄድ ፡ በማድረግም ፤ ማዕድኖቻቸውንም ፡ እያወጡ ፡ በመጠቀም ፤ ብዙ ፡ አዳዲሶች ፡ ከተሞች ፡ በመሥራትም ፤ ያገራቸውን ፡ መልክ ፡ ፈጽሞ ፡ ለውጠውት ፡ ይታያል ።

ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ የበቁት ፡ ከገራቸው ፡ ልጆች ፡ ቴክኒሲ ያኖች ፡ በማስተማራቸው ፡ ነው ። ልጆቿ ፡ እንደዚህ ፡ አድርገው ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ በመሥራት ፡ ሀብቷን ፡ እንዲሠራበት ፡ አድር ገው ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለዚህ ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ የሚያበቋት ፡ የሚ ያሳምርዋትና የሚያበለጽጓት ፡ መቼ ፡ ነው ?

ልጆቻችንን ፡ ወደ ፡ ቴክኒክ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እየላክን ፡ የስ ልክ ፤ መድኃኒት ፡ የመቀመም ፤ የቆዳ ፤ ከብት ፡ የማርባት ፤ ብረት ፡

የማቅለጥ ፤ የባቡርና ፤ የመርከብ ፡ አሠራር ፤ የሰዓት ፤ የአርኪቴክቱር ፡ ሌሎችም ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉትን ፡ ሥራዎች ፡ እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ መጠን ፡ ቀደምትነቱ ፡ እየታየ ፡ በጥንቃቄ ፡ በተጠና ፡ አቅድ ፡ እየመራን ፡ ብናስተምራቸው ፡ ባገራችን ፡ ውስጥ ፡ ትልቅ ፡ ተስፋ ፡ የሚጣልበት ፡ አዲስ ፡ ትውልድ ፡ ፈጥረናል ፡ ለማለት ፡ እንችላለን ። መንግሥታችንም ፡ አገራችንን ፡ ከፍ ፡ ሊያደርጋት ፡ የሚችለው ፡ በዚህ ፡ አዲስ ፡ ትውልድ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ያሳብ ፡ ባለ ፡ ጸጎች ፡ የሆኑትን ፡ ቴክኒሲያኖች ፡ መሣሪያ ፡ ሲያደርግ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መንግሥታችን ፡ አገሩንና ፡ ሕዝቡን ፡ በሥልጣኔ ፡ ለመለዋወጥ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ተበድሮም ፡ ቢሆን ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ፕላን ፡ ለማዘጋጀትና ፡ በድፍረት ፡ ለመፈጸም ፡ ይችላል ። አሁን ፡ ያለንበትን ፡ ሁኔታ ፡ ስናስተውለው ፡ ግን ፡ መንግሥታችን ፡ እንደምን ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ እንደገጠመው ፡ ሳንገነዘበው ፡ ብንቀር ፡ ዕውር ፡ መሆን ፡ ነው ። በጃፓን ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እንደተመለከትነው ፡ ጃፓኖች ፡ መጀመሪያ ፡ ለመነሣት ፡ የበቁት ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ባገኙት ፡ እርዳታና ፡ የገንዘብ ፡ ብድር ፡ ነው ። እንግሊዝም ፡ ጃፓንን ፡ የረዳቻት ፡ ከመስኮብ ፡ ጋር ፡ ላላት ፡ ውድድር ፡ ጃፓን ፡ ረዳቷ ፡ እንድትሆን ፡ ለማድረግ ፡ አስባ ፡ ነው ። የጃፓኖችን ፡ ታሪክ ፡ ለብቻው ፡ ትተን ፡ የማነኛውንም ፡ መንግሥት ፡ ታሪክ ፡ ብንመረምረው ፡ ከሌሎች ፡ መንግሥታት ፡ እርዳታንና ፡ የገንዘብ ፡ ብድርን ፡ ካላገኘ ፡ ሥራዎቹን ፡ ለማከናወን ፡ አይችልም ። ለምሳሌ ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ካሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ በያይነቱ ፡ እርዳታና ፡ የገንዘብ ፡ ብድር ፡ እየጠየቀ ፡ የማይቀበል ፡ መንግሥት ፡ የት ፡ ይገኛል ? አገራችን ፡ ገንዘብ ፡ ብትበደርም ፡ ሥራዎቿን ፡ የሚያስኬዱላት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቴክኒሲያኖች ፡ ስለሆኑ ፡ በመለገምም ፡ ሆነ ፡ ችላ ፡ በማለት ፡ የሚወጣው ፡ ገንዘብ ፡ የሚገባውን ፡ ፍሬ ፡ ሳይሰጥ ፡ ባክኖ ፡ ያልቃል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ቴክኒሲያኖቹ ፡ ያገርዋ ፡ ሰዎች ፡ ቢሆኑ ፡ ኖሮ ፡ በጥቂት ፡ ገንዘብ ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ የሚሰጥ ፡ ሥራ ፡ በተሠራበት ፡ ነበር ። እስቲ ፡ በግል ፡ ኑሮዋችን ፡ እንኳ ፡ ብንመለከተው ፡ ያንዱን ፡ ሰው ፡ ትዳር ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ሊያለማለት ፡ ይችላልን ? ስለዚህ ፡ ቴክኒሲ

ያኖች ፡ ሳይኖሩን ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ ብለን ፡ ብናስብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስሕተት ፡ እናደርጋለን ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ቴክኒሲያኖችን ፡ እያስተማረ ፡ በማዘጋጀት ፤ የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ደግሞ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ እንዲፈጠሩ ፡ እያደረገ ፡ ጃፓኖች ፡ ለነጋዴዎቻቸው ፡ ቴክኒሲያኖች ፡ እየሰጧቸውና ፡ ኢንዱስትሪያቸውን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በዘመናዊው ፡ መሣሪያ ፡ እንዲሠሩ ፡ እያስገደዷቸው ፡ እንደመሩዋቸው ፡ ሁሉ ፡ ይህንኑ ፡ መንገድ ፡ ተከትሉ ፡ እንዲመራቸው ፡ ያስፈልጋል ።

ያማርኛ ፡ ቋንቋችን ፡ ደግሞ ፡ እንዲሠለጥን ፡ ለማድረግ ፡ የትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ሰፊ ፡ ፕሮግራም ፡ ማዘጋጀት ፡ ይገባዋል ። ሕዝባችንን ፡ በሥልጣኔ ፡ መንፈስ ፡ ልናንቀሳቅሰው ፡ የምንችለው ፡ ቋንቋችንን ፡ መሣሪያ ፡ አድርገን ፡ ነው ። ለዚሁም ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ ዕውቀትና ፡ ጥበብ ፡ ያለባቸውን ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፉትን ፡ መጻሕፍት ፡ እየመረጡ ፡ መተርጐም ፡ ይገባል ። ይህም ፡ ሲደረግ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ባማርኛ ፡ ብቻ ፡ ለማስተማር ፡ እንዲቻል ፡ ለማድረግ ፡ ለዚሁ ፡ ክፍል ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ የትምህርት ፡ መጻሕፍት ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ እንዲተረጐሙ ፡ ማድረግ ፡ ያሻል ። ቀጥሎ ፡ ለሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ እንደዚሁ ፡ እየተደረገ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እያለ ፡ እስከ ፡ ዑኒቬርሲቴ ፡ ድረስ ፡ ይሄዳል ። ይህንን ፡ ሥራ ፡ ሊመራው ፡ የሚችል ፡ አካዴሚ ፡ ስለሆነ ፡ እሱን ፡ ሊያቋቁሙት ፡ የሚችሉ ፡ ሊቃውንት ፡ ካሁኑ ፡ ጀምሮ ፡ መሰብሰብና ፡ መምረጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ድንቁርና ፡ እየጠፋ ፡ የሕዝቡ ፡ መንፈስ ፡ የዕውቀትና ፡ የጥበብ ፡ ብርሃን ፡ ለማግኘት ፡ የሚችለው ፡ ትምህርት ፡ የሚገኝባቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ በራሱ ፡ ቋንቋ ፡ ለማንበብ ፡ የሚችል ፡ ሲሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ያማርኛን ፡ ቋንቋ ፡ መሣሪያ ፡ አድርገው ፡ ይህንን ፡ ተግባር ፡ ሊፈጽሙ ፡ የሚችሉ ፡ ደራስያንና ፡ ጋዜጠኞች ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ዓላማ ፡ ለመድረስ ፡ የሚቻለው ፡ ይህንኑ ፡ መሣሪያ ፡ የትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ካሁኑ ፡ ጀምሮ ፡ ቀጥቅጦና ፡ ሠርቶ ፡ ሲያዘጋጅላቸው ፡ ነው ።

ማስተዋል ፡ የሚገባን ፡ አሁንም ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አለ ።
አንድ ፡ ሕዝብ ፡ በሥልጣኔ ፡ በስሎ ፡ አሳቡ ፡ ጥበብን ፡ እያፈለቀ ፡
እጁም ፡ ሠራተኛ ፡ ሆኖ ፡ ከመንፈሱ ፡ የመነጨውን ፡ ጥበብ ፡ በቴክኒክ ፡
ሥራ ፡ እያከናወነ ፡ ራሱን ፡ ከቻለ ፡ በኋላ ፡ ማንኛውም ፡ ኃይለኛ ፡ መንግ
ሥት ፡ ሊያጠፋው ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ አለብን ። ይኸውም ፡
በጀርመንና ፡ በጃፓን ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ የምናየው ፡ ነው ። ጀርመኖች ፡
ባሁኑ ፡ ጦርነት ፡ ከተሞቻቸውና ፡ ኢንዱስትሪዎቻቸው ፡ በቦምብ ፡
ፈርሰው ፤ አገራቸውና ፡ ሕዝባቸውም ፡ የተፈታ ፡ መስሎ ፡ ይታይ ፡
ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ የጠፋውን ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ አድሰው ፡ በሚያስደንቅ ፡ ፍጥነት ፡ በኤኮኖሚ ፡ በኩል ፡ በመ
ልካም ፡ ስለተቋቋሙ ፡ ጎረቤቶቻቸው ፡ የሆኑት ፡ ሌሎቹ ፡ ሕዝቦች ፡
እንደገና ፡ ሌላ ፡ ጦርነት ፡ አንሥተው ፡ አደጋ ፡ ይጥሉብን ፡ ይሆናል ፡
ብለው ፡ አሁን ፡ ሥጋት ፡ አድሮባቸዋል ። ይህ ፡ ነገር ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሊተ
ማመን ፡ የሚገባው ፡ ካሳቡ ፡ በሚፈልቀው ፡ ዕውቀት ፡ ነው ፡ እንጅ ፡
በገንዘብ ፡ አይዶለም ፡ ላልነው ፡ አስተያየት ፡ ደጋፊ ፡ ሊሆን ፡ የሚ
ችል ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

እኛም ፡ አገራችን ፡ ትልቅ ፡ መንግሥት ፡ እንድትሆን ፡ እንደዚህ ፡ አደ
ርገን ፡ መልካሙን ፡ መሠረት ፡ ብንጥል ፡ የወደፊቱን ፡ መጪ ፡ ጊዜ ፡
በትልቅ ፡ ተስፋ ፡ ልንጠብቀው ፡ እንችላለን ። አገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡
ቀድሞ ፡ በዮዲትና ፡ በግራኝ ፤ በኋላም ፡ በኢጣሊያ ፡ ወረራ ፡ ምክ
ንያት ፡ የደረሰባትን ፡ መከራ ፡ ስናስታውሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁል
ጊዜ ፡ በታምር ፡ እየጠበቀና ፡ እያዳነ ፡ እስካሁን ፡ በነፃነቷና ፡ በክብ
ርዋ ፡ አኖራት ። ስለዚህ ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ በበኩላችን ፡ ለዚህ ፡ ጊዜ ፡
ያደረሰንን ፡ አምላክ ፡ ለማመስገን ፡ የምንችለው ፡ ነፃነታችንን ፡ የስ
ንፍና ፡ አልጋ ፡ ማድረጋችን ፡ ቀርቶ ፡ ክብራችንን ፡ ጠብቀን ፡ የም
ናኖርበትን ፡ መሣሪያ ፡ በዘመኑ ፡ ጥበብና ፡ ዕውቀት ፡ ሠርተን ፡ ለሚ
መጣብን ፡ ጠላት ፡ መከላከያ ፡ ስናደርገው ፡ ነው ። የጀርመንን ፡ አገር ፡
ትልቅ ፡ መንግሥት ፡ ካደረጓት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ የሆነው ፡ ቢስማ
ርክ ፡ የሚባለው ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ሲናገር ፡ ጀርመን ፡ አንድ ፡
ትልቅ ፡ ሥራ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ እንድትፈጽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጫት ፡
አገር ፡ ነች ፡ ብዬ ፡ አምናለሁ ። ይህን ፡ የመሰለ ፡ እምነት ፡ በልቤ ፡

ውስጥ ፡ ባይኖርግ ፡ ኖሮ ፡ ሕዩወቴን ፡ እንደዚህ ፡ አድርጌ ፡ በድካ ምና ፡ በትግል ፡ ለማሳለፍ ፡ የምችልበትን ፡ ብርታት ፡ አላገኝም ፡ ነበር ፡ ብሏል ። እኛም ፡ ስላገራችን ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይህንኑ ፡ የመሰለ ፡ እምነት ፡ ሊኖረን ፡ ይገባል ። ባገራቸውና ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥ ታቸው ፡ ፍቅር ፡ የተቃጠሉት ፤ አሳበ ፡ ሰፊው ፡ ሊቅ ፤ አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በልጆቿ ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እምነት ፡ ሲገልጡ ፡ ከጻፉዋቸው ፡ እንደ ፡ ማር ፡ ጣፋጮች ፡ ከሆኑት ፡ ግጥሞቻቸው ፡ አንዳንዶቹን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በመጥቀስ ፡ ለአሳቤ ፡ መደምደሚያ ፡ አደርጋቸዋለሁ ።

እናንት ፡ እንጂ ፡ ናችሁ ፡ ያፍሪቃ ፡ ራስ ፡ ቅል ፡
ባለ ፡ ዘውድ ፡ ቋንቋ ፡ ባለ ፡ ነፃ ፡ አክሊል ።
ግዕዝ ፡ አማርኛም ፡ ሁለቱ ፡ ቋንቋች ፡
ታላቅ ፡ ታናሽ ፡ ዓባይ ፡ ያፍሪቃ ፡ ወንዞች ፤
ካፍሪቃ ፡ አልፈው ፡ ተርፈው ፡ በባሕር ፡ በየብስ ፡
ገና ፡ ይፈሳሉ ፡ እንደ ፡ እግዜር ፡ መንፈስ ።
ስለ ፡ አማርኛና ፡ ስለ ፡ ግዕዝ ፡ ክብር ፡
ዋዜማ ፡ ተቆሟል ፡ በብዙ ፡ አህጉር ።

. . . . . . . . . . .

መጣፍ ፡ የሚበላ ፡ የመጣፍ ፡ ቀበኛ ፡
ዛሬ ፡ በኛ ፡ ዘመን ፡ አይገኝም ፡ ከኛ ።

. . . . . . . . .

ኩበቱም ፡ እንጨቱም ፡ የጥበብ ፡ ትምህርት ፡
አውሮፖች ፡ በመጣፍ ፡ የለቃቀሙት ።
እናንተም ፡ ለቃቅሙ ፡ ሰብስቡ ፡ በቅጥ ፡
ቤታችሁ ፡ እንዲሞቅ ፡ እንዲገለምጥ ፡
በቋንቋችሁ ፡ መጣፍ ፡ ባርጌው ፡ ብራና
ሐዲሱ ፡ ሥልጣኔ ፡ አልተጣፈምና ።



ከብደ ሚካኤል በኢትዮጵያ ሥነፅሁፍ ታሪክ ውስጥ ገናና ከሆኑት ደራስያን አንዱ ናቸው። ጥቅምት 23፣ 1909 የተወለዱ ባለቅኔ የቤተክህነትን ትምህርት ካገባደዱ በኋላ በአሊያንስ ፍራንሴዝና በላዛሪስት ሚስዮን ዘመናዊ ትምህርትን ተከታትለዋል። የግሪክ፣ የሮማውያን፣ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይ፣ የጀርመን፣ የሩስያና የጣሊያንን በርካታ መፃህፍት ከመረመሩም በኋላ ሃያ በላይ መፃህፍትን ለወገኖቻቸው አበርክተዋል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለዚህ ተግባራቸው የክብር ዶክትርናን ዲግሪን በ1990 በሰጠበት ወቅትም፣ «በድርሰቶቻቸው ውስጥ የሚታዩት የእኒህ ታላቅ ደራሲ የሃሳብ ምጥቀት ጌዎች፤ ቃላት፣ ዘይቤዎችና ሌሎች የአፃፃፍ ስልት ገፅታዎች በኋላ ለመጡ ደራሲዎች ያደረጉት አስተዋፅኦ ቀላል አይደለም። በተለይ ከ1950ዎቹ ወዲህ የተነሱ በርካታ ደራሲዎች የሳቸውን ድርሰቶች አንብበው፣ በሳቸው ድርሰቶች ሥነፅሁፍን አውቀውና አጣጥመው ደራሲ ሊሆኑ በቅተዋል» ብሏል።

ሜጋ አሳታሚ ድርጅትም የኒህን ሊቅ ሥራዎች ጠቃሚነት በማጤን ለዘመናችን ትውልድ የሚኖራቸውን ፋይዳ በማሰብ የሚከተሉትን መፅሐፎቻቸውን በድጋሚ አቅርቧል።

1. ታሪክና ምሣሌ (፩ኛ መፅሐፍ)
2. ታሪክና ምሣሌ (፪ኛ መፅሐፍ)
3. የቅኔ ውበት
4. ሮሚዮና ዡልየት
5. የዕውቀት ብልጭታ
6. ጃፓን እንደምን ሠለጠነች?
7. ታላላቅ ሰዎች

ሜጋ አሳታሚ ድርጅት

ዋጋ ብር 9.00